# በኦሮሚያ ክልላዊ መስተዳድር በሮቤ መምህራን ኮሌጅ በ10+3 የዲፕሎማ መርሃ ግብር የፕራክቲከም ኮርስ አተገባበር ፍተሻ

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

ለአማርኛ ማስተማር (TeAm) ኤም. ኤ. ዲግሪ
በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ
ሙሐመድ ጀማል

የካቲት 1999

# በኦሮሚያ ክልላዊ መስተዳድር በሮቤ መምህራን ኮሌጅ በ10+3 የዲፕሎማ መርሃ ግብር የፕራክቲከም ኮርስ አተገባበር ፍተሻ

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

ለአማርኛ ማስተማር (TeAm) ኤም. ኤ. ዲግሪ
በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ


ሙሐመድ ጀማል


የካቲት 1999

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# በኦሮሚያ ክልላዊ መስተዳድር በሮቤ መምህራን ኮሌጅ በ10+3 የዲፕሎማ መርሃ ግብር የፕራክቲከም ኮርስ አተገባበር ፍተሻ

በ


ሙሐመድ ጀማል

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም


የካቲት 1999

የፈተና ቦርድ አባላት

አቶ ስለም እሸቱ (ረ/ፕሮፌሰር) ፊርማ

አማካሪ

ዶ/ር ብርሃኑ ቦጋለ ፊርማ

የውጭ ፈታኝ

አቶ ጌታቸው እንዳላማው(ረ/ፕሮፌሰር) ፊርማ

የውስጥ ፈታኝ

# ምስጋና

የነገሮች ሁሉ ሰበብና አስተናባሪ የሆነውን ፈጣሪ፤ ከሁሉ አስቀድሜ «አልሃምዱሊሏህ» ማለቱ ግድ ይሆንብኛል። በማስከተልም ለዚህ ሥራ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ድጋፍ ያደረጉልኝን መዘከር ይጠበቅብኛል።

የነዛን አስተያየቶችህን ብስለትና ጥልቀት ዘግይቼም ቢሆን ተረድቻቸዋለሁ፤ ብዙ ቶምነገርም አግኝቼባቸዋለሁ። ከዚህም በላይ ደግሞ በወደፊቱ ሕይወቴም የማይዘነጋኝን– የክስተቶችን ሁለት ተቃራኒ ገፅታዎች በትዕግስት የመጠበቅን ውጤት በተግባር አሳይተኸኛል። በመሆኑም ካንተ በፊት የማመሰግነው አይኖርም– መምህሬ፤ አማካሪዬ ረዳት ፕሮፌሰር አለም እሹቱ።

ተሾመ ነጋሳ ሁሉ ነገሬ ነበርክ፤ በየትኛውም ነገር የማልለካቸው ውለታዎችህ አሉብኝ፤ ለዚህ ጥናትም የለፋህልኝ ብዙ ነው። የሮቤ መምህራን ኮሌጁ (ዲን) አባተ ለገሠ፤ የመረጃ ማሰባሰቢያዎቼን መስመር አስይዘህልኛል፤ ጠቃሚ አስተያየቶችም ሰተኸኛል። አብዱልቃዲር ሹቢም በሰጠኸኝ ጓኝቶች ብዙ ነገር ሠርቼበታለሁ። የዶዶላው አምሃ አስረስ ኘሪንት አስደርገህልኛል። የሮቤ መምህራን ኮሌጁ የኘራክቲከም ኃላፊው ደበበ ቶላም የሰጠኸኝ መረጃ ቀላል አይደለም፤ የአዳማው መሠረት ኩምሳም እንዲሁ። የመቀሌ ዩኒቨርስቲው አታኸልቲ መኮንን፤ ያዲሳባዋ ሒሩት አምሃ ልዑልሰገድ፤ የአዋሳው ዘላለም ጌታቸው፤ የሬዲዮ ፋናዋ አፀደ ውድነህ፤ "የድላችን" ካሌ ዓለሙ የክፍል ጓደኞቼ ብቻ አልነበራችሁም፤ ያደረጋችሁልኝን ሁሉ ... አልረሳም። የሮቤ መምህራን ኮሌጆቹ ነገሰ ገመቹ እና ደረሰ ዳባም ሁለገብ እገዛችሁ አልተዘነጋኝም።

የደቡብ ዩኒቨርስቲው የቀድሞው ሞጁል አስተማሪዬ እና ያሁኑ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲው ረዳት ፕሮፌሰር– ጌታቸው እንዳላማው፤ ሞራል-ንስስቴ ተዳክሞ፤ በተሰላቸሁበት ሰዓት ላይ ነው የደረስክልኝ። ዳግም እንዳንሰራራ አድርገኸኛል፤ የዲላውን ብርታቴን አስመልሰህልኛል። እንደቀድሞዬ በአዲስ ተስፋ ተሞልቼ፤ አዲስ ራዕይ ሰንቄ በኩራት ወደሥራ ዓለም እንድመለስ በውስጤ የለኮስከውን የብርታት መንፈስ መቼም ቢሆን እንዳስታወስኩት ይኖራል።

ባለቤቴ ሙኒራ አህመድ ከነልጆ (አህመድ ሙሐመድ) የሠላሜ መሠረት ነበራችሁ፤ ናችሁም። ታናሽ ወንድሜ ሙክታር ጀማል፤ የጋሠራው ያሲን ተማም፤ የደምቢዶሎው ኢታና ሐብቴ፤ የሮቤ መምህራን ኮሌጁ አህመድ ማህሙድ፤ የሳሪስ ሼክ ሙሐመድ-ሲራጅ አሚን ... ከባች ወትት የሆናችሁልኝን... የምረሳው አይሆንም።

# ማውጫ


ርዕስ ገፅ

ምስጋና ---------- i

ማውጫ ---------- ii

የአባሪዎች ዝርዝር ---------- v

የሰንጠረዥ ማውጫ ---------- vi

የምህፃረ ቃላት ዝርዝር ---------- x

አጠቃሎ ---------- xi

ምዕራፍ አንድ ፡ መግቢያ ---------- 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ---------- 1

1.2 የጥናቱ አላማ ---------- 4

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ ---------- 5

1.4 የጥናቱ ክልልና ገደብ ---------- 6

1.5 ስለርቢ መምህራን ኮሌጅ አጭር ቅኝት ---------- 6

ምዕራፍ ሁለት ፡ የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት ---------- 8

2.1 የመምህራን ስልጠናና የማስተማር ልምምድ ---------- 8

2.1.1 ማስተማር ምንድነው? ---------- 8

2.1.2 የመምህራን ስልጠና ---------- 11

2.1.3 የማስተማር ልምምድ ---------- 12

2.1.3.1 የማስተማር ልምምድ ምንነት እና ታሪካዊ ዳራ ---------- 13

2.1.3.2 የማስተማር ልምምድ አላማና ግብ ---------- 15

2.1.3.3 የማስተማር ልምምድ ሞዴሎች ---------- 16

2.1.3.4 ሱፐርቪዥንና የማስተማር ልምምድ ---------- 18

2.1.3.4.1 የሱፐርቪዥን ምንነት ---------- 19

2.1.3.4.2 የሱፐርቪዥን አላማና ተግባራት ---------- 19

2.1.3.4.3 የሱፐርቫይዘር ሚናና የሱፐርቪዥን አከናወን ሂደት ---------- 21

2.1.3.4.3.1 የሱፐርቫይዘር ሚና ---------- 21

2.1.3.4.3.2. የሱፐርቪዥን አከናወን ሂደት ---------- 21

2.1.3.4.3.2 ምጋቤ ምላሽ በሱፐርቪዥን ሂደት ---------- 24

2.2 በፕራክቲከም / የማስተማር ልምምድ ላይ የቀረቡ ሀገራዊ ጥናቶች ዳሰሳ ---------------25

ምዕራፍ ሦስት - የጥናቱ ዘዴ ---------------29
3.1 የጥናቱ ተተኳሪዎችና የናሙና አወሳሰድ ---------------29
3.1.1 የጥናቱ ተተኳሪዎች ---------------29
3.1.2 የናሙና አወሳሰድ ---------------29
3.1.2.1 የኮሌጅ መምህራን ---------------29
3.1.2.2 ተማሪ አስተማሪዎች ---------------30
3.1.2.3 የተባባሪ ት/ቤት መምህራን ---------------31
3.1.2.4 ኮሌጁ እና ተባባሪ ት/ቤቶች ---------------31
3.2 የመረጃ አሰባሰብ ---------------31
3.2.1 የጽሑፍ መጠይቅ ---------------31
3.2.2 ቃለመጠይቅ ---------------32
3.2.3 ምልከታ ---------------33
3.2.4 የግምገማ ቅፅ ---------------33
3.3 የመረጃ አተናተን ---------------33
ምዕራፍ አራት - የመረጃ ትንተና ---------------35
4.1 የኮሌጁ መምህራን የሥራ ድርሻና ኃላፊነት ---------------35
4.1.1 የኮሌጁ መምህራን የሥራ ድርሻ፣ ቅድመ እና ድህረ ፕራክቲከም ---------------36
4.1.2 የኮሌጁ መምህራን የሥራ ድርሻ፣ በፕራክቲከም ሂደት (ሱፐርቪዥን) ---------------41
4.2 የተባባሪ ት/ቤት መምህራን የሥራ ድርሻና ኃላፊነት ---------------47
4.3 የተማሪ አስተማሪዎች የሥራ ድርሻና ኃላፊነት ---------------53
4.3.1 የተማሪ አስተማሪዎች የትምህርት እቅድ ዝግጅት ---------------54
4.3.2 የተማሪ አስተማሪዎች የትምህርት አቀራረብ ---------------58
4.3.3 የተማሪ አስተማሪዎቹ በማስተማር ልምዱ ሂደት ተግባራዊ ያደረጉት የምዘና ሁኔታ ---------------62
4.3.4 የተማሪ አስተማሪዎች የአጋዥ የማስተማሪያ መሣሪያዎች ዝግጅት ---------------65
4.3.5 ከማስተማር ውጪ ባሉ ተግባራት ላይ የተማሪ አስተማሪዎች ያላቸው ተሳትፎ ---------------66

4.4 በፕራክቲከም ሂደት ውስጥ የኮሌጁ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት ----------------------------68
4.5 የተባባሪ ት/ቤቶች የሥራ ድርሻና ኃላፊነት ----------------------------76
4.6 በኮሌጁ ፕራክቲከሙን በአግባቡ ለመተግበር እንቅፋት የሆኑ
ዋና ዋና ችግሮች ---------------------------- 83
4.6.1 ኮሌጁ ለመርሃ ግብሩ የሰጠው ትኩረት አነስተኛነት ----------------------------84
4.6.2 የመርሃ ግብሩ በበቂ እቅድና ቅድመ ዝግጅት ላይ አለመመስረት ----------------------------86
4.6.3 ከተባባሪ ት/ቤቶች ጋር ያለው ቅርብ መላላት ----------------------------89
4.6.4 የተማሪ አስተማሪዎችና የመምህራን ቁጥር አለመመጣን ----------------------------90
4.6.5 የተማሪ አስተማሪዎችና የተባባሪ ት/ቤቶች ቁጥር አለመመጣን ----------------------------90
4.6.6 የምሳ ወይም የውሎ አበል አለመኖር ----------------------------91
ምዕራፍ አምስት - ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳብ ----------------------------92
51. ማጠቃለያ ----------------------------92
52. የመፍትሄ ሃሳብ ----------------------------97
ዋቢ ፅሁፎች ----------------------------99
መዘርዝር ቃላት ---------------------------- 104

# የአባሪዎች ዝርዝር


አባሪ 1 የኮሌጅ መምህራን የፅሑፍ መጠይቅ ---------- 105

አባሪ 2 የተማሪ አስተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ ---------- 108

አባሪ 3 የት/ቤት መምህራን የፅሑፍ መጠይቅ ---------- 111

አባሪ 4 ለኮሌጁ የፐራክቲከም ክፍል ኃላፊ የቀረቡ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች ---------- 114

አባሪ 5 ለት/ቤት ርዕሳነ መምህራን የቀረቡ የቃለመጠይቅ ጥያቄዎች ---------- 115

አባሪ 6 የምልከታ ቅፅ ---------- 116

አባሪ 7 የመገምገሚያ ቅፅ ---------- 118

# የሰንጠረዥ ማውጫ


ሰንጠረዥ 1፡- በሮቤ መምህራን ኮሌጅ የቋንቋ ስትሪም መምህራን አጠቃላይ ዳራዊ መግለጫ ---------- 35

ሰንጠረዥ 2፡- የኮሌጅ መምህራን ከፕራክቲከም በፊት ከተማሪዎች ጋር ተገናኝተው መወያየታቸውን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ የመምህራኑና የተማሪዎቹ ምላሽ ---------- 36

ሰንጠረዥ 3፡- የኮሌጅ መምህራን ከፕራክቲከም በኋላ ከተማሪዎች ጋር ተገናኝተው መወያየታቸውን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ የመምህራኑና የተማሪዎቹ ምላሽ ---------- 38

ሰንጠረዥ 4፡- በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት የኮሌጁ መምህራን በት/ቤት ተገኝተው ምልከታና ግምገማ ማድረጋቸውን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ የኮሌጁ መምህራን፣ የተማሪ አስተማሪዎችና የት/ቤት መምህራን ምላሽ ---------- 41

ሰንጠረዥ 5፡- በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት የኮሌጅ መምህራን በት/ቤት ተገኝተው ተገቢውን ምጋቢ ምላሽ መስጠታቸውን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ የኮሌጅ መምህራን፣ የተማሪ አስተማሪዎችና የት/ቤት መምህራን ምላሽ ---------- 44

ሰንጠረዥ 6፡- ከሮቤ መምህራን ኮሌጅ ጋር ፕራክቲከምን በጋራ በሚያከናወኑ ተባባሪ ት/ቤቶች የሚገኙ የቋንቋ መምህራን አጠቃላይ ዳራዊ መግለጫ ---------- 47

ሰንጠረዥ 7፡- የት/ቤት መምህራን በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት ለተማሪ አስተማሪዎች ያደረጉትን ሱፐርቫይዘራዊ ድጋፍ በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄዎች የት/ቤት መምህራን፣ የተማሪ አስተማሪዎችና የኮሌጅ መምህራን ምላሽ ---------- 49

ሰንጠረዥ 8፡- የት/ቤት መምህራን በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ
ሂደት ተገቢውን ምጋቢ ምላሽ ለተማሪ አስተማሪዎች
መስጠታቸውን በተመለከተ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች
የት/ቤት መምህራን፣ የተማሪ አስተማሪዎችና የኮሌጅ መምህራን ምላሽ --------51
ሰንጠረዥ 9፡- በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት የትምህርት
ዕቅድ አዘጋጃጀታቸውን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ
የተማሪ አስተማሪዎች፣ የት/ቤት መምህራንና የኮሌጅ
መምህራን ምላሽ--------54
ሰንጠረዥ 10፡- የተማሪ አስተማሪዎችን የትምህርት ዕቅድ ዝግጅት
በተመለከተ በመከታተያ ቅፁ ላይ ለቀረቡት ዝርዝር
ነጥቦች የኮሌጅ መምህራን ምላሽ --------55
ሰንጠረዥ 11፡- በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት ያለውን
የተማሪ አስተማሪዎች የትምህርት አቀራረብ
በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄዎች የተማሪ አስተማሪዎች፣
የት/ቤት መምህራንና የኮሌጅ መምህራን ምላሽ --------58
ሰንጠረዥ 12፡- የተማሪ አስተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ሥራዎች
/ተግባራት (activities) አቀራረብ በተመለከተ በመከታተያ
ቅፁ ላይ ለቀረቡት ዝርዝር ነጥቦች የኮሌጅ መምህራን ምላሽ --------59
ሰንጠረዥ 13፡- ተማሪ አስተማሪዎች በሚያስተምሩበት ወቅት የት/ቤት
ተማሪዎች የነበሩበትን ሁኔታ በተመለከተ ለቀረቡት ዝርዝር
ነጥቦች የኮሌጅ መምህራን ምላሽ --------61
ሰንጠረዥ 14፡- ተማሪ አስተማሪዎች በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ
ሂደት እክፍል ገብተው ሲያስተምሩ ያለውን የምዘና ሁኔታ
በተመለከተ ለቀረበ ጥያቄ የተማሪ አስተማሪዎች፣ የት/ቤት
መምህራንና የኮሌጅ መምህራን ምላሽ --------62
ሰንጠረዥ 15፡- የተማሪ አስተማሪዎችን የምዘና ሁኔታ በተመለከተ

በመከታተያ ቅፁ ላይ ለቀረቡት ዝርዝር ነጥቦች የኮሌጅ መምህራን ምላሽ ---------- 63
ሰንጠረዥ 16፡- በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት አጋዥ የማስተማሪያ መሣሪያዎችን በማዘጋጀት/ በመጠቀም በኩል ያከናወኑትን ተግባራት በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ ተማሪ አስተማሪዎች፣ የት/ቤት መምህራንና የኮሌጅ መምህራን ምላሽ ---------- 65
ሰንጠረዥ 17፡- በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት ከማስተማር ውጪ ባሉ ተግባራት ላይ ያላቸውን ተሳትፎ በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ የተማሪ አስተማሪዎች፣ የት/ቤት መምህራንና የኮሌጅ መምህራን ምላሽ ---------- 66
ሰንጠረዥ 18፡- ለፕራክቲከም የማስተማር ልምምዱ ሂደት ኮሌጁ ያዘጋጀውን የጊዜ ሰሌዳና የትራንስፖርት አገልግሎት በተመለከተ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የኮሌጅ መምህራን የት/ቤት መምህራንና የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ ---------- 69
ሰንጠረዥ 19፡- ለፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት አስፈላጊ የሆኑ የማስተማሪያ መሣሪያዎችንና ቅፆችን ኮሌጁ ማዘጋጀቱን በተመለከተ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የኮሌጅ መምህራን፣ የት/ቤት መምህራንና የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ ---------- 72
ሰንጠረዥ 20፡- በፕራክቲከም የማስተማር ልምምዱ ሂደት ኮሌጁ ለተማሪዎች ተገቢውን እገዛ የሚሰጥ መምህር መመደቡን፣ መምህራኑና ት/ቤቶች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን መከታተሉን በተመለከተ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የኮሌጅ መምህራን፣ የት/ቤት መምህራንና የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ ---------- 73
ሰንጠረዥ 21፡- ተባባሪ ት/ቤቶች ተገቢውን ልምድ ከት/ቤት ለመቅሰም

የሚያስችል የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀታቸውን በተመለከተ
ለቀረበላቸው ጥያቄ የኮሌጅ መምህራን፣ የት/ቤት
መምህራንና የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ ----------------------------------------76
ሰንጠረዥ 22፡- በፕራክቲከም ሂደት ለተማሪ አስተማሪዎች አስፈላጊውን
እገዛ የሚሰጥ መምህር በመመደብና ክትትል በማድረግ
በኩል ተባባሪ ት/ቤቶች ያደረጉትን በተመለከተ ለቀረቡላቸው
ጥያቄዎች የኮሌጅ መምህራን፣ የት/ቤት መምህራንና የተማሪ
አስተማሪዎች ምላሽ ----------------------------------------78
ሰንጠረዥ 23፡- ተባባሪ ት/ቤቶች በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ
ሂደት ተማሪ አስተማሪዎች የሚፈለገውን ልምድ ከት/ቤት
የሚቀስሙበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠራቸውንና ክትትል
ማድረጋቸውን በተመለከተ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የኮሌጅ
መምህራን፣ የት/ቤት መምህራንና የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ ----------------80

## የምኅረ ቃላት ዝርዝር

| | |
|---|---|
| መሚትስሂ | የመምህራን ሚና በትምህርትና ስልጠና ሂደት |
| መሚ | ማስታወቂያ ሚኒስቴር |
| ትሚ | ትምህርት ሚኒስቴር |
| ኢመትአግስፓ | የኢፌዴሪ መንግስት የትምህርትና የአቅም ግንባታ ስትራቴጂና ፖሊሲዎች |
| DES | Development of Education and Science |
| HDP | Higher Diploma Program |
| ICDR | Institute of Curriculum Development and Research |
| MOE | Ministry of Education |
| TESO | Teacher Education System Overhall |

# አጠቃሎ

በሮቤ መምህራን ኮሌጅ በ10+3 የዲፕሎማ መርሃ ግብር በቋንቋ ስትሪም ያለውን የፕራክቲከም አራት ኮርስ አተገባበር መፈተሽ፣ የዚህ ጥናት ዓይነተኛ ትኩረት ነው፡፡ በዚህም ጥናቱ በፕራክቲከም ትግበራው ሂደት ተሳታፊ የሆኑትን አካላት (የኮሌጅ መምህራን፣ የት/ቤት መምህራን፣ የተማሪ አስተማሪዎች፣ የኮሌጁና የተባባሪ ት/ቤቶችን) የሥራ ድርሻና ኃላፊነት ተመልክቷል፡፡ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችም ከነዚሁ የመርሃ ግብሩ ተሳታፊዎች በፅሑፍ መጠይቅ፣ በቃለመጠይቅ፣ በምልከታና በግምገማ ቅፅ አማካይነት ተጠናቅረዋል፡፡ የተጠናቀሩት መረጃዎችም በሊከርት የመቶኛ ምላሽ ተሰልተው በገላጭ የትንተና ዘዴ አማካይነት ተተንትነዋል፡፡ ከትንተናውም በመነሳት፣ በኮሌጁ የቋንቋ ስትሪም ያለው የፕራክቲከም አራት ኮርስ ትግበራ ሂደት በርካታ ችግሮች የሚንፀባረቁበት መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡ ከነዚህ ችግሮችም የተነሳ የመርሃ ግብሩ ተሳታፊዎች የሥራ ድርሻና ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ለመወጣት እንዳልቻሉም ለመመልከት ተችሏል፡፡

የኮሌጁ መምህራን ስለፕራክቲከሙ በተለይም ስለሱፐርቪዥኑ ካላቸው አሉታዊ አመለካከትና ለፕራክቲከም ከሚያማክሯቸው ተማሪዎች መብዛት የተነሳ ቅድመ ፕራክቲከም፣ በፕራክቲከሙ ሂደትና ድህረ ፕራክቲከም ለተማሪ አስተማሪዎች ያደረጉት ሱፐርቫይዘራዊ ድጋፍ በቂ ካለመሆኑም በላይ በተገቢው መንገድ የተከናወነም አልነበረም፡፡ በአንፃሩ የተባባሪ ት/ቤት መምህራን ግን ከኮሌጁ መምህራን አኳያ ለተማሪ አስተማሪዎቹ የሰጡት አጠቃላይ የሆነ ድጋፍና እገዛ ከፍተኛ ነበር፡፡ ይህም ለተማሪ አስተማሪዎቹ ከኮሌጁ መምህራን ያላገኙትን ድጋፍ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ያካካሰላቸው ቢሆንም፣ በተለይ የሱፐርቪዥኑ ሥራ ግን በዘርፉ የተካኑ ባለሙያዎችን የሚሻ ጉዳይ በመሆኑ የት/ቤት መምህራኑ የሰጡትን ሱፐርቫይዘራዊ ድጋፍ ብቃትና አስተማማኝነት አጠያያቂ አድርጎታል፡፡ ተማሪ አስተማሪዎቹ ደግሞ ቅድመ ፕራክቲከም ያለበቂ ንድፈ ሃሳባዊ ግንዛቤ ወደ ት/ቤቶች በመሠማራታቸው፣ ት/ቤቶቹም ቢሆኑ አስፈላጊውን ሙያዊ ልምድ ለመቅሰም ምቹ ሆነው ባለመገኘታቸው፣ በዚያ ላይ በት/ቤቶቹ ተገኝቶ ተከታታይና ቀጣይነት ያለው ሱፐርቫይዘራዊ ድጋፍ የሚሰጣቸው ባለሙያ (መምህር) ባለማግኘ ታቸው፣ ከት/ቤት ሲመለሱም ቢሆን ምን እንዳከናወኑ ተከታትሎ አቅጣጫ የሚያመላክታቸው ባለመኖሩ፣ (ተማሪዎቹ) በፕራክቲከም የማስተማር ልምምዱ ሂደት ከትምህርት ዕቅድ ዝግጅት አንስቶ ያከናወኗቸው አንዳንድ ተግባራት በበቂ ሁኔታ የዳበሩና የጎለበቱ ሆነው ሊገኙ አልቻሉም፡፡ ኮሌጁም ቢሆን የተጠናከረ የፕራክቲከም መምሪያ አደራጅቶ አጠቃላዩን መርሃ ግብር ባለማስተባበሩ፣ ከተባባሪ ት/ቤቶች ጋር በቅርበት በመስራት ለተማሪ አስተማሪዎቹ ተገቢውን ሙያዊ መቼት ባለመፍጠሩ፣ መምህራንና ተባባሪ ት/ቤቶች ተገቢውን ድጋፍ ለተማሪ አስተማሪዎቹ የሚሰጡበትን መንገድ ባለማመቻቸቱ እና አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥርም ባለማድረጉ፣ ጠቅላላው የፕራክቲከም መርሃ ግብር ሂደት እንዲመሰቃቀልና፣ ተማሪዎቹም አስፈላጊውን ሙያዊ ክህሎት እንዳይቀስሙ እንቅፋት ሆኗል፡፡ ከኮሌጁ ጋር ፕራክቲከምን

በትብብር የሚያከናውኑት ተባባሪ ት/ቤቶችም ቢሆኑ ከኮሌጁ ጋር የጠበቀ የሥራ ግንኙነት የሌላቸው በመሆኑ፤ ለተማሪ አስተማሪዎቹ ምቹና ተፈላጊው ሙያዊ ክህሎት የሚገበይባቸው ቦታዎች ሆነው ሊገኙ አልቻሉም።

ከነዚህም ምክንያቶች የተነሳ በኮሌጁ ያለው የፕራክቲከም ትግበራ ሂደት በተገቢው መንገድ ሊተገበር አልቻለም። ለዚህም ሰበብ ከሆኑት ጉዳዮች መካከል ዋና ዋናዎቹ የኮሌጁ ለመርሃ ግብሩ ተገቢውን ትኩረት አለመስጠት፤ የመርሃ ግብሩ በበቂ እቅድና ቅድመ ዝግጅት ላይ አለመመስረት፤ ከተባባሪ ት/ቤቶች ጋር ያለው ቅርርብ መላላት፤ የኮሌጁ መምህራንና የተማሪ አስተማሪዎቹ ቁጥር አለመመጣጠን፤ የተማሪ አስተማሪዎችና የት/ቤቶች ቁጥር አለመመጣጠን፤ ለተማሪ አስተማሪዎች የምሳ ወይም የውሎ አበል አለመኖር መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል። በመጨረሻም ጥናቱ ከተመለከታቸው ችግሮች በመነሳት፣ የተለያዩ የመፍትሄ ሃሳቦችን በመጠቆም ተቋጭቷል።

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ንድፈ ሃሣባዊ ትምህርትና ተግባራዊ ልምምድ በማንኛውም የትምህርትና የሙያ ስልጠና መርሃ ግብር ውስጥ የጎላ ሊገኙ የሚጠበቅባቸው ሁለት ተጣማሪ የትምህርት ገጽታዎች ናቸው (Wallace 1991፣121 Ellis 1986፣91 Walters 1960፣520)፡፡ የመምህራን ስልጠናም እንደ ሙያ ስልጠናነቱ ሁለቱን ገጽታዎች (ንድፈ ሃሣባዊ ትምህርትንና ተግባራዊ ልምምድን) አቀናጅቶ ይይዛል፡፡ ብቃትና ጥራት ያላቸውን መምህራንን ለማፍራትም በመምህራን ስልጠናው ሂደት እነዚህ ሁለት ገጽታዎች አንድ ላይ ተቆራኝተውና ተገቢው ትኩረት ተሰጥቷቸው ሊገኙ ይገባል፡፡ ይሁንና በኢትዮጵያ መምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት ውስጥ ተግባራዊው የማስተማር ልምምድ (teaching practices) ከንድፈሃሣባዊው ዕውቀት ጋር ሲነፃፀር ተገቢ የሆነ ትኩረትና ጊዜ ተሰጥቶት በአግባቡ እንደማይከናወን የተለያዩ ጥናታዊ ጽሁፎችና መንግስታዊ ሰነዶች ያመለክታሉ (ኅለም 1988፣ መስለ 1990፣ ተሰጠ 1997፣ ት.ሚ፣ 1994 ማ.ሚ. 1994 Azeb 1984 Alemayehu 1998 Gebremedhin 2001 Kindalem 2005 ICDR 1999)፡፡

በመምህራን ስልጠና መርሃ ግብር ብቁና ጥራት ያላቸው መምህራንን ለማፍራት ይቻል ዘንድ፣ ተማሪ አስተማሪዎች (student teachers) ንድፈ ሀሣብን ከተግባራዊው ክህሎት ያዋሃደ እውቀትን ከመምህራን ማሰልጠኛ ተቋሙ እንዲሁም በቂ የሆነ የማስተማር ልምድን (ክህሎትን) ከት/ቤቶች መቅሰም ይኖርባቸዋል (Walters 1960፣ 52 Perrot 1982፣8 Ellis 1986፣91 Wallace 1991፣ 121)፡፡ ይህ ተማሪ አስተማሪዎች በት/ቤት አውዳዊ መቼት ውስጥ ተገኝተው ማስተማርን የሚለማመዱበት ተግባራዊ የመማር ሂደትም የማስተማር ልምምድ ይባላል፡፡ በዚህ ሂደትም ተማሪ አስተማሪዎቹ ስለማስተማሩ ሙያ ተግባራዊ ልምምድ ያደርጋሉ፤ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ የቀሰሙትን ዕውቀት በት/ቤቶች ውስጥ ተገኝተው በተግባር ይፈትሻሉ፡፡ በዚህም ወደፊት በማስተማሩ ስራ ላይ ሲሰማሩ በት/ቤቶችና በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ በተጨባጭ ሊያጋጥሟቸው ስለሚችሉ ሁኔታዎች ከወዲሁ በተግባር የተደገፈ መፍትሔ ማዘጋጀት ይችላሉ (Brown 1975፣13 Srivastava and Bose 1978፣112 Gowers and Walters 1983፣1)፡፡ ይህም በመምህራን ስልጠና ሂደት ተግባራዊው ልምድ ያለውን ወሳኝ ሚና ያመለክታል፡፡

ይሁን እንጂ ይህ ወሳኝ ተግባራዊ ልምድ በኢትዮጵያ በሚገኙ የመምህራን ስልጠና ተቋማት ውስጥ በተገቢው ሥርአት የተከናወነ አልነበረም፡፡ ከዚህም የተነሳ በተለይ የመጀመሪያ ደረጃ መምህራን ስልጠና መርሃ ግብር ብቃትና ጥራት ከሚጠበቀው በታች እንዲሆን ማድረጉን

የተለያዩ ጥናታዊ ጽሁፎችና መንግስታዊ ሰነዶች በአጽንኦት ይገልፃሉ:: ይህንንም እውነታ ICDR (1999፣248) እንደሚከተለው አጠቃሎ ያስቀምጠዋል::

> . . .(በኢትዮጵያ) የመጀመሪያ ደረጃ መምህራን ስልጠናው ከታች፣ ከተማሪዎች ምልመላ ጀምሮ ያለው አጠቃላዩ የስልጠና ሂደት አጥጋቢ አይደለም:: ከዚህ አንፃርም በንድፈ ሃሳባዊና ሙያዊ ክህሎት የበለፀጉ (ብቁ) መምህራንን ለማፍራት የሚያስችሉ የተለያዩ ማሻሻያዎች ተደርገዋል፤ ይሁንና አሁንም ድረስ በመምህራን ስልጠናው ብቃትና ጥራት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሣድሩ ነገሮች መኖራቸው አልቀረም:: ከነዚህም መካከል የማስተማር ልምምድን በተገቢው ሥርአት ያለመተግበር በግምባር ቀደምትነት የሚጠቀስ ችግር ነው:: ...

ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው፣ የመምህራን ስልጠናው ሂደት (በተለይም የመጀመሪያ ደረጃው) በበርካታ ውስብስብ ችግሮች የተተበተበ እና የሰልጣኞችን ሙያዊ ክህሎት የማጎልበት አቅሙም ዝቅተኛ መሆኑን ነው:: ይህንንም ለማሻሻል የተለያዩ እርምጃዎች ቢወሰዱም ችግሩን ከመሰረቱ ሊያስወገዱ አልቻሉም:: በቀላሉ ሊስተካከሉ ካልቻሉ ችግሮችም መካከል በዋናነት የሚጠቀሰው ደግሞ በማስተማር ልምምድ ላይ የሚስተዋለው ጉልህ የአተገባበር ድክመት ነው:: ይህም በአጠቃላዩ የመምህራን ስልጠና መርሃ ግብር ብቃትና ጥራት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አሳድሯል:: ስለሆነም የአጠቃላዩን ስልጠና ሂደት ለማሻሻልና ለማሣደግ ቀደም ሲል በነበረው የማስተማር ልምምድ ልማድ (trend) ላይ ስር ነቀል የሆነ ለውጥ ይደረግ ዘንድ ግድ ይላል:: አዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲም ይህንና መሰል የቀደምት የመምህራን ስልጠናውን ድክመቶች ለመቅረፍ ታልሞ የተቀረፀ መሆኑን የተለያዩ መንግስታዊ ሰነዶች ያመለክታሉ (ት.ሚ. 1994 ማ.ሚ. 1994 መ.ሚ.ት.ስ.ሂ. 1998 ኢ.መ.ት.እ.ግ.ስ.ፖ. 1998 MOE 2003)::

በአዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ቀደም ሲል ተገቢው ትኩረትና ጊዜ ያልተሰጠው የማስተማር ልምምድ፣ ፕራክቲከም (practium) በሚባል ኮርስ አማካይነት የተሻለ ቦታና ትኩረት ተሰጥቶት ይገኛል:: ፕራክቲከም ተማሪ አስተማሪዎች ረዘም ያለ ጊዜ ወስደው፣ ወደፊት በሚሰማሩበት ተጨባጭ ሙያዊ መቼት (professional setting) ውስጥ በአካል ተገኝተው፣ ሙያዊ ነገሮችንና ሁነቶችን ተግባራዊ በሆነ አውድ ውስጥ የሚማሩበት የማስተማር ልምምድ ኮርስ ነው (MOE 2003፣ 12):: በፕራክቲከም ተማሪ አስተማሪዎች ከምልከታ አንስቶ እስከ ተግባራዊው የክፍል ውስጥ የማስተማር ሥራ ያሉ በርካታ ሙያዊ ተግባራትን በማከናወን የተሟላ የመምህርነት ልምድ ይቀስማሉ:: ከዚህም በተጨማሪ ከማስተማር መማሩ ሂደት ጋር በተያያዘ ተግባራዊ ምርምር ያካሂዳሉ::

ፕራክቲከም በተሻሻለው የMOE TESO (2003) ሰነድ መሠረት፣ በመጀመሪያ ደረጃ የሁለተኛ ሳይክል መምህራን ስልጠና መርሃ ግብር (10+3) በአራት ኮርሶች ተከፋፍሎ ይሰጣል:: የየኮርሶቹ ዋና ዋና ትኩረትም በአጭሩ የሚከተለውን ይመስላል::

ፕራክቲከም አንድ፡- በአንደኛው ዓመት በሁለቱም ሴሚስተሮች ላይ የሚሰጥ ባለ4 ክሬዲት የፕራክቲከም መግቢያ (introduction) ኮርስ ሲሆን ዋንኛ ትኩረቱም ምልከታ (observation)፣ ጥናታዊ ምርመርና ዕብረታ (reflection) ነው:: በዚህ ኮርስ ከመምህሮቻቸው በሚደረግላቸው ማብራሪያ እየታገዙ፣ ተማሪ አስተማሪዎች ስለፕራክቲከም ምንነት አጠቃላይ የሆነ ግንዛቤን ይጨብጣሉ፣ እንዲሁም ስለጥናታዊ ምርምር አከናወን መሠረታዊ ክሁሎትን ይቀስማሉ:: በት/ቤት ተገኝተው በሚያደርጉት የምልከታ ሂደትም የተገነዘቡትን በዕብረታ አማካይነት እርስበርሳቸው ሃሳብ በመለዋወጥ ሙያዊ ግንዛቤያቸውን ያጎለብታሉ (TESO 2003)::

ፕራክቲከም ሁለት፡- በሁለተኛ ዓመት በሁለቱም ሴሚስተሮች ላይ የሚሰጥ ባለ4 ክሬዲት ኮርስ ነው:: ዓይነተኛ ትኩረቱም ምልከታና ረዳት መምህርነት ነው:: ይህ ኮርስ ተማሪ አስተማሪዎች ወደ ዋናው የማስተማር ሥራ ለመግባት ቅድመ ዝግጅት የሚያደርጉበት እንደመሆኑ መጠን፣ተገቢውን የማስተማር ልምምድ ለማድረግ የሚያስችል መሠረታዊ ግንዛቤና ክሁሎትን መቅሰም ይጠበቅባቸዋል:: ይህንንም መሠረት በማድረግ በዚህ ኮርስ ለት/ቤት መምህራን የተወሰኑ ተግባራዊ እገዛዎችን እየሰጡ ማስተማርን ይለማመዳሉ (TESO 2003)::

ፕራክቲከም ሦስት፡- በሦስተኛ ዓመት አንደኛው ሴሚስተር ላይ የሚሰጥ ባለ4 ክሬዲት ኮርስ ነው:: ዋንኛ ትኩረቱም የማስተማር ልምምድ፣ ጥናታዊ ምርምርና ዕብረታ ናቸው:: በዚህ ኮርስ ተማሪ አስተማሪዎች ከቀደሙት የፕራክቲም ኮርሶች የበለጠ ሰፊ ጊዜ ወስደው ማስተማርን ይለማመዳሉ:: በተናጠልም ሆነ በቡድን ሆነው የሚያስተምሩበት አጋጣሚም ከፍ ይላል:: በአጭሩ በመምህሮቻቸው (ሱፐርቫይዘሮቻው) የቅርብ ክትትልና ምክር ሥር ሆነው የሚሰለጥኑበትን የትምህርት ዓይነት ማስተማርን ይለማመዳሉ:: ከማስተማሩ ውጪ ባሉ (co-curricular) ተግባራትም ላይ ተሳትፎ ያደርጋሉ (TESO 2003)::

ፕራክቲከም አራት፡- በሦስተኛ ዓመት የመጨረሻው ሴሚስተር ላይ በ5 ክሬዲት የሚሰጥ ኮርስ ነው:: ኮርሱ ሙሉ በሙሉ የሚያተኩረውም በማስተማር ተግባር ላይ ነው (full integration):: ተማሪ አስተማሪዎች ሙሉውን ጊዜያቸውን በክፍል ውስጥ የማስተማር ተግባር ላይ ተሳትፈው፣ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ የቀሰሙትን የማስተማር ትወራዎችና ሥነዘዴዎችን በእውናዊው መቼት ውስጥ ይተገብራሉ፣ ንድፈሃሳብን ከተግባር ያዋህዳሉ:: ከዚህም ባሻገር ከተማሪዎች ወላጆች ጋር መወያየት፣ የማስተማሪያ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት፣ሥርዓተ ትምህርቱን መሠረት ያደረገ ጥናታዊ ምርምር ማካሄድ፣ በተለያዩ መረጃዎች የተካበተ ጥራዝ መጣጥፍ (portfolio) ማዘጋጀት ወዘተ. ይጠበቅባቸዋል:: በዚህ የፕራክቲከም ሂደትም ተማሪ አስተማሪዎች በተቻለ መጠን ከከተማ ወጣ ባሉ ት/ቤቶች ላይ ቢመደቡ ተመራጭ ነው (TESO 2003)::

በአጠቃላይ ከፍሲል ከተመለከቱት የፕራክቲከም ኮርሶች መካከል ይህ ጥናት መሠረት የሚያደርገው የስልጠና መርሃ ግብሩ የመጨረሻ የሆነውን፣ ፕራክቲከም አራትን ይሆናል። በዚህም ላይ በመመስረት በኦሮሚያ ክልላዊ መስተዳድር በሮቤ መምህራን ኮሌጅ በ10+3 የዲፕሎማ መርሃ ግብር በቋንቋ ስትሪም ያለውን የፕራክቲከም አራት ኮርስ አተገባበር ሂደት መፈተሽ የጥናቱ ዓይነተኛ ትኩረት ነው። አጥኚውን በዋናነት ለዚህ ጥናት ያነሳሳውም፣ በሮቤ መምህራን ኮሌጅ በሚያስተምርበት ወቅት በኮሌጁም ሆነ በሌሎች አቻ የክልሉ ኮሌጆች በፕራክቲከም አተገባበር ዙሪያ ያስተዋላቸው ግራ መጋባቶች ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ ተሰጠ (1997) «በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ» እንዲሁም Kindalem (2005) «በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሥነ ትምህርት ኮሌጅ» ፕራክቲከምን አስመልክቶ ባካሄዱት ጥናት የተመለከቷቸው አንዳንድ  ጉዳዮች (ችግሮች)፣ አጥኚውን ለዚህ ጥናት ይበልጥ ገፋፍተውታል። በሌላ በኩል ደግሞ የፕራክቲከም መርሃ ግብር በሃገር አቀፍ ደረጃም (ገና) ከ1996 ጀምሮ ሥራ ላይ የዋለና አዲስ ከመሆኑም አንፃር፣ በአፈፃፀሙ/ አተገባበሩ ሂደት ላይ እየተከሰቱ የሚገኙትን ግራ መጋባቶችና ችግሮች በአፋጣኝ ተከታትሎ መፍትሄ መፈለግ ተገቢ ይሆናል። አለበለዚያ ግን እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ፣ በአጠቃላዩ የመምህራን ስልጠና መርሃ ግብር ብቃትና ጥራት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል የሚል ስጋት አለ። ከዚህም የተነሳ የፕራክቲከም ትግበራው ሂደት በተገቢው መልኩ ታይቶ መፈተሽ  እንዳለበት አጥኚው ያምናል። ይህን ጥናት ለማካሄድ አጥኚውን ያነሳሱት መሠረታዊ ጉዳዮችም እነዚህ ናቸው።

## *1.2. የጥናቱ ዓላማ*

በኦሮሚያ ክልላዊ መስተዳድር በሮቤ መምህራን ኮሌጅ በ10+3 የዲፕሎማ መርሃ ግብር፣ በቋንቋ ስትሪም ያለውን የፕራክቲከም ኮርስ የአተገባበር ሁኔታ መፈተሽ የዚህ ጥናት ዐብይ ዓላማ ነው። ለዚህም ጥናቱ መሠረት የሚያደርገው TESO (2003) በፕራክቲከም መርሃ ግብሩ ትግበራ ሂደት የሚሳተፉ አካላትን የሥራ ድርሻና ኃላፊነት በተመለከተ ያስቀመጠውን ሃገር አቀፍ መመሪያ ነው። ይህንንም መነሻ በማድረግ ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል።

1. በሮቤ መምህራን ኮሌጅ በ10+3 የዲፕሎማ መርሃ ግብር በቋንቋ ስትሪም ያለውን የፕራክቲከም አራት ኮርስ የኮሌጁ መምህራን፣ የት/ቤት መምህራን እና ተማሪ አስተማሪዎች እንዴት እየተገበሩት ነው?
2. የሮቤ መምህራን ኮሌጅና ተባባሪ ት/ቤቶች ለአጠቃላዩ የፕራክቲከም መርሃ ግብር ትግበራ መሳካት ምን ያህል የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ እየተወጡ ነው?
3. በሮቤ መምህራን ኮሌጅ በ10+3 የዲፕሎማ መርሃ ግብር (በቋንቋ ስትሪም) ፕራክቲከምን በመተግበሩ ሂደት ያጋጠሙ ዋና ዋና እንቅፋቶች/ችግሮች የትኞቹ ናቸው?

## 1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት በቅርቡ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ መሆን የጀመረውን የፕራክቲከም(አራት) ኮርስ የአተገባበር ሂደት ይፈትሻል። በዚህም በአተገባበር ሂደቱ ላይ የታዩ አዎንታዊና አሉታዊ ሁኔታዎችን ለይቶ ያሳያል፤ ተጠናክረው የሚቀጥሉበትንና የሚቀረፉበትን/ የሚሻሻሉበትን መንገድም ያመላክታል። ከዚህ አንፃርም ጥናቱ በማስከተል የተመለከቱትን ጠቀሜታዎች ሊያስገኝ ይችላል ተብሎ ይታሰባል።

1. በርቤ መምህራን ኮሌጅ ያለውን የፕራክቲከም አራት አተገባበር ሂደት በመመርመር በሚገኘው ውጤት፤ ኮሌጁ በትግበራው ሂደት የታዩትን ዋና ዋና ጠንካራና ደካማጎኖች ለይቶ ለማወቅ ያስችለዋል። ይህም ደካማ ጎኖቹ የሚቃኑበትን፤ ጠንካራ ጎኖቹም ይበልጥ የሚጠናከሩበትን መንገድ እንዲያፈላልግ ትልቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በመሆኑም ኮሌጁ ከዚህ ጥናት የመጀመሪያው ቀጥተኛ ተጠቃሚ ይሆናል።

2. በኦሮሚያ ክልላዊ መስተዳድር ሥር ከሚገኙ ከ6 በላይ የመምህራን ስልጠና ተቋማት አንዱ ሮቤ መምህራን ኮሌጅ ነው። ስለሆነም በኮሌጁ የሚስተዋለው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ሁኔታ በሌሎቹም የክልሉ አቻ ተቋማት ላይ መንፀባረቁ አይቀርም። ስለዚህም በዚህ ጥናት በኮሌጁ ያለውን የፕራክቲከም ትግበራ ሂደት በተመለከተ የሚደረስበትን ውጤት/ ድምዳሜ መሠረት አድርጎ፤ የክልሉ የትምህርት ቢሮ የክልሉን የመምህራን ስልጠና ሂደት እንዲገመግም፤ ከዚህም ተነስቶ የማስተካከያ እርምጃዎችን እንዲወስድ ያስችለዋል ተብሎ ይታሰባል።

3. ይህ ጥናት በ10+3 የመምህራን ስልጠና መርሃ ግብር የሚሰጠውን የፕራክቲከም ኮርስ የአተገባበር ሁኔታ የሚፈትሽ እንደመሆኑ መጠን፤ ለደረጃው መርሃ ትምህርት የሚቀርፁና (ለመርሃ ግብሩ) የአተገባበር መመሪያ የሚያዘጋጁ አካላትም የዚህ ጥናት ተጠቃሚ ይሆናሉ። በዚህም (ጥናቱ) እነዚህ አካላት በፕራክቲከም ዙሪያ ያሉትን ሁኔታዎችና እየተከሰቱ ያሉትን ችግሮች እንዲመለከቱበት፤ የተሻለ መርሃ ትምህርትና የፕራክቲከም አተገባበር መመሪያ እንዲያደራጁ መነሻ ይሆናቸዋል ተብሎ ይገመታል።

4. ፕራክቲከም  በኢትዮጵያ የመምህራን ትምህርትና ስልጠና ሂደት ውስጥ ለረጅም  ጊዜ የቆየውን የማስተማር ልምምድ ተክቶ፤ በአዲስ መልክ ብቅ ያለ አቀራረብ ነው። ስለሆነም በጉዳዩ ዙሪያ ወደፊት ተከታታይና ቀጣይነት ያላቸው ጥናቶች ይካሄዳሉ ተብሎ ይጠበቃል። ይህ ጥናትም ፕራክቲከምን በተመለከተ ተጨማሪ ጥናት ሊደረግባቸው የሚገቡ ነጥቦችን በመጠቆም፤ ወደፊት ለሚካሄዱ ጥናቶችም የመነሻ ሃሳብ በመስጠት ሊያገለግል ይችላል ተብሎ ይታሰባል።

## 1.4. የጥናቱ ክልልና ገደብ

በሮቤ መምህራን ኮሌጅ በ10+3 የዲፕሎማ መርሃ ግብር፣ በቋንቋ ስትሪም ያለውን የፕራክቲከም የአተገባበር ሂደት መፈተሽ የዚህ ጥናት ዓላማ ነው። ዓይነተኛ ትኩረቱም በፕራክቲከም መርሃ ግብሩ ትግበራ ላይ ተሳታፊ በሆኑት አካላት ላይ ሲሆን፤ እነሱም ኮሌጁ፣ ተባባሪ ት/ቤቶች፣ የኮሌጁ መምህራን፣ የት/ቤቶቹ መምህራንና ተማሪ አስተማሪዎች ናቸው። በዚህም ጥናቱ ተሳታፊ አካላቱ በፕራክቲከም አራት ሂደት በሚኖራቸው የሥራ ድርሻና ኃላፊነት (duties and responsibilities) ላይ ብቻ የተገደበ ነው። ለዚህም ጥናቱ በ10+3 መርሃ ግብር ካሉት የፕራክቲከም ኮርሶች መካከል ፕራክቲከም አራትን (IV) ብቻ መሠረት የሚያደርግ ይሆናል። ስለዚህ ጥናቱ በሁሉም የፕራክቲከም ጉዳዮችና ኮርሶች ላይ የሚያተኩር ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም።

## 1.5. ስለ ሮቤ መምህራን ኮሌጅ አጭር ቅኝት

የሮቤ መምህራን ኮሌጅ በኦሮሚያ ክልላዊ መስተዳድር በባሌ ዞን ዋና ከተማ—በሮቤ፣ ከአዲስ አበባ 430 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ይገኛል። የኮሌጁ ምስረታ በ1972 ሲሆን፤ እስከ 1984 ድረስም 'ሮቤ መምህራን ማሰልጠኛ ተቋም' በሚል ስያሜ በትምህርት ሚኒስቴርና በከፍተኛ ትምህርት ተቋም (አስተዳደር) ሥር ሆኖ የመጀመሪያ ደረጃ መምህራንን በሰርተፊኬት ደረጃ ሲያስለጥን ቆይቷል። ከ1985 ጀምሮ ግን በኦሮሚያ ክልላዊ መስተዳድር ሥር ሆኖ፣ ለክልሉ የአንደኛና የሁለተኛ ሳይክል መምህራንን በማሰልጠን ላይ ይገኛል። ከዚህ ጊዜ ጀምሮም የሚያስለጥናቸውን መምህራን ከአማርኛና ከእንግሊዘኛ ኮርሶች በስተቀር (ያሉትን ኮርሶች) ሙሉ በሙሉ የሚያስለጥነው በክልሉ የሥራ ቋንቋ — በአፋን ኦሮሞ ሆኗል ።

ኮሌጁ ከሮቤ መምህራን ማሰልጠኛ ተቋምነት" ወደ 'ሮቤ መምህራን ኮሌጅነት" ያደገው ከ24 ዓመታት በኋላ በ1995 ነው። በነዚህ ዓመታት ውስጥም በመደበኛ፣ በክረምት እና በማታው መርሃ ግብር 15,168 የመጀመሪያ ደረጃ መምህራንን (11,241 ወንድና 3,927 ሴት) በሰርተፊኬት ደረጃ አሰልጥኖ ለሥራ አብቅቷል (Kolleejjii Barsiisotaa Roobee 1995፣12-15)። ኮሌጁ ከሰርተፊኬት ስልጠና ወደ ዲፕሎማ መርሃ ግብር በተሸጋገረበት ወቅትም (1995) 450 መደበኛ ተማሪዎችን (371 ወንድና 79 ሴት) ተቀብሎ፤ በ1996 በስድስት የትምህርት ዘርፎች (አፋን ኦሮሞ፣ አማርኛ፣ እንግሊዝኛ፣ ታሪክ፣ ጂኦግራፊና ፊዚክስ) ለመጀመሪያ ጊዜ በ12+2 ደረጃ አስመርቋል።

በአሁኑ ወቅት ኮሌጁ ከ1996 አንስቶ በሃገር አቀፍ ደረጃ መተግበር በጀመረው የ TESO ፓራዳይም ሺፍት (Paradigm shift) መርሃ ግብር መሠረት ተማሪዎችን ተቀብሎ በአምስት የመምህራን ስልጠና ስትሪሞች (በተፈጥሮ ሳይንስ፣ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በቋንቋ፣ በሥነውበት እና በሥነዜጋና ሒሳብ) እያስተማረ ነው (Robe Techers College 2004)። በዚህ መረሠትም

ኮሌጁ በ10+3 እና በ10+1 መርሃ ግብር ከ7,000 በላይ ተማሪዎችን (በቀን፣ በማታና በክረምት) በማሰልጠን ላይ ይገኛል:: ኮሌጁ ከመምህራን ስልጠና ውጪም በአሰልጣኝነት (Coaching) እና በሰው ኃይል አስተዳደር (human resource management) 369 ሰልጣኞችን ተቀብሎ በማስተማር ላይ እንደሚገኝ ከኮሌጁ የሬጅስትራር ፅ/ቤት የተገኘው መረጃ ያመለክታል:: በአጠቃላይ የሮቤ መምህራን ኮሌጅ ካለው የረጅም ጊዜ ልምድና አሁን ከሚገኝበት ይዞታ አንፃር፣ በቅርቡ በከተማው የተመሠረተው - የሮቤ መደወላቡ ዩኒቨርስቲ አካል ይሆናል ተብሎ ይገመታል::

# ምዕራፍ ሁለት
# የተዛማጅ ፅሑፎች ቅኝት

## 2.1. የመምህራን ስልጠናና የማስተማር ልምምድ

### 2.1.1 ማስተማር ምንድነው?

ወደ መምህራን ስልጠና አጠቃላይ ባህሪ ዘልቀን ለማለፍ ከመሞከራችን በፊት በቅድሚያ ማስተማር ምንድነው የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ እንሞክራለን፡፡ ማስተማር ምንድነው? ሲባል ብዙውን ጊዜ «ጥበብ ነው» ወይም «ሳይንስ ነው» የሚሉ ምላሾች ሲቀርቡ ይስተዋላል፡፡ ምንም እንኳን ሁለቱም ምላሾች የተለያየ መሠረትን መነሻ አድርገው የቀረቡ ቢሆንም ለረጅም ጊዜ ግን ጎን ለጎን ተቀምጠው፣ አገልግሎት ላይ ሲውሉ ቆይተዋል፡፡ ለዚህም ዋነኛው ምክንያት ሁለቱም የማስተማርን መሠረታዊ ባህሪያት ይዘው መገኘታቸው ነው፡፡

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ማስተማር ጥበብ (art) ብቻ ነው ተብሎ ይታሰብ ነበር፡፡ በመሆኑም መምህራንም ሙያቸውን ሙሉ በሙሉ ጥበብ አድርገው ይመለከቱ ነበር፡፡ ይህም የማስተማር ሙያ በመሠረቱ የማይተነተን (unanalysable) እና የማይማሩት፤ አንድ ሰው ከውስጡ ያለውን ተፈጥሮአዊ ችሎታ ብቻ በልምምድ አዳብሮት የሚያገኘው ተደርጎ በመወሰዱ ነው (Corder 1973፣9 Celce-Murcia 1991 ፣12)፡፡ ከዚህም ማስተማር በትምህርት ወይም በስልጠና የሚመጣ ሳይሆን እንደተፈጥሮአዊ ስጦታ ተደርጎ መታየቱን መረዳት ይቻላል፡፡

ይህ ማስተማር ጥበብ ነው የሚለው አመለካከት በጣም ጥንታዊ ሲሆን መሠረታዊ እንኳሉም ማስተማርን እንደ አንድ የጥበብ ዘርፍ አካል ከመመልከት የመጣ ነው፡፡ Stones and Morries (1972) Smith (1980) እንደሚሉት በወቅቱ ማስተማር እንደ ዕደጥበብ፣ ስዕል፣ ግጥም... ሁሉ ምድቡ ከሥነ ጥበብ ነበር፡፡ ስለሆነም ቀራቢነትን፣ ሰዓሊነትን ወይም ገጣሚነትን በትምህርት ወይም በስልጠና ብርታት ብቻ ማግኘት እንደማይቻለው ሁሉ፤ መምህርነትንም ከዚህ መንገድ ውጪ ማግኘት አይቻልም ተብሎ ይታሰብ ነበር፡፡ ከዚህም የተነሳ "መምህራን ይወለዳሉ (born) እንጂ አይፈጠሩም (made)" የሚል ዕሳ እምነት ሊዳብር ችሏል (Dunkin 1987፣682)፡፡ ስለዚህ በዚህ አተያይ መሠረት አንድ ሰው ተምሮ ወይም ስልጠና ወስዶ ብቻ መምህር መሆን አይችልም፤ የማስተማር ተፈጥሯዊ ስጦታ ወይም ተሰጥኦ ከሌለው በቀር፡፡ ይሁንና ይህ አተያይ በርግጥም የማስተማርን ጥበብነት ወይም ክህሎትነት ቢያመለክትም፤ ሙሉ በሙሉ ግን ማስተማርን ጥበብ ሊያሰኘው የሚያስችል አይደለም፡፡

እነ Brown (1975፣4) Celce-Murcia (1991፣12) እንደሚሉት ማስተማር ጥበብ ነው ማለት፤ በሌላ አገላለፅ ማስተማርን አያስተምሩትም ማለት ነው፡፡ ይህም ማለት መምህርነት በትምህርት አይገኝም ወይም መምህር ለመሆን መስልጠን አያስፈልግም ማለት ነው፡፡ ይሁን

እንጂ መምህር ለመሆን ጥበብ /ክህሎት ብቻ በቂ አይደለም፤ ስልጠና ወይም ትምህርትም ያስፈልጋል። ምክንያቱም ማስተማር እንደ ዕደጥበብ ክህሎትን ብቻ የሚጠይቅ ሳይሆን የሚማሩት ሙያም ነው። አንድ መምህር የማስተማር ቴክኒኮችን የተካነ መሆኑ ብቻ በቂ አይደለም፤ ስለሚያስተምረው የትምህርት ዓይነትም የጠለቀ ዕውቀት ሊኖረው ይገባል። 'እንደውም ስኬታማ ማስተማር (ክህሎት ብቻ ባላቸው ሳይሆን) በደንብ በተማሩም ሰዎች ብቻ ነው መከናወን የሚችለው'(Dent 1961፣73)። በWalters (1960፣19) ሃሳብ መሠረትም መምህርነት እንደ ሾፌርነት የጥበብ/ ክህሎት ውጤት ብቻ አይደለም። መምህርነት ከዚህም ባሻገር የሰውየውን የግል ስብዕና (personal qualities)፣ ከመሠረታዊ ዕውቀትና ሙያዊ ክህሎት ጋር አንድ ላይ ተጣምሮ መገኘትን ግድ የሚል ነው። መምህሩ ይህን አሟልቶ መገኘት የሚችለው ደግሞ ተገቢውን ስልጠና ወይም ትምህርት ሲያገኝ ብቻ ነው። ስለዚህ ብቃት ያለው መምህር ለመሆን ስልጠና ግድ ነው።

በመደበኛው የማስተማር ሂደት ውስጥ መምህር መሆን፣ አራት ጉዳዮችን ጠንቅቆ ማወቅና መተግበርን ይጠይቃል። በዚህ ሂደት ውስጥ መምህሩ ሥራውን በአግባቡ ለማከናወን (ከሃገሪቷ አጠቃላይ ሥርዓት አንፃር) የትምህርት ሥርዓቱን ዓላማና ግብ፣ የትምህርቱን አስፈላጊነትና ጠቀሜታ፣ ትምህርቱ መሠረት የሚያደርጋቸውን ሳይንሳዊ ትወራዎች እና የማስተማር ሥነ ዘዴውን (አቀራረቡን) በወጉ ማወቅ ይጠበቅበታል (Kelly 1976፣1)። ይህም ማስተማርን ወይም መምህርነትን መሰልጠን ወይም መማር የሚቻል ብቻ ሳይሆን፣ የግድ የሚያስፈልግ መሆኑንም ያጠናክራል። ይህም ማስተማር ጥበብ/ክህሎት ብቻ ሳይሆን ሳይንስም ጭምር መሆኑን ያሳያል።

በአጠቃላይ ሲታይ ማስተማር «ጥበብ ነው» የሚለውም ሆነ «ሳይንስ ነው» የሚለው ምልከታ ለየብቻቸው የማስተማርን ምንነት በደንብ የማሳየት አቅም የላቸውም። ማስተማር ገላጭ ተሰጥኦን ለመተግበር ማመቻቱ፣ በተከታታይ ልምምድ ሊዳበርና ሊጎለብት መቻሉ የጥበብ ፡ ክህሎትነቱ መገለጫ ነው። ይህ ማለት ግን ሊማሩት የማይችሉና የማይተነተን ነው ማለት አይደለም። ማስተማርን ማስተንተንና መማር/መሰልጠንም ይቻላል። ይቻላል ብቻም ሳይሆን መምህር ለመሆን ማስተማርን መማር ወይም መሰልጠን ግድ ነው። ማስተማር እንደስዕል መሳል ወይም መኪና መንዳት የጥበብ ወይም የክህሎት ጉዳይ ብቻ አይደለም። 'ማስተማር በራሱም ተግባራዊ ሳይንስ (applied science) ነውና' (Kelly1976 Walters1960 Celce-Murcia1991 Corder 1973)። ስለሆነም መምህሩ በሚያስተምርበት ወቅት የግድ መሠረት ሊያደርጋቸው የሚገቡ ሳይንሳዊ መርሆዎች፣ መመሪያዎች፣ ደንቦችና ሥርዓቶች አሉ። ይህ፣ ማስተማር በራሱ ተግባራዊ ሳይንስ መሆኑ፣ ሊተነተንና ሊማሩት (ሊሰለጥኑበት) መቻሉ ደግሞ የሳይንስነቱ መገለጫ ነው። ስለዚህ ማስተማር የጥበብም የሳይንስም ውሁድ አሃድ ነው። ብቃት ያለው መምህርም የነዚህ ሁለቱ የማስተማር ባህሪያት

ባለቤት ነው። እንደነ Corder (1973፣10) Celce-Murcia (1991፣13) ሃሳብም የተዋጣለት መምህር በመሠረቱ አርቲስት ሆኖ ያን አርቲስትነቱን በሳይንሳዊ መርሆዎች፣ መመሪያዎችና ደንቦች ገደብ ውስጥ (frame work) የሚተገብር ነው። በአጠቃላይ ስለማስተማር ጥበብ ሳይንስነት ይህን ካልን፤ በማስከተል ደግሞ «ማስተማር ምንድነው?» የሚለውን በአጭሩ ለመመለስ እንሞክራለን።

እንደKelly ማስተማር ማለት ሁለት መሠረታዊ ነገሮችን ይዞ መገኘት መቻል ነው። የሚያስተምሩት ትምህርት በተማሪዎች ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ፤ ተወዳጅ እንዲሆን ማስቻል አንደኛው ሲሆን፤ ያን ተማሪዎች የተቀበሉትንና ለመማር የፈቀዱትን ትምህርት እንዲረዱት ማድረግ ማስቻል ደግሞ ሌላኛው ነው (1976፣ 278)። እነዚህ ሁለቱ የማስተማር መሠረታዊ ነገሮችም የውጤትና ሳቢያ ተዛምዶ ስላላቸው አንዳቸው ከሌላኛው ተለይተው የሚታዩ አይሆኑም። ምክንያቱም ተማሪዎች አንድን ትምህርት ለመማር ፍላጎት ካላደረባቸው ለመረዳትም ዝግጁ አይሆኑም፤ ለመማር የፈቀዱትን ትምህርት ደግሞ ለመረዳት አይቸገሩበትም። ከዚህ አንፃር ማስተማር ማለት ተማሪዎች አንድን ትምህርት ወደውና ፈቅደው እንዲማሩትና፣ ብሎም እንዲገነዘቡት የማድረግ ሂደት ነው። በአጭሩ እንደ Venkataiah (2004፣ 27) አገላለፅ «ጥሩ ማስተማር ማለት፣ ተማሪዎች የሚያስተምሯቸውን ትምህርት እንዲረዱ፤ እና በቀጣይነትም ስለትምህርቱ የበለጠ ለማወቅ ጉጉት ወይም ፍላጎት እንዲያድርባቸው ማስደረግ መቻል ነው» ብለን ልናጠቃልለው እንችላለን።

በአጠቃላይ ከፍሲል ከቀረቡት ንድፈሃሳባዊ ምልከታዎች ለመረዳት እንደሚቻለው፣ ማስተማር የተማሪዎችን ሁለንተናዊ ብቃት (የዕውቀት፣ የክህሎት፣ የአስተሳሰብ፣ የአመለካከት፣ ወዘተ) የማዳበር ሂደት ነው። ለዚህ ሂደት እውን መሆንም የሂደቱ ዘዋሪ፣ የመምህሩ ሚና ወሳኝና አይተኬ ነው። ምንም እንኳን የማስተማሩ ሂደት በመምህሩ የግልና ተናጥላዊ ጥረት ብቻ የሚሳካ ባይሆንም፤ የስኬቱ ቁልፍ ግን ዞሮ ዞሮ ያው መምህሩ መሆኑ አይቀርም። መምህሩ ደግሞ ያለፈበት ስልጠና ውጤት ነው። ስለሆነም ለማስተማሩ ሂደት ስኬትም ሆነ ውድቀት መምህሩ የተማረው ትምህርትና የወሰደው ስልጠና ቀጥተኛ የሆነ ተፅዕኖ ይኖረዋል። Kelly (1976፣384) እንደሚለውም «(በተለይ ቋንቋን) በማስተማር ሂደት የአንድ ፅንስ ሃሳብ ህልውናም ሆነ ሞት በቀናንት ፅንስሃሳቡን በሚተገብረው መምህር እጅ ነው የሚገኘው። ፅንስሃሳቡን በክፍል ውስጥ የመተግበሩን ዕጣ ፈንታ ደግሞ የሚወስነው፤ መምህሩ በስልጠናው ወቅት የቀሰመው ንድፈሃሳባዊና ተግባራዊ ትምህርት ነው»። ከዚህም ለማስተማሩ ሂደት መሳካት መምህሩ የተማረው ትምህርት ወይም የሚወስደው ስልጠና ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ መመልከት ይቻላል። በማስከተል የምንመለከተውም ይህንኑ የመምህራን ትምህርት ወይም ስልጠና ጉዳይ ይሆናል።

## 2.1.2 የመምህራን ስልጠና

የመምህራን ስልጠና ምድቡ ከሙያ ስልጠና ነው:: ይሁን እንጂ ከሌሎች የሙያ ስልጠናዎች በእጅጉ የተለየ ነው:: እንደ Devroede (1981) ገለፃ እንደ ህክምና፣ ምህንድስና እና ግብርና ያሉትን ሙያዊ ስልጠናዎች ብንወስድ፤ በየትኛውም የዓለም ክፍል ቢሆን ከሞላ ጎደል አንድ ዓይነት ምስስሎሽ ይታይባቸዋል:: የመምህራን ስልጠና ግን ምንም እንኳን ከሌሎቹ የሙያ መስኮች ጋር የሚጋራው ነገር ቢኖርም፤ በባህሪው ግን ከቦታ ቦታ ይለያያል:: ለዚህም ዋናው ምክንያት የመምህራን ስልጠና ከኢኮኖሚያዊ ዕድገት ደረጃ እና ከማህበራዊ አውድ ጋር በከፍተኛ ሁኔታ ስለሚቆራኝ ነው:: ከዚህም በተጨማሪ ከአካባቢያዊ ባህልና ታሪክ ጋርም በእጅጉ የተያያዘ ነው ይላል:: ስለዚህ የመምህራን ስልጠና እንደየሃገሩ ተጨባጭ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ ሁኔታ የተለያየ በመሆኑ ከቦታ ቦታ ወጥነት ላይታይበት ይችላል::

የመምህራን ስልጠና እንደሚካሄድበት ተጨባጭ አውዳዊ ሁኔታ ሊለያይ ቢችልም፤ በመሠረቱ ግን ሊከተላቸውና ሊያካትታቸው የሚገባ መሠረታዊ መርሆዎች የሉትም ማለት አይደለም:: እንደ Wooding (1957)፤ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ የሚካሄድ የመምህራን ትምህርት ምንጊዜም ቢሆን ሊመልሳቸውና ሊመሠረትባቸው የሚገቡ አራት ዋናዋና ጉዳዮች አሉ:: እነሱም የትምህርቱ/ የስልጠናው ዓላማ ምንድነው? ዓላማው ምን ያህል በግለሰቦች መካከል ያለውን ልዩነት ከግምት አስገብቷል? ከዚህ ዓላማስ እንዴት ይደረሳል? ዓላማው ከግብ መድረሱስ እንዴት ሊረጋገጥ ይችላል? የሚሉ ናቸው:: Fish (1989)ም በበኩሉ የመምህራን ትምህርት/ስልጠና የስልጠናው ዓላማና ግብ ምንድነው? በምንስ ላይ ነው የሚያተኩረው? የኮርሶቹ ሁኔታ ምን መምሰል አለበት? ኮርሶቹ ከሥርዓተ ትምህርቱ ዓላማና ግብ አንፃር ምን ያህል ተገቢነት አላቸው? ምን ያህልስ ንድፈሃሳብን ከተግባር አጣጥመዋል? እና ሰልጣኞችስ የትኛውን የመማር ስልት ተከትለው መማር/መሰልጠን አለባቸው? የሚሉትን ስድስት ጥያቄዎች መመለስ ይኖርበታል ይላል:: ከዚህም በመነሳት ማንኛውም የመምህራን ስልጠና መርሃ ግብር የስልጠናውን ዓላማና ግብ፤ ከዓላማው ለመድረስ የሚያስችሉ ኮርሶችን፤ ኮርሶቹ እንዴት ባለመንገድ ቢሰጡ ከሚጠበቀው ግብ ሊያደርሱ እንደሚችሉ፤ በመጨረሻም ዓላማው ግቡን መምታቱን እንዴት ማረጋገጥ እንደሚቻል በአግባቡ መመለስ ይጠበቅበታል ማለት እንችላለን:: እነዚህን መሠረታዊ ጥያቄዎች በወጉ የሚመልስ የመምህራን ስልጠና መርሃ ግብርም ተከታዮቹን ጉዳዮች አካቶ መገኘት ይኖርበታል በማለት ምሁራን ይገልፃሉ::

Woodring (1957) Weber (1972) Herbst (1979) እንደሚሉት የመምህራን ስልጠና ሦስት የተዋሃዱና የተቀናጁ ትምህርቶችን ያካተተ መሆን አለበት:: እነዚህም 1) መሠረታዊ ሥነ ትምህርት (education) – ፍልስፍና፣ ታሪክ፣ ሥነ ማህበረሰብ፣ እና ንፅፅራዊ ሥነ ትምህርት (comparative education)፤ **2) ተጨባጭ** (empirical) ጥናታዊ ምርምር — የምርምር

ዘዴዎች፣ ምዘናና ግምገማ፣ እና 3) ተግባራዊ (applied) ሥነ ትምህርት የማስተማር ሥነ ዘዴ፣ ቴክኖሎጂና ሙያዊ ልምምድ ናቸው:: እነAlexander (1979) Turney (1981)ም የመምህራን ስልጠና መርሃ ግብር በመሠረቱ አጠቃላይ ሥነ ትምህርትን፣ ስልጠናው የሚያተኩርባቸውን ዐብይ የትምህርት ዓይነቶች፣ ጠንካራ የሥነልቦና ግንዛቤን የሚያስጨብጡ ትምህርቶችን፣ እና ሰፊ የማስተማር ሥነ ዘዴና ቴክኒክን ያካተተ መሆን ይገባዋል ይላሉ::

ከላይ በተለያዩ ምሁራን የቀረቡትን ዝርዝሮች መሠረት በማድረግ የመምህራን ስልጠና መርሃ ግብር ሊያካትታቸው የሚገባውን የትምህርትና የስልጠና ገፅታዎችን በጥቅሉ ንድፈሃሳባዊና ተግባራዊ ብሎ መመደብ ይቻላል:: ንድፈሃሳባዊው፣ ሰልጣኞች ስለሚሰለጥኑበት የትምህርት ዘርፍና ስለሥነ ትምህርት ግንዛቤን የሚጨብጡበት ሲሆን፣ ይህም እንደ ሥነልቦና፣ ፍልስፍና፣ ታሪክ፣ ሥነ ማህበረሰብ... ያሉትን ትምህርቶች ያካተተ ነው:: ተግባራዊው ደግሞ በማስተማር-መማሩ ሂደት በቀጥታ ተግባራዊ የሚሆኑ ሙያዊ ክህሎቶችን የሚያዳብሩበት ነው:: እነዚህም በቅድሚያ በንድፈሃሳብ ደረጃ ከተማሩዋቸው በኋላ በተግባር መለማመድን የሚጠይቁ ሲሆኑ፣ የማስተማር ሥነ ዘዴና ቴክኒክን፣ ተግባራዊ የምርምር ዘዴዎችን፣ የተማሪዎች ምዘናና ግምገማን... የሚያጠቃልል ይሆናል:: ከሁሉም በላይ ደግሞ በስልጠናው ሂደት እነዚህ ንድፈሃሳባዊና ተግባራዊ የትምህርት ገፅታዎች የግድ ተቀናጅተውና ተዋህደው መገኘት መቻል ይኖርባቸዋል::

በአጠቃላይ እስካሁን ስለመምህራን ስልጠና አስፈላጊነት መሠረታዊ ባህሪና ሊያካትታቸው ስለሚገቡ ዐብይ ንድፈሃሳባዊና ተግባራዊ የትምህርት ገፅታዎች ባጭሩ ለማየት ሞክረናል:: ከዚህም በተጨማሪ ማንኛውም የመምህራን ስልጠና መርሃ ግብር ለንድፈ ሃሳባዊውና ለተግባራዊው ስልጠና ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ መገኘት እንዳለበትም አይተናል:: ከዚህ በማስከተል ደግሞ በመምህራን ስልጠና መርሃ ግብር ውስጥ ወሳኝ ቦታ ያለውን ተግባራዊውን ስልጠና (የማስተማር ልምምድን) በተናጥል ወስደን እንመለከታለን::

## 2.1.3 የማስተማር ልምምድ

የማስተማር ልምምድን በተመለከተ ዝርዝር ጉዳዮችን ከማየታችን በፊት በቅድሚያ ከመምህራን ስልጠና ጋር ያለውን የጠበቀ ቁርኝት መመልከቱ ተገቢ ይሆናል:: እንደነ Walters (1960፣52) Perrot (1982፣8) Ellis (1986፣91) Wallace (1991፣121) በማንኛውም የሙያ ስልጠና መርሃ ግብር ውስጥ የግድ ተጣምረው ሊገኙ የሚገቡ ሁለት የትምህርት ገፅታዎች አሉ:: እነዚህም ንድፈሃሳባዊ ትምህርትና ተግባራዊ ልምምድ ናቸው:: ንድፈሃሳባዊው ትምህርት ለእውናዊው የማስተማር ተግባር የሚያስፈልጉ መርሆዎችን፣ መመሪያዎችን፣ ትወራዎችን በተመለከተ ግንዛቤ የሚጨብጡበት ነው:: ተግባራዊው ደግሞ እነዚህን በንድፈሃሳብ ደረጃ የተማሩትን በተጨባጩ ሙያዊ መቼት ውስጥ ተገኝተው እየተለማመዱ ማስተማርን በተግባር የሚለማመዱበት ሂደት ነው:: ምንም እንኳን በመምህራን ስልጠና ሂደት የሁለቱም አንድ ላይ

መገኙት የግድ ቢሆንም፤ ያለማስተማር ልምምድ ግን የሂደቱ ስኬታማነት የሚታሰብ አይሆንም፡፡ የዚህንም ምክንያት Dukin (1987፣686) «በመምህራን ስልጠና ሂደት የሰልጣኞችን ሙያዊ ብቃት ለማዳበር የማስተማር ልምምድ ብቸኛና አማራጭ የሌለው ግብዓት ስለሆነ ነው» በማለት ያስቀምጠዋል፡፡ ከነዚህም ገለፃዎች በመምህራን ስልጠናና በማስተማር ልምምድ መካከል ያለውን ፅኑ ግንኙነት መመልከት ይቻላል፡፡

## 2.1.3.1. የማስተማር ልምምድ ምንነትና ታሪካዊ ዳራ

የማስተማር ልምምድ ሂደትን ለመግለፅ የተለያዩ ስያሜዎች ጥቅም ላይ ሲውሉ ይታያል፡፡ ከነዚህም መካከል ማስተማርን መለማመድ (practice teaching)፣ የት/ቤት ልምድ (school experience)፣ የት/ቤት ውስጥ ልምድ (in-school experience)፣ ፕራክቲከም (practicum)፣ የማስተማር ሂደት (teaching rounds) እና ተማሪዎችን ማስተማር (student teaching) ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እንደነ Stones and Morris (1972) Stones (1978) ሃሳብም እነዚህ ስያሜዎች ከሚያመለክቱት ነገር ስፋትና ጥበት አንፃር መጠነኛ የሆነ አካባቢያዊ ልዩነት ቢንፀባረቅም፤ በየትኛውም ቦታ ይሁን የማስተማር ልምምድ ካለ ግን መሠረታዊ ባህሪቱ እና ሂደቶቹ ያው ናቸው፡፡

የማስተማር ልምምድ ተማሪ አስተማሪዎች በት/ቤት ውስጥ የሚያከናውኑትን ተግባራት የሚያመለክት ጥቅል ፅንሰሃሳብ ነው (Reece and Walker 2004፣72)፡፡ ይህም ባብዛኛው በት/ቤት ውስጥ የሚከናወን ቢሆንም እንደሁኔታው ግን በዛው በስልጠና ተቋሙ ውስጥ የሚካሄድበት ሁኔታም ሊኖር ይችላል፡፡ በመሠረቱ ግን የማስተማር ልምምድ በት/ቤት ውስጥ የሚከናወነን ተግባር ነው የሚያመለክተው " (Brown 1975፣13)፡፡

Srivastava and Bose (1978፣112) እንደሚሉት፣ የማስተማር ልምምድ ንድፈ ሃሳብ ከተግባር የሚዋሃድበት ሂደት ነው፡፡ በዚህም ተማሪ አስተማሪዎች ስለሚሰለጥኑበት የትምህርት ዓይነትና ስለማስተማሪያ ዘዴው በንድፈሃሳብ ደረጃ የተማሩትን ዕውቀት በት/ቤት ተገኝተው እንዴት መተግበር እንዳለባቸው ልምምድ ያደርጋሉ፡፡ በዚህም ብቁ መምህር የሚያደርጋቸውን ሙያዊ ክህሎት ይቀስማሉ፡፡

በእነ Gower and Walters (1983፣1) ማብራሪያ ደግሞ በተለይ ለሰልጣኝ የቋንቋ መምህራን የማስተማር ልምምድ ማለት አራት መሠረታዊ ሙያዊ ብቃቶችን የሚያዳብሩበት ሂደት ነው፡፡ ይኸውም ተማሪ አስተማሪዎች የሚሰለጥኑበትን ቋንቋ እንዴት በመማሪያ ክፍል ውስጥ እንደሚያቀርቡት፤ እንዴት ባለመንገድ ቢያቀርቡት ለተማሪዎች እንደሚቀል፤ በማስተማሩ ሂደት እንዴት የክፍል ውስጡን ሥርዓት ማስከበር እንደሚችሉ እና፤ አጠቃላዩን የማስተማር ሂደት የተሳካ ለማድረግ ምን ምን ቴክኒኮችንና ዘዴዎችን መጠቀም እንዳለባቸው በተግባር የሚለማመዱበት ሂደት ነው፡፡

በአጠቃላይ ከፍሊል ከተመለከቱት ሃሳቦች በመነሳት የማስተማር ልምምድን ምንነት እንደሚከተለው ማጠቃለል ይቻላል። የማስተማር ልምምድ በተለያዩ ስያሜዎች የሚገለፅ ቢሆንም፤ በመሠረቱ ግን ተማሪ አስተማሪዎች በት/ቤት ተገኝተው ማስተማርን የሚማሩበት፣ ንድፈሃሳብን ከተግባር የሚያዋህዱበት ሂደት ነው። ይህ ሂደት ተማሪ አስተማሪዎች የማስተማር ክሁሎትን የሚማሩበት ብቻ ሳይሆን በንድፈሃሳብ ደረጃ የቀሰሙትን ዕውቀትም ከተግባር የሚያዋህዱበት ነው። ስለሆነም የማስተማር ልምምድን ተማሪ አስተማሪዎች የተሟላ ሙያዊ ክሁሎት (ንድፈሃሳባዊና ተግባራዊ) የሚቀስሙበት ሂደት ነው ብለን ባጭሩ ልናስቀምጠው እንችላለን። በማስከተል ደግሞ ታሪካዊ ዳራውን በመጠኑ እንቃኛለን።

የማስተማር ልምምድ ታሪካዊ አነሳስ ከዕደጥበብ የሥራ ላይ ልምምድ (craft apprenticeship) ፅንሰሃሳብ የመነጨ ወይም የተቀዳ ነው። ለመገኘቱም ምክንያት የሆነው በወቅቱ በአውሮፓ ተከስቶ የነበረው ከፍተኛ የመምህራን እጥረት ነበር (Dunkin 1987)። በ19ኛው ክፍለ ዘመን ከኢንዱስትሪ አብዮት መስፋፋት ጋር ተያይዞ የኢንዱስትሪ ባለቤት በሆኑ አገሮች ውስጥ የትምህርት ለሁሉም (education for mass) መርህ በስፋት ተቀባይነት እያገኘ እና ትኩረትም እየተሰጠው ሲመጣ፤ ከፍተኛ የመምህራን እጥረትን አስከተለ። ይህን ለመቅረፍም የት/ቤት መምህራን ከሚያስተምሯቸው ተማሪዎች መካከል ለመምህርነት የሚመጥኑትን (ተሰጥኦውን ያላቸውን) ተማሪዎች እንዲመለምሉ ማድረግ ተጀመረ። የሚመለምሉትም በመምህሮቻቸው አማካይነት ምን ምን ማድረግ እንዳለባቸውና እንዴት ባለመንገድ ማስተማር እንደሚኖርባቸው በተግባር የተደገፈ ገለፃ (እያስተማሩ በማሳየት) ከተደረገላቸው በኋላ ነበር። ያንን ከመምህሮቻቸው የተመለከቱትን የማስተማር ሂደትም በቀጥታ ኮርጀው እየደጋገሙ እንዲያስተምሩ ይደረጋል። የዚህ ሂደት ዋንኛ ግብም ብቃት ያላቸውን ተማሪዎች ለይቶ ለመምህርነት ለማሰልጠን ሳይሆን፤ ከተማሪዎቹ መካከል በቀጥታ «መምህሮችን» መመልመል ነበር። ከመምህራቸው የኮረጁትን እየደጋገሙ እንዲለማመዱ የሚደረገውም የመምህርነት ተሰጥኦ ያላቸውን ተማሪዎች ለመለየት፤ ወይም ተሰጥኦዎቻቸውን አውጥተው እንዲያሳዩ/እንዲያስመሰክሩ ዕድል ለመፍጠር ነው። በዚህም ችሎታቸውን አላቸው ተብሎ የታመነባቸው ተማሪዎች በቀጥታ የመምህርነት ዕውቅና ይሰጣቸዋል፤ የበለጠ እንዲያጎለብቱትም ይነገራቸዋል (Dunkin 1987)።

ታሪካዊ ዳራው እንደሚያመለክተው፤ የማስተማር ልምምድ (እንደ ዛሬው) ማስተማርን የሚለማመዱበት ሂደት አልነበረም። ከዚህ ይልቅ ተሰጥኦ አላቸው ተብሎ የታመነባቸው ተማሪዎች በቀጥታ «ለመምህርነት» የሚመለመሉበት ሂደት ነበር። ይህ ሁኔታ ግን እየተለወጠ መጥቶ፤ የማስተማር ልምምድ 'መምህራን' የሚመለመሉበት ሳይሆን፤ ሰልጣኝ ተማሪ አስተማሪዎች ወደ ሙሉ መምህርነት የሚያሸጋግራቸውን ልምድ የሚቀስሙበት ሂደት ሲሆን ችሏል። ከዚህም በተጨማሪ ሂደቱ በአጠቃላዩ የመምህራን ስልጠና መርሃ ግብር ውስጥ ከሚገኙ

ኮርሶች ሁሉ የላቀውን ቦታ ሊይዝ በቅቷል፤ ዓላማውም ከአጠቃላዩ የስልጠና መርሃ ግብሩ ዓላማና ግብ ተለይቶ ከማይታይበት ደረጃ ላይ ሊደርስ ችሏል (Peters 1968 DES 1981)::

### 2.1.3.2. የማስተማር ልምምድ ዓላማና ግብ

በመሠረታዊ ዕውቀት የበለፀጉ፤ ሙያዊ ሥነ ምግባርን የጠበቁና፣ ተግባራዊውን የማስተማር ክሁሎት የተካኑ መምህራንን ማፍራት የማንኛውም የመምህራን ስልጠና መርሃ ግበር አጠቃላይ ዓላማና ግብ ነው (Walters 1960፤ 53 Perrot 1982፤ 8 Ellis 1986፤ 91 Wallace 1991፤121):: ለዚህም ግብ መቿንት ንድፈሃሳባዊውን ትምህርት ከተግባራዊው ሙያዊ ልምምድ ያቀናጀ ስልጠና መስጠቱ ግድ ነው:: ለመርሃ ግብሩ ዓላማ ግቡን መምታት የንድፈሃሳባዊውም ሆነ የተግባራዊው ትምህርት ወሳኝነት ከፍተኛ ቢሆንም የተግባራዊው ትምህርት (የማስተማር ልምምድ) ሚና ግን የላቀ ነው:: እንደ በርካታ ጥናቶች አገላለፅ ከሆነ፤ የማስተማር ልምምድ ዓላማዎችን ከአጠቃላዩ የመምህራን ስልጠና ዓላማዎች ለይቶ መመልከት ይቸግራል:: ወይም በአጠቃላዩ የመምህራን ስልጠና ዓላማና በማስተማር ልምምድ ዓላማ መካከል ድንበር ለማበጀት ያስቸግራል:: ከዚህም በመነሳት ስለማስተማር ልምምድ ዓላማዎች የተለያዩ ምሁራን (Smith1972 Gowers and Walters 1983 Richards and Nunan 1990) ከተለያየ አቅጣጫ በርካታ ዝርዝሮችን ያቀርባሉ:: እነዚህ ዝርዝሮች ከሚያተኩሩባቸው መሠረታዊ ነጥቦች መካከልም ተማሪ አስተማሪዎች የማስተማር ክሁሎትን ወይም ልምድን፤ የት/ቤትና የመማሪያ ክፍል ነባራዊ ሁኔታን፣ ንድፈሃሳባዊ ዕውቀትን ወደ ተግባር መለወጥን፤ ሁለንተናዊ ሙያዊ ብቃትን፣ የግል ሥብዕናና ሥነልቦናን፣ የህፃናት ትምህርትን (child education) ... በተመለከተ ክሁሎትን ወይም ዕውቀትን እንዲያዳብሩ ማስቻል በዋናነት ሊጠቀሱ የሚችሉ የማስተማር ልምምድ አጠቃላይ ዓላማዎች ናቸው:: በአጠቃላይ Smith (1972፤241) Srivastava and Bose (1978፤114) Gowers and Walters (1983፤1-2) Richards and Nunan (1990፤150) Siandu and Omulando (1992፤229) ከሚያቀርቧቸው ዝርዝሮች በመነሳት የማስተማር ልምምድ ዓላማ ተማሪ አስተማሪዎች ተከታዮቹን ሙያዊ ብቃቶች እንዲኖራቸው ማስቻል ነው በማለት ማጠቃለል ይቻላል::

- ንድፈሃሳባዊ የማስተማር መርሆዎችን፤ ሥነዘዴዎችን፤ ቴክኒኮችን ወደ ተግባር እንዲለውጡ፣
- የሚያስተምሩትን ትምህርት በደንብ ተገንዝበው በአግባቡ ማቀድና ማዘጋጀት እንዲችሉ፣
- የክፍል ውስጡን የመማር ማስተማር ሂደት ምቹ የሚያደርጉና የሚያደናቅፉ ነገሮችን ለይተው እንዲያውቁ፤
- የራሳቸውን የማስተማር ሂደት መገምገምና መሄስ እንዲችሉ፤
- የመማሪያ ክፍል ሥርዓትን በደንብ የመቆጣጠርና የማስከበር ክሁሎት እንዲያዳብሩ፣
- ስለህፃናት ዕድገትና ትምህርት መሠረታዊ ግንዛቤን እንዲጨብጡ፤

- የራሳቸውንና የተማሪዎቻቸውን ለውጥ (progress) በየጊዜው መከታተልና መገምገም እንዲችሉ፣
- የማስተማርን ውስብስብ ባህሪያት ተረድተው፣ ሙያው ምን ዓይነት ብቃት (quality) ያላቸውን ሰዎች እንደሚፈልግ እንዲገነዘቡ፣
- መምህር የመሆንን ከባድ ኃላፊነት ለመቀበል ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ፣
- ከአንድ መምህር የሚጠበቁ ሙያዊና ሥነ ምግባራዊ ባህሪያትን፣ አመለካከቶችንና ችሎታዎችን እንዲያካብቱ፣
- ስለት/ቤቶች መዋቅራዊ፣ አስተዳደራዊ እና ድርጅታዊ ባህሪያት እንዲገነዘቡ፣
- ወደፊት በማስተማሩ ሥራ ላይ ሲሰማሩ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ከወዲሁ ለይተውና አውቀው ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ፣
- ስለማስተማሩ ሙያ ጥሩ አመለካከት እንዲያዳብሩ፣
- ከነገሮች መለዋወጥ ጋር በቀላሉ የመተጣጠፍና ከአዳዲስ ሁኔታዎች ጋር የመላመድ ችሎታን እንዲያጎለብቱ ወዘተ. ማስቻል የማስተማር ልምምድ ዓላማዎች ናቸው።

ስለማስተማር ልምምድ ዓላማና ግብ በጥቅሉ ይህን ካልን በማስከተል ደግሞ ከዚሁ ከዓላማው ጋር የጠበቀ ትስስር ያለውን የማስተማር ልምምድ ሞዴልን እንመለከታለን።

### 2.1.3.3 የማስተማር ልምምድ ሞዴሎች

የማስተማር ልምምድ ሞዴሎች ከማስተማር ልምምድ ዓላማዎች ጋር ከፍተኛ የሆነ ቁርኝት አላቸው። የማስተማር ልምምድ ዓላማዎች የሚነደፉት፣ ልምምዱ መሠረት አድርጎ የሚካሄድበትን የአቀራረብ (approach) ሞዴል ነው። ከዚህ አንፃም የተለያዩ የማስተማር ልምምድ አቀራረብ ሞዴሎች አሉ። ከነዚህም መካከል በስፋት የሚታወቁት ሦስቱ ሞዴሎች የኩረጃ ሞዴል፣ የልምምድ ሞዴልና ሳይንሳዊ ሞዴል ናቸው። እነዚህንም ቀጥለን በአጭር ባጭሩ ለመዳሰስ እንሞክራለን።

**የኩረጃ ሞዴል (model of the master-teacher approach)**

የኩረጃ ሞዴል ተለምዷዊና ዕድሜ ጠገብ የማስተማር ልምምድ አቀራረብ ሞዴል ነው። በዚህ ሞዴል መሠረት ማስተማር ጥበብ ነው። የሞዴሉ አነሳስም ከማስተማር ልምምድ ታሪካዊ ዳራ ጋር የተያያዘ ነው። የማስተማር ልምምድ ፅንሰ ሃሳብ ከዕደጥበብ የሥራ ላይ ልምምድ የተቀዳ እንደመሆኑ መጠን፣ የማስተማሩ ተግባርም ከዕደጥበብ ተለይቶ በማይታይበት ወቅት የተከሰተ ሞዴል ነው። በዚህም መሠረት ሞዴሉ ሰልጣኝ የዕደጥበብ ተማሪዎች የአሰልጣኞቻቸውን የዕደጥበበ ውጤት በትኩረት በማጤን እንዲኮርጁት በማድረግ እንደሚሰለጥኑት

ሁሉ፣ ተማሪ አስተማሪዎችም የመምህሮቻቸውን የማስተማር እንቅስቃሴ እንዳለ በመቅዳት መምህርነትን «እንዲኮርጁ» ያደርጋል፡፡ ይህ ተማሪ አስተማሪዎች የአሰልጣኝ መምህሮቻቸውን አጠቃላይ የማስተማር እንቅስቃሴ በቀጥታ በመኮረጅ ማስተማርን የሚለማመዱበት ሂደትም የኩረጃ ሞዴል ይባላል (Peters 1968፣ Stones and Morris 1972)፡፡ ይህ ሞዴል በጣም ውጤታማ፣ ለመተግበርም የማያስቸግር፣ ተጨማሪ ትምህርትንም (መማርን) የማይጠይቅ መሆኑን በጠንካራ ጎንነቱ የሚያቀርቡ ቢኖሩም፣ አጠቃላይ ባህሪው ሲታይ ግን በርካታ ድክመቶች እንዳሉበት የዘርፉ ባለሙያዎች በአንፅንኦት ይገልፃሉ፡፡ ከነዚህም መካከል ተማሪ አስተማሪዎች ያፈነገጡ (የተዛቡ) የማስተማር ልምዶችን በአርዓያነት ሙጥኝ እንዲሉ በር መክፈቱ፣ በመምህሮቻቸው ላይ ከተመለከቱት ውጪ ያሉ የማስተማር ተግባራትን እንዳያስቡ መገደቡ፣ ተግባራቸው በርግጥም በአርዓያነት ሊኮረጅ የሚችል አሰልጣኝ መምህራን እንደሚፈለገው መገኘት አለመቻላቸው፣ ለወግ አጥናባቂነትና ለልማዳዊ ቀኖና የተጋለጠ መሆኑ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ለሙከራ (experiment) እና ለግላዊ ፈጠራ ቦታ አለመስጠቱ ከኩረጃ ሞዴል ዋና ዋና ድክመቶች መካከል ተጠቃሽ ናቸው (Stones and Morris 1972 Dunkin 1987)፡፡

## የልምምድ ሞዴል (master the teaching model approach)

የልምምድ ሞዴል ከልማዳዊው የኩረጃ ሞዴል በኋላ የተከሰተ የማስተማር ልምምድ አቀራረብ ሞዴል ነው፡፡ ሞዴሉ የአሰልጣኝ መምህራኑን አጠቃላይ የማስተማር እንቅስቃሴ ተድቶ ከመገልበጥ ይልቅ፣ ሞዴል የሚሆኑ የማስተማር ንድፈሃሳቦችንና የምርምር ውጤቶችን በተግባር በማለማመድ ላይ ያተኩራል፡፡ ተማሪ አስተማሪዎች በየጊዜው ይፋ የሚሆኑ አዳዲስ ንድፈሃሳባዊና ጥናታዊ ውጤቶችን ወስደው ተግባር ላይ በማዋል የማስተማር ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩ ወይም እንዲካኑ ማድረግ የልምምድ ሞዴል አይነተኛ ትኩረት ነው፡፡ ከቀደመው የኩረጃ ሞዴል አንፃር ሲታይም በርካታ ጠንካራ ጎኖች ያሉት ሞዴል ነው፡፡ ከነዚህም መካከል ከልምምድ በፊት ለማስተማሩ ሂደት የሚያስፈልጉ ንድፈሃሳባዊ ግንዛቤዎችን ለተማሪ አስተማሪዎች ማስጨበጡ፣ ብቁ የማስተማር ክህሎትን የሚያስቀስሙ ሳይንሳዊ ሞዴሎችን በተግባር እንዲለማመዱት ማስደረጉ፣ የተለያዩ ንድፈሃሳባዊ ሞዴሎችን በማቅረብ የሚያስተምሩትን ትምህርት እንዴት ማቀድ፣ መተግበርና መገምገም እንደሚችሉ በተግባር የሚያለማምድ መሆኑ የልምምድ ሞዴል ጠንካራ ጎኖች ተደርገው ይጠቀሳሉ (Stones and Morris 1972)፡፡

## ሳይንሳዊ ሞዴል (teaching as a science approach)

ሳይንሳዊ ሞዴል የቅርብ ጊዜ የማስተማር ሞዴል ሥነ አቀራረብ ነው፡፡ በባህሪው ከኩረጃ ሞዴል ተፃራሪ ሲሆን፣ ከልምምድ ሞዴል ደግሞ ተቀራራቢ ነው፡፡ ሞዴሉ ማስተማርን እንደ

ሳይንስ መመልከቱ የኩረጃ ሞዴል ተፃራሪ ሲያደርገው (የኩረጃ ሞዴል ማስተማርን እንደ ጥበብ ስለሚያይ)፣ ለማስተማር ልምምዱ ሳይንሳዊ ንድፈ ሃሳቦችንና የምርምር ውጤቶችን መሠረት ማድረጉ ደግሞ ከልምምድ ሞዴል ጋር ተዛማጅ አድርጎታል። በማስተማር ልምምድ ሂደት ለሳይንሳዊ አካሄዶች (ምልከታ፣ መላምት፣ሙከራ፣ ትወራ) ከፍተኛ ትኩረት መስጠቱ የሳይንሳዊ ሞዴል ዓይነተኛ ባህሪው ነው። ሞዴሉ የተማሪ አስተማሪዎችን የማስተማር ክህሎት ለማጎልበትም ይረዳ ዘንድ ሳይንሳዊ ትወራዎችን መሠረት ያደረጉ ምክንያታዊ ተግባራትን እየተለማመዱ ትወራዎችን በተግባር እንዲፈትሹ ያደርጋል። በማስተማር ልምምዱ ሂደትም በመምህር-ተማሪ የክፍል ውስጥ መስተጋብር፣ በማስተማር ቴክኒኮችና ስትራቴጂዎች አተገባበር፣ በመማሪያ ክፍል ሥርዓትና ደንብ ማስከበሪያ ቴክኒኮች፣ ከአንድ መምህር በሚጠበቁ ሙያዊና ሥነ ምግባራዊ ባህሪያት ወዘተ. ላይ ማተኮር የሳይንሳዊ ሞዴል መገለጫዎች ናቸው (Stones and Morris 1972 Dukin 1987)።

በአጠቃላይ እስካሁን በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር የማስተማር ልምምድንና ከመምህራን ስልጠና ጋር ያለውን የጠበቀ ቁርኝት፣ ምንነቱንና ታሪካዊ አነሳሱን፣ ዓላማዎቹንና ሞዴሎቹን ተመልክተናል። በማስከተል ደግሞ በመምህራን ስልጠና መርሃ ግብር ውስጥ የማስተማር ልምምድ መገኘት ወሳኝና የግድ እንደሆነው ሁሉ፣ በማስተማር ልምምድ ሂደትም ወሳኝና አይቀሬ የሆነውን ጉዳይ (ሱፐርቪዥንን) ለማየት እንሞክራለን።

## *2.1.3.4 ሱፐርቪዥን እና የማስተማር ልምምድ*

ስለሱፐርቪዥን ምንነት፣ ዓላማና ተግባራት አጠቃላይ የሆነ ምልከታ ከማድረጋችን በፊት ከማስተማር ልምምድ ጋር ያለውን ተዛምዶና ቁርኝት ለመንደርደሪያ ያህል እንመልከት። የመምህራን ስልጠና ያለ ማስተማር ልምምድ እንደ ማይታሰበው ሁሉ፣ የማስተማር ልምምድም ያለ ሱፐርቪዥን የሚታሰብ አይሆንም። እንደ Dukin አገላለፅ «በመምህራን ስልጠና መርሃ ግብር ሂደት የሰልጣኞችን ሁለንተናዊ ሙያዊ ብቃት ለማጎልበት ብቸኛውና አማራጭ የሌለው መፍትሄ የማስተማር ልምምድ ነው። ከማስተማር ልምምድ የሚፈለገውን ሙያዊ ብቃት ለማግኘት ደግሞ የሱፐርቪዥን መኖር ብቸኛና ምትክ የማይገኝለት ጉዳይ ነው» (1987፣ 686)። ይህም በማስተማር ልምምድ ሂደት የሱፐርቪዥንን አይቀሬነት ያመለክታል።

Srivastava and Bose (1978፣115) እንደሚሉት፣ የመምህራን ስልጠና መርሃ ግብር ግቡን ይመታ ዘንድ የማስተማር ልምምድን ማካተቱ የግድና አማራጭ የሌለው ነገር ነው። ይሁንና የማስተማር ልምምዱ ወሳኝነትም ሆነ አስፈላጊነት የሚመረኮዘው በውስጡ በሚይዘው የሱፐርቪዥን ባህሪና አተገባበር ላይ ነው። ይህንንም Walters (1960፣66) «የማስተማር ልምምድ የስኬት ቁልፍ በልምምዱ ሂደት በሚኖረው ሱፐርቪዥን ጥራትና ብቃት ውስጥ ነው» በማለት ያጠናክረዋል። ከዚህም በማስተማር ልምምድና በሱፐርቪዥን መካከል ምን ያህል

የጠበቀ ትስስር እንዳለ መመልከት ይቻላል:: ስለትስስራቸው ይህ ካልን ዘንዳ ቀጥለን ደግሞ ሱፐርቪዥንን ለብቻው ወስደን እንመለከታለን::

### 2.1.3.4.1 የሱፐርቪዥን ምንነት

ሱፐርቪዥን በተለያዩ የሙያ መስኮች ውስጥ ሊካሄድ የሚችል በመሆኑ፤ እንደሚገኝበቱ ሙያዊ አውድ የተለያዩ ብያኔዎች ሊኖሩት ይችላል:: በመማር ማስተማሩ ማዕቀፍ ውስጥ እንኳን ቢታይ በሥርዓተ ትምህርት ቀረፃ፣ በየሥራ ላይ (inservice) መምህራን ስልጠና እና በማስተማር ሂደቶች ግምገማ ውስጥ የተለያዩ እንድምታዎች አሉት:: ከዚህም የተነሳ የሱፐርቪዥንን ምንነት በቀላሉ ለማስቀመጥ ይቸግራል (Harris 1985):: ይሁንና ግን Dukin (1987፣ 756-7) እንደሚለው፤ ከማስተማር መማር ሂደት አንፃር በየትኛውም ዓይነት የት/ቤት መዋቅር ውስጥ ያለን የማስተማር መማር ሂደት ለማሻሻልና ይበልጥ ለማጠናከር የሚከናወንን የክትትል፣ የቁጥጥርና የፍተሻ ተግባርን ሱፐርቪዥን ልንለው እንችላለን:: ከዚህ አጠቃላይ ምልከታ በመነሳትም የሱፐርቪዥንን ምንነት ከመምህራን ስልጠና ወይም ከማስተማር ልምምድ አንፃር እንደሚከተለው ለማስቀመጥ እንሞክራለን::

በነGebhard (1990) Fanselow (1990) Wallace (1991) እና Gowers (1995) ማብራሪያ መሠረት፣ ሱፐርቪዥን ከፍ ያለ የማስተማር ዕውቀት፣ ክህሎትና ልምድ ያለው አሰልጣኝ መምህር ወይም ባለሙያ ከሱ ያነሰ ሙያዊ ብቃትም ሆነ ልምድ ያላቸውን (ሰልጣኞችን) የተሟላ ሙያዊ ክህሎት እንዲቀስሙ ሲል የሚያደርገውን አጠቃላይ እንቅስቃሴ የመለከታል:: በዚህም ሰልጠኞችን ወደ ትክክለኛው ሙያዊ ክህሎት የመምራት፣ የተሻለና ውጤታማ የማስተማር ዘዴን የመጠቀም፣ አስፈላጊውን ሙያዊ ምክርና እገዛ የመስጠት እና የመገምገም ሂደትን ሱፐርቪዥን እንለዋለን:: እንደነ Srivastava and Bose (1978፣12) እና Lovell and Kimballwiles (1983፣2) አገላለፅ ደግሞ ሱፐርቪዥን ሰልጣኞችን በማስተማር ልምምድ ሂደት የመምራት፣ የመገምገም፣ የመምከር እና የማገዝ ሂደት ብቻ አይደለም፤ ትርጉምና ድህረ የማስተማር ልምምድ ሊከናወኑ የሚገቡ ተግባራትንም የሚያካትትም ጭምር እንጂ:: ከዚህም በመነሳት ሱፐርቪዥን ማለት ለሰልጣኞች የተሟላ ሙያዊ ክህሎት ሊያስቀስም የሚችል ንድፈሃሳባዊ ግንዛቤን የማስጨበጥ (ቅድመ ልምምድ)፤ የተገነዘቡትን ነገር በአግባቡ መተግበራቸውን በቅርበት የመከታተል፤ ስህተት ግድፈታቸውን የማረቅ፤ ትክክለኛውን አቅጣጫ የማስያዝ እና፤ በመጨረሻም በሰልጣኞች ዘንድ የሚጠበቀው ለውጥ መምጣቱን በግምገማ የማረጋገጥ ሂደት ነው በማለት ማጠቃለል እንችላለን::

### 2.1.3.4.2 የሱፐርቪዥን ዓላማና ተግባራት

እንደነ Brown (1975፣139) Srivastava and Bose (1978፣115) ገለፃ የሱፐርቪዥን ዓላማና ግብ ተማሪ አስተማሪዎች ከተለያዩ የማስተማር ስልቶችና ተግባራዊ ክህሎቶች ጋር

እንዲላመዱ፣ የራሳቸውን የማስተማር ሂደት በራሳቸው እንዲፈትሹ እና የተሟላ ሙያዊ ክህሎት እንዲያጎለብቱ መርዳት ነው ይላሉ:: ምንም እንኳን ከፍ ሲል የተጠቀሱት ምሁራን በዚህ መልኩ የሱፐርቪዥንን ዓላማ ለብቻው ነጥለው ቢያስቀምጡትም፣ በርካቶቹ የዘርፉ ባለሙያዎች ግን ዓላማዎቹን ከተግባራቱ ነጥለው አያዩዋቸውም:: በሌላ አገላለፅ በሱፐርቪዥን ዓላማዎች (objectives) እና ተግባራት (tasks) መካከል ግልፅ የሆነ ድንበር ሲያስቀምጡ አይስተዋልም:: በዚህ መሠረት ለምሳሌ Gebhard (1990) Richards and Nunan (1990) በሱፐርቪዥን ዓላማነት የሚስቀምጧቸውን አምስት ነጥቦች እነ Caroll (1995) Hollway and Caroll (1999) ደግሞ ሰባት በማድረግ ብቻ በሱፐርቪዥን ተግባርነት ያቀርቧቸዋል:: በሁለቱም አቅጣጫ እንደዓላማነትም ሆነ እንደተግባርነት በሚቀርቡት ዝርዝሮች መካከል ከቁጥር መለያየት የዘለለ የጎላ ልዩነት አይንፀባረቅባቸውም:: ከዚህም በመነሳት ሱፐርቪዥን ቀጥለው የተመለከቱትን ዓላማና ተግባራት አሉት ብለን ልናስቀምጥ እንችላለን::

- የማስተማር/መማር ክንውኖችን አቅጣጫ ማስያዝና መምራት፣
- የተሻሉና ውጤታማ የሆኑ የማስተማር ስልቶችን ማመላከት/ማሳየት፣
- ተገቢውን ሙያዊ ምክርና እገዛ መስጠት እና፣
- መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ ዘዴዎችን/መንገዶችን ተጠቅሞ አፈፃፀማቸውን መገምገም ዋናዋዎቹ የሱፐርቪዥን ዓላማና ተግባራት ናቸው ማለት ይቻላል (Gebhard 1990 Richards and Nunan 1990 Caroll 1995 Holloway and Caroll 1999) ::

ከፍሲል ከተመለከቱት ሃሳቦች መረዳት እንደሚቻለው፣ የሱፐርቪዥን ዓላማና ተግባራት ጎይንተኛ ግብ ተማሪ አስተማሪዎች የተሟላ ሙያዊ ክህሎት እንዲያጎለብቱ ማስቻል ወይም ማገዝ ነው:: ለዚህ እውን መሆን ደግሞ ሱፐርቫይዝ የሚያደርገው አሰልጣኝ መምህር ወይም ባለሙያ ሚና ወሳኝ ነው:: ያለሱ ንቁ ተሳትፎ የሂደቱ ግብ መቼነት አይታሰብም:: ሱፐርቫይዘሩ ይህን ወሳኝ ኃላፊነቱን በአግባቡ መወጣት ይችል ዘንድም ለቀጣዮቹ አራት ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ማግኘት እንደሚኖርበት እነ Caroll (1995) Holloway and Caroll (1999) ይገልፃሉ::

1. በሱፐርቫይዘርነቴ ምን ምን ተግባራትን ነው ማከናወን የሚጠበቅብኝ?

2. ከሙያዊ ሥነ ምግባር አንፃር ምን ምን ኃላፊነቶች አሉብኝ?

3. በሰልጣኞች ዘንድ የሚጠበቀውን ሙያዊ ብቃት ለማስገኘት ምን ምን ሂደቶችን መከተል ይኖርብኛል?

4. ለአጠቃላዩ የስ·ፐርቪዥን ሂደት መሳካት ከኔም ሆነ ከስልጣኞቹ ምንምን ተግባራትንና ኃላፊነቶችን መወጣት ይጠበቅብናል? ለሚሉት ጥያቄዎች ተገቢ የሆነ ምላሽ ማግኘት ይጠበቅበታል።

### *2.1.3.4.3 የስ·ፐርቫይዘር ሚና እና የስ·ፐርቪዥን አከናወን ሂደት*

#### *2.1.3.4.3.1 የስ·ፐርቫይዘር ሚና*

ያለ ስ·ፐርቫይዘሩ ንቁ ተሳትፎ፣ የስ·ፐርቪዥን ሂደት ግብ መቺነት አይታሰብም። ስለሆነም ለሂደቱ ስኬታማነት የስ·ፐርቫይዘሩ ሚናውን በአግባቡ መወጣት ግድ ነው። ይህ ሆኖ ሲገኝም ነው ብቃት ያላቸው መምህራንን ማፍራት የሚቻለው። ይህንንም ሁኔታ Sirvastava and Bose ሲገልፁ «የፈለገውን ያህል ጠንካራና ተግባራዊ ሊሆን የሚችል መሠረትን ይዞ የተደራጀ የስ·ፐርቪዥን መርሃ ግብር ቢኖር፣ በብቁና ኃላፊነታቸውን በአግባቡ በሚወጡ ስ·ፐርቫይዘሮች ንቁ ተሳትፎ ካልታገዘ ወይም ካልተከናወነ በቀር ትክክለኞቹን መምህራን ማፍራቱ አይታሰብም» (1978፣ 116) በማለት ይገልፃሉ። ከዚህም በማስተማር ልምምዱ ሂደት ተማሪ አስተማሪዎች ተገቢውን ሙያዊ ልምድ መቅሰም ይችሉ ዘንድ በስ·ፐርቫይዘርነት የሚያገለግለው ባለሙያ ያለውን ወሳኝ ሚና መመልከት ይቻላል።

የስ·ፐርቫይዘር ሚና ወይም ተግባራት እንደሚገኙበት የማስተማር ልምምድ ሂደት አደረጃጀት ወይም አተገባበር ሊለያይ ይችላል። ይሁንና ግን Brown (1975፣ 139) እንደሚለው የመጀመሪያውም ስ·ፐርቫይዘር ዓይነተኛ ሚና «ተማሪ አስተማሪው የራሱን የማስተማር ተግባራት (tasks) በራሱ ማሻሻል እንዲችል መርዳት ወይም ማገዝ ነው»። የነ Gowers and Walters ሃሳብም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው። የስ·ፐርቫይዘር ግንባር ቀደም ተግባር ተማሪ አስተማሪዎችን ስ·ፐርቫይዝ ማድረግ ነው። ይህም ለማስተማር ልምምዱ ሂደት ብቁ የሚያደርጋቸውን መመሪያና ማብራሪያ መስጠትን፣ በልምምዱ ሂደትም ተከታታይ ምልከታ ማድረግን እና ገንቢ ግብረ መልስ መስጠትን ያካትታል (1983፣ 179)። ስለዚህ ተማሪ አስተማሪዎችን ለማስተማር ልምምዱ የሚያበቃ መመሪያ መስጠት፣ በሚለማመዱበትም ወቅት በቅርብ ሆኖ መመልከት /መከታተል፣ ቀስበቀስ ወደ ተገቢው የማስተማር ክህሎት እንዲያመሩ መቅረፅ እና፣ ተከታታይ ግብረ መልስ መስጠት የስ·ፐርቫይዘር ግንባር ቀደም ሚና ይሆናል ማለት ነው። ስለሚናው በጥቅሉ ይህን ካልን፣ በማስከተል ደግሞ ሚናውን እንዴት ባለመንገድ መወጣት/ ማከናወን እንዳለበት እንመልከት።

#### *2.1.3.4.3.2 የስ·ፐርቪዥን አከናወን ሂደት*

Dukin በፕሬክቲከም ሂደት ልንከተለው የሚገባ ተገቢ የሱፐርቪዥን ሂደት የትኛው ነው ተብሎ ቢጠየቅ በቀላሉ የሚመለስ አይሆንም ይላል (1987፣693)። ለዚህም ዋናው ምክንያት፣ በተግባር የሚታየው የሱፐርቪዥን ሂደት በአብዛኛው ወጥ የሆነ ሥርዓትን የሚከተል አለመሆኑ ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ ሂደቱ በሱፐርቫይዘሮቹ የግል አመለካከት ላይ ስለሚወሰን የትኛውን መከተል እንዳለብን ለመወሰን ይቸግራል ይላል። ከዚህም የተነሳ በሱፐርቪዥን ሂደት፣ በተለይ የክፍል ውስጡን የማስተማር ክንውን/ ተግባራት መመልከትና መገምገም ከናካቴው እየተተወ መቷል። ስለዚህ ይህን በሱፐርቪዥን አከናወን ሂደት ላይ የሚታየውን ክፍተት ለመሙላት የሚችል ዘመናዊ አቀራረብን መከተል ግድ ይሆናል። ለዚህም ፍቱን የሆነው ዘመናዊ መፍትሔ ክሊኒካዊ ሱፐርቪዥን (Clinical Supervision) ነው (Dukin 1987፣693)።

ክሊኒካዊ ሱፐርቪዥን ዘመናዊና ውጤታማ የሆነ የሱፐርቪዥን አቀራረብ/ አከናወን ሂደት ነው። አቀራረቡም በተግባራዊ የማስተማር ክንውን ሂደት ያለውን ሁኔታ በቦታው ተገኝቶ በሚደረግ፣ ቀጥተኛ ምልከታ የሚሰበሰብ መረጃችን መሠረት ያደርጋል። በዚህም የማስተማር ባህሪያትን (behaviors)ና ክንውኖችን (activities) መተንተንን፣ የተማሪ አስተማሪዎችን ከሱፐርቫይዘሮቻቸው ጋር ፊት ለፊት መገናኘትን ግድ የሚል የሱፐርቪዥን ሂደት ነው (Goldhammer et al 1980፣19)። Richards and Nunan እንደሚሉት ደግሞ፣ ክሊኒካዊ ሱፐርቪዥን የተማሪ አስተማሪዎችን የማስተማር ክንውን ሥርዓታዊ በሆነ መንገድ የመመልከት፣ የመተንተን እና የመገምገም ሂደት ነው (1990፣167)። በዚህም ሱፐርቫይዘራዊ ተግባራትን ሥርዓታዊ በሆነ መንገድ ማቅረብ፣ ተማሪ አስተማሪዎች በአንድ ጊዜ በተወሰነ የማስተማር ጉዳይ ላይ አተኩረው ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ማገዝ የሂደቱ መሠረታዊ መርሆዎች ናቸው (Goldhammer et al 1980)። የክሊኒካዊ ሱፐርቪዥን ዓይነተኛ ዓላማና ግብም ተማሪ አስተማሪዎች በተግባራዊው (actual) የማስተማር ባህሪያት እና በሃሳባዊ (ideal) ባህሪያቱ መካከል ያለውን ተለያይቶ (discrepancy) ተጨባጭ በሆነ መልኩ እንዲመለከቱ ወይም እንዲገነዘቡ ማድረግ ነው (Richards and Nunan 1990)።

በአጠቃላይ ክሊኒካዊ ሱፐርቪዥን ሥርዓታዊ፣ የክፍል ውስጡን የማስተማር ክንውን (performance) በቀጥታ በመመልከት መረጃችን የሚያጠናቅር፣ በዚህም ላይ ተመስርቶ ተማሪ አስተማሪዎች ደረጃ በደረጃ እያደገ የሚሄድ የማስተማር ልምድ እንዲቀስሙ የሚያግዝ ሂደት ነው። አጠቃላይ ሂደቱም ሦስት ዋና ዋና እርከኖችን ወይም ደረጃዎችን በውስጡ የያዘና ዑደታዊ (cyclical) ቅደም ተከተልን ጠብቆ የሚከናወን ነው (Cogan 1973 Boyan and Copeland 1978 Sirvastava and Bose 1978 Goldhammer et al 1980 Richards and Nunan 1990)። እነዚህን እርከኖችም Sirvastava and Bose (1978፣115-20) Stones and Morris (1972፣ 90-92) ቅድመ ማስተማር፣ በማስተማር ሂደት እና ድህረ

ማስተማር ሂደት በማለት በሦስት ይከፍሏቸዋል:: በተመሳሳይ ሁኔታም እነ Goldhammer (1980፣ 19-20) የቅድመ ምልከታ ውይይት፣ የድህረ ምልከታ ውይይት እና የድህረ ውይይት ትንተና በማለት በሦስት ከፍለው ያስቀምጡዋቸዋል:: እነ Richards and Nunan (1990፣168-69) ደግሞ ቅድመ ምልከታ እና ድህረ ምልከታ በማለት በሁለት ያጠቃልሏቸዋል:: ምንም እንኳን በነዚህ ምሁራን አከፋፈል መካከል የስያሜና የትኩረት ልዩነት ቢኖርም መሠረታዊ ነጥቦቹ/ ተግባራቱ ግን ከሞላ ጎደል አንድ ዓይነት ናቸው:: ከዚህም በመነሳት የሱፐርቪዥንን አከናወን ሂደቶችን የቅድመ ምልከታ ውይይት፣ የምልከታ ሂደት እና፣ የድህረ ምልከታ ውይይት በማለት በሦስት ዋና ዋና እርከኖች ወይም ደረጃዎች ከፍለን እንመለከታለን።

### *i. የቅድመ ምልከታ ውይይት (Pre-observation conference)*

ተማሪ አስተማሪዎች ለተግባራዊው የክፍል ውስጥ የማስተማር ክንውን ወደ ት/ቤት ከመሰማራታቸው በፊት የሚገኝ ደረጃ ነው:: በዚህ ደረጃ ተማሪውና ሱፐርቫይዘሩ ስለማስተማር ክንውኖች ውይይት ያደርጋሉ ወይም ዕቅድ ያወጣሉ:: በዚህም አክፍል ገብተው የማስተማሩን ተግባር በአግባቡና በልበ ሙሉነት ለማከናወን የሚያስችላቸውን ችሎታዎችና ክህሎቶች ጠንቅቀው ይገነዘባሉ። ከዚህም በተጨማሪ ሱፐርቫይዘሩ በክፍል ውስጥ ተገኝቶ ስለሚያደርገው ምልከታ (አጠቃላይና ዝርዝር) ዓላማ፣ በምልከታው ሊተኮርባቸው ስለሚገቡ ነጥቦች፣ እና ምልከታው ስለሚካሄድበት አውድ ወይም ሁኔታ (context) ተወያይተው ይወስናሉ (Stones and Morris 1972 Sirvatava and Bose 1978 Goldhammer et al 1980 Richards and Nunan 1990)።

### *ii. የምልከታ ሂደት (Observation )*

ሱፐርቫይዘሩ የተማሪ አስተማሪዎችን የማስተማር ክንውን በቀጥታ በክፍል ውስጥ ተገኝቶ የሚመለከትበት ሂደት ነው:: የምልከታውም ሂደት ቀደም ሲል በቅድመ ምልከታው ውይይት ወቅት ለተቀመጠው ወይም ለተወሰነው ዕቅድ፣ ዓላማና ሁኔታ የተገዛ መሆን ይኖርበታል:: በዚህ መሠረትም ሱፐርቫይዘሩ ከተመለከተው የማስተማር ክንውን ውስጥ የውይይት መነሻ የሚሆኑ የማስተማር ጉዳዮችን ለይቶ ማውጣትና መመዝገብ ይጠበቅበታል (Stones and Morris 1972 Sirvatava and Bose 1978 Goldhammer etal 1980)::

### *iii. የድህረ ምልከታ ውይይት (Post- observation conference)*

ይህ ደረጃ የትንተናና የስትራቴጂ ሂደት (phase) በመባል ይታወቃል:: የተማሪ አስተማሪውን የማስተማር ክንውን በተመለከተ በምልከታው ሂደት የተጠናቀሩት መረጃዎች በዝርዝር ይተነተናሉ፣ ይፈተሻሉ:: እንዲሁም ተማሪ አስተማሪው ቀደም ሲል የተሰጠውን

መመሪያና ገለፃ ተግባራዊ ማድረጉ የሚጣራበት/ የሚረጋገጥበት፤ እሲያም እንደገና ተጨማሪ ንድፈሃሳባዊ ማብራሪያ የሚሰጥበት ሂደት ነው። በጥቅሉ በማስተማር ክንውኑ ሂደት የተከሰቱትን ጉዳዮች (ሱፐርቫይዘሩና ተማሪው) አንድ ባንድ እያነሱ የሚወያዩበት፤ ጠንካራና ሊበረታቱ የሚገባቸው ጉዳዮች ተለይተው የሚታወቁበት፤ ደካማና ሊሻሻሉ የሚገባቸው ጉዳዮች ታውቀው መፍትሔ የሚፈለግበት ሂደት ነው። በመሆኑም ይህ ደረጃ የአጠቃላዩ ሱፐርቪዥን ዑደት አምብርት ተደርጎ ይታያል (Stones and Morris 1972 Sirvatava and Bose 1978 Goldhammer et al 1980 Richards and Nunan 1990)።

በአጠቃላይ በዚህ ሂደት በክፍል ውስጡ የማስተማር ክንውን ምልከታ ሂደት የተጠናቀሩት መረጃች በምጋቤ ምላሽ አማካይነት ወደ ተማሪ አስተማሪው ይተላለፋሉ፤ ቀጣዩ የምልከታ ሂደትም ምን መምሰል እንዳለበት ምክክር ይደረጋል። በዚህ ደረጃ ላይ የሚደረጉት ውይይቶችና ምክክሮችም ቀደም ሲል በቅድመ ምልከታው ውይይት ላይ የተነሱትን ጉዳዮች መሠረት ያደረጉ ሊሆን ይገባል። በድክመትነት የሚነሱ የማስተማር ክንውኖችም የሚሻሻሉበትና ይበልጥ የሚጠናከሩበት መንገድ ሊቀመጥላቸው ይገባል (Stones and Morris 1972 Sirvatava and Bose 1978 Goldhammer et al 1980 Richards and Nunan 1990)።

### *2.1.3.4.3.3 ምጋቤ ምላሽ፣ በሱፐርቪዥን ሂደት*

የማስተማር ልምምድ በበቂ ሱፐርቪዥን ካልተደገፈ፤ ሱፐርቪዥን ደግሞ በተገቢ ምጋቤ ምላሽ ካልተጠናከረ ብቁ የሆኑ መምህራንን ማፍራቱ አይታሰብም (Sirvastava and Bose 1978)። ይህም በሱፐርቪዥን ሂደት ምጋቤ ምላሽ የተለየ አትኩሮት ሊሰጠው እንደሚገባ ያመለክታል። እንደ Reece and Walker (2004፣421) ምጋቤ ምላሽ «አንድን የማስተማር ተግባር (task) በማከናወን ረገድ ምን ያህል ችሎታና ብቃት እንዳላቸው የሚያመላክት መረጃን ለተማሪ አስተማሪዎች የማስተላለፍ ሂደት ነው»። በዚህም በሚፈለግባቸውና ባከናወኑት የማስተማር ተግባራት መካከል የሚታየውን ልዩነት በግልፅ ይመለከቱበታል፤ ልዩነቱንም ለማጥበብ ይተጉበታል (Perlberg 1976፣17)። በአጠቃላይ ምጋቤ ምላሽ ለተማሪ አስተማሪዎች ስላከናወኗቸው የማስተማር ተግባራት ተገቢነት ማረጋገጫ የሚያገኙበት፤ ስህተት ገድፈታቸውን ተመልክተው የሚያስተካክሉበት/ የሚያርቁበት፤ በደንብ ያልገባቸውን አጥርተው የሚገነዘቡበት፤ የተለያዩ የማስተማር ክህሎቶችን እንዴት መካን (master) እንደሚችሉ ጠንቅቀው የሚረዱበት፤ በመጨረሻም ስለሚያስተምሩት ትምህርት ከፍተኛ የሆነ በራስ መተማመን የሚጎናፀፉበት ሂደት ነው (Ausubel and Robinson 1969፣299-300)።

ከምጋቤ ምላሽ ሂደት ተማሪ አስተማሪዎች ተገቢውን ሙያዊ ልምድ መገብየት ይችሉ ዘንድ በአቀራረቡ ላይ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል። Reece and Walker እንደሚሉት የምጋቤ ምላሽ አቀራረቡ የማስተማር ክህሎታቸውን እንዴት የበለጠ ማሻሻል እንደሚችሉ በማመላከት፤

ምን ምን ነጥቦችን ቢያካትቱ ኖሮ የተሻለ እንደሚሆን በመጠቋቆም፣ በጣም ግልፅ ያልሆኑላቸውን ጉዳዮች አንስቶ ሰፊ የውይይት መድረክን መፍጠር ላይ ቢያተኩር ይመረጣል። ይህም በቃል ብቻ ሳይሆን በፅሑፍም የተደገፈ ቢሆን ይበልጥ ውጤታማ ይሆናል (2004፣ 304)። እነ Stones and Morris ደግሞ ምጋቤ ምላሹ ተገቢውን አቀራረብ መከተሉ ብቻ በቂና ውጤታማ አያስኘውም ይላሉ፤ ይኸውም «ቡቴፕ ወይም በቪዲዮ እስካልተቀረፀ ድረስ የግድ በቶሎ ወይም ሳይዘገይ መሰጠት አለበት» (1972፣ 242)። Dukinም የተማሪ አስተማሪዎች የማስተማር ክሆሎት የሚጎለብተው አዎንታዊ ጎኖችን መሠረት አድርጎ፣ ቶሎ ቶሎና በተከታታይ በሚሰጥ ምጋቤ ምላሽ አማካይነት ነው በማለት ይህንኑ ያጠናክራሉ (1978፣ 123)። ስለዚህ ምጋቤ ምላሽ ሂደት ለነዚህ ጉዳዮች ተገቢውን ትኩረት መስጠት አስፈላጊ ይሆናል።

በአጠቃላይ በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር በማስተማር ልምምድ ሂደት ውስጥ ወሳኝ ቦታ ስላለው፣ ስለሱፐርቪዥን ለማየት ሞክረናል። በዚህም ከማስተማር ልምምድ ጋር ስላለው የጠበቀ ቁርኝት፣ ስለምንነቱ፣ ስለዓላማና ተግባሩ፣ ስለሱፐርቫይዘር ሚናና የሱፐርቪዥን አከናወን ሂደት፣ እንዲሁም ስለምጋቤ ምላሽ አጠቃላይ የሆነ ምልከታ አድርገናል። ከዚህ በማስከተል ደግሞ በፕራክቲከምና ማስተማር ልምምድ ላይ የቀረቡ ሃገራዊ ጥናቶችን ለመዳሰስ እንሞክራለን።

## 2.3. በፕራክቲከምና በማስተማር ልምምድ ላይ የቀረቡ ሃገራዊ ጥናቶች ዳሰሳ

በኢትዮጵያ የመምህራን ስልጠና መርሃ ግብርም ሆነ የማስተማር ልምምዱን ሂደት በተመለከተ ከተለያየ አንፃር በርካት ያሉ ጥናቶች ቀርበዋል። ጥናቶቹም ከቀረቡበት ጊዜና ምክንያት፣ መሠረት ካደረጉት ሥርዓተ ትምህርት፣ ከሚያተኩሩበት ርዕስ ጉዳይ... አንፃር የተለያዩ ናቸው። ስለሆነም በዚህ ጥናት በመምህራን ስልጠናም ሆነ በማስተማር ልምምድ ላይ የቀረቡ ቀደምት ጥናቶችን ባጠቃላይ ለመዳሰስ አልተሞከረም። ከዚህ ይልቅ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም የማስተማር ልምምድንና ፕራክቲከምን በተመለከተ የቀረቡ ጥናቶችን ብቻ ነው ለመቃኘት የተሞከረው።

ዓለም እሸቱ (1989)፣ ‹በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሑፍ ክፍል ድህረ የማስተማር ልምምድ ውይይት የሱፐርቫይዘሮች ምግበ-መረጃ ትንተና› በሚል ርዕስ ጠለቅ ያለ ጥናት አቅርቧል። ዓለም፣ በዚህ ጥናቱ በኮሌጁ ያለውን የማስተማር ልምምድና የሱፐርቪዥን ሂደት፣ ሱፐርቫይዘሮቹ የሚያዘወትሩትን የሱፐርቪዥን አቀራረብ፣ ስለሱፐርቪዥኑ ሂደት ተማሪ አስተማሪዎች ያላቸውን አተያይ፣ እና በኮሌጁ ያለውን አጠቃላይ የማስተማር ልምምድና የሱፐርቪዥን ሂደት በጥልቀት መርምሯል። ከዚህም በመነሳት በኮሌጁ በሚካሄደው የማስተማር ልምምድ ሂደት ሱፐርቫይዘሮች ለተማሪ አስተማሪዎች የሚሰጡት ምግበ መረጃ በምን ላይ ያተኩራል? እንዴትስ ይቀርባል? ለተማሪ አስተማሪዎች ዘላቂ ሙያዊ ዕድገትስ ምን ያህል የጠነከረ እገዛ ይሰጣል? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ችሏል።

ዓለም፣ ጥናቱን መሠረት ያደረገው በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ፅሑፍ ትምህርት ክፍል በ1988 የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት ላይ የተካሄደውን የማስተማር ልምምድ ሂደት ነው። በዚህም በትምህርት ክፍሉ የሚገኙ የዲግሪና የዲፕሎማ መርሃ ግብር ተመራቂ ተማሪዎችንና ሱፐርቫይዘሮቻቸውን (መምህሮቻቸውን) የጥናቱ ተተኳሪዎች አድርጓል። ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችንም ከነዚሁ ተተኳሪዎች በአራት የተለያዩ መንገዶች አጠናቅሯል። የተማሪ ማስታወሻ፣ የካሴት ቅጅ (የሱፐርቪዥን ምግበ መረጃ ሂደትን)፣ የፅሑፍ መጠይቅ እና የመገምገሚያ ቅፅን በመጠቀም። እነዚህን ከተለያየ አንግር ያጠናቀራቸውን መረጃዎችም መሠረት በማድረግ፣ በኮሌጁ የነበረው የማስተማር ልምምድ ሂደትና የሱፐርቪዥን ምግበ መረጃ አቀራረብ በተገቢው መንገድ እንደማይካሄድ ለማሳየት ችሏል። በተቃና መልኩ ላለመካሄዱ፣ የሱፐርቫይዘሮቹ በቂ ስልጠና አለማግኘት፣ የኮሌጁ ለማስተማር ልምምዱ ሂደት ተገቢውን ትኩረት አለመስጠት፣ የማስተማር ልምምዱ በበቂ ቅድመ ዝግጅት ላይ አለመመስረት፣ እና የማስተማር ልምምዱን ዓይነተኛ ዓላማና ግብ በተመለከተ ሱፐርቫይዘሮችም ሆኑ ተማሪ አስተማሪዎቹ ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛነት ዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች መሆናቸውን በጥናቱ አመልክቷል። በመጨረሻም ለኮሌጁ መምህራን ሙያዊ ብቃታቸውን የሚያዳብር ስልጠና (ሱፐርቪዥንን በተመለከተ) ቢሰጥ፣ በማስተማር ልምምዱ ሂደት ላይ የተባባሪ ት/ቤቶች መምህራን እንዲሳተፉ ቢደረግ፣ እንዲሁም የማስተር ልምምዱን ሂደት አጠቃላይ ዓላማና ግብ በግልፅ የሚያሳይ መርሃ ግብር ቢቀረፅና ለሱፐርቫይዘሮችም እንዴት ኃላፊነታቸውን መወጣት እንዳለባቸው የሚያመለክት ዝርዝር መግለጫ ቢሰጣቸው፣ በኮሌጁ የሚስተዋለው ደካማ የማስተማር ልምምድና የሱፐርቪዥን ሂደት ሊሻሻልና ሊቃና እንደሚችል አስተያየት በመስጠት ጥናቱን አጠቃሏል።

ተስጠ አሰፋ (1997)፣ የፕራክቲከም፣ የማስተማር ልምምድና የሱፐርቪዥን አተገባበር፣ በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሰርተፍኬት (10+1) መርሃ ግብር" በሚል ርዕስ ሰፋ ያለ ጥናት አካሂዷል። ተስጠ፣ በዚህ ጥናቱ በአዲሱ የመምህራን ሥልጠና ፖሊሲ መሠረት በ10+1 የሰርተፊኬት መርሃ ግብር በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ እየተከናወነ ያለው የፕራክቲከም፣ የማስተማር ልምምድና የሱፐርቪዥን ትግበራ ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ሞክሯል። ባደረገው ፍተሻም፣ በኮሌጁ የፕራክቲከም፣ የማስተማር ልምምድና የሱፐርቪዥን ትግበራው እንዴት እየተከናወነ ነው? የሂደቱን ተግባራዊነት ለመከታተል ምን ዓይነት ስልት ጥቅም ላይ ውሏል? የሂደቱ ተሳታፊ የሆኑት የተባባሪ ት/ቤቶች መምህራን ኃላፊነታቸውን ምን ያህል እየተወጡ ነው? ተማሪ አስተማሪዎች ለሂደቱ ያላቸው አስተያየትስ ምን ይመስላል? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥቷል።

ተስጠ፣ ጥናቱን ያጠናቀረው በኮሌጁ ለአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል መምህርነት (በአፃፃፍ ትምህርት) በመሰልጠን ላይ የሚገኙ ተማሪዎች በፕራክቲከም ሦስትና አራት ላይ ያደረጉትን የፕራክቲከም ልምምድ በመከታተል ነው። የጥናቱ ተተኳሪዎችም ተማሪ

አስተማሪዎች፣ የኮሌጁ መምህራንና የተባባሪ ት/ቤቶች መምህራን ናቸው፤ ከነዚሁ ተተኳሪዎችም በተማሪ ማስታወሻ፣ በምልከታ፣ በፅሑፍና በቃለመጠይቅ፣ እንዲሁም በመገምገሚያ ቅፅ አማካይነት ለጥናቱ የሚያስፈልጉትን መረጃዎች አሰባስቧል:: ባጠናቀራቸው መረጃዎች መሠረትነትም፣ በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በ10+1 የአሃዳዊ ትምህርት መምህራን ስልጠና መርሃ ግብር ያለው የፕራክቲከም፣ የማስተማር ልምምድና የሱፐርቪዥን አተገባበር በአግባቡ እንደማይከናወን አሳይቷል:: በአግባቡ ላለመተግበሩም ዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች የቅድመ ፕራክቲከም ውይይት አለመካሄድ፣ የተባባሪ ት/ቤት መምህራን ግንዛቤ አናሳነት፣ የኮሌጁ ለፕራክቲከሙ ሂደት ተገቢውን ትኩረት አለመስጠት፣ የኮሌጁ መምህራን የሱፐርቪዥኑንና የምገባ መረጃውን ሂደት በአግባቡ አለመተግበር፣ እና የኮሌጁ በፍላጎት ላይ ያልተመሠረተና ዝቅተኛ ውጤት ያላቸውን ሰልጣኞች መቀበል መሆናቸውን አመልክቷል::

**Kindalem Damte (2005)** "The Implementation of Practicum in the Education Faculty of Addis Ababa University: ELT in Focus" በሚል ርዕስ ባጠናቀረው ጥናት፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሥነትምህርት ፋካልቲ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ያለውን የፕራክቲከም አተገባበር ሂደት ተመልክቷል:: ከንዳለም፣ በዚህ ጥናቱ የተመለከተው ዋና ጉዳይ በፕራክቲከም ትግበራው ሂደት የሚሳተፉት አካላት (ተማሪ አስተማሪዎች፣ የዩኒቨርስቲውና የተባባሪ ት/ቤቶች መምህራን፣ የዩኒቨርስቲውና የተባባሪ ት/ቤቶች የፕራክቲከም አመራሮች) ስለፕራክቲከም ያላቸውን ግንዛቤ እና የሥራ ኃላፊነታቸውን ነው:: ከዚህም በመነሳት በጥናቱ፣ የፕራክቲከም መርሃ ግብር ተሳታፊዎች የሥራ ድርሻና ኃላፊነት ለመወጣት ምን ያህል ዝግጁ ናቸው? ስለፕራክቲከሙ ሂደት ያላቸው ግንዛቤና አመለካከት ምን ይመስላል? በመካከላቸው ያለው ግንኙነትና ትንጅታዊ እንቅስቃሴ እንዴት ያለ ነው? በዩኒቨርስቲውና በት/ቤቶች ያለው ሁኔታ ለፕራክቲከሙ ምን ያህል የተመቸ ነው? ለተማሪ አስተማሪዎች የሚሰጠው እገዛስ ምን ይመስላል? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሯል::

ከንዳለም፣ ጥናቱን ያተኮረው በሁለተኛ ደረጃ መምህራን ስልጠና ሂደት ከሚሰጡት አምስት የፕራክቲከም ኮርሶች መካከል በፕራክቲከም ሁለትና ሦስት ላይ ሲሆን፣ ተጠኝዎቹም በፕራክቲከም ትግበራው ሂደት ላይ የሚሳተፉቱ አምስቱ አካላት ናቸው:: ለጥናቱ የሚያስፈልጉትን መረጃዎችም በተማሪዎች የመገምገሚያ ቅፅ፣ በፅሑፍ መጠይቅ፣ በቃለ መጠይቅ እና በምልከታ አማካይነት አጠናቅሯል:: ካጠናቀራቸው መረጃዎችም በመነሳት፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሥነ ትምህርት ፋካልቲ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ያለው የፕራክቲከም ትግበራ ሂደት በአጠቃላዩ ሃገር አቀፍ የፕራክቲከም መመሪያም ሆነ ዩኒቨርስቲው ራሱ ባወጣው መርሃ ግብር መሠረት እንደማይከናወን አመልክቷል:: ለዚህም እንቅፋት የሆኑት የግንዛቤ እጥረት፣ የተሳታፊ አካላቱ ተቀራርቦና ተቀናጅቶ አለመሥራት እና ኃላፊነትና የሥራ ድርሻቸውን ችላ ማለት፣ ተገቢና አመቺ የጊዜ ሰሌዳ አለመንደፍ፣ ለተማሪዎች የሚሰጠው እገዛ

በጣም አነስተኛ መሆን፤ በምዘናው ሂደት ወጥነት አለመታየቱና ከናካቴውም አለመካሄዱ፤ ለተማሪዎችና ለት/ቤት መምህራን የሚሰጠው የገንዘብ ማበረታቻ አነስተኛ መሆን፣ እና እንዲሁም ከመንግስት በኩል (በተለይ ከትምህርት ሚኒስቴር) ጫና መደረጉ መሆናቸውን ጠቅሷል።

**Gebremedhin Simon (2001)** «Aspects of Teacher Development for English Language Teaching» በሚል ርዕስ ጥናት አካሂዷል። ጥናቱን ያካሄደው በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ላይ ሲሆን፤ በዚህም የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህራን ዝግጅት ሂደቱንና የአተገባበሩን ሁኔታ ለመፈተሽ ሞክሯል። በጥናቱ ያተኮረበት ጉዳይም የመምህራን ስልጠናው ሂደትና የማስተማር ልምምዱ ሲሆን፤ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችንም ከተለያዩ ተዛማጅ ሥራዎችና ከእንግሊዝኛ ቋንቋ የድህረ ምረቃ እና የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች አሰባስቧል። በክፍለ ትምህርቱ ያለውን የመምህራን ስልጠናና የማስተማር ልምምድ ሂደቱን አተገባበር ለመፈተሽም እነዚህ የድህረ ምረቃ ተማሪዎች የሚያቀርቧቸውን ሰሌዳች መርምሯል፤ የቅድመ ምረቃ ተማሪ አስተማሪዎች የሚያካሂዱትን የክፍል ውስጥ የማስተማር ልምምድ ሂደትም ለአንድ ወር ያህል ተከታትሏል። በጥናቱ መጨረሻም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም ያለው የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህራን ስልጠና ሂደትና አተገባበሩ በርካታ ችግሮች ያሉበት መሆኑን አሳይቷል። አብዛኞቹ ተማሪ አስተማሪዎች ስለማስተማር ልምምድ (አስፈላጊነት) ያላቸው ግንዛቤም ሆነ ለልምምዱ ሂደት ያላቸው መነሳሳት በጣም አነስተኛ መሆኑ በስልጠናው ሂደት ላይ ከሚንፀባረቁት ችግሮች መካከል በዋናነት የሚጠቀሱ መሆኑን አመልክቷል። በጥናቱ ማጠቃለያ ላይም ተማሪ አስተማሪዎች ለንዑስ ማስተማርና ለማስተማር ልምምድ ያላቸውን ግንዛቤ ይበልጥ ማዳበር ቢቻል፤ ለማስተማር ልምዱ የሚመደበው የክፍለ ጊዜ መጠን ቢራዘምና ተገቢው ክትትልም ቢደረግበት፤ እንዲሁም በማስተማር ልምምዱ ሂደት ጫና የማይበዛባቸው (ነፃ የሆኑ) ተባባሪ ት/ቤቶች ተሳታፊ እንዲሆኑ ቢደረግ በስልጠናው ሂደት ላይ የሚንፀባረቁትን ችግሮች ለመቅረፍ እንደሚያስችል ጠቁሟል።

# ምዕራፍ ሦስት

# የጥናቱ ዘዴ

## 3.1. የጥናቱ ተተኳሪዎችና የናሙና አወሳሰድ

### *3.1.1. የጥናቱ ተተኳሪዎች*

የፕራክቲከም መርሃ ግብርን በመተግበሩ ሂደት አምስት አካላት ተሳትፎ ያደርጋሉ፡፡ እነሱም የመምህራን ስልጠና ተቋሙ፣ የተቋሙ መምህራን፣ ተባባሪ ት/ቤቶች፣ የት/ቤቶቹ መምህራን እና ተማሪ አስተማሪዎች ናቸው፡፡ ሁሉም ለሂደቱ መሳካት የየራሳቸው የሥራ ድርሻና ኃላፊነት (duties and responsibilities) አላቸው፡፡ እነዚህ አምስቱ አካላት በሚያደርጉት ቅንጅታዊ እንቅስቃሴ አማካይነትም የፕራክቲከም መርሃ ግብሩ ትግበራ እውን ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡

የዚህ ጥናት ዓይነተኛ ትኩረትም በሮቤ መምህራን ኮሌጅ በ10+3 የዲፕሎማ መርሃ ግብር በቋንቋ ስትሪም ያለውን የፕራክቲከም ኮርስ (IV) የአተገባበር ሂደት መፈተሽ እንደመሆኑ መጠን፣ አምስቱም የመርሃ ግብሩ ተሳታፊዎች የጥናቱ ተተኳሪዎች ተደርገዋል፡፡ በዚህም መሠረት ኮሌጁ፣ የኮሌጁ የቋንቋ ስትሪም መምህራን፣ ተባባሪ ት/ቤቶች፣ የተባባሪ ት/ቤቶች የቋንቋ መምህራን እና የቋንቋ ስትሪም የሦስተኛ ዓመት መደበኛ ተማሪ አስተማሪዎች የጥናቱ ተተኳሪዎች ሆነዋል፡፡

### *3.1.2. የናሙና አወሳሰድ*

የፕራክቲከም መርሃ ግብርን በቅንጅት ተግባራዊ የሚያደርጉት ከፍ ሲል የተጠቀሱት አምስቱም ተሳታፊ አካላት የጥናቱ ተተኳሪዎች ናቸው፡፡ ከነዚህ አካላትም ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለማጠናቀር የሚያስችሉ ወካይ ናሙናዎች ተወስደዋል፡፡ ናሙናዎቹ የተወሰዱበትም አግባብ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

#### *3.1.2.1. የኮሌጁ መምህራን*

በሮቤ መምህራን ኮሌጅ የቋንቋ ስትሪም 12 መምህራን ይገኛሉ፡፡ ስትሪሙም ሦስት የትምህርት ክፍሎችን በሥሩ ይዟል፡፡ እነሱም የአፋን ኦሮሞ፣ የአማርኛ እና የእንግሊዝኛ የትምህርት ክፍሎች ሲሆኑ፣ እንደየቅደም ተከተላቸውም 4፣ 2፣ 6 መምህራን አላቸው፡፡ ከነዚህ በስትሪሙ ከሚገኙ 12 መምህራን መካከልም ከአንዲት መምህርት በቀር (ዓይነ ሥውር በመሆኗና በፕራክቲከም ሂደት ላይም ስለማትሳተፍ) የተቀሩት 11 መምህራን በግኝት (availability) ንሞና ተወስደዋል፡፡

### 3.1.2.2. ተማሪ አስተማሪዎች

በኮሌጁ የቋንቋ ስትሪም በመደበኛው የቀን መርሃ ግብር ከ1ኛ-3ኛ ዓመት 650 ተማሪዎች በመማር ላይ ይገኛሉ። ከነዚህም የዚህ ጥናት (ቀጥተኛ) ተተኳሪ የተደረጉት በሦስተኛ ዓመት ላይ የሚገኙቱ 250 ተማሪ አስተማሪዎች ብቻ ናቸው። ይህም የሆነበት ምክንያት እነዚህ ተማሪዎች የፕራክቲከም መርሃ ግብር በሃገር አቀፍ ደረጃ መተግበር ከጀመረበት ከ1996 ጀምሮ የነበሩበት በመሆናቸው፣ አንፃራዊ በሆነ መልኩ ከሌሎቹ ተማሪዎች የተሻለና የበሰለ መረጃ ይሰጣሉ ተብሎ ስለታመነበት ነው። ከዚህም ባሻገር ጥናቱ ፕራክቲከም አራትን (IV) መሠረት ያደረገ እንደመሆኑ መጠን፣ ይህን ኮርስ የሚወስዱ ብቸኞቹ የስትሪሙ ተማሪዎች እነሱ በመሆናቸው ነው። ከዚህም የተነሳ 250ዎቹ የሦስተኛ ዓመት የቋንቋ ስትሪም ተማሪ አስተማሪዎች ብቻ የጥናቱ ተተኳሪዎች እንዲሆኑ ሆኗል። ከነዚህም መካከል አስፈላጊውን መረጃ ይሰጣሉ ተብለው የታመነባቸው 112 ተማሪ አስተማሪዎች በዓላማዊ (Purposive) ንሞና ተለይተው ተወስደዋል። አወሳሰዱም ኮሌጁ ያዘጋጀውን የሚከተለውን የፕራክቲከም የምደባ (ሁኔታ) መሠረት አድርጎ የተከናወነ ነው።

| የክፍል ደረጃ | የተመደቡባቸው ት/ቤቶች | | | | | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | መደወላቡ | ጋሰማ | አሊቢራ | ዘይበላ | አማኑዔል | ኪጵጡቴ | ቱሉዲምቱ (ጎባ) | |
| ከ1ኛ- 4ኛ | 39 | 22 | 11 | 15 | 12 | 11 | 10 | 120 |
| ከ5ኛ- 8ኛ | 35 | 32 | 22 | 18 | - | - | 23 | 130 |
| ድምር | 74 | 54 | 33 | 33 | 12 | 11 | 33 | 250 |

ሰንጠረዥ፦ በሮቤ መምህራን ኮሌጅ የሦስተኛ ዓመት የቋንቋ ስትሪም ተማሪዎች የፕራክቲከም ምደባ

ከሰንጠረዡም መመልከት እንደሚቻለው፣ ካሉት 250 ተማሪዎች መካከል 120ዎቹ ከ1ኛ-4ኛ ክፍል እንዲያስተምሩ፣ የተቀሩት 130 ደግሞ ከ5ኛ-8ኛ ክፍል እንዲያስተምሩ ተመድበዋል። ከነዚህም ከ1ኛ-4ኛ ክፍል ላይ የተደለደሉት፣ ከሚሰለጠኑበት የሁለተኛ ሳይክል (5-8) መምህርነት ቡታች ወይም ውጪ የተመደቡ በመሆናቸው በጥናቱ እንዲካተቱ አልተደረገም። በዚህም መሠረት ከ5ኛ-8ኛ ባሉ የክፍል ደረጃዎች ላይ የተደለደሉት ተማሪዎች ብቻ ለጥናቱ ተመርጠዋል። እነዚህም ከ7ቱ ት/ቤቶች በ5ቱ ላይ የተደለደሉ ናቸው። ከነዚህም በዘይበላ ት/ቤት የተመደቡት ብቻ ሲቀሩ ሌሎቹ ግን ሙሉ በሙሉ በጥናቱ ተካተዋል። የዘይበላ ት/ቤት ግን ከዚህ ቀደም በአማርኛ ቋንቋ ብቻ ያስተምር የነበረ የመንግስት ት/ቤት ቢሆንም፣ በዚህ ዓመት (1998) አዲስ ተማሪዎች ባለማግኘቱ ሙሉ በሙሉ ወደ አፋን ኦሮሞ ተመልሶ በአዲስ መልክ በመዋቀሩ በጥናቱ እንዲካተት አልተደረገም። በመሆኑም ጥናቱ በአራቱ ት/ቤቶች (ማለትም መደወላቡ፣ ጋሰማ፣ አሊ ቢራ እና ቱሉ ዲምቱ) ላይ ከ5ኛ - 8ኛ ክፍል የተመደቡትን 112

ተማሪ አስተማሪዎች ብቻ በግኝት ንሞና ወስዷል። እነዚህም ከአጠቃላዩ የሦስተኛ ዓመት የቋንቋ ስትሪም ተማሪዎች 45 እጁን ይሸፍናሉ።

### 3.1.2.3. የተባባሪ ት/ቤት መምህራን

ለዚህ ጥናት የተመረጡት ተማሪ አስተማሪዎች በመደወላቡ፣ በጋለማ፣ በአሊቢራ እና ቱሉ ዲምቱ ት/ቤቶች ከ5ኛ-8ኛ ክፍል የተመደቡት ናቸው። በተመሳሳይ መንገድ በነዚሁ ት/ቤቶች ከ5ኛ-8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የቋንቋ መምህራን በዒላማዊ ንሞና ተለይተው ተመርጠዋል። በነዚህ ት/ቤቶችም በተጠቀሰው የክፍል ደረጃ ላይ አፋን ኦሮሞን፣ አማርኛን እና እንግሊዝኛን የሚያስተምሩ 24 መምህራን የሚገኙ ሲሆን፣ እነዚህም በቅደም ተከተላቸው መሠረት 10፣ 7፣ 7 ናቸው። 24ቱም በግኝት ንሞና አማካይነት በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርጓል።

### 3.1.2.4. ኮሌጁና ተባባሪ ት/ቤቶች

በኮሌጁና በተባባሪ ት/ቤቶች በኩል የፕራክቲከሙን መርሃ ግብር በበላይነት የሚመሩ አካላትም፣ ሌሎቹ የዚህ ጥናት ተተኳሪዎች ናቸው። በሮቢ መምህራን ኮሌጅ በኩል መርሃ ግብሩን በበላይነት የሚመራው የኮሌጁ የፕራክቲከም ክፍል ኃላፊ ሲሆን፣ በት/ቤቶች በኩል ደግሞ ርዕሳነ መምህራኑ ናቸው። በዚህም መሠረት ጥናቱ የኮሌጁን የፕራክቲከም ክፍል ኃላፊ እና ቀደም ሲል የተወሰኑትን 4 ት/ቤቶች (መደወላቡ፣ ጋለማ፣ አሊ ቢራና ቱሉ ዲምቱ) ርዕሳነ መምህራን በዒላማዊ ንሞና ወስዷል።

## 3.2 የመረጃ አሰባሰብ

ለዚህ ጥናት የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለማሰባሰብ አራት የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች ጥቅም ላይ ውለዋል። እነዚህም የፅሑፍ መጠይቅ፣ ቃለመጠይቅ፣ ምልከታና የግምገማ ቅፅ ናቸው። የፅሑፍ መጠይቅ ከኮሌጁ መምህራን፣ ከተማሪ አስተማሪዎቹና ከት/ቤት መምህራን አጠቃላይ የፕራክቲከም አተገባበር ሂደትን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለማሰባሰብ የዋለ ሲሆን፣ ቃለ መጠይቅም ከኮሌጁ የፕራክቲከም ክፍል ኃላፊና ከት/ቤቶቹ ርዕሳነ መምህራን ተጓዳኝ መረጃዎችን ለመሰብሰቢያነት አገልግሏል። ምልከታና የግምገማ ቅፅ ደግሞ የተማሪ አስተማሪዎችን የክፍል ውስጥ የማስተማር ክንውን የሚመለከቱ መረጃዎችን ከኮሌጁ መምህራንና ከተማሪ አስተማሪዎቹ ለማሰባሰብ ጥቅም ላይ ውለዋል። እያንዳንዱ የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያ በጥናቱ ውስጥ ያገለገለበትም መንገድ የሚከተለውን ይመስላል።

### 3.2.1. የፅሑፍ መጠይቅ

የፅሑፍ መጠይቅ በኮሌጁ ያለውን አጠቃላይ የፕራክቲከም ትግበራ ሂደት በተመለከተ ከኮሌጁ መምህራን፣ ከተማሪ አስተማሪዎችና ከት/ቤት መምህራን መረጃ ለመሰብሰብ የዋለ ዋንኛ መሣሪያ ነው። የፅሑፍ መጠይቁ Kindlem Damte (2005) በሁለተኛ ደረጃ መምህራን ስልጠና መርሃ ግብር ያለውን የፕራክቲከም ትግበራ ለመፈተሽ ከተገለገለበት ላይ፣ ለ10+3 መምህራን ስልጠና መርሃ ግብር በሚያመች መልኩ የተወሰደ ነው። ብቃትና አስተማማኝነቱንም

ለማረጋገጥ፣ ዋናው ጥናት ከሚካሄድበት ኮሌጅ ጋር አቻ በሆነው በአዳማ መምህራን ኮሌጅ ላይ የሙከራ ጥናት (pilot study) ተደርጓል:: በዚህም ከኮሌጁ (አዳማ) የቋንቋ ስትሪም መምህራን፣ ከሦስተኛ ዓመት የቋንቋ ስትሪም ተማሪ አስተማሪዎች እና ከተባባሪ ት/ቤት (አዳማ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት) የቋንቋ መምህራን የተገኘውን ምላሽ መሠረት በማድረግ፤ ባለሙያዎችም ተጨማሪ ሙያዊ አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጓል:: በሁለቱም በኩል የተገኙትን ምላሾችና አስተያየቶች መነሻ በማድረግም ማሻሻያዎች ተደርገዋል:: በዚህ መንገድ ተሸሽሎ በተዘጋጀው የፅሑፍ መጠይቅ ውስጥ የተካተቱት ጥያቄዎችም ውስን (closed) እና ልቅ (open) የአጠያየቅ መንገድን ተከትለው የቀረቡ ሲሆን፤ ሁሉም ጥያቄዎች በፕራክቲከም አተገባበር ሂደት TESO ለኮሌጁና ለት/ቤት መምህራን፣ ለተማሪ አስተማሪዎች፣ ለኮሌጁና ለተባባሪ ት/ቤቶች ያስቀመጠውን የሥራ ድርሻና ኃላፊነት የተመለከቱ ናቸው:: በዚህም መሠረት ተመሳሳይ ይዘት (content) ያላቸው የፅሑፍ መጠይቆች ለኮሌጁ የቋንቋ ስትሪም መምህራን፣ ለት/ቤት የቋንቋ መምህራን እና ለተማሪ አስተማሪዎቹ ተዘጋጅተዋል:: እንዲሞሉም ተደርጓል::

በሮቤ መምህራን ኮሌጅ በቋንቋ ስትሪም ለሚገኙ ለ11ም መምህራን የተዘጋጀላቸው መጠይቅ ተሠራጭቶ፤ ሁሉም ተሞልቶ ተመልሷል:: በተመሳሳይ መንገድ ጥናቱ ባተኮረባቸው አራቱ ተባባሪ ት/ቤቶች ውስጥ ለሚገኙ 24 የቋንቋ መምህራንም የተዘጋጀላቸው የፅሑፍ መጠይቅ ተሠራጭቷል:: ከ24ቱ መጠይቆችም መካከል 17ቱ ብቻ ተመልሰዋል:: ለጥናቱ በተመረጡት አራት ት/ቤቶች ከ5ኛ-8ኛ ክፍል ላይ ለተመደቡት 112 ተማሪ አስተማሪዎችም የተዘጋጀው መጠይቅ ተሠራጭቷል:: በት/ቤቶቹ የተሠራጨውና የተመለሰው የፅሑፍ መጠይቅ ዝርዝርም የሚከተለውን ይመስላል::

| የፅሑፍ መጠይቆቹ ሥርጭት | ተማሪ አስተማሪዎቹ የተመደቡባቸው ት/ቤቶች | | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| | መደወላቡ | ጋሰማ | አሊ. ቢራ | ቱሉዲምቱ | |
| የተሠራጨው | 35 | 32 | 22 | 23 | 112 |
| የተመለሰው | 31 | 30 | 18 | 21 | 100 |

### 3.2.2. ቃለመጠይቅ

ቃለ መጠይቁ ከፅሑፍ መጠይቆቹ የተሰበሰበውን መረጃ ይበልጥ ለማጠናከር ይረዳ ዘንድ ለፕራክቲከም ኃላፊውና ለት/ቤት ዳይሬክተሮች የተዘጋጀ ነው:: በዚህም መሠረት በቃለመጠይቁም፣ በፅሑፍ መጠይቆቹ ውስጥ ከተካተቱት ጥያቄዎች ጋር ተዛማጅ የሆኑ ጥያቄዎች ተካተዋል:: እንዲሁም ለፕራክቲከም ትግበራው ሂደት መሳካት በኮሌጁና በት/ቤቶቹ በኩል መከናወን አለባቸው ተብለው በTESO (2003) የተቀመጡትን ተግባራት የሚመለከቱ ጥያቄዎችም እንዲካተቱ ሆኗል:: ሁሉም ጥያቄዎች በከፊል ዝግጅት የተደረገባቸው (semi structured) ናቸው:: በዚህ መንገድ የተዘጋጁት የቃለመጠይቅ ጥያቄዎችም በኮሌጁ በኩል

ለፐራክቲከም ክፍሉ ኃላፊ፣ በተባባሪ ት/ቤቶች በኩል ደግሞ ለአራቱ (መደ ወላቡ፣ ጋሰማ፣ አሰ. ቢራና ቱሉ ዲምቱ) ት/ቤቶች ዳይሬክተሮች ቀርበዋል:: በካሴትም ተቀርፀዋል::

### 3.2.3. ምልከታ

ምልከታ የተማሪ አስተማሪዎችን የክፍል ውስጥ የማስተማር ክንውን ወይም ተግባራት (teaching tasks or activities) ብቃት ለመገምገም የተዘጋጀ ነው:: ምልከታውም በመመልከቻ ቅፅ አማካይነት በኮሌጁ የቋንቋ ስትሪም መምህራን የተከናወነ ሲሆን፣ በቅፁም የማስተማር መማር ሂደቶችን አጠቃላይ ሁኔታ የተመለከቱ ጥያቄዎችም ተካተውበታል:: እነዚህ ጥያቄዎችም ኮሌጁ ለተማሪ አስተማሪዎች መገምገሚያነት ካዘጋጀው ቅፅ የተወሰዱ ሲሆን፣ ይህም ትምህርት ሚኒስቴር ለHiher Diploma መርሃ ግብር ስልጠና ካዘጋጀው ሰነድ ላይ የተቀዳ ነው:: ይህን የምልከታ ቅፅ መሠረት አድርገውም ተማሪ አስተማሪዎችን እንዲመለከቱ፣ ለአሥራ አንዱም የኮሌጁ የቋንቋ ስትሪም መምህራን ሦስት ሦስት ቅፆች ተሠራጭተዋል:: ከተሰራጩት 33 የምልከታ ቅፆችም 21 ብቻ ተሞልተው ተመልሰዋል::

### 3.2.4. የግምገማ ቅፅ

በኮሌጁ የቋንቋ ስትሪም መምህራን የተከናወነውን የምልከታ ሂደት ለማጠናከሪያነት ይረዳ ዘንድ፣ ተማሪ አስተማሪዎችም የራሳቸውን የማስተማር ክንውን በተመለከተ የራስ ግምገማ ማስታወሻ (self-assessment reflective diary) እንዲፅፉ ተደርጓል:: ማስታወሻውም ኮሌጁ ተማሪ አስተማሪዎች በማስተማሩ ሂደት ማከናወን አለባቸው ብሎ የሰጣቸውን የግምገማ ቅፅ መሠረት አድርጐ የተዘጋጀ ነው:: ይህም አጠቃላይ ዕለታዊ የክፍል ውስጥ የማስተማር ክንውናቸውን ዝርዝር ሁኔታ እንዲያካትት ሆኖ በቅፅ መልክ ተዘጋጅቶ፣ ለ8 ተማሪ አስተማሪዎች ተሰጥቷል:: እነዚህ ተማሪ አስተማሪዎችም መምህራኑ ምልከታ ሲያደርጉ የሚገቡበትን ክፍል ተከታትሎ በመግባት የተመረጡ ናቸው:: በዚህ መንገድ ለጥናቱ በተመረጡት አራቱ ት/ቤቶች በመገኘት፣ ከየት/ቤቶቹ ሁለት ሁለት ተማሪ አስተማሪዎች በተዘጋጀላቸው የግምገማ ቅፅ ላይ ተመስርተው የራስ ግምገማ ማስታወሻ እንዲፅፉ ተደርጓል::

## 3.3 የመረጃ አተናተን

ለዚህ ጥናት የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ጥቅም ላይ የዋሉት መሣሪያዎች የፅሑፍ መጠይቅ፣ ቃለመጠይቅ፣ ምልከታና የግምገማ ቅፅ ናቸው:: በነዚህ መሣሪያዎች አማካይነት የተጠናቀሩት መረጃዎችም አሃዛዊና ዓይነታዊ ተብለው በሁለት ምድብ ከተለዩ በኋላ በንዓቄ የትንተና ዘዴ ተተንትነዋል::

ከፅሑፍ መጠይቅና ከምልከታ የተጠናቀሩት መረጃዎች በአመዛኙ አሃዛዊ (quantitative) ናቸው:: በፅሑፍ መጠይቆቹ ውስጥ «በጣም እስማማለሁ»፣ «እስማማለሁ»፣ «በመጠኑ እስማማለሁ»፣ «አልስማማም» እና፣ «ጨርሶ አልስማማም» የሚሉ አምስት አምስት አማራጮች ያላቸው ዝርዝር ጥያቄዎች ቀርበዋል:: ለያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጭ

ምላሾች መካከል «በመጠኑ እስማማለሁ» የሚለው ምላሽ ብቻውን ተደምሮ ሲቀመጥ፤ ሁለቱ አዎንታዊ ምላሾች (በጣም እስማማለሁና እስማማለሁ) እና ሁለቱ አሉታዊ ምላሾች (አልስማማምና ጨርሶ አልስማማም) ደግሞ አንድ ላይ እንዲደመሩ ተደርጓል፡፡ ከዚያም የሊከርት (likert) ዘዴ አካል በሆነው በመቶኛ ምላሽ (percentage responses) አማካይነት ተተንትነዋል፡፡ በምልከታ ቅፅ ውስጥም ለቀረቡት ውስን ጥያቄዎች ሦስት ሦስት አማራጭ ምላሾች (አዎ፣ እርግጠኛ አይደለሁምና አይ) የተቀመጠላቸው ሲሆን፤ ለየጥያቄዎቹ የተሰጡት ምላሾችም ለየብቻቸው ተደምረው በመቶኛ ምላሽ ተተንትነዋል፡፡

ከቃለመጠይቅና ከግምገማ ቅፅ፣ እንዲሁም በተወሰነ ደረጃ ከፅሑፍ መጠይቅና ከምልከታ ቅፁ የተጠናቀሩት መረጃዎች ደግሞ ዓይነታዊ (qualitative) ናቸው፡፡ በዚህ መንገድ የተጠናቀሩት ዓይነታዊ መረጃዎችም ከአሃዛዊ መረጃዎቹ ጋር እንዲሰናሰሉ ከተደረገ በኋላ ገላጭ የትንተና ዘዴን (descriptive analysis) መሠረት በማድረግ እንዲተነተኑ ተደርጓል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተና

በኦሮሚያ ክልላዊ መስተዳድር በሮቤ መምህራን ኮሌጅ በ10+3 የዲፕሎማ መርሃ ግብር ያለውን የፕራክቲከም አተገባበር ሂደት መፈተሽ የዚህ ጥናት ዓይነተኛ ትኩረት ነው። ለዚህም ይረዳ ዘንድ በፅሑፍ መጠይቅ፣ በቃለመጠይቅ፣ በምልከታ እና በኮሌጁ የግምገማ ቅፅ አማካይነት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ተችሏል። በነዚህ የመረጃ ማሰባሰቢያ መንገዶች የተጠናቀሩት መረጃዎችም ቀጥለው ይተነተናሉ።

## 4.1 የኮሌጅ መምህራን የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

የኮሌጅ መምህራን በፕራክቲከም መርሃ ግብር ሂደት ያከናወኗቸውን ተግባራት ከመመልከታችን በፊት በሮቤ መምህራን ኮሌጅ የቋንቋ ስትሪም ስለሚገኙት መምህራን አጠቃላይ የሆነ ዳራዊ ምልከታ ማድረግ ተገቢ ይሆናል።

ሰንጠረዥ 1፦ በሮቤ መምህራን ኮሌጅ የቋንቋ ስትሪም መምህራን አጠቃላይ ዳራዊ መግለጫ

| የትምህርት ደረጃ | | በማስተማር ላይ የቆዩበት ዓመት | | | | የሚያስተምሩት ቋንቋ | | | በሳምንት ያላቸው የክ/ጊዜ መጠን | | | ለፕራክቲከም የተመደቡላቸው ተማሪዎች ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የመጀመሪያ ዲግሪ | ሁለተኛ ዲግሪ | 1-5 | 6-10 | 11-15 | ከ15 በላይ | አፋን ኦሮሞ | አማርኛ | እንግሊዝኛ | 10-15 | 16-20 | 21-25 | 15-20 | 21-25 | ከ25 በላይ |
| 9 | 2 | 5 | 1 | 2 | 3 | 4 | 2 | 5 | 3 | 3 | 5 | 3 | 2 | 6 |
| 11 | | 11 | | | | 11 | | | 11 | | | 11 | | |

በሰንጠረዡ ላይ ከተመለከተው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው፣ በኮሌጁ የቋንቋ ስትሪም 11 መምህራን ይገኛሉ። ከነዚህም መካከል ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው 2 ብቻ ሲሆኑ የተቀሩት የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ናቸው። ከልምድ አንፃርም ግማሽ የሚሆኑት ከ10 ዓመት በታች ያስተማሩ ሲሆን፣ ከነዚህም አብዛኞቹ (5ቱ) በረዳት መምህርነት ደረጃ ላይ ይገኛሉ። አዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ በዚህ ደረጃ (10+3) ለሚሰጥ ስልጠና ይመጥናል ብሎ ካስቀመጠው የአስልጣኝ መምህራን የትምህርት ዳራ አንፃር ሲታይም፣ የኮሌጁ መምህራን አጥጋቢ በሆነ የትምህርት ደረጃ ላይ ናቸው ለማለት አያስችልም። ይህም የኮሌጁ የቋንቋ ስትሪም መምህራን በትምህርት ደረጃና በልምድ በኩል ይበልጥ መጠናከር እንደሚኖርባቸው ያመለክታል። ይሁንና በዚህ ረገድ ኮሌጁ (ሁሉም መምህራን) የከፍተኛ ዲፕሎማ (HDP) ስልጠና እንዲወስዱ

ማድረጉ፣ ሙያዊ ብቃታቸውን በተወሰነ ደረጃ ሊያጠናክረው ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኞቹ የስትሪሙ መምህራን በመደበኛው የቀን መርሃ ግብር ብቻ ከ20 በላይ ሳምንታዊ ክፍለ ጊዜ አላቸው። በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደትም ብዙዎቹ የስትሪሙ መምህራን ከ20 በላይ መደበኛ ተማሪዎችን ሱፐርቫይዝ ያደርጋሉ።

በአጠቃላይ ስለኮሌጁ የቋንቋ ስትሪም መምህራን ከቀረበው መረጃ/ መግለጫ መገንዘብ እንደሚቻለው፣ መምህራኑ በትምህርት ደረጃቸውም ሆነ በልምዳቸው በአስተማማኝ ደረጃ ላይ ናቸው ለማለት አይቻልም። በሳምንት ያላቸው ክፍለ ጊዜና ለፕራክቲከም የሚያማክሩት ተማሪ አስተማሪዎች በጣትም ከፍተኛ የሥራ ጫና እንዳለባቸው ያመለክታል። ስለመምህራኑ ዳራዊ ሁኔታ ይህን ካልን ዘንድ፣ በማስከተል ደግሞ በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት ለተማሪ አስተማሪዎች ያደረጉትን እገዛ ካላቸው የሥራ ድርሻና ኃላፊነት አንፃር እንመልከት።

## 4.1.1 የኮሌጅ መምህራን የሥራ ድርሻ፣ ቅድመና ድህረ ፕራክቲከም

የኮሌጅ መምህራን ከፕራክቲከም በፊትና በኋላ ለተማሪ አስተማሪዎች ምን እገዛ አድርገዋል የሚለውን ለመፈተሽ በፅሑፍ መጠይቅ—ከኮሌጅ መምህራኑና ከተማሪ አስተማሪዎች፣ እንዲሁም በቃለ መጠይቅ ከኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊና ከት/ቤቶች ርዕሳነ መምህራን መረጃዎች ተሰባስበዋል። በማስከተልም የኮሌጅ መምህራን ቅድመና ድህረ ፕራክቲከም ያከናወኗቸውን ተግባራት አስመልክቶ ለቀረበላቸው መጠይቅ የኮሌጅ መምህራንና ተማሪ አስተማሪዎች የሰጡትን ምላሽም እርስ በርሳቸውና በቃለ መጠይቅ ከተገኘው መረጃ ጋር እያገናዘብን እንመለከታለን።

ሰንጠረዥ 2፡- የኮሌጅ መምህራን ከፕራክቲከም በፊት ከተማሪዎች ጋር ተገናኝተው መወያየታቸውን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ የመምህራኑና የተማሪዎቹ ምላሽ

| | ዝርዝር መጠይቆች | በጣም እስማማለሁ (5) | እስማማለሁ (4) | ድምር | በመጠኑ እስማማለሁ (3) | አልስማማም (2) | ጨርሶ አልስማማም (1) | ድምር | ያልተመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የኮሌጅ መምህራን ምላሽ | ከፕራክቲከም በፊት ተገናኝተን ትብብር ሂደው ስለሚያከናውኗቸው ተግባራት ወስነናል | 3 | 5 | 8 (72.2%) | 1 (9.1%) | - | 2 | 2 (18.2%) | - |
| | ከፕራክቲከም በፊት ተገናኝተን ስለመሰረታዊ የማስተማር ክህሎት ተወያይተናል | 1 | 3 | 4 (36.4%) | 2 (18.2%) | 3 | 2 | 5 (45.4%) | - |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ | ከፕራክቲከም በፊት ተገናኝተን ት/ቤት ሄደን ስለምናከናውናቸው ተግባራት ወስነናል | 6 | 9 | 15 (15%) | 25 (25%) | 19 | 39 | 58 (58%) | 2 (2%) |
| | ከፕራክቲከም በፊት ተገናኝተን ስለመሰረታዊ የማስተማር ክህሎት ተወያይተናል | 5 | 11 | 16 (16%) | 19 (19%) | 30 | 32 | 62 (62%) | 3 (3%) |

ከፍ ሲል የተመለከተው የኮሌጅ መምህራን ምላሽ እንደሚያሳየው፣ መምህራኑ ከፕራክቲከም በፊት ከተማሪዎቻቸው ጋር ተገናኝተው በት/ቤት ስለሚከናወኑ ተግባራት እና ስለመሠረታዊ የማስተማር ክህሎት ይወስናሉ፣ ይወያያሉ የሚያስብል ነው:: ተማሪዎች በት/ቤት ተገኝተው ስለሚያከናውኗቸው ተግባራት ከፕራክቲከም በፊት ተገናኝተው መወሰናቸውን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ በከፍተኛ ሁኔታ አዎንታዊ ምላሽ (72.7%) ሰጥተዋል:: ይሁንና ስለመሠረታዊ የማስተማር ክህሎት ውይይት ማድረጋቸውን አስመልክቶ ለቀረበው ጥያቄም 36.4% አዎንታዊ፣ 18.2% በመጠኑ እስማማለሁና 45.4% አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: ይህም ምንም እንኳን ከፕራክቲከም በፊት መገናኘታቸውንና በት/ቤት ስለሚያከናውኗቸው ተግባራት መወሰናቸውን ቢያረጋግጡም፣ ስለመሠረታዊ የማስተማር ክህሎት መወያየታቸውን ግን እንደሚጠራጠሩ ያሳያል:: ይህም ከተማሪ አስተማሪዎቹ በኩል የተገኘውን መረጃ በተወሰነ ደረጃ የሚያጠናክር ይመስላል::

ተማሪ አስተማሪዎች ከፕራክቲከም በፊት ከመምህሮቻቸው ጋር ተገናኝተው መወያየታቸውን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ከመምህራኑ ጋር ሲስተያይ፣ አሉታዊነቱ ያመዝናል:: በት/ቤት ስለሚያከናውኗቸው ተግባራት መወሰናቸውን አስመልክቶ ከሰጡት ምላሽ 15% ብቻ አዎንታዊ ሲሆን፣ 25% በመጠኑ እስማማለሁ፣ 58% ደግሞ አሉታዊ ነው:: ይህም መምህራኑ ለቀረበላቸው ተመሳሳይ ጥያቄ ከሰጡት 72.7% አዎንታዊ ምላሽ ጋር በእጅጉ ይቃረናል:: በሌላ በኩል ደግሞ የማስተማር ክህሎትን በተመለከተ የሰጡት ምላሽ ከመምህራኑ ጋር የሚደጋገፍ ነው (ሆኖ ተገኝቷል):: መምህራኑ 36.4% አዎንታዊ፣ 18.2% በመጠኑ እስማማለሁና 45.4% አሉታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ ተማሪዎቹም 16% አዎንታዊ፣ 19% በመጠኑ እስማማለሁና 62% አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: በዚህ ረገድ በሁለቱም በኩል ከተሰጡት ምላሾች አሉታዊው ያመዘነ ነው::

የኮሌጅ መምህራን ከፕራክቲከም በፊት ከተማሪዎቻቸው ጋር ተገናኝተው በት/ቤት ስለሚያከናውኗቸው ተግባር መወያየታቸውን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ መምህራኑ የሰጡት ምላሽ በጥቅሉ ሲታይ አዎንታዊነቱ ይጎላል:: ተማሪ አስተማሪዎቹ የሰጡት ምላሽ

ደግሞ አሉታዊነቱ ያመዘነ ነው። ይሁንና ግን ስለመሠረታዊ የማስተማር ልምምድ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሁለቱም የሰጡት ምላሽ የሚደጋገፍና አሉታዊነቱ የሚጎላ ነው። ስለዚህ በሁለቱም በኩል የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው የኮሌጅ መምህራን ከፕራክቲከም በፊት ከተማሪዎች ጋር ተገናኝተው ስለመሠረታዊ የማስተማር ክህሎት ውይይት አያደርጉም ለማለት ይቻላል። በተባባሪ ት/ቤቶች ርዕሳነ መምህራን በኩል ያለው አመለካከትም፣ ተማሪ አስተማሪዎቹ ወደ ት/ቤት ሲመጡ ምን ማከናወን እንደለባቸው በቂ መመሪያ ይዘው እንደማይመጡ የሚያመለክት ነው። ለዚህም ማስረጃነት "ተማሪዎች ከኮሌጁ አስፈላጊውን መመሪያ እና ማሳሰቢያ ተቀብለው (ወደ ት/ቤት) የመጡ አይመስሉም። ተገቢው ትዕዛዝ ካላው (ከኮሌጁ) ቢሰጣቸው ኖሮ እዚህ ከኛ ጋር የሚያጨቃጭቃቸው ነገር አይኖርም" የሚለው የጋለማ ት/ቤት ርዕሰ መምህር አባባል በአብነት ሊወሰድ ይችላል። እንደ ርዕሰ መምህሩ አባባል ተማሪዎቹ ምን ለማከናወን ወደ ት/ቤት እንደመጡ በግልፅ አያውቁም፣ ከዚህም የተነሳ ጭቅጭቅ ውስጥ ይገባሉ። ስለዚህ ተማሪ አስተማሪዎቹ ስለመሰረታዊ የማስተማር ክህሎት ብቻ ሳይሆን፣ ት/ቤት ሄደው ስለሚያከናውኗቸው ተግባራትም ከመምህሮቻቸው ጋር ተገናኝተው መወያየታቸው ያጠራጥራል። ቀጥለን ደግሞ ከፕራክቲከም በኋላ ተገናኝተው መወያየታቸውን እንመልከት።

ሰንጠረዥ 3፡- **የኮሌጅ መምህራን ከፕራክቲከም በኋላ ከተማሪዎች ጋር ተገናኝተው መወያየታቸውን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ የመምህራኑና የተማሪዎቹ ምላሽ**

| | ዝርዝር መጠይቆች | በጣም እስማማለሁ (5) | እስማማለሁ (4) | ድምር | በመጠኑ እስማማለሁ (3) | አልስማማም (2) | በጭራሽ አልስማማም (1) | ድምር | ያልተመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| በኮሌጅ መምህራን የተሞላ | ከፕራክቲከም በኋላ ተገናኝተን በት/ቤት ስላከናወኗቸው ተግባራት ተወያይተናል | 5 | 5 | 10 (90.9%) | 1 (9.1%) | - | - | - | - |
| በተማሪ አስተማሪዎች የተሞላ | ከፕራክቲከም በኋላ ተገናኝተን በት/ቤት ስላከናወንናቸው ተግባራት ተወያይተናል | 10 | 16 | 26 (26%) | 22 (22%) | 20 | 22 | 42 (42%) | 10 (10%) |

ከላይ ከተመለከተው የኮሌጅ መምህራን ምላሽ ማየት እንደሚቻለው፣ መምህራኑ ከፕራክቲከም በኋላ ከተማሪዎች ጋር ተገናኝተው በት/ቤት ስላከናወኗቸው ተግባራት ውይይት አድርገዋል ለማለት ይቻላል። ከሰጧቸው ምላሽ ውስጥ 90.9% የሚሆነው የሚያሳየውም ይህንኑ ነው። ይህን ግን ተማሪ አስተማሪዎቹ ከሰጡት ምላሽ ጋር በጣም የተራራቀ ነው:: ተማሪዎቹ ለቀረበላቸው ተመሳሳይ ጥያቄ 26% ብቻ አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ፤ 22% በመጠኑ እስማማለሁና 42% አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፤ ከምላሾቹም መካከል አብላጫውን እጅ የሚይዘው አሉታዊው (42%) ነው። ስለዚህ የኮሌጅ መምህራን ከፕራክቲከም በኋላ ከተማሪዎች ጋር ተገናኝተው በት/ቤት ስላከናወኗቸው ተግባራት መወያየታቸውን በከፍተኛ ሁኔታ ሲገልፁ፤ ተማሪ አስተማሪዎች ግን ይህን አቋማቸውን ደግፈው አልተገኙም:: ስለሆነም ጉዳዩን በደንብ ለማጣራትና አቋም ለመያዝ ከቃለመጠይቅ የተገኘውን መረጃ መመርመር ያስፈልጋል::

የኮሌጅ መምህራን ከፕራክቲከም በፊትና በኋላ ለተማሪ አስተማሪዎች የሚያደርጉትን እገዛ በተመለከተ ከኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊ ጋርም ቃለመጠይቅ ተደርጓል:: በዚህም የተገኘው መረጃ ከፍ ሲል ከኮሌጅ መምህራን በፅሑፍ መጠይቅ ከተገኘው መረጃ ጋር ሲቃረን፣ ከተማሪ አስተማሪዎቹና ከት/ቤቶች ርዕሳነ መምህራን ጋር ግን የሚደጋገፍ ሆኖ ተገኝቷል:: በፕራክቲከም ሂደት (በፊትም ሆነ በኋላ) በመምህሮቹና በተማሪዎች መካከል ያለውን የቅርርብ ሁኔታ የፕራክቲከም ክፍል ኃላፊው እንደሚከተለው ይገልፃሉ::

> *የኛ (የኮሌጁ) መምህራን (ት/ቤት ሄደው) class ገብተው ገምግመው ከመውጣት ውጪ፤ እንደውም የኛን ተማሪዎች ይዘው መብትና ግዴታቸውን (በተመለከተ) አያናግሯቸውም (አያወያዩአቸውም):: ለሚገመግሙት ተማሪዎች እንኳን! class ገባ፣ ገመገመ፤ ተመልሶ ይወጣል:: እና የዚህ ዓይነቱ (ሁኔታ) አለ:: በርግጥ አስቸጋሪ ነገር ነው። እና ግንኙነታቸው እስከዚህም ነው ማለት ይቻላል::...*

ከፍሲል ከተመለከተው የኮሌጁ የፕራክቲከም ክፍል ኃላፊ ገለፃ መረዳት እንደሚቻለው፣ በኮሌጅ መምህራን እና በተማሪ አስተማሪዎቹ መካከል እምብዛም የጠበቀ ግንኙነት አይስተዋልም። ከዚህም የተነሳ የተማሪዎቹን መብትና ግዴታ በተመለከተ አብረው የሚያደርጉት ውይይት አይታይም። ይኸውም ተማሪዎቹ ወደ ት/ቤት ሄደው ስለሚከናወኑት ጉዳይ ስለማስተማር ከሀሉት በቂ ግንዛቤ የማግኘት መብት አላቸው፤ ያን የተገነዘቡትን ደግሞ ት/ቤት ሄደው ማከናወን (ማስተማር) ግዴታቸው ነው:: ነገር ግን መምህራኑ ተማሪዎቹ ወደ ት/ቤት ስለሚሄዱበት ጉዳይ (ከፕራክቲከም በፊት) በበቂ ሁኔታ አያወያዩዋቸውም፤ ት/ቤት ሄደው ከገመገሟቸውም በኋላ እንኳን (ስላከናወኑት ተግባራት) ቆም ብለው አያዋሯቸውም:: እንደ ኮሌጁ የፕራክቲከም ክፍል ኃላፊ አባባል፤ መምህሩ 'class ገባ፤ ገመገመ፤ ተመልሶ ይወጣል።'

በአጠቃላይ ትድመና ድህረ ፕራክቲከም የኮሌጅ መምህራን ከተማሪ አስተማሪዎች ጋር እየተገናኙ የመወያየታቸውን ጉዳይ በተመለከተ ከተለያየ አቅጣጫ የተጠናቀሩትን መረጃዎች

ተመልክተናል፡፡ የኮሌጁ መምህራን የሰጡት መረጃ (በፅሑፍ መጠይቅ) የሚያመለክተው እና ተማሪ አስተማሪዎች፣ የት/ቤቶች ርዕሳን መምህራንና የኮሌጁ የፕራክቲከም ክፍል ኃላፊ የሰጡት መረጃ እርስ በርሱ የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከኮሌጅ መምህራን የተገኘው ከፕራክቲከም በፊትና በኋላ ከተማሪዎች ጋር እየተገናኙ መወያየታቸውን ቢያመለክትም፤ የተማሪዎቹና የፕራክቲከም ኃላፊው፣ እንዲሁም የርዕሳን መምህራኑ ግን ተቃራኒውን ነው ያመለከተው፡፡ አጥኚው በቦታው በነበረበት ወቅት በተጨባጭ የተመለከተውም ከመምህራኑ ሃሳብ ጋር የሚጣጣም አልነበረም፡፡ (ወደፊት የምናያቸው የተማሪ አስተማሪዎችን የሥራ ድርሻና ኃላፊነት በተመለከተ የተጠናከሩት መረጃዎችም ይህንኑ እንደሚያጠናክሩ እንመለከታለን)፡፡ ስለዚህ ተማሪ አስተማሪዎቹ ከፕራክቲከም በፊትም ሆነ በኋላ ከመምህሮቻቸው ተገቢውን እገዛ ወይም ድጋፍ አግኝተዋል ለማለት ይቸግራል፡፡ የኮሌጅ መምህራን የሰጡት ምላሽ ግን ድጋፍ መስጠታቸውን ነው የሚያሳየው፡፡ ይህም ምናልባት፣ ካለባቸው ከፍተኛ የሥራ ውጥረት (ጫና) አንፃር ተመልክተው የሰጡት ምላሽ ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም በተጨባጭ የሚታየው እውነታ፣ መምህራኑ ድጋፍ መስጠት ይቅርና ከተማሪዎች ጋር በቅርበት መገናኘታቸውንም አያሳይም፡፡ ይህ ደግሞ በተለይ ተማሪ አስተማሪዎች ሙሉውን ጊዜያቸውን በማስተማር ተግባር ላይ በሚሰማሩበት ወቅት (በፕራክቲከም አራት ላይ) መሆኑ ጉዳዩን ይበልጥ አሳሳቢ ያደርገዋል፡፡ ተማሪ አስተማሪዎች ከማስተማር ልምምዱ ምን ያህል ክህሎትን ይቀስማሉ የሚለውንም ወሳኝ ጥያቄ ያስነሳል፡፡

እንደምሁራን እምነት (Walters 1960 Perrot 1982 Ellis 1986 Wallace 1991 ወዘተ.) የማስተማር ልምምድ የተማሪ አስተማሪዎች በንድፈሃሳብ ደረጃ የቀሰሙትን ዕውቀት በት/ቤት ተገኝተው በተግባር እየፈተሹ ማስተማርን የሚለማመዱበት ሂደት ነው፡፡ ለዚህ ሂደት መሳካት ደግሞ እነ Sirvastava and Bose (1978) Goldhammer et al (1980) እንደሚሉት ከመምህራቸው (ሱፐርቫይዘራቸው) ጋር ቅድመና ድህረ የማስተማር ልምምድ የሚያደረጉት ግንኙነት ወሳኝ ነው፡፡ ከፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ በፊት በሚያደርጉት ውይይት፣ መማሪያ ክፍል ገብተው የማስተማሩን ተግባር እንዴት በአግባቡ ማከናወን እንደሚችሉ መሠረታዊ ግንዛቤዎችን ይጨብጣሉ፤ ባጠቃላይ በት/ቤት ተገኝተው የሚያከናውኑትን ዝርዝር ጉዳዮች ተወያይተው ይወስናሉ፡፡ እንዲሁም ተማሪ አስተማሪዎቹ ክፍል ገብተው አስተምረው ከወጡ በኋላም ከመምህሮቻቸው ጋር መገናኘት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህም ስላከናወኑት የማስተማር ተግባራት ተገቢነት አስፈላጊውን ማረጋገጫ ከመምህራቸው በምጋቢ ምላሽ አማካይነት ያገኛሉ፤ ስህተት ግድፈታቸውንም ይመለከቱበታል፤ ጠንካራ ጎናቸውንም ለይተው ይበልጥ ይተጉበታል፡፡ በርቤ መምህራን ኮሌጅ መምህራን እና በተማሪ አስተማሪዎቹ መካከል ግን ይህ ሁኔታ አይስተዋልም፡፡ ተማሪ አስተማሪዎች ወደ ማስተማር ልምምዱ ከመግባታቸው በፊትም ሆነ በኋላ ከመምህሮቻቸው የሚያገኙት ሱፐርቫይዘራዊ ድጋፍና ክትትል በጣም አናሳ ነው፡፡ ስለዚህም የኮሌጅ መምህራን ቅድመና ድህረ ፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ከተማሪ

አስተማሪዎች ጋር እየተገናኙ ተገቢውን እገዛ ከመስጠት አንፃር፣ የሥራ ድርሻቸውን በአግባቡ ተወጥተዋል ለማለት የሚቻል አይሆንም። በአጠቃላይ የኮሌጅ መምህራንን ቅድመና ድህረ ፕራክቲከም የሥራ ድርሻ አስመልክቶ ይህን ካልን፣ በማስከተል ደግሞ በፕራክቲከም የማስተማር ልምምዱ ሂደት ማከናወን የሚጠበቅባቸውን ዋነኛ ተግባር (ምን ያህል እንዳከናወኑ) እንመለከት።

### 4.1.2 የኮሌጁ መምህራን የሥራ ድርሻ፣ በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት

የኮሌጁ መምህራን በዋናው የፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት በት/ቤት ተገኝተው ለተማሪ አስተማሪዎች ያደረጉት ስትርቫይዘራዊ ድጋፍ ምን ይመስላል? የሚለውን ለመመለስ የሚረዱ መረጃዎች በፅሑፍ መጠይቅና በቃለ መጠይቅ ተጠናቅረዋል። በፅሑፍ መጠይቅ የተጠናቀረው መረጃ ከኮሌጁ መምህራን፣ ከተማሪ አስተማሪዎች እና ከት/ቤት መምህራን ሲሆን፣ ቃለ መጠይቁ ደግሞ ከኮሌጁ የፕራክቲከም ክፍል ኃላፊ የተገኘ ነው። እነዚህንም ከዚህ በማስከተል ጎን ለጎን እያስተያየን እንመለከታለን።

ሰንጠረዥ 4፡ በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት የኮሌጁ መምህራን በት/ቤት ተገኝተው ምልከታና ግምገማ ማድረጋቸውን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ የኮሌጁ መምህራን፣ የተማሪ አስተማሪዎችና የት/ቤት መምህራን ምላሽ

| | ዝርዝር መጠይቆች | በጣም እስማማለሁ (5) | እስማማለሁ (4) | ድምር | በመጠኑ እስማማለሁ (3) | አልስማማም (2) | ጨርሶ አልስማማም (1) | ድምር | ያልተመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የኮሌጁ መምህራን ምላሽ | በትምህርቴ በመገኘት ተከታትያ ምልከታ (observation) አድርጊያለሁ | 1 | - | 1 (9.1%) | 10 (90.9%) | - | - | - | - |
| | ኮሌጁ ባስቀመጠው መስፈርት መሠረት የማስተማር ክንውናቸውን (performance) ገምግሚያለሁ | - | - | - | 11 (100%) | - | - | - | - |
| የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ | በትምህርቴ በመገኘት ተከታትያ ምልከታ (observation) አድርገውልኛል | 5 | 18 | 23 (23%) | 50 (50%) | 12 | 12 | 24 (24%) | 3 (3%) |
| | ኮሌጁ ባስቀመጠው መስፈርት መሠረት የማስተማር ክንውኔን (performance) ገምግመዋል | 22 | 8 | 30 (30%) | 62 (62%) | 3 | 3 | 6 (6%)? | 2 (2%) |
| የት/ቤት መምህራን ምላሽ | በትምህርት በመገኘት ተከታትያ ምልከታ (observa tion) አድርገዋል | 3 | 4 | 7 (41.2%) | 6 (35.3%) | 2 | 2 | 4 (23.5%) | - |
| | ኮሌጁ ባስቀመጠው መስፈርት መሠረት የማስተማር ክንውናቸውን (performanc) ገምግመዋል | - | 4 | 4 (23.5%) | 8 (47.1%) | 3 | 1 | 4 (23.5%) | 1 (5.9%) |

ከፍ ሲል የተመለከተው ምላሻቸው እንደሚያሳየው ከሆነ፣ የኮሌጅ መምህራን በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት በት/ቤት ተገኝተው ተከታታይ ምልከታና ግምገማ ስለማድረጋቸው እርግጠኝነት ይጎላቸዋል። የኮሌጅ መምህራኑ ተከታታይ ምልከታ ስለማድረጋቸው ለቀረበላቸው ጥያቄ 90.9%፣ የማስተማር ክንውናቸውን በኮሌጁ መስፈርት መሠረት ስለመገምገማቸው ደግሞ 100% በመጠኑ እስማማለሁ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። ይህም በዚህ ረገድ ማከናወን የሚጠበቅባቸውን ተግባር ሙሉ በሙሉ ተወጥተናል ብለው እንደሚያምኑ ያመለክታል። በተማሪ አስተማሪዎቹና በት/ቤት መምህራን በኩል ያለው ሃሳብም የመምህራኑን አቋም የሚጠናክር ይመስላል። ተማሪ አስተማሪዎቹ መምህራኑ ተከታታይ ምልከታ ስለማድረጋቸው ከሰጡት ምላሽ ውስጥ 23% አዎንታዊ፣ 50% በመጠኑ እስማማለሁና 24% አሉታዊ ምላሽ ነው። የት/ቤት መምህራን ደግሞ 41.2% አዎንታዊ፣ 35.3% በመጠኑ እስማማለሁ እና 23.5% አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። የኮሌጅ መምህራን በት/ቤት ተገኝተው ተከታታይ ምልከታ ስለማድረጋቸው ለቀረበላቸው ጥያቄም አብዛኞቹ ተማሪ አስተማሪዎች በመጠኑ እስማማለሁ (50%) የሚል ምላሽ ሲሰጡ፣ የአብዛኞቹ የት/ቤት መምህራን ምላሽ ግን አዎንታዊ (41.2%) ሆኖ ተገኝቷል። ይህ የት/ቤት የመምህራን ምላሽ ከተማሪ አስተማሪዎቹ ብዙ ሳይርቅ ራሳቸው የኮሌጅ መምህራን ስለራሳቸው ከሰጡት (90.9% በመጠኑ እስማማለሁ) ምላሽ ጋርም ይጋጫል (ይቃረናል)። በሌላ በኩል የኮሌጁ መምህራን ተማሪ አስተማሪዎችን ኮሌጁ ባስቀመጠው መስፈርት መሠረት የማስተማር ክንውናቸውን መገምገማቸውን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ ተማሪዎቹም ሆኑ የት/ቤት መምህራን የሰጡት ምላሽ ተቀራራቢ ነው። ተማሪ አስተማሪዎቹ ከሰጧቸው ምላሾች ውስጥ 62%፣ የት/ቤት መምህራን ከሰጧቸው ውስጥ ደግሞ 47.1% የሚሆነው በመጠኑ መስማማታቸውን ያመለክታል። ይህም የኮሌጅ መምህራን ስለራሳቸው የሰጡትን (100% በመጠኑ እስማማለሁ) ምላሽ የሚያጠናክር ነው።

የኮሌጁ መምህራን በዋናው የፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት በት/ቤት ተገኝተው ተከታታይ ምልከታ ማድረጋቸውን፣ ኮሌጁ ባስቀመጠው መስፈርት መሠረት የማስተማር ክንውናቸውን መገምገማቸውን በተመለከተ መምህራኑም ሆኑ ተማሪዎቹ የሰጡት ምላሽ እርግጠኝነት አይንፀባረቅበትም። በሦስቱም በኩል የተሰጡት ምላሾች በመጠኑ መስማማታቸውን የሚያመለክቱ ናቸው። (ሦስቱም) የኮሌጁ መምህራን በዚህ ረገድ የሚጠበቅባቸውን አከናውነዋል ወይም አላከናወኑም ለማለት ማመንታት ይታይባቸዋል። ስለሆነም በልሑፍ መጠይቅ አማካይነት ከኮሌጅ መምህራን፣ ከተማሪ አስተማሪዎችና ከት/ቤት መምህራን የተገኘው መረጃ መምህራኑ በት/ቤት ተገኝተው ተከታታይ ምልከታ ማድረጋቸውንና በኮሌጁ መስፈርት መሠረት መገምገማቸውን ወይም አለመገምገማቸውን በእርግጠኝነት አያመለክትም። በዚህ ረገድ የተሟላ መረጃ በመስጠት ጥርጣሬያችንን ሊያስወግድልን

(እርግጠኝነታችንን ሊያጠናክርልን) የሚችለው በቃለ መጠይቅ አማካይነት ከኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊ የተገኘው መረጃ ነው። የፕራክቲከም ኃላፊው የኮሌጁ መምህራን በት/ቤት ተገኝተው ተከታታይ ምልከታና ግምገማ ያደርጋሉ ወይ? ለሚለው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ የሚከተለው ነው።

> *(በግምገማ በኩልም ከአንድ ጊዜ በላይ አይገመግሙም) ... ከአንድ ጊዜ በላይ እንዳይገመገሙ ያደረጋቸው... እዚህ ካላቸው የክፍለጊዜ ጫና ባሻገር፣ (ወደት/ቤት) ይዘው የሚሄዱት የተማሪ ብዛት ነው። ለምሳሌ ወደ አንድ...30 ተማሪ ይዞ ይሄድና... አንድን ተማሪ ሦስት ጊዜ የሚገመግም ከሆነ 90 ክፍለጊዜ ያስፈልገዋል ማለት ነው። ለአንድ አስተማሪ። ያንን ደግሞ ሊያገኝ አይችልም (ከት/ቤት)።...ስለዚህ ያው... ሁሌም ተስማምተን አንዳንድ ጊዜ ብቻ ነው የሚገመግሙት።...*

ይህ ከፍ ሲል የቀረበው የኮሌጁ የፕራክቲከም ክፍል ኃላፊ ንግግር፣ ቀደም ሲል በፅሑፍ መጠይቅ የተገኘውን መረጃ ይበልጥ ግልፅ አድርጎ ያስቀምጠዋል። የኮሌጁ መምህራን፣ የት/ቤት መምህራን እና የተማሪ አስተማሪዎች በእርግጠኝነት ለመወሰን ያመነቱበትን ጉዳይ በማያሻማ መልኩ ማስረጃ አበጅቶለታል። ከዚህም በመነሳት የኮሌጁ መምህራን በፕራክቲከም የማስተማር ልምምዱ ሂደት፣ ለተማሪ አስተማሪዎች ያደረጉት (ስትርቫይዘራዊ) እገዛ በቂ አልነበረም ብሎ ማስረገጥ ይቻላል። የኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊ እንዳስቀመጡት እና አጥኚውም በቦታው ተገኝቶ እንደተመለከተው፣ የኮሌጁ መምህራን ከአንድ ጊዜ በላይ ተማሪዎችን አይገመግሙም። የሚጠበቅባቸውም ይኸው ብቻ ነው። አንድ ጊዜ ብቻ መገምገማቸው ሳያንስ እሱንም በተገቢው መንገድ ሲያከናውኑ አይታዩም። አጥኚው ለመታዘብ እንደቻለው፣ (ሁሉም መምህራን ለማለት ይቻላል) አንዳንዶቹ ተማሪው ክፍል ገብቶ ማስተማር ከጀመረ በኋላ ዘግይተው ይመጣሉ፤ አሊያም አብረው ገብተው አፍታም ሳይቆዩ ተመልሰው ይወጣሉ። በዚህ አኳኋን እነሱ ወደ ት/ቤቱ በመጡበት ሰዓት ላይ እክፍል ገብተው ያገኟቸውን ተማሪዎች ሁሉ እንዲሁ ለክፍ ለክፍ እያደረጉ «ገምግመው» ይመለሳሉ። ስለዚህ የኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊ በግልፅ እንዳስቀመጠው «ገመገሙ ይወጣሉ ... ገመገሙ ይወጣሉ።» ነው። ስለዚህ በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት የኮሌጅ መምህራን ለተማሪ አስተማሪዎች ተከታታይ ምልከታና ግምገማ በማድረግ በኩል ተገቢውን ስትርቫይዘራዊ እገዛ አድርገዋል ሊባል አይችልም።

የኮሌጁ መምህራን በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት በት/ቤት ተገኝተው ምልከታና ግምገማ ማድረጋቸውን አስመልክቶ በፅሑፍ መጠይቅና በቃለ መጠይቅ የተጠናቀሩት መረጃዎች መምህራኑ የሚጠበቅባቸውን የሥራ ድርሻ እንዳልተወጡ አመልክተዋል። በማስከተል ደግሞ ከዚሁ የፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት ጋር ተያያዥ የሆነውን የምጋቢ ምላሽ አሰጣጥ በተመለከተ የኮሌጅ መምህራን ያከናወኑትን ተግባር እንመለከታለን። በቅድሚያም በፅሑፍ መጠይቅ አማካይነት ከኮሌጁ መምህራን፣ ከተማሪ አስተማሪዎችና ከት/ቤት መምህራን የተጠናቀረውን መረጃ እንይ።

ሰንጠረዥ 5፡- በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት የኮሌጅ መምህራን በት/ቤት ተገኝተው ተገቢውን ምጋቢ ምላሽ መስጠታቸውን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ የኮሌጅ መምህራን፣ የተማሪ አስተማሪዎችና የት/ቤት መምህራን ምላሽ

| | ዝርዝር መጠይቆች | በጣም እስማማለሁ (5) | እስማማለሁ (4) | ድምር | በመጠኑ እስማማለሁ (3) | አልስማማም (2) | በፍጹም አልስማማም (1) | ድምር | ያልተመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የኮሌጅ መምህራን ምላሽ | ከምልከታ/ግምገማ በኋላ ገንቢ የሆነ አስተያየትና ምጋቢ ምላሽ (feedback) ሰጥቻለሁ | 2 | - | 2 (18.2%) | 8 (72.7%) | 1 | - | 1 (9.1%) | - |
| | ከምልከታ/ግምገማ በኋላ በዛው ቀን ገንቢ የሆነ አስተያየትና ምጋቢ ምላሽ ሰጥቻለሁ | 2 | 3 | 5 (45.4%) | 4 (36.4%) | 1 | 1 | 2 (18.2%) | - |
| | ከምልከታ/ግምገማ በኋላ የቃልና የፅሁፍ ምጋቢ ምላሽ ሰጥቻለሁ | - | - | - | 7 (63.6%) | 3 | - | 3 (27.3%) | 1 (9.1 %) |
| የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ | ከምልከታ/ግምገማ በኋላ ገንቢ የሆነ አስተያየትና ምጋቢ ምላሽ (feedback) ሰጥተውኛል | 17 | 9 | 26 (26%) | 66 (66%) | 4 | 2 | 6 (6%) | 2 (2%) |
| | ከምልከታ/ግምገማ በኋላ በዛው ቀን ገንቢ የሆነ አስተያየትና ምጋቢ ምላሽ ሰጥተውኛል | 9 | 16 | 25 (25%) | 61 (61%) | 9 | 5 | 14 (14%) | - |
| | ከምልከታ/ግምገማ በኋላ የቃልና የፅሁፍ ምጋቢ ምላሽ ሰጥተውኛል | 10 | 23 | 33 (33%) | 52 (52%) | 11 | 4 | 15 (15%) | - |
| የት/ቤት መምህራን ምላሽ | ከምልከታ/ግምገማ በኋላ ገንቢ የሆነ አስተያየትና ምጋቢ ምላሽ (feedback) ሰጥተዋል | 6 | - | 6 (35.3%) | 9 (52.9%) | 1 | 1 | 2 (11.8%) | - |
| | ከምልከታ/ግምገማ በኋላ በዛው ቀን ገንቢ የሆነ አስተያየትና ምጋቢ ምላሽ ሰጥተዋል | 3 | 4 | 7 (41.2%) | 7 (41.2%) | - | 1 | 1 (5.8%) | 2 (11.8 %) |
| | ከምልከታ/ግምገማ በኋላ የቃልና የፅሁፍ ምጋቢ ምላሽ ሰጥተዋል | 3 | 4 | 7 (41.2%) | 6 (35.3%) | - | 4 | 4 (23.5%) | - |

ከፍ ሲል የተመለከተው የኮሌጁ መምህራን፣ የተማሪ አስተማሪዎችና የት/ቤት መምህራን ምላሽ እንደሚያመለክተው፣ በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት የኮሌጅ መምህራን ተገቢውን ምጋቢ ምላሽ ሰጥተዋል ለማለት አይቻልም፡፡ የኮሌጁ መምህራን ከምልከታ/ ግምገማ

በኋላ በዛው ቀን ገንቢ የሆነ አስተያየትና ምጋቤ ምላሽ በቃልና በፅሑፍ ለተማሪ አስተማሪዎች መስጠታቸውን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ የኮሌጁ መምህራን፣ የተማሪ አስተማሪዎችና የት/ቤት መምህራን በአንድነት የሰጡት ምላሽም ይህንኑ ያሳያል:: በሦስቱም በኩል ከተሰጡት ምላሾች መካከል አብላጫውን እጅ የሚይዙት በመጠኑ መስማማታቸውን ነው የሚያመለክቱት:: ስለዚህ ራሳቸው የኮሌጅ መምህራንም ሆኑ ተማሪዎቹና የት/ቤት መምህራኑ ገንቢ የሆነ ምጋቤ ምላሽ በዛው ቀን በቃልና በፅሑፍ መስጠታቸውን በእርግጠኝነት ማመልከት አልቻሉም:: ይህ በሦስቱም በኩል የተሰጠው እርግጠኝነት የጎደለው (በመጠኑ መስማማታቸውን ብቻ የሚገልፅ) ምላሽ በርግጥም የኮሌጅ መምህራን በዚህ ረገድ ተገቢውን ሥራ ማከናወናቸውን አጠያያቂ ያደርገዋል:: ጉዳዩን ይበልጥ ለማጥራትና ቁርጥ ያለ አቋም ለመያዝ ያስችለን ዘንድ የኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊ የሰጡትን ምላሽ መመልከት አስፈላጊ ነው:: የፕራክቲከም ኃላፊው የኮሌጁ መምህራን በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት በት/ቤት ተገኝተው ተገቢውን ምጋቤ ምላሽ ለተማሪዎች መስጠታቸውን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሚከተለውን ምላሽ ነው የሰጡት::

> ... lesson plan አዘገጃጀት ላይ አንድ አስተማሪ feed back ሊሰጥ ይችላል (በዛው በወረቀቱ ላይ በመፃፍ):: ይኼ ችግር የለም:: እንደአንድ ችግር ልጠቅስልህ የምፈልገው ነገር ምንድነው?... አብዛኞቹ አስተማሪዎቻችን (ለተማሪዎች) እንደውም feed back አይሰጡም:: (ይህም የሆነበት ምክንያት) አንድ ለፕራክቲከሙ ራሱ ያላቸው አመለካከት... ሁለተኛ ደግሞ ከተማሪ ብዛት የተነሳ... ለእያንዳንዱ ተማሪ ምጋቤ ምላሽ አይሰጡም:: ገመገሙ ይወጣሉ... ገመገሙ ይወጣሉ:: መጨረሻ ብቻ ውጤቱን ብቻ ለፕራክቲከም ክፍል ያስገባሉ:: እንጂ (ተማሪዎችን) ተከታትለው እዚህ ጋ ችግር አለብህ የሚል feed back መስጠት... የተለመደ አይደለም::...

ቀደም ሲል ከፅሑፍ መጠይቅ ያጠናቀርነው መረጃ የኮሌጁ መምህራን በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት ለተማሪ አስተማሪዎች ገንቢ[1] ወቅቱን የጠበቀና በቃልና በፅሑፍ የተደገፈ አስተያየትና ምጋቤ ምላሽ ስለመስጠታቸው ቁርጥ ያለ ምላሽ መስጠት እንዳልቻለ አይተናል:: ይህ ከኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊ የተገኘው መረጃ ግን መምህራኑ ተገቢውን ምጋቤ ምላሽ በሚፈለገው ጊዜና ሁኔታ አለመስጠታቸውን ከነምክንያቱ ያስቀምጣል:: በኮሌጁ መምህራን፣ በተማሪ አስተማሪዎቹና በት/ቤት መምህራን በኩል የነበረውን (የታየውን) ማመንታትና መዋለልም (መጠነኛ ስምምነትም) ወደ አንድ አቅጣጫ ይመልሰዋል:: እንደፕራክቲከም ኃላፊው ገለፃ አብዛኞቹ የኮሌጁ መምህራን "እንደውም ምጋቤ ምላሽ አይሰጡም":: ምጋቤ ምላሽ ተሰጠ ከተባለም በትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት ላይ ነው:: (ይህም ቢሆን መስተጋብራዊ (interactive) በሆነ መንገድ የሚካሄድ አይደለም::) ከዚህ በተረፈ ተማሪዎቹ በማስተማር ልምምዱ ሂደት ያሳዩትን ጠንካራና ደካማ እንቅስቃሴ የሚመለከቱበት ገንቢ አስተያየትና ምጋቤ ምላሽ መስጠት የተለመደ አይደለም:: ለዚህም ምክንያት ከሆኑት አንዱ የኮሌጁ መምህራን ለፕራክቲከሙ (የሱፐርቪዥን ሂደቱ) ያላቸው አዎንታዊ ያልሆነ

(1978) እንደሚያስገነዝቡትም፣ የምጋቤ ምላሹ ገንቢ መሆን በራሱ አስተማማኝ ሆኖ ሊወሰድ አይችልም። በዛው ቀን (በፍጥነት) ለተማሪዎቹ መድረስ መቻሉ፣ በቃልና በፅሑፍም የተደገፈ መሆኑ ነው የበለጠ ውጤታማ የሚያሰኘው። ከፍ ሲል በዝርዝር የቀረቡት መረጃዎች እንደሚያሳዩትም በርቢ መምህራን ኮሌጅ አስተማሪዎች ዘንድ እነዚህ መሠረታዊ የሱፐርቪዥን ፍሬ ነገሮች ተግባራዊ ሆነው አልተገኙም። በተለይ ደግሞ ተማሪ አስተማሪዎቹ ይህን የማስተማር ልምምድ ከጨረሱ በኋላ «መምህር» ተብለው ሲመረቁ የታጩ መሆናቸው፣ ጉዳዩን አሳሳቢ ያደርገዋል። ምክንያቱም ያለ መምህሮቻቸው የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ት/ቤት ውስለው መመለሳቸው፣ ማስተማርን ተለማመዱ የሚያሰኝ አይሆንም። Sirvastava and Bose (1978) እንደሚሉትም፣ «ሱፐርቪዥኑ የፈለገውን ያህል በጠንካራ መሠረት ላይ የተደራጀ ቢሆንም፣ ኃላፊነታቸውን በብቃት በሚወጡ ሱፐርቫይዘሮች የቅርብ እገዛ ሥር ሆኖ እስካልተከናወነ ድረስ ትክክለኞቹን መምህራን ያፈራል ማለቱ ዘበት ነው»። ስለዚህ የኮሌጅ መምህራኑ (የሮቢ) በዚህ ወሳኝ ሂደት ማከናወን የሚጠበቅባቸውን የሥራ ድርሻ በብቃት አልተወጡም፣ ስለሆነም ኮሌጁ ትክክለኛውን ሙያዊ ብቃት የተጎናፀፉ መምህራንን ማፍራት መቻሉ አጠያያቂ ይሆናል ማለት ነው።

## 4.2 የተባባሪ ት/ቤት መምህራን የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

የት/ቤት መምህራን በፕራክቲከም ትግበራው ሂደት ለተማሪ አስተማሪዎች ምን እገዛ አድርገዋል የሚለውን ከመመልከታችን አስቀድሞ፣ የመምህራኑን አጠቃላይ ዳራዊ ሁኔታ እንመልከት።

ሰንጠረዥ 6፡- ከሮቢ መምህራን ኮሌጅ ጋር ፕራክቲከምን በጋራ በሚያከናወኑ ተባባሪ ት/ቤቶች የሚገኙ የቋንቋ መምህራን አጠቃላይ ዳራዊ መግለጫ

| የሚያስተምሩበት ት/ቤት | | | | የትምህርት ደረጃ | | በማስተማር ላይ የቆዩበት ዓመት | | የሚያስተምሩት ቋንቋ | | | በሳምንት ያላቸው የክ/ጊዜ መጠን | | | | ለፕራክቲከም የተመደቡላቸው ተማሪዎች ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| [illegible] | [illegible] | [illegible] | [illegible] | ሰርተፊኬት | ዲፕሎማ | 1-5 | 15 በላይ | አፋን ኦሮሞ | አማርኛ | እንግሊዝኛ | 10-15 | 16-20 | 21-25 | ከ25 በላይ | 11-20 | 15-25 | ከ25 በላይ |
| 3 | 4 | 4 | 5 | 6 | 11 | 4 | 13 | 7 | 5 | 5 | 4 | 4 | 6 | 3 | 11 | 3 | 3 |
| 17 | | | | 17 | | 17 | | 17 | | | 17 | | | | 17 | | |

በሰንጠረዥ 6 እንደተመለከተው፣ ከ17ቱ የት/ቤት መምህራን 11 ዲፕሎማ ሲኖራቸው የተቀሩት ደግሞ ሰርተፊኬት ያላቸው ናቸው። ከነዚህም አብዛኞቹ (13) ከ15 ዓመት በላይ

ያስተምሩ ናቸው። በሳምንት ያላቸው የክፍለጊዜ መጠንም ከ15 - 25 መካከል የሚገኝ ሲሆን፤ ለፕራክቲከም የሚመደቡላቸው ተማሪዎችም በአማካይ ከ20 በታች ናቸው። በሌላም በኩል ከፕራክቲከም ጋር በተያያዘ በርቢ መምህራን ኮሌጅ በኩል በዓመት ሁለት ጊዜ ወይም አንድ ጊዜ ስልጠና (workshop) እንደሚሰጣቸው በቃለ መጠይቅ ከተገኘው መረጃ ለመገንዘብ ተችሏል። አጥኚው መረጃ ለመሰብሰብ በኮሌጁ በተገኘበት ወቅትም ይህን ለማረጋገጥ ችሏል። ስለዚህ የት/ቤት (የቋንቋ) መምህራን ካላቸው የረጅም ጊዜ ልምድ፤ በኮሌጁ ከሚሰጣቸው ስልጠና እና፤ በፕራክቲከሙ ሂደት ከማስተማሩ ሥራ ነፃ ከመሆናቸው አንፃር ተማሪ አስተማሪዎችን በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ለመርዳት በሚያስችል ሁኔታ ውስጥ ናቸው ለማለት ይቻላል። ከዚህ አኳያም (በፕራክቲከም ሂደት) ለተማሪ አስተማሪዎች ያደረጉት እገዛ ወይም ድጋፍ ምን እንደሚመስል ቀጥለን እናያለን።

የተባበሩ ት/ቤት መምህራን በፕራክቲከም ሂደት ለተማሪ አስተማሪዎች ያደረጉትን ስትራቴጂያዊ እገዛ በተመለከተ ከፅሑፍ መጠይቅ እና ከቃለ መጠይቅ መረጃዎች ተጠናቅረዋል። የፅሑፍ መጠይቁ ለራሳቸው ለት/ቤት መምህራን፣ ለኮሌጅ አቻዎቻቸው እና ለተማሪ አስተማሪዎቹ ተሰጥቷል። ሦስቱም በፅሑፍ መጠይቃቸው ላይ በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት የት/ቤት መምህራን ለተማሪ አስተማሪዎች ያደረጉትን ስትራቴጂያዊ ድጋፍ በተመለከተ ለቀረበላቸው ዝርዝር መጠይቅ የሰጡትን ምላሽም ቀጥለን ተራ በተራ እንመለከታለን።

ሰንጠረዥ 7፦ የት/ቤት መምህራን በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት ለተማሪ አስተማሪዎች ያደረጉትን ሱፐርቫይዘራዊ ድጋፍ በተመለከተ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የት/ቤት መምህራን፣ የተማሪ አስተማሪዎችና የኮሌጅ መምህራን ምላሽ

| | ዝርዝር መጠይቆች | በጣም እስማማለሁ (5) | እስማማለሁ (4) | ድምር | በመጠኑ እስማማለሁ (3) | አልስማማም (2) | ጨርሶ አልስማማም (1) | ድምር | ያልተመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የት/ቤት መምህራን ምላሽ | ለማስተማር ተግባራት ተገቢ የሆነ መመሪያና መግለጫ ሰጥቻለሁ | 7 | 4 | 11 (64.7%) | 4 (23.5%) | - | - | - | 2 (11.8%) |
| | ተከታታይ ምልከታ አድርጌያለሁ | 2 | 6 | 8 (47%) | 7 (41.2%) | 1 | - | 1 (5.9%) | 1 (5.9%) |
| | በሂደቱ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት የማስተማር ክንውናቸውን ገምግሜያለሁ | 5 | 7 | 12 (70.6%) | 4 (23.5%) | 1 | - | 1 (5.9%) | - |
| የኮሌጅ መምህራን ምላሽ | ለማስተማር ተግባራት ተገቢ የሆነ መመሪያና መግለጫ ሰጥተዋል | 1 | 6 | 7 (63.6%) | 2 (18.2%) | 1 | - | 1 (9.1%) | 1 (9.1%) |
| | ተከታታይ ምልከታ አድርገዋል | 1 | 5 | 6 (54.5%) | 2 (18.2%) | 3 | - | 3 (27.3%) | - |
| | በተቀመጠው መስፈርት መሠረት የማስተማር ክንውናቸውን ገምግመዋል | 5 | 2 | 7 (63.6%) | 4 (36.4%) | - | - | - | - |
| የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ | ለማስተማር ተግባራት ተገቢ የሆነ መመሪያና መግለጫ ሰጥተውናል | 13 | 17 | 30 (30%) | 34 (34%) | 16 | 19 | 35 (35%) | 1 (1%) |
| | ተከታታይ ምልከታ አድርገውልናል | 17 | 17 | 34 (34%) | 31 (31%) | 24 | 6 | 30 (30%) | 5 (5%) |
| | በሂደቱ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት የማስተማር ክንውናችንን ገምግመዋል | 35 | 29 | 64 (64%) | 24 (24%) | 9 | 2 | 11 (11%) | 1 (1%) |

የት/ቤት መምህራን በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት ለተማሪ አስተማሪዎች ያደረጉትን እገዛ በተመለከተ ለቀረቡላቸው ዝርዝር ጥያቄዎች በመምህራኑም ሆነ በተማሪዎቹ በኩል የተሰጠው ምላሽ አዎንታዊ የሚባል ነው። የት/ቤት መምህራን ለተማሪ አስተማሪዎች ተገቢ የሆነ መመሪያና መግለጫ መስጠታቸውን፣ በማስተማር ልምምዱ ሂደት ተከታታይ

ምልከታ ማድረጋቸው፣ እና በተቀመጠው መስፈርት መሠረት የማስተማር ክንውናቸውን መገምገማቸውን በተመለከተ የት/ቤት መምህራኑና የኮሌጅ አቻዎቻቸው የሰጡት ምላሽ በአመዛኙ አዎንታዊ (ከ50% በላይ) ነው፡፡ በዚህ ረገድ ሁለቱም (የት/ቤትና የኮሌጅ መምህራን) ከሰጡት ምላሾች መካከል ዝቅተኛ ነው ተብሎ ሊጠቀስ የሚችለው የት/ቤት መምህራን ተከታታይ ምልከታ ማድረጋቸውን በተመለከተ የሰጡት 47.0% አዎንታዊ ምላሽ ነው፡፡ ይህም ቢሆን 41.2% በመጠኑ እስማማለሁ የሚል ምላሽ ስላለው አዎንታዊነቱ የጎላ ነው፡፡ ስለዚህ እንደ ት/ቤት መምህራንና የኮሌጅ አቻዎቻቸው እምነት የት/ቤት መምህራን በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት ተገቢውን ሱፐርቫይዘራዊ እገዛ ለተማሪ አስተማሪዎች አድርገዋል ለማለት ይቻላል፡፡

የት/ቤት መምህራን በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት ያደረጉላቸውን እገዛ በተመለከተ ተማሪ አስተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ደግሞ ከፍ ሲል መምህራኑ ከሰጡት ምላሽ ጋር ሲስተያይ ዝቅ ያለ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ከቀረቡላቸው ሦስት ጥያቄዎች መካከል ለሁለቱ የሰጡት ምላሽ መምህራኑ ከሰጡት አንፃር አነስተኛ ሲሆን፣ አንደኛው ግን ተመጣጣኝ ነው፡፡ ተገቢውን መመሪያ መስጠታቸውን በተመለከተ 30% አዎንታዊ፣ 34% በመጠኑ እስማማለሁና 35% አሉታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ ተከታታይ ምልከታ ማድረጋቸውን በተመለከተ ደግሞ 34% አዎንታዊ፣ 31% በመጠኑ እስማማለሁና 30% አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህን በተመለከተ ለቀረበላቸው ተመሳሳይ ጥያቄ የት/ቤት መምህራንና የኮሌጅ መምህራን የሰጡት ምላሽ ግን በከፍተኛ ሁኔታ አዎንታዊ ነው (ከ50% በላይ)፡፡ የት/ቤት መምህራን በተለይ ስለማስተማር ተግባራት ተገቢ የሆነ መመሪያና ገለፃ መስጠታቸውን አስመልክቶ በተማሪ አስተማሪዎቹ በኩል የተሰጠው ዝቅተኛ የሆነ አዎንታዊ ምላሽ፣ መምህራኑ ከሰጡት ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ ምላሽ ይበልጥ ተቀባይነት ያለው ይመስላል፡፡ ምክንያቱም የት/ቤት መምህራኑ ካላቸው የስልጠና ዳራ አንፃር ሲታይ ስለክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ተግባራት ተገቢ የሆነ ማብራሪያ ለተማሪዎቹ መስጠት ይችላሉ ለማለት ይቸግራልና፡፡

ከፍ ሲል በት/ቤት መምህራን፣ በኮሌጅ መምህራንና በተማሪ አስተማሪዎች በተሰጠው ምላሽ መካከል የተወሰነ ልዩነት ቢስተዋልም (በተለይ በተማሪዎቹ በኩል ዝቅ ያለ መሆኑ) እንደአጠቃላይ ሲታይ ግን አዎንታዊነቱ ያመዘነ ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ የት/ቤት መምህራን የሚጠበቅባቸውን የሥራ ድርሻ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ተወጥተዋል ለማለት ይቻላል፡፡ በማስከተልም ከማስተማር ልምምዱ ሂደት ጋር በተያየዘ የምጋቢ ምላሽ አሰጣጣቸውን ለመመልከት እንሞክራለን፡፡

ሰንጠረዥ 8፡- የት/ቤት መምህራን በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት ተገቢውን ምጋቤ ምላሽ ለተማሪ አስተማሪዎች መስጠታቸውን በተመለከተ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የት/ቤት መምህራን፣ የተማሪ አስተማሪዎችና የኮሌጅ መምህራን ምላሽ

| | ዝርዝር መጠይቆች | በጣም እስማማለሁ (5) | እስማማለሁ (4) | ድምር | በመጠኑ እስማማለሁ (3) | አልስማማም (2) | ጨርሶ አልስማማም (1) | ድምር | ያልተመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የት/ቤት መምህራን ምላሽ | ከምልከታ/ግምገማ በኋላ ተገቢ የሆነ አስተያየትና ምጋቤ ምላሽ ለተማሪው | 7 | 4 | 11 (64.7%) | 4 (23.5%) | 1 | - | 1 (5.9%) | 1 (5.9%) |
| | ከምልከታ/ግምገማ በኋላ በዛው ቀን ተገቢ የሆነ አስተያየትና ምጋቤ ምላሽ ለተማሪው | 8 | 4 | 12 (70.6%) | 3 (17.6%) | 2 | - | 2 (11.8%) | - |
| | ከምልከታ/ግምገማ በኋላ የቃልና የፅሁፍ ምጋቤ ምላሽ ለተማሪው | 3 | 5 | 8 (47.1%) | 6 (35.3%) | 2 | 1 | 3 (17.6%) | - |
| የኮሌጅ መምህራን ምላሽ | ከምልከታ/ግምገማ በኋላ ተገቢ የሆነ አስተያየትና ምጋቤ ምላሽ ይሰጣል | 3 | 2 | 5 (45.4%) | 3 (27.3%) | 3 | - | 3 (27.3%) | - |
| | ከምልከታ/ግምገማ በኋላ በዛው ቀን ተገቢ የሆነ አስተያየት ምጋቤ ምላሽ ይሰጣል | 3 | 1 | 4 (36.4%) | 4 (36.4%) | 2 | 1 | 3 (27.3%) | - |
| | ከምልከታ/ግምገማ በኋላ የቃልና የፅሁፍ ምጋቤ ምላሽ ይሰጣል | 1 | 3 | 4 (36.4%) | 2 (18.2%) | 2 | 2 | 4 (36.4%) | 1 (9%) |
| የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ | ከምልከታ/ግምገማ በኋላ ተገቢ የሆነ አስተያየትና ምጋቤ ምላሽ ይሰጡናል | 34 | 28 | 62 (62%) | 26 (26%) | 6 | 5 | 11 (11%) | 1 (1%) |
| | ከምልከታ/ግምገማ በኋላ በዛው ቀን ተገቢ የሆነ አስተያየትና ምጋቤ ምላሽ ይሰጡናል | 36 | 26 | 62 (62%) | 28 (28%) | 5 | 3 | 8 (8%) | 2 (2%) |
| | ከምልከታ/ግምገማ በኋላ የቃልና የፅሁፍ ምጋቤ ምላሽ ይሰጡናል | 12 | 35 | 47 (47%) | 28 (28%) | 16 | 9 | 25 (25%) | - |

የት/ቤት መምህራን በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት ተማሪ አስተማሪዎችን ከተመለከቱ/ ከገመገሙ በኋላ የሰጡት ምጋቤ ምላሽ ምን ይመስላል ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ በመምህራኑም ሆነ በተማሪዎቹ በኩል የተሰጠው ምላሽ አዎንታዊነቱ ያመዝናል ነው፡፡ በተለይም ተገቢ የሆነ አስተያየትና ምጋቤ ምላሽ መስጠታቸውንና የሰጡትም በዛው ቀን መሆኑን

በተመለከተ የት/ቤት መምህራንና ተማሪ አስተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ከ62% በላይ አዎንታዊ ነው፡፡ ይሁንና ግን በቃልና በፅሑፍ የተደገፈ ምጋቢ ምላሽ መስጠታቸውን በተመለከተ በት/ቤት መምህራንም ሆነ ተማሪ አስተማሪዎቹ የሰጡት ምላሽ 47% ብቻ አዎንታዊ ሆኗል፡፡ ይህም የምጋቢ ምላሽ አሰጣጣቸውን በተመለከተ ከተሰጡት ምላሾች መካከል ዝቅተኛው ነው፡፡ (ይህም ሆኖ አዎንታዊነቱ ያመዘነ ምላሽ ነው)፡፡ በተረፈ ግን እንደ ት/ቤት መምህራኑና ተማሪ አስተማሪዎቹ ሃሳብ ከሆነ፣ መምህራኑ በተለይ ተገቢ አስተያየትና ምጋቢ ምላሽ በዛው ቀን ከመስጠት አንፃር ሥራቸውን በወጉ ተወጥተዋል ለማለት የሚቻል ነው፡፡

ከላይ ከተመለከተው የት/ቤት መምህራንና የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ አንፃር ሲታይ፣ በኮሌጅ መምህራን በኩል የት/ቤት መምህራንን የምጋቢ ምላሽ አሰጣጥ በተመለከተ የተሰጠው ምላሽ አነስተኛ ነው፡፡ መምህራኑ ተገቢ የሆነ አስተያየትና ምጋቢ ምላሽ መስጠታቸውን በተመለከተ 45.4% አዎንታዊ፣ 27.3% በመጠኑ እስማማለሁና 27.3% አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ምጋቢ ምላሹንና አስተያየቱን በዛው ቀን መስጠታቸውን በተመለከተ ደግሞ 36.4% አዎንታዊ፣ 36.4% በመጠኑ እስማማለሁና 27.3% አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ እንዲሁም ምጋቢ ምላሹ በቃልና በፅሑፍ መደገፉን/ መታገዙን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ 36.4% አዎንታዊ፣ 18.2% በመጠኑ እስማማለሁና 36.4% አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ (በቃልና በፅሑፍ የተደገፈ ምጋቢ ምላሽ መስጠትን በተመለከተ ከፍ ሲል ያየነው የት/ቤት መምህራንና የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽም ዝቅተኛ መሆኑን ልብ ይሏል)፡፡ በመሆኑም ይህ የኮሌጅ መምህራን ምላሽ እንደ ት/ቤት መምህራኑና ተማሪ አስተማሪዎቹ ምላሽ የት/ቤት መምህራን ተገቢውን አስተያየትና ምጋቢ ምላሽ በዛው ቀን በቃልና በፅሑፍ አስደግፎ ከመስጠት አኳያ ሥራቸውን ማከናወናቸውን ያሳያል ለማለት አያስችልም፡፡

የት/ቤት መምህራን በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት ተገቢውን ምጋቢ ምላሽ ወዲያው በቃልና በፅሑፍ አስደግፈው መስጠታቸውን በተመለከተ የት/ቤት መምህራን፣ ተማሪ አስተማሪዎችና የኮሌጅ መምህራን የሰጡት ምላሽ በደምሳሳው ሲታይ አዎንታዊ ሊባል የሚችል ነው፡፡ በዚህ ረገድ በተለይ የት/ቤት መምህራንና ተማሪ አስተማሪዎቹ የሰጡት ምላሽ ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ አዎንታዊ ቢሆንም፣ የኮሌጅ መምህራን የሰጡት ግን ከዚህ ያነሰ ነው፡፡ የት/ቤት መምህራንና ተማሪ አስተማሪዎቹ ከሰጡት ምላሽ ውስጥ ዝቅተኛ የሚባለው አዎንታዊ ምላሽ 47% ሲሆን፣ አብዛኞቹ አዎንታዊ ምላሾች ግን ከ62% በላይ ናቸው፡፡ በኮሌጅ መምህራን በኩል ከተሰጡት ምላሾች ግን ከፍተኛ የሚባለው አዎንታዊ ምላሽ 45.4% ሲሆን፣ የተቀሩት (ሁለት አዎንታዊ ምላሾች) ደግሞ 36.4% ብቻ አዎንታዊ ናቸው፡፡ ይህም ሁኔታ የት/ቤት መምህራንና ተማሪ አስተማሪዎቹ በሰጡትና የኮሌጅ መምህራን በሰጡት ምላሽ መካከል ልዩነት እንዳለ ያመለክታል፡፡ ከተጨባጩ የት/ቤት መምህራን የትምህርት ዳራ (academic background) አንፃር ሲታይም የኮሌጅ መምህራን የሰጡት ምላሽ የበለጠ ተቀባይነት ያለው

ይመስላል። (እንዲሁም ቀደምሲል ስለማስተማሩ ተግባራት ተገቢ የሆነ መመሪያና መግለጫ መስጠታቸውን በተመለከተ ተማሪ አስተማሪዎቹ የሰጡትን ዝቅተኛ አዎንታዊ ምላሽ ልብ ይሏል።) ምክንያቱም ካሉት 17 የት/ቤት የቋንቋ መምህራን መካከል 11 ዲፕሎማ ያላቸው ሲሆኑ፤ የተቀሩት ደግሞ ሰርተፍኬት ያላቸው ናቸው። እናም ይህን የስልጠና ዳራ ይዘው በማስተማር ልምምዱ ሂደት ተገቢ የሆነ ሱፐርቫይዘራዊ ድጋፍ (በተለይም ስለማስተማር ተግባራትና ምጋቢ ምላሽ) ይሰጣሉ ብሎ መጠበቅ አስቸጋሪ ይሆናል። በተግባር ከሚታየው የት/ቤት መምህራኑ ሙያዊ ብቃት (professional competency) ጋርም የሚሄድ አይደለም። በደምሳሳው ግን በኮሌጅ መምህራን በኩል የተሰጠው ዝቅተኛ ምላሽ መሠረት ያለውና ተቀባይነት ያለው ቢሆንም፤ የተባባሪ ት/ቤት መምህራን ግን ማድረግ የሚችሉትን ከማድረግ ወደኋላ እንዳላሉ መመልከት ይቻላል።

በአጠቃላይ የት/ቤት መምህራን በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት ለተማሪ አስተማሪዎች ማድረግ ያለባቸውን ያህል አድርገዋል። ከኮሌጅ መምህራን አኳያም የሥራ ድርሻቸውን በወጉ ተወተዋል ለማለት ይቻላል። ለተማሪ አስተማሪዎችም በኮሌጅ መምህራን በኩል ያላገኙትን ድጋፍ፤ አንፃራዊ በሆነ መልኩ አካክሰውላቸዋል። ለዚህም የኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊ በት/ቤት መምህራንና በተማሪ አስተማሪዎቹ መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ሲገልፁም፤ "... *እንዲያውም በኛ ተማሪዎችና በት/ቤቱ መምህራን መካከል ነው፤ ጥሩ የሆነ ግንኙነት ያለው (ከኮሌጅ መምህራን ይልቅ)*" በማለት የጠቀሱት ነጥብ ጥሩ አስረጅ ይሆናል። ይህም በማስተማር ልምምዱ (በፕራክቲከም መርሃ ግብሩ) ትግበራ ሂደት የተባባሪ ት/ቤቶች መምህራን መሳተፋቸው ጠቃሚ መሆኑን የሚያመለክት ነው። እንዲሁም ዓለም (1989) ባደረገው ጥናት፤ የተባባሪ ት/ቤቶች መምህራን በሱፐርቪዥን ሂደት እንዲሳተፉ ቢደረግ ብሎ ያቀረበው የመፍትሄ ሃሳብም ተገቢነት ያለው መሆኑን ያረጋግጣል። በዚህ ላይ ለት/ቤት መምህራንም እንደኮሌጅ መምህራን ሁሉ የገንዘብ ማበረታቻ ቢደረግላቸው ኖሮ ከዚህ የበለጠ ውጤታማ ሥራ ሊሠሩ ይችላሉ (Kindalem 2005)። ከዚህ ባሻገር ግን መታየት ያለበት ተጨማሪ ነጥብም አለ። ይኸውም ሱፐርቪዥን ከፍ ያለ የማስተማር ዕውቀት፣ ክህሎትና ልምድ ባለው ባለሙያ (መምህር) የሚከናወን ተግባር እንደመሆኑ መጠን (Gebhard 1990 Fanselow 1990 Wallace 1991 Gowers 1995)፤ ለት/ቤት መምህራን ልዩ የሱፐርቪዥን ስልጠና ቢሰጣቸው ለተማሪ አስተማሪዎች ከዚህ የተሻለ እገዛ ሊያደርጉ ይችላሉ፤ ከኮሌጅ መምህራንም የሥራ ጫናን ይቀንሳሉ ብሎ አጥኚው ያምናል።

## 4.3 የተማሪ አስተማሪዎች የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት የኮሌጅና የት/ቤት መምህራን ከሚያደርጉላቸው እገዛ በተጓዳኝ ተማሪ አስተማሪዎቹም ማከናወን የሚገባቸው የሥራ ድርሻ

አላቸው። ተማሪ አስተማሪዎቹ ይህን የበኩላቸውን ድርሻ ምን ያህል ተወተዋል የሚለውን በተመለከተ በፅሑፍ መጠይቅ፣ በምልከታ፣ በመገምገሚያ ቅፅ እና በቃለ መጠይቅ መረጃዎች ተጠናቅረዋል። በፅሑፍ መጠይቅ የተጠናቀረው መረጃ ከራሳቸው ከተማሪዎቹ፣ ከኮሌጅና ከት/ቤት መምህራን የተገኘ ነው። በምልከታ የተጠናቀረው መረጃ ከኮሌጅ መምህራን የተገኘ ሲሆን፣ በመገምገሚያ ቅፅ የተጠናቀረው ደግሞ ከተማሪ አስተማሪዎቹ የተገኘ ነው:: እንዲሁም በቃለ መጠይቅ የተጠናቀረው መረጃ ከት/ቤት ርዕሳነ መምህራን የተገኘ ነው:: እነዚህን ከተለያየ አቅጣጫ ስለተማሪ አስተማሪዎች የሥራ ድርሻ የተጠናቀሩትን መረጃዎችም ከዚህ ቀጥለን እርስ በርስ እያገናዘብን እንመለከተለን። በቅድሚያም የክፍል ውስጥ የማስተማር ክንውን ሂደት መሠረት/ መነሻ የሆነውን የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀታቸውንእናያለን::

## 4.3.1 የተማሪ አስተማሪዎች የትምህርት ዕቅድ ዝግጅት

ሰንጠረዥ ፱. በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት የትምህርት ዕቅድ አዘጋጃጀታቸውን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ የተማሪ አስተማሪዎች፣ የት/ቤት መምህራንና የኮሌጅ መምህራን ምላሽ

| | ዝርዝር መጠይቆች | በጣም እስማማለሁ (5) | እስማማለሁ (4) | ድምር | በመጠኑ እስማማለሁ (3) | አልስማማም (2) | ጨርሶ አልስማማም (1) | ድምር | ያልተመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ | ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ አዘጋጅቻለሁ | 27 | 31 | 58 (58%) | 31 (31%) | 6 | 5 | 11 (11%) | - |
| የት/ቤት መምህራን ምላሽ | ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ አዘጋጅተዋል | 7 | 6 | 13 (76.5%) | 3 (17.6%) | - | - | - | 1 (5.9%) |
| የኮሌጅ መምህራን ምላሽ | ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ አዘጋጅተዋል | 3 | 4 | 7 (63.6%) | 2 (18.2%) | 1 | - | 1 (9.1%) | 1 (9.1%) |

በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት እክፍል ገብቶ ለማስተማር መሠረት የሆነውን የትምህርት ዕቅድ ዝግጅት በተመለከተ ተማሪ አስተማሪዎች ምን እንዳከናወኑ ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ በጥቅሉ ሲታይ አዎንታዊ ነው። ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀታቸውን በተመለከተም ተማሪ አስተማሪዎቹ 58%፣ የት/ቤት መምህራን 76.5%፣ የኮሌጅ ምህራን ደግሞ 63.6% አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ይህ በሦስቱም በኩል የቀረበው አዎንታዊነቱ የጎላ ምላሽ

እንደሚያመለክተውም ከሆነ፤ ተማሪ አስተማሪዎቹ በማስተማር ልምምዱ ሂደት ተገቢ የሆነ ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ አዘጋጅተዋል ማለት ነው። በማስከተል የምንመለከተው ከምልከታ የተገኘ መረጃም ይህንኑ የሚጠናከር ሆኖ ተገኝቷል።

ተማሪ አስተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ገብተው የሚያከናወኑት የማስተማር ክንውን ምን እንደሚመስል ይመለከቱ ዘንድ ለኮሌጅ መምህራን የምልከታ ቅፅ ተዘጋጅቷል። በተዘጋጀላቸው የምልከታ ቅፅ ላይ የተማሪ አስተማሪዎቹን የትምህርት ዕቅድ በተመለከተ ለቀረቡላቸው ዝርዝር ነጥቦች የሰጡት ምላሽም ከፍ ሲል በፅሑፍ መጠይቅ ከተገኘው መረጃ ጋር የሚደጋገፍ ነው። የዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ዝግጅታቸውን ብቃት (ዓላማና ይዘቱን) በተመለከተ የሰጡት የምልከታ ምላሽም የሚከተለው ነው።

ሰንጠረዥ 10፦ የተማሪ አስተማሪዎችን የትምህርት ዕቅድ ዝግጅት በተመለከተ በመከታተያ ቅፁ ላይ ለቀረቡት ዝርዝር ነጥቦች የኮሌጅ መምህራን ምላሽ

| የማስተማር ክንውኖች (activeties) | አዎ | አርግጠኛ አይደለሁም | አይ |
|---|---|---|---|
| 1. የትምህርቱ ዓላማ (objectives) | | | |
| 1.1 መርሃ ትምህርቱን መሠረት ያደረገ ነው | 14 (66.7%) | 4 (19%) | 3 (14.3%) |
| 1.2 ግልፅ ውስን (specific) ነው | 15 (71.4%) | 3 (14.3%) | 3 (14.3%) |
| 1.3 ሊለካ ሊመዘን ይችላል | 13 (61.9%) | 5 (213.8%) | 3 (14.3%) |
| 1.4 የሚደረስበት (attainable) ነው | 16 (76.2%) | 3 (14.3%) | 2 (9.5%) |
| 1.5 እውነኛ (realistic)ነው | 19 (90.6%) | 1 (4.7%) | 1 (4.7%) |
| 1.6 በጊዜ የተወሰነ ነው | 16 (76.2%) | 1 (4.7%) | 4 (19%) |
| **ድምር (መቶኛ)** | **93 (73.8%)** | **17 (13.5%)** | **16 (12.7%)** |
| 2. የትምህርት ይዘት (content) | | | |
| 2.1 ከተቀመጠው ዓላማ/ግብ ጋር የተያያዘ ነው | 15 (71.5%) | 4 (19%) | 2 (9.5%) |
| 2.2 ለመረዳት የማያስቸግር/የማይከብድ ነው | 18 (85.7%) | 1 (4.7%) | 2 (9.5%) |
| 2.3 ከግብ መድረሱ ሊለካ ሊመዘን ይችላል | 14 (66.7%) | 6 (28.6%) | 1 (4.7%) |
| 2.4 ለተማሪዎች ግልፅ (demonstrated) ነው | 11 (52.4%) | 9 (42.9%) | 1 (4.7%) |
| **ድምር (መቶኛ)** | **58 (69.05%)** | **20 (23.871%)** | **6 (7.14%)** |

ከፍ ሲል የተመለከተው የኮሌጁ መምህራን ምልከታ እንደሚያሳየው ከሆነ የተማሪ አስተማሪዎች የትምህርት ዕቅድ ዝግጅት ከፍተኛ የሆነ ብቃት አለው፡፡ የዕለታዊ የትምህርት ዕቅዳቸውን ግላጋ በተመለከተ ለቀረቡት ዝርዝር ነጥቦች መምህራኑ የሰጧቸው ምላሾች አዎንታዊ ናቸው፤ ሁላቸውም ምላሾች ከ61% በላይ ናቸው፡፡ የትምህርት ዕቅዳቸውን ይዘት አስመልክቶ ለቀረቡት ዝርዝር ነጥቦችም እንዲሁ ሙሉ በሙሉ አዎንታዊ የሆነ ምላሽ ሰጥተዋል ከእነዚህም መካከል ምናልባትም ዝቅተኛ ነው ተብሎ ሊጠቀስ የሚችለው፣ ይዘቱ ለተማሪዎች ግልፅ መሆኑን በተመለከተ የሰጡት 52.4% አዎንታዊ ምላሽ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ይዘትን በተመለከተ ለቀረቡት ዝርዝር ነጥቦች የሰጧቸው ምላሾች ከ66% በላይ አዎንታዊ ናቸው ስለዚህ ቀደም ሲል በፅሑፍ መጠይቅ በተገኘው መረጃ ላይ እንደተመለከተውና፤ በምልከታ አማካይነት ከኮሌጅ መምህራን በተገኘው መረጃም እንደተጠናከረው ከሆነ የተማሪ አስተማሪዎች የትምህርት ዕቅድ ዝግጅት ከፍተኛ የሆነ ብቃት ያለው ነው ማለት ይቻላል፡፡

በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት ተማሪ አስተማሪዎች የሚያዘጋጁት የትምህርት ዕቅድ ብቃት ምን ይመስል እንደነበር ለመፈተሽ የተጠናቀሩት የፅሑፍ መጠይቅና የምልከታ መረጃዎች እንደሚያሳዩቱ ከሆነ ተማሪዎቹ ተገቢውን ሥራ አከናውነዋል ማለት ይቻላል ይሁንና ግን እነዚህን ከላይ የተመለከቱትን መረጃዎች በሌላ መንገድ ከተገኙት መረጃዎች ጋር ስናነፃፅር የሚገኘው አጠቃላይ ምስል አዎንታዊነቱን አጠያያቂ ያደርጋል፡፡ ለዚህም የኮሌጅ መምህራን ራሳቸው በምልከታ ቅፁ ላይ በክፍት የአጠያየቅ መንገድ ለቀረበላቸው ጥያቄ ከሰጡት ምላሽ እና ተማሪ አስተማሪዎቹ በግምገማ ቅፃቸው ላይ ካሰፈሩት የግምገማ ማስታወሻቸው የተገኘው መረጃ በአስረጅነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡ በነዚህ መንገዶች የተጠናቀሩት መረጃዎች ቀደም ሲል በስፋት ስንመለከታቸው የነበሩት መረጃዎች ካሳዩት አዎንታዊ አንድምታ ጋር የሚደጋገፍ አልሆነም፡፡

የኮሌጁ መምህራን በተዘጋጀላቸው የምልከታ ቅፅ ላይ በክፍት የአጠያየቅ መንገድ "ከተመለከቱት የማስተማር ክንውን መሻሻል አለባቸው የሚሉትን ጉዳዮች ያስፍሩ፡፡" የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸዋል፡፡ ከተመለከቷቸው የማስተማር ክንውኖች ውስጥ ተማሪ አስተማሪዎቹ ሊያሻሽሏቸው ይገባል በማለት ካስቀመጧቸው ድክመቶች መካከልም በግንባር ቀደምትነት የተነሱት በትምህርቱ ዓላማ ላይ ያተኩሩ ናቸው፡፡ በዚህም "የትምህርቱን ዓላማ በአግባቡ አለመስፈር፣ አለመግለፅ" የተማሪ አስተማሪዎቹ መሠረታዊ ድክመት መሆኑን ደጋግመው አመልክተዋል፡፡ ይህ የኮሌጁ መምህራን አስተያየት ቀደም ሲል ራሳቸው በፅሑፍ መጠይቅና በምልከታ ቅፅ ላይ ከሰጡት ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ ምላሽ ጋር በእጅጉ የሚቃረን ነው፡፡ ከተማሪ አስተማሪዎቹ የራስ ግምገማ ማስታወሻ (self assessment diary) ላይ የተገኘው መረጃም ቢሆን ቀደም ሲል በፅሑፍ መጠይቅና በምልከታ ቅፅ (በውስን የአጠያየቅ መንገድ)

ከተጠናቀረው ጋር የሚቃረን ሆኖ ነው የተገኘው። ተማሪዎቹ በማስታወሻቸው ላይ ካሰፈሩት ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ውስጥም ቀጥለው ለናሙናነት የተመለከቱትን ዓይነት የትምህርት ዓላማዎች ሰፍረው ተገኝተዋል።

1. ተማሪዎች ምንባቡን በተራ ያነባሉ።
2. ተማሪዎች መልመጃዎችን ሰርተው ያሳያሉ።
3. ተማሪዎች በዕለቱ ትምህርት ላይ ይወያያሉ።
4. ተማሪዎች የመንስኤና የውጤትን ምንነት ይናገራሉ።
5. ተማሪዎች ንሥል ሚስጥራዊ እንስሳ የሚለውን ምንባብ ያነባሉ።
6. ተማሪዎች በባሌ ብሔራዊ ፓርክ የሚገኙትን የዱር አራዊቶችና አዕዋፋት ይለያሉ።
7. ተማሪዎች የሶማና የአንበሳን ምንባብ አንብበው የቋንቋ ክሂላቸውን ይለማመዳሉ።
8. ተማሪዎች በመልመጃ ለቀረቡ ጥያቄዎች በግልና በቡድን በመወያየት መልስ ይሰጣሉ።
9. ተማሪዎች ንሥል ሚስጥራዊ እንስሳ በሚለው ርዕስ ስር መልመጃ አንድና ሁለትን ይሠራሉ።

ከላይ ለአስረጂነት የቀረቡት ዓይነት "ዓላማዎች" በበርካቶቹ የተማሪ አስተማሪዎቹ የራስ መገምገሚያ ቅፅ ላይ ተስተውለዋል። ከዚህም በመነሳት ተማሪ አስተማሪዎቹ የቋንቋ ትምህርት ዓላማ በተግባር ምን መምሰል እንዳለበት ያውቃሉ ወይ? ተብሎ ቢጠየቅ አዎንታዊ ምላሽ ማግኘት ይከብዳል። ቀደም ሲል ከፅሑፍ መጠይቅና ከምልከታ ቅፅ (በውስን አጠያየቅ) የተገኘው መረጃ ተአማኒነትም አጠያያቂ ያደርገዋል። ምክንያቱም በተጨባጭ ተማሪ አስተማሪዎቹ ካላቸው ብቃት ጋር ይጣረሳልና። ስለዚህ ቀደም ሲል የተጠናቀሩት መረጃዎች እንዳመለከቱት፣ የተማሪ አስተማሪዎቹ የትምህርት ዕቅድ ዝግጅት ከፍተኛ ብቃት ያለው ነው ብሎ ለመደምደም ያስቸግራል።

በአጠቃላይ ለክፍል ውስጥ የማስተማር መማር ክንውን ሂደት ስኬት መሠረት የሆነውን የትምህርት ዕቅድ ዝግጅትን በተመለከተ ተማሪ አስተማሪዎች ምን እንዳከናወኑ የሚያመለክቱ የተለያዩ መረጃዎችን በስፋት አይተናል። በፅሑፍ መጠይቅ (ከተማሪ አስተማሪዎቹ፣ ከት/ቤት መምህራን፣ ከኮሌጁ መምህራን) እና በውስን የአጠያየቅ ስልት በምልከታ ቅፅ (ከኮሌጅ መምህራን) የተገኘው መረጃ ተማሪዎቹ አዎንታዊ የሆነ ተግባር ማከናወናቸውን አመልክተዋል። በአንፃሩ ደግሞ በጥልቀት የአጠያየቅ ስልት ከምልከታ (ከኮሌጅ መምህራን) የተጠናቀረውና ከተማሪ አስተማሪዎች የራስ ግምገማ ማስታወሻ የተጠናቀረው መረጃ አሉታዊ ሆኖ ተገኝቷል። ይህም በተጨባጭ በተማሪ አስተማሪዎቹ ዘንድ ከሚስተዋለው እውነታ ጋር ይበልጥ የሚቀራረብ ሆኗል። ከዚህም የተነሳ የተማሪ አስተማሪዎቹ የትምህርት ዕቅድ ዝግጅት ብቃት ያለው ነው ለማለት አያስችልም። እስካሁን ስለተማሪ አስተማሪዎቹ የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት ያየነው ይህን ይመስላል። በማስከተል ደግሞ ባዘጋጁት የትምህርት ዕቅድ መሠረትነት፣ በማስተማር ክንውናቸው ሂደት ያለውን የትምህርት አቀራረብ እንመለከታለን።

## 4.3.2 የተማሪ አስተማሪዎቹ የትምህርት አቀራረብ

ሰንጠረዥ 11፡ በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት ያለውን የተማሪ አስተማሪዎች የትምህርት አቀራረብ በተመለከተ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የተማሪ አስተማሪዎች፣ የት/ቤት መምህራንና የኮሌጅ መምህራን ምላሽ

| | ዝርዝር መጠይቆች | በጣም እስማማለሁ (5) | እስማማለሁ (4) | ድምር | በመጠኑ እስማማለሁ (3) | አልስማማም (2) | በፍጹም አልስማማም (1) | ድምር | ያልተመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ | ተማሪዎችን ያማከለ (student centerd) ትምህርት አስተምራለሁ | 76 | 18 | 94 (94%) | 1 (1%) | 1 | 1 | 2 (2%) | 3 (3%) |
| | ተማሪዎችን ንቁ (active) ተሳታፊ ያደረገ ትምህርት ሰጥቻለሁ | 69 | 24 | 93 (93%) | 4 (4%) | 1 | 1 | 2 (2%) | 1 (1%) |
| የት/ቤት መምህራን ምላሽ | ተማሪዎችን ያማከለ (student centerd) ትምህርት አስተምረዋል | 7 | 6 | 13 (76.5%) | 3 (17.6%) | 1 | - | 1 | - |
| | ተማሪዎችን ንቁ (active) ተሳታፊ ያደረገ ትምህርት ሰጥተዋል | 4 | 6 | 10 (58.8%) | 3 (17.6%) | 1 | - | 1 (5.9%) | 3 (17.6%) |
| የኮሌጅ መምህራን ምላሽ | ተማሪዎችን ያማከለ (student centerd) ትምህርት አስተምረዋል | 5 | 2 | 7 (63.6%) | 4 (36.4%) | - | - | - | - |
| | ተማሪዎችን ንቁ (active) ተሳታፊ ያደረገ ትምህርት ሰጥተዋል | 4 | 2 | 6 (54.5%) | 5 (45.5%) | - | - | - | - |

ተማሪ አስተማሪዎች ለፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ እክፍል ገብተው ሲያስተምሩበት የነበረው የትምህርት አቀራረብ ስልት፣ ተማሪዎችን ያማከለና ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑም ያስቻላቸው መሆኑን ከፍ ሲል ከተሰጡት ምላሾች መመልከት ይቻላል:: የትምህርቱ አቀራረብ ተማሪዎቹን ማዕከል ያደረገና በንቃት ያሳተፈ መሆኑን አስመልክቶ ለቀረቡት ጥያቄዎች በተማሪ አስተማሪዎች፣ በት/ቤት መምህራንና በኮሌጅ መምህራን በኩል የተሰጠው ምላሽ በወጥነት አዎንታዊ ነው:: ተማሪ አስተማሪዎቹ ደግሞ ለሁለቱም ጥያቄዎች የሰጡት ምላሽ ከ90% በላይ አዎንታዊ ነው:: በመምህራኑ በኩል ግን በተለይ "ተማሪዎችን በንቃት ያሳተፈ" መሆኑን አስመልክቶ ለቀረበው ጥያቄ ከተማሪዎቹ እንስ ያለ አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: ይህን በተመለከተ ተማሪዎቹ 93% አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ የት/ቤት መምህራን 58.8%፣ የኮሌጅ መምህራን 54.5% ብቻ አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: ይህም መምህራኑ በዚህ ረገድ ሙሉ እምነት እንደሌላቸው ያመለክታል:: ስለዚህ የተማሪ አስተማሪዎቹ የትምህርት

አቀራረብ ተማሪዎችን ያማከለ መሆኑን ሦስቱም ያመኑበት ቢሆንም፤ የትምህርቱን ተማሪዎችን በንቃት ማሳተፍ በተመለከተ ግን መምህራኑ ጥርጣሬ አላቸው:: ጉዳዩን ይበልጥ ለማረጋገጥ ያመች ዘንድም ከዕሑፍ መጠይቅ ውጪ የተገኙትን መረጃዎች እንመልከት::

የኮሌጅ መምህራን በተዘጋጀላቸው የምልከታ ቅፅ አማካይነት የተማሪ አስተማሪዎቹን የትምህርት አቀራረብ ስልት ምልከታ እንዲያደርጉ ውስን የአጠያየቅ መንገድን የተከተሉ ነጥቦች ተሰጥተዋቸዋል:: በዚህም መሠረት ተማሪ አስተማሪዎቹ የክፍል ውስጥ ሥራዎችን /ተግባራትን (activities) እንዴት ባለመንገድ እንዳከናወኑ እንዲመለከቱ ተደርጓል:: ይህን በተመለከተም የሰጡት ምላሽ የሚከተለውን ይመስላል::

ሰንጠረዥ 12፡ የተማሪ አስተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ሥራዎች /ተግባራት (activities) አቀራረብ በተመለከተ በመከታተያ ቅፁ ላይ ለቀረቡት ዝርዝር ነጥቦች የኮሌጅ መምህራን ምላሽ

| የማስተማር ክንውኖች (activeties) | አዎ | አርግጠኛ አይደለሁም | አይ |
|---|---|---|---|
| 1. የክፍል ውስጥ ሥራዎች/ተግባራት (activities) | | | |
| 1.1 በአግባቡ የተደራጁ (organized) ናቸው | 13 (61.9%) | 6 (28.6%) | 2 (9.5%) |
| 1.2 ከየጉዳዩ የተወሰኑ (varied) ናቸው | 7 (33.3%) | 9 (42.9%) | 5 (23.8%) |
| 1.3 ተማሪዎችን በንቃት (actively) ያሳተፉ ናቸው | 11 (52.4%) | 5 (23.8%) | 5 (23.8%) |
| 1.4 ተማሪዎችን ማዕከል ያደረጉ (student-centred) ናቸው | 13 (61.9%) | 2 (9.5%) | 6 (28.6%) |
| 1.5 በክፍል ውስጥ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተጣጥመዋል | 5 (23.8%) | 10 (47.6%) | 6 (28.6%) |
| 1.6 ተማሪዎች በትጋት እንዲሰሩ (challenge) ማድረግ ችለዋል | 9 (42.9%) | 5 (23.8%) | 7 (33.3%) |
| **ድምር (መቶኛ)** | **58 (46.0%)** | **37 (29.4%)** | **31 (24.6%)** |

የኮሌጅ መምህራን ያደረጉት የምልከታ ውጤት በድምሩ እንደሚያሳየው ከሆነ ተማሪ አስተማሪዎቹ የክፍል ውስጥ ክንውኖችን ያቀረቡበት መንገድ ጥሩ ሊባል የሚችል ነው:: ይህን አስመልክቶ ከቀረቡላቸው ስድስት ዝርዝር ነጥቦች መካከልም ለብዙዎቹ የሰጡት ምላሽ አዎንታዊና ከ50% በላይ ነው:: ቢሆንም ግን በአንዳንድ ነጥቦች ረገድ የተማሪ አስተማሪዎቹ የአቀራረብ ሁኔታ ድክመት የሚታይበት መሆኑን የሚያመለክቱ ምላሾችንም ሰጥተዋል:: ከሌሎቹ ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ አዎንታዊ ምላሽ የሰጡባቸው ነጥቦችም የክፍል ውስጥ ሥራዎቹ

ከየግድነቱ መውጣጣታቸውን (33.3% አምንታዊ)፣ በክፍል ውስጥ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር መጣጣማቸውን (23.8% አምንታዊ) እና፣ ተማሪዎች እንዲተጉ ማድረጋቸውን (42.9% አምንታዊ) አስመልክቶ የቀረቡት ናቸው። ስለዚህ ተማሪ አስተማሪዎቹ ያከናወኑት ተግባር በአመዛኙ በአምንታዊነት የሚታይ ቢሆንም፣ አንዳንድ ድክመቶችም ይስተዋሉባቸዋል ለማለት ይቻላል። በክፍት የአጠያየቅ መንገድ ለኮሌጅ መምህራን በምልከታው ቅፅ ላይ ከቀረበውና ለተማሪ አስተማሪዎች በራስ መገምገሚያ ማስታወሻው ላይ ከቀረበው ጥያቄ የተገኘው ምላሽም እንዲሁ ድክመት ያለባቸው መሆኑን የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል።

ለኮሌጅ መምህራን በምልከታ ቅፃቸው ላይ ከተመለከቱት የማስተማር ክንውን መሻሻል አለባቸው የሚሏቸውን ጉዳዮች ያስፍሩ' የሚል ክፍት ጥያቄ ቀርቦላቸዋል። በተመሳሳይ በራስ መገምገሚያ ማስታወሻቸው ላይ ከዕለቱ የማስተማር ክንውን ላሻሽላቸው ይገባል የምትሏቸውን ጉዳዮች አስፍር/ሪ' የሚል ጥያቄ ለተማሪ አስተማሪዎቹ ተሰጥቷል። በሁለቱም በኩል ከክፍል ውስጥ ሥራዎች/ ተግባራት አከናወን ጋር በተያያዘ መሻሻል አለባቸው ተብለው ከተዘረዘሩት ዋና ዋና ድክመቶች መካከል የሚከተሉቱ ተጠቃሽ ናቸው።

| በምልከታ ቅፃቸው ላይ የኮሌጅ መምህራን ያነሷቸው ድክመቶች | በራስ መገምገሚያ ማስታወሻቸው ላይ ተማሪ አስተማሪዎች ያነሷቸው ድክመቶች |
| --- | --- |
| • የትምህርቱ ከአካባቢያዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር አለመያያዝ | • (ከቡድን ሥራ ውጪ) ተማሪዎችን የሚያሳትፉ የተለያዩ ዘዴዎችን አፈራርቆ አለመጠቀም |
| • ተማሪዎችን በንቃት የሚያሳትፉ የተለያዩ ዘዴዎችን አለመጠቀም | • ለአፈፌትና ለኢ-አፈፌት ተማሪዎች የተለያየ አቀራረብን አለመጠቀም |
| • ከተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ጋር የሚመጣጠን አቀራረብ አለመጠቀም | • የቡድን ሥራዎችን በአግባቡ አለማሠራት |
| • ተማሪዎችን ማዕከል ያደረገ ትምህርት አለመስጠት | • ተማሪዎችን ያማከለ ትምህርት አለማቅረብ |

ከነዚህ በኮሌጅ መምህራንም ሆነ በተማሪ አስተማሪዎቹ በኩል መሻሻል አለባቸው ተብለው ከተዘረዘሩት ነጥቦች መረዳት እንደሚቻለው፣ የክፍል ውስጥ ሥራዎችን በአግባቡ በማከናወን ረገድ በተማሪዎቹ ላይ የጎላ ድክመት ይታይባቸዋል። በተለይ ተማሪዎችን ያማከለ ትምህርት ከመስጠት፣ ትምህርቱን ከአካባቢያዊ ሁኔታዎች ጋር ከማዛመድ፣ የተማሪዎችን ደረጃ የሚመጥን አቀራረብ ከመጠቀም አንፃር የጎላ ድክመት ያለባቸው መሆኑን ለማየት ይቻላል። (እዚህ ላይ ቀደም ሲል የት/ቤትና የኮሌጅ መምህራን በፅሑፍ መጠይቅ ሰንጠረዥ 11 ላይ፣ እንዲሁም የኮሌጅ መምህራን በምልከታ ቅፅ ላይ እና ተማሪ አስተማሪዎች በራስ መገምገሚያ ማስታወሻቸው ላይ የሰጡትን ምላሽና አስተያየት ልብ ይሏል።) ይህንንም ይበልጥ ለማጠናከር

ይረዳን ዘንድ ተማሪ አስተማሪዎቹ የማስተማር ክንውናቸውን በሚያካሂዱበት ወቅት የት/ቤት ተማሪዎች የነበሩበትን ሁኔታ መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ተማሪ አስተማሪዎች በሚያስተምሩበት ወቅት ተማሪዎቻቸው በምን ሁኔታ ላይ ይገኙ እንደነበር ይመለከቱ ዘንድ ለቀረቡላቸው ዝርዝር ነጥቦች የኮሌጅ መምህራን የሰጡት ምላሽም የሚከተለው ነው፡፡

ሰንጠረዥ 13፡ ተማሪ አስተማሪዎች በሚያስተምሩበት ወቅት የት/ቤት ተማሪዎች የነበሩበትን ሁኔታ በተመለከተ ለቀረቡት ዝርዝር ነጥቦች የኮሌጅ መምህራን ምላሽ

| የማስተማር ክንውኖች (activeties) | አዎ | እርግጠኛ አይደለሁም | አይ |
|---|---|---|---|
| 7. የክፍል ተማሪዎች ሁኔታ (students) | | | |
| 7.1 በትምህርቱ መማሪያቸውን በግልፅ አሳይተዋል | 8 (38.1%) | 9 (42.9%) | 4 (19.0%) |
| 7.2 በትምህርቱ ላይ በንቃት (actively) ተሳትፎ አድርገዋል | 12 (57.1%) | 3 (14.3%) | 6 (28.6%) |
| 7.3 በትምህርቱ ላይ እንደግላዊ ልዩነታቸው ተሳትፈዋል (treated as individuals) | 9 (42.8%) | 6 (28.6%) | 6 (28.6%) |
| 7.4 በትምህርቱ መጨረሻ ላይ የሚጠበቅባቸውን ተረድተዋል | 8 (38.1%) | 8 (38.1%) | 5 (23.8%) |
| 7.5 ከመምህሩ ተገቢውን ማበረታቻ አግኝተዋል (encouraged) | 10 (47.6%) | 3 (14.3%) | 8 (38.1%) |
| 7.6 በትምህርቱ ሂደት ተደስተዋል (enjoyed) | 8 (38.1%) | 7 (33.3%) | 6 (28.6%) |
| ድምር (መቶኛ) | 55 (43.6%) | 36 (28.6%) | 35 (27.8%) |

ከፍ ሲል የተመለከተው የኮሌጁ መምህራን ምላሽ እንደሚያሳየው፣ ተማሪ አስተማሪዎቹ በሚያስተምሩበት ወቅት በተማሪዎቻቸው ላይ ይንፀባረቅ የነበረው ሂደት ጥሩ የሆነ የመማር ማስተማር ሁኔታ ተካሂዷል የሚያስብል አይደለም፡፡ በዚህ ረገድ የኮሌጅ መምህራን ለቀረቡላቸው ዝርዝር ነጥቦች የሰጡት አጠቃላይ ምላሽም በአዎንታዊነት የሚወሰድ አይሆንም፡፡ በተለይም ተማሪዎቹ በትምህርቱ መማሪያቸውን፣ እንደግላዊ ልዩነታቸው በትምህርቱ ላይ መሳተፋቸውን፣ በትምህርቱ መጨረሻ ላይ የሚጠበቅባቸውን መረዳታቸውን፣ እና በትምህርቱ አጠቃላይ ሂደት መደሰታቸውን በተመለከተ ለቀረቡት ነጥቦች የተሰጡት አዎንታዊ ምላሾች ዝቅተኛ ናቸው፡፡ ይህም ቀደም ሲል በሰንጠረዥ 11 እና 12 ሥር የት/ቤትና የኮሌጅ መምህራን የሰጡትን ዝቅተኛ አዎንታዊ ምላሽ የሚደግፍ ነው፡፡ ይህም በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት ያለው የተማሪ አስተማሪዎች የትምህርት አቀራረብ ስልት ተገቢውን አካሄድ የተከተለ ነበር ለማለት አያስችልም፡፡

በአጠቃላይ ተማሪ አስተማሪዎች የማስተማር ልምምድ በሚያካሂዱበት ወቅት የነበረው የትምህርት አቀራረብ ስልት ምን እንደሚመስል ከፅሑፍ መጠይቅ፣ ከምልከታና ከመገምገሚያ ቅፅ የተጠናቀሩትን መረጃዎች መሠረት በማድረግ ፈትሸናል። ከፅሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንዳሳየው ከሆነ የተማሪ አስተማሪዎቹ የትምህርት አቀራረብ በተወሰነ ደረጃ ተማሪዎችን ያማከለና ንቁ ተሳታፊ ያደረገ መሆኑን ያመለክታል። እንዲሁም በምልከታ (በውስን የአቀራረብ መንገድ ከቀረቡት ዝርዝር ነጥቦች) የተገኙት መረጃዎችም በተወሰነ ደረጃ በፅሑፍ የተገኘውን መረጃ የሚደግፉ ሆነዋል። በአንፃሩ ግን በውስን አጠያየቅ ከቀረቡት የምልከታ ነጥቦች መካከል አንዳንዶቹና በክፍት አጠያየቅ የቀረቡት ጥያቄዎች በመሉ፣ እንዲሁም ከተማሪዎች የመገምገሚያ ቅፅ የተጠናቀሩት መረጃዎች የተማሪ አስተማሪዎቹን የትምህርት አቀራረብ ድክመት ያሳዩ ነበሩ። በዚህም ምክንያት የተማሪ አስተማሪዎቹ የትምህርት አቀራረብ ስልት ተገቢውን መንገድ /ሥርዓት የተከተለ ነው ለማለት (ለመደምደም) አይቻልም። ይህም ተማሪ አስተማሪዎች በዚህ ረገድ የሚጠበቅባቸውን ሥራ በአግባቡ እንዳልተወጡ ያመለክታል። ስለተማሪ አስተማሪዎቹ የትምህርት አቀራረብ ስልት ይህን ካልን ዘንዳ፣ ቀጥለን ደግሞ ከማስተማሩ ሂደት ጋር በተያያዘ ያከናወኑትን የምዘና ሁኔታ እንይ።

### 4.3.3 የተማሪ አስተማሪዎቹ በማስተማር ልምምዱ ሂደት ተግባራዊ ያደረጉት የምዘና ሁኔታ

ሰንጠረዥ 14፡ ተማሪ አስተማሪዎች በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት እክፍል ገብተው ሲያስተምሩ ያለውን የምዘና ሁኔታ በተመለከተ ለቀረበ ጥያቄ የተማሪ አስተማሪዎች፣ የት/ቤት መምህራንና የኮሌጅ መምህራን ምላሽ

| | ዝርዝር መጠይቆች | በጣም እስማማለሁ (5) | እስማማለሁ (4) | ድምር | በመጠኑ እስማማለሁ (3) | አልስማማም (2) | ጨርሶ አልስማማም (1) | ድምር | ያልተመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| [illegible] | ተከታታይ ምዘናን (continuous assessment) ተግባሪያለሁ | 41 | 40 | 81 (81%) | 16 (16%) | - | 2 | 2 (2%) | 1 (1%) |
| [illegible] | ተከታታይ ምዘናን (continuous assessment) ተግባሪዋል | 3 | 7 | 10 (58.8%) | 6 (35.3%) | 1 | - | 1 (5.9%) | - |
| [illegible] | ተከታታይ ምዘናን (continuous assessment) ተግባሪዋል | 4 | 2 | 6 (54.5%) | 4 (36.4%) | - | - | - | 1 (9.1 %) |

ከፍ ሲል ከተመለከተው ምላሽ መመልከት እንደሚቻለው ተማሪ አስተማሪዎቹ በማስተማር ልምምዳቸው ወቅት ያካሄዱት የምዘና ሁኔታ አዎንታዊ ሊባል የሚችል ነው። ይህን በተመለከተ ለቀረበው ጥያቄ በተማሪ አስተማሪዎች፣ በት/ቤት መምህራንና በኮሌጅ መምህራን በኩል የተሰጠው ምላሽ ከሞላ ጎደል በአዎንታዊነት የሚታይ ነው። ከነዚህም መካከል ከፍተኛውን ደረጃ የሚይዘው አዎንታዊ ምላሽ የተሰጠው በተማሪ አስተማሪዎቹ ነው። 81% አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። በት/ቤት መምህራንና በኮሌጅ አቻዎቻቸው በኩል የተሰጠው ግን ከዚህ በጣም ያነሰ ነው። የት/ቤት መምህራን 58.8%፣ የኮሌጅ መምህራን ደግሞ 54.5% አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ይህም በተወሰነ ደረጃ ጥርጣሬ/ ማመንታት እንደሚታይባቸው ያመለክታል። ይህ ሁኔታ (ማመንታቱ) ለኮሌጅ መምህራኑ በተሰጠው የምልከታ ቅፅ ላይም ተንፀባርቋል። የኮሌጅ መምህራን የተማሪ አስተማሪዎቹን የማስተማር ሂደት እንዲመለከቱበት በተዘጋጀላቸው ቅፅ ላይ የምዘና ሁኔታቸውን በተመለከተ የሰጡት ምላሽ ቀጥሎ ያለው ነው።

ሰንጠረዥ 15፡ የተማሪ አስተማሪዎችን የምዘና ሁኔታ በተመለከተ በመከታተያ ቅፁ ላይ ለቀረቡት ዝርዝር ነጥቦች የኮሌጅ መምህራን ምላሽ

| የማስተማር ክንውኖች (activities) | አዎ | እርግጠኛ አይደለሁም | አይ |
|---|---|---|---|
| 4. ምዘና (assessment) | | | |
| 4.1 ተገቢነት (appropriateness) አለው | 15 (71.5%) | 5 (23.8%) | 1 (4.7%) |
| 4.2 ብቃት (effectiveness) አለው | 8 (38.1%) | 8 | 5 (23.8%) |
| 4.3 ተከታታይነት (continuity) አለው | 5 (23.8%) | 8 (38.1%) | 8 (38.1%) |
| 4.4 ተማሪዎች ስለመመዘናቸው ያውቃሉ (aware) | 6 (26.8%) | 5 (23.8%) | 10 (47.6%) |
| 4.5 ተማሪዎች ገንቢ ምጋቢ ምላሽ (feedback) አግኝተዋል | 10 (47.6%) | 5 (23.8%) | 6 (26.8%) |
| ድምር (መቶኛ) | 44 (41.9%) | 31 (29.5%) | 30 (28.6%) |

ከላይ ከተመለከተው የኮሌጅ መምህራን ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው ከሆነ የተማሪ አስተማሪዎቹ የምዘና ሁኔታ በርካታ ድክመቶች ይታዩበታል። መምህራኑ ከተመለከቷቸው ነጥቦች ውስጥ በአዎንታዊነት ሊጠቀሱ የሚችሉት ሁለት ብቻ ናቸው። ስለምዘናው ተገቢነት የተሰጠው 71.5% አዎንታዊ ምላሽና ለተማሪዎች ገንቢ ምጋቢ ምላሽ መስጠታቸውን በተመለከተ የተሰጠው 47.6% አዎንታዊ ምላሽ ነው። ይህም ቢሆን ለተቀሩት ሌሎች ነጥቦች ከተሰጠው አነስተኛ አዎንታዊ ምላሽ አንፃር ሲታይ ምላሹን አጠራጣሪ ያደርገዋል። ለምሳሌ

ያህል ብናይ የምዘናውን ብቃት በተመለከተ 38.1% አዎንታዊና 38.1% እርግጠኛ አይደለሁም የሚል ምላሽ ሲሰጡ፣ የምዘናውን ተከታታይነት በተመለከተም 38.1% እርግጠኛ አይደለሁምና 38.1% አይ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። እንዲሁም ስለመመዘናቸው ተማሪዎቹ ማወቃቸውን በተመለከተ 23.8% እርግጠኛ አይደለሁምና 47.6% አይ የሚል ምላሽ ነው የሰጡት። ከዚህም መመልከት እንደሚቻለው፣ የተማሪ አስተማሪዎቹ የምዘና ሁኔታ በርካታ ድክመቶች እንዳሉበት ነው። ይህም ከፍ ሲል እንደተመለከትነው በፅሑፍ መጠይቅ ላይ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ ውስጥ የሚታየውን ማመንታት ግልፅ ያደርጋል። ስለዚህም ተማሪ አስተማሪዎቹ ተገቢ የሆነ ምዘና አካሂደዋል ለማለት ይከብዳል።

በአጠቃላይ ከፍ ሲል የተመለከትናቸው መረጃዎች ለየብቻቸው ሲታዩ ቁርጥ ያለ ምላሽ የሚሰጡ አይደሉም። የተማሪዎቹን የምዘና ሂደት በተመለከተ በፅሑፍ መጠይቅ የተጠናቀረው መረጃ በአመዛኙ አዎንታዊነት ይታይበታል። ይህም ሆኖ ግን ከተማሪ አስተማሪዎቹ በስተቀር የመምህራን አዎንታዊ ምላሽ ዝቅተኛ ነው። በምልከታ ቅፅ የተጠናቀረው መረጃ ግን አዎንታዊ የሆነ ምላሽ የታየበት አይደለም። ስለዚህ እነዚህ የተጠናቀሩት መረጃዎች በጥቅሉ ሲታዩ የሚሰጡት ምስል እንደሚያሳየው ከሆነ፣ ተማሪ አስተማሪዎቹ በሚያስተምሩበት ወቅት ያካሄዱት የምዘና ሁኔታ ብቃት ያለው ነው ለማለት አያስደፍርም። በመሆኑም ተማሪ አስተማሪዎቹ በዚህ ረገድ የሚጠበቅባቸውን ሥራ በአግባቡ አላከናወኑም ለማለት ይቻላል። ስለምዘና አከናወናቸው ይህን ያህል ካልን፣ በማስከተል ደግሞ በፕራክቲከም የማስተማር ልምምዱ ሂደት ጋር በተያያዘ ለማስተማር መማር ሥራው አስፈላጊ የሆኑ የማስተማሪያ መማሪያዎችን በማዘጋጀት/ በመጠቀም በኩል ያከናወኑትን ተግባር እንመልከት።

### 4.3.4 የተማሪ አስተማሪዎች የአጋዥ የማስተማሪያ መሣሪያዎች ዝግጅት

ሰንጠረዥ 16፦ በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት አጋዥ የማስተማሪያ መሣሪያዎችን በማዘጋጀት/ በመጠቀም በኩል ያከናወኑትን ተግባራት በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ ተማሪ አስተማሪዎች፣ የት/ቤት መምህራንና የኮሌጅ መምህራን ምላሽ

| | ዝርዝር መጠይቆች | በጣም እስማማለሁ (5) | እስማማለሁ (4) | ድምር | በመጠኑ እስማማለሁ (3) | አልስማማም (2) | በጭራሽ አልስማማም (1) | ድምር | ያልተመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| [illegible] | አጋዥ የማስተማሪያ መሣሪያዎችን አዘጋጅቻለሁ/ ተጠቅሚያለሁ | 16 | 32 | 48 (48%) | 31 (31%) | 12 | 6 | 18 (18%) | 3 (3%) |
| [illegible] | አጋዥ የማስተማሪያ መሣሪያዎችን አዘጋጅተዋል/ ተጠቅመዋል | 2 | 5 | 7 (41.2%) | 5 (29.4%) | 3 | 2 | 5 (29.4%) | - |
| [illegible] | አጋዥ የማስተማሪያ መሣሪያዎችን አዘጋጅተዋል/ ተጠቅመዋል | 1 | 3 | 4 (36.4%) | 2 (18.2%) | 4 | 1 | 5 (45.4%) | - |

ከላይ የተመለከተው ምላሽ እንደሚያሳየው፣ ተማሪ አስተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት አጋዥ የሆኑ መሣሪያዎችን በማዘጋጀት/ በመጠቀም በኩል አጥጋቢ ነገር ሠርተዋል ለማለት አያስችልም፡፡ ይህን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ ተማሪ አስተማሪዎች 48% አዎንታዊ፣ 31% በመጠኑ እስማማለሁና 18% አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህም በዚህ ረገድ አጥጋቢ ሥራ ማከናወናቸውን በተመለከተ ራሳቸው ተማሪዎቹ እርግጠኝነት እንደሚጎላቸው የሚያሳይ ነው፡፡ በመምህራኑ በኩል የተሰጠው ምላሽም ይህን የሚያጠናክር ነው፡፡ የት/ቤት መምህራን ለቀረበላቸው ጥያቄ 41.2% አዎንታዊ፣ 29.4% በመጠኑ እስማማለሁና 29.4% አሉታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ የኮሌጅ መምህራን ደግሞ 36.4% አዎንታዊ፣ 18.2% በመጠኑ እስማማለሁና 45.4% አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከመምህራኑ ምላሽ በግልፅ መመልከት እንደሚቻለውም፣ ተማሪ አስተማሪዎች ለመማር ማስተማሩ ተግባር አጋዥ የሆኑ ማስተማሪያ መሣሪያዎችን በማዘጋጀትም ሆነ በመጠቀም በኩል የሠሩት ሥራ አመርቂ አይደለም፡፡ ይህም ከዚህ ቀደም በማስተማር ልምምዱ ሂደት ያከናወኗቸውን ተግባራት (የትምህርት ዕቅድ ዝግጅት፣ የትምህርት አቀራረብና የምዘና ሁኔታን) በተመለከተ ካጠናቀርናቸው መረጃዎች ጋር

ሲዳመር፣ ተማሪ አስተማሪዎቹ ውጤታማ የሆነ የማስተማር ልምምድ እንዳላካሄዱ ያመለክታል።

የተማሪ አስተማሪዎችን የሥራ ድርሻና ኃላፊነት በተመለከተ እስካሁን የተመለከትናቸው ነጥቦች ከማስተማሩ ተግባር ጋር በቀጥታ የተያያዙ ናቸው። በማስከተል የምናየው የመጨረሻው ጉዳያችን ደግሞ ከማስተማሩ ተግባር ውጪ ያሉትን የሚመለከት ይሆናል።

### 4.3.5 ከማስተማር ውጪ ባሉ ተግባራት ላይ ተማሪ አስተማሪዎች ያላቸው ተሳትፎ

ሰንጠረዥ 17፡ በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት ከማስተማር ውጪ ባሉ ተግባራት ላይ ያላቸውን ተሳትፎ በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ የተማሪ አስተማሪዎች፣ የት/ቤት መምህራንና የኮሌጅ መምህራን ምላሽ

| | ዝርዝር መጠይቆች | በጣም እስማማለሁ (5) | እስማማለሁ (4) | ድምር | በመጠኑ እስማማለሁ (3) | አልስማማም (2) | ጨርሶ አልስማማም (1) | ድምር | ያልተመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ | ከማስተማር ውጪ ባሉ (co-curricular) ተግባራት ላይ ተሳትፌያለሁ | 10 | 25 | 35 (35%) | 29 (29%) | 14 | 16 | 30 (30%) | 6 (6%) |
| የት/ቤት መምህራን ምላሽ | ከማስተማር ውጪ ባሉ (co-curricular) ተግባራት ላይ ተሳትፈዋል | 3 | 4 | 7 (41.2%) | 3 (17.6%) | 4 | 3 | 7 (41.2%) | - |
| የኮሌጅ መምህራን ምላሽ | ከማስተማር ውጪ ባሉ (co-curricular) ተግባራት ላይ ተሳትፈዋል | 1 | 1 | 2 (18.2%) | 4 (36.4%) | 5 | - | 5 (45.4%) | - |

ከላይ ሲል የተመለከተው የተማሪ አስተማሪዎች፣ ት/ቤት መምህራንና የኮሌጅ መምህራን ምላሽ እንደሚያመለክተው ተማሪዎቹ ከክፍል ውስጡ የማስተማር ተግባር ውጪ ባሉ ጉዳዮች ላይ የነበራቸው ተሳትፎ በጣም አናሳ ነው። ራሳቸው ተማሪዎቹም ሆኑ መምህራኑ የሰጡት ምላሽ በመጠኑት ያሳየውም ይህንኑ ነው። ከቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃም ይህንኑ የሚያጠናክር ሆኖ ነው የተገኘው። ለአብነት ያህልም የመደወላቡ ት/ቤት ርዕሰ መምህር ይህን አስመልክቶ የሰጡትን አስተያየት ትርጉም መመልከት ይቻላል።

> *ተማሪዎቹ ፕራክቲከምን፣ በሙሉ (የሚያካትታቸውን ተግባራት ሁሉ) የመቀበል ፍላጎት የላቸውም። በክፍለ ጊዜያችን ብቻ መጥተን አስተምረን መመለስ አለብን ይላሉ። ፕራክቲከም ክፍል ገብቶ ማስተማር ብቻ አይደለም። የማስተማሪያ መሣሪያዎች ማዘጋጀትና በተለያዩ የልማት ሥራዎች ላይ መሳተፍ*

*አለባቸው:: የት/ቤቱ ሥራ እንዴት እንደሚከናወን፣ ተማሪዎች እንዴት እንደሚያዙ፣ በት/ቤቱ ማህበረሰብ መካከል ያለው መስተጋብር ምን እንደሚመስል... ማወቅ አለባቸው:: ተማሪዎች ግን ይህን ለመቀበል ገና ናቸው:: (ይህን በተመለከተ) በኮሌጁ በኩልም ተገቢውን መመሪያና ምክር (ማሳሰቢያ) ተቀብለው የመጡ አይመስሉም:: ከዛው ትዕዛዝ ቢሰጣቸው... ለምን እኛን (እዚህ) ያስቆያሉ! አንዳንዶቹ እንደውም በሳምንት ያለኝ ... ሁለት ክፍለ ጊዜ ነው:: እኔ ግን አምስት ቀን ሙሉ እዚህ ውላለው:: ለምን ይኼ ይሆናል!? በማለት ጉዳዩን የመብት ጥያቄ አድርገው ያቀርባሉ::...*

የመደወሻው ት/ቤት ርዕሰ መምህር ከሰጡት ሃሳብ መመልከት እንደሚቻለው የተማሪ አስተማሪዎቹ ክፍል ገብተው ከማስተማር ውጪ ያሉትን ተግባራት አያከናውኑም፤ ፍላጎትም የላቸውም፡ እንደ የትርፍ ሰዓት መምህር በሰዓታቸው መጥተው መመለስ ነው የሚፈልጉት:: ከክፍለ ጊዜያቸው ቀድመው አይመጡም፤ ካስተማሩም በኋላ በት/ቤት ውስጥ አይቆዩም:: ከዚህም የተነሣ በፕራክቲከም የማስተማር ልምምዱ ሂደት ከማስተማር ውጪ ባሉ ተግባራት ላይ ሊሳተፉ አልቻሉም:: ተሣትፎ ማድረጋቸው ግዴታቸው ቢሆንም፣ እነሱ ግን የተገላቢጦሽ መብታቸው እንደተገኘ አድርገው ነው የሚወስዱት:: በዚህ ረገድ በኮሌጁ በኩል በተዘጋጀላቸው የመገምገሚያ ቅፅ ላይ ከማስተማር ውጪ የሚሠሯቸው ጉዳዮች እንዳሉ በግልፅ የተቀመጡላቸው ቢሆንም ለማከናወን ግን ፍቃደኛ አልሆኑም:: ይህን ማከናወናቸውን በተመለከተም በኮሌጁ በኩል ተጨማሪ ክትትልና ቁጥጥር አልተደረገባቸውም:: ስለዚህ ቀደም ሲል በፅሑፍ መጠይቅ በተገኘው መረጃ እና በቃለ መጠይቅም በተረጋገጠው መሰረት ተማሪ አስተማሪዎች ከማስተማር ውጪ ባሉ ተግባራት ላይ ያላቸው ተሣትፎ በጣም አነስተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡ ይህም የማስተማር ልምምድ ክንውናቸው የተሟላ እንዳይሆን ያደርገዋል:: ተገቢውን ልምድ ቀስመዋል ለማለትም ይቸገራል። ምክንያቱም በዚህ ሂደት ማስተማርን ከመለማመድ ጎን ለጎን የማስተማሪያ መሣሪያዎችን በማዘጋጀት (አጋዥ የማስተማሪያ መሣሪያዎችን በማዘጋጀት፣ በመጠቀም በኩል የሠሩት ሥራ እናሳ መሆኑን ልብ ይሏል)፤ በት/ቤት መዋቅራዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ ተሣትፎ በማድረግ፣ ከተማሪዎች ወላጆች ጋር ውይይት በማድረግ ሙያው ምን አይነት ብቃት (quality) ያላቸውን ባለሙያዎች እንደሚሻ ልምድ መቅሰም ይጠበቅባቸዋል (Smith 1972 Gowers and Walters 1983 Richards and Nunan 1990):: ነገር ግን በተለያየ አቅጣጫ የተጠናቀሩት መረጃዎች እንዳመለከቱት ተማሪ አስተማሪዎች በዚህ ረገድ አመርቂ ስራ አልሠሩም::

በአጠቃላይ በዚህ ክፍል ስር ትኩረት ሰጥተን የተመለከትነው ተማሪ አስተማሪዎች በፕራክቲከም የማስተማር ልምምዱ ሂደት ሊያከናውኗቸው የሚገቡትን የሥራ ድርሻዎችና ኃላፊነቶች ነው:: በዚህም በልምምዱ ወቅት ያለው የትምህርት ዕቅድ ዝግጅታቸውን፣ የትምህርት አቀራረብ/ አሰጣጣቸውን፣ የምዘና አከናወናቸውን፣ አጋዥ የማስተማሪያ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት/ መጠቀማቸውን፣ እና ከማስተማር ውጪ ባሉ ተግባራት ላይ መሳተፋቸውን ተመልክተናል:: በፅሑፍ መጠይቅ፣ በምልከታ፣ በግምገማ ቅፅና በቃለ መጠይቅ

የተጠናቀሩት መረጃዎች እንዳመለከቱትም፤ ተማሪ አስተማሪዎቹ በፕራክቲከም የማስተማር ልምምዱ ሂደት ማከናወን የሚጠበቅባቸውን በአግባቡ አከናውነው አልተገኙም። እክፍል ውስጥ ገብተው በማስተማርም ሆነ ከማስተማር ውጪ ባሉ ተግባራት ላይ በመሳተፍ በኩል በርካታ ድክመቶች እንዳሉባቸው ለመረዳት ተችሏል። ይህም ቀደም ባለው ክፍል የኮሌጅ የመምህራንን የሥራ ድርሻ በተመለከተ የተጠናቀሩት መረጃዎች ያሳዩትን እውነታ የሚጠናክር ነው። ይኸውም ተማሪ አስተማሪዎች ከፕራክቲከም በፊት ከመምህሮቻቸው ጋር ተገናኝተው በት/ቤት ስለሚያከናውኗቸው ተግባራት እንደማይወስኑ፤ ስለመሠረታዊ የማስተማር ተግባር/ ክህሎትም እንደማይወያዩ የቀረበው መረጃ ትክክል መሆኑን ያመለክታል። እንዲሁም በፕራክቲከም ሂደት መምህሮቻቸው በት/ቤት ተገኝተው ተከታታይ ምልከታ እንደማያደርጉ፤ ተገቢውን ግምገማ እንደማያካሂዱ፤ በቃልና በፅሑፍ የተደገፈ ምጋቤ ምላሽና አስተያየት በወቅቱ እንደማይሰጧቸው የቀረበውን መረጃ እውነትነት ያጎላል። ከዚህም በተጨማሪ የኮሌጅ መምህራን ከፕራክቲከም በኋላ (ከት/ቤት መልስ) ከተማሪዎች ጋር ተገናኝተው ስላከናወኗቸው ተግባራት እንደማይወያዩአቸው የቀረበውን መረጃ ተገቢነት ያጠናክራል። ስለሆነም ቀደም ሲል በኮሌጅ መምህራን በኩል የተደረገላቸው እገዛ በቂ ካለመሆኑ አንፃር ሲታይ፤ ተማሪ አስተማሪዎቹ የሚጠበቅባቸውን ተግባር በወጉ አለማከናወናቸው የሚያስገርም አይሆንም። ምክንያቱም መምህራኑ ይህን ለማከናወን የሚያስችላቸውን በቂ ግንዛቤ ጨብጠው ወደ ልምምዱ አልገቡም፤ ወደ ማስተማር ልምምዱ ከገቡም በኋላ የተደረገላቸው እገዛና ክትትል አናሳ ነበር። የማስተማር ልምምድ ንድፈ ሃሳብ (የማስተማር ሥነ ዘዴ፣ መርሆ፣ ቴክኒክ፣ ስልት ...) ወደ ተግባር የሚለወጥበት/ የሚተረጎምበት ሂደት ነው (Sirvastava and Bose 1978 Gowers and Walters 1983 Sindau and Omulando 1992)። በዚህም ሂደት ተማሪ አስተማሪዎች በት/ቤት ተገኝተው በሚያከናውኗቸው በርካታ ተግባራት አማካይነት ማስተማርን ይለማመዳሉ፤ የተማሪዎቹን የት/ቤት ልምድ ይቀስማሉ፤ የማስተማሩ ሙያ ምን ዓይነት ባለሙያዎችን እንደሚፈልግ አውቀው ራሳቸውን ዝግጁ ያደርጋሉ (Stores 1978 Brown 1975 Richords and Nunan 1990 TESO 2003)። ከዚህ አንፃር ሲታይ ተማሪ አስተማሪዎቹ ይህን ዓይነቱን ሙያዊ ብቃት (Quality) ለመጎናፀፍ የሚያስችላቸውን ተግባራት አከናውነዋል ለማለት አያስደፍርም።

## 4.4 በፕራክቲከም ሂደት ውስጥ የኮሌጁ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

ለአጠቃላዩ የፕራክቲከም መርሃ ግብር ሂደት መሳካት በሮቤ መምህራን ኮሌጅ በኩል ምን ምን ሥራዎች እንደተከናወኑ ለመፈተሽ ከፅሑፍና ከቃለመጠይቅ መረጃዎች ተሰባስበዋል። በፅሑፍ መጠይቅ ኮሌጁ በፕራክቲከም ሂደት ለተማሪ አስተማሪዎች ያደረጋቸውን እገዛዎች በተመለከተ፤ ከኮሌጅ መምህራን፣ ከት/ቤት መምህራን እና ከተማሪ አስተማሪዎች መረጃዎች ተጠናቅረዋል፡ በቃለመጠይቅ ደግሞ በተለይ ኮሌጁ ለአጠቃላዩ የፕራክቲከም ሂደት ስኬት

ያከናወናቸውን ተግባራት በሚመለከት፣ ከኮሌጁ የፕራክቲከም ክፍል ኃላፊ መረጃ ለማጠናቀር ተችሏል። እነዚህንም እርስ በርስ እያነፃፀርን ቀጥለን እንመለከታቸዋለን፡፡ በቅድሚያም ለፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት በኮሌጁ በኩል የተዘጋጀውን የጊዜ ሰሌዳና የትራንስፖርት አገልግሎት በተመለከተ ከተጠናቀሩት መረጃዎች እንጀምራለን፡፡

ሰንጠረዥ 18፡ ለፕራክቲከም የማስተማር ልምምዱ ሂደት ኮሌጁ ያዘጋጀውን የጊዜ ሰሌዳና የትራንስፖርት አገልግሎት በተመለከተ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የኮሌጅ መምህራን፣ የት/ቤት መምህራንና የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ

| | ዝርዝር መጠይቆች | በጣም እስማማለሁ (5) | እስማማለሁ (4) | ድምር | በመጠኑ እስማማለሁ (3) | አልስማማም (2) | ጨርሶ አልስማማም (1) | ድምር | ያልተመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የኮሌጁ መምህራን ምላሽ | ተማሪዎች ተገቢውን ልምድ ከት/ቤት ለመቅሰም የሚያስችል የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቷል | 3 | 6 | 9 (81.8%) | - - | 2 | - | 2 (18.2%) | - |
| | በተገቢው ሰዓት ከት/ቤት ለመድረስ የሚያመች ትራንስፖርት ተዘጋጅቷል | 1 | 6 | 7 (63.66 %) | 3 (27.3%) | 1 | - | 1 (9.1%) | - |
| የት/ቤቱ መምህራን ምላሽ | ተገቢውን ልምድ ከት/ቤት ለመቅሰም የሚያስችል የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቷል | 3 | 5 | 8 (47.1%) | 4 (23.5%) | 3 | 2 | 5 (29.4%) | - |
| | በተገቢው ሰዓት ከት/ቤት ለመድረስ የሚያመች ትራንስፖርት ተመቻችቷል | 2 | 2 | 4 (23.5%) | 3 (17.6%) | 4 | 5 | 9 (52.9%) | 1 (5.9%) |
| የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ | ተገቢውን ልምድ ከት/ቤት ለመቅሰም የሚያስችል የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቷል | 21 | 22 | 43 (43%) | 20 (20%) | 12 | 22 | 34 (34%) | 3 (3%) |
| | በተገቢው ሰዓት ከት/ቤት ለመድረስ የሚያመች ትራንስፖርት ተመቻችቷል | 5 | 13 | 18 (18%) | 14 (14%) | 18 | 50 | 68 (68%) | - |

በፕራክቲከም የማስተማር ልምምዱ ሂደት ተማሪ አስተማሪዎችን ተገቢ የሆነ ልምድ ከት/ቤት ለማስቀሰም የሚያስችል የጊዜ ሰሌዳ መዘጋጀቱን እና በሚፈለገው ሰዓት ከት/ቤት የሚያደርሳቸው የትራንስፖርት አገልግሎትም መመቻቸቱን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ

የኮሌጅ መምህራን የሰጡት ምላሽ ከሌሎቹ በጣም ይለያል:: ይኸውም ተገቢ የሆነ የጊዜ ሰሌዳ መዘጋጀቱን በተመለከተ 81.8% አዎንታዊ ፤ አመቺ የትራንስፖርት አገልግሎት መኖሩን በተመለከተ ደግሞ 63.6% አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: ይህም የት/ቤት መምህራንና ተማሪ አስተማሪዎች ለተመሳሳይ ጥያቄ ከሰጡት ምላሽ በእጅጉ የተለየ ነው:: የት/ቤት መምህራን የጊዜ ሰሌዳ ዝግጅቱን በተመለከተ 47.1% አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ፤ ተማሪዎቹ ደግሞ 43% ብቻ አዎንታዊ የሆነ ምላሽ ሰጥተዋል:: ይህም የት/ቤት መምህራንና ተማሪ አስተማሪዎች ለተመሳሳይ ጥያቄ ከሰጡት ምላሽ በእጅጉ የተለየ ነው:: እንዲሁም የትራንስፖርት አገልግሎቱን አመቺነት በተመለከተ የት/ቤት መምህራን 52.9% አሉታዊና 23.6% አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ፤ ተማሪዎቹ ደግሞ 68% አሉታዊና 18% አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: ስለዚህም የኮሌጁ መምህራን ኮሌጁ ተገቢ የሆነ የጊዜ ሰሌዳና በቂ የትራንስፖርት አገልግሎት ማዘጋጀቱን በከፍተኛ ሁኔታ ሲያረጋግጡ፤ የት/ቤት መምህራንና ተማሪ አስተማሪዎቹ ደግሞ ተቃራኒውን አቋም ይዘው ተገኝተዋል:: ይህን ለማስታረቅና ቁርጥ ያለ አቋም ለመያዝ ያስችል ዘንድም ቀጥሎ የቀረበውን በቃለመጠይቅ የተጠናቀረ መረጃ እንመልከት::

ኮሌጁ ተማሪዎች ተገቢውን ልምድ ከት/ቤት ለመቅሰም የሚያስችላቸው የጊዜ ሰሌዳ አዘጋጅቶአል ወይ? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ በኮሌጁ የፕራክቲከም ክፍል ኃላፊ በኩል የተሰጠው መልስ፤ በፕራክቲከም ዙሪያ በኮሌጁ ያለውን ሦስት ተጨባጭ ሁኔታዎች ያሳያል:: ይኸውም በእርግጥ ተማሪዎቹ ከፕራክቲከሙ መርሃ ግብር ተገቢውን ልምምድ ቀስመዋል? ለመርሃ ግብሩ የተዘጋጀው የጊዜ ሰሌዳስ ምን ያህል ተገቢ ነው? ተማሪዎቹ የተመደቡበት ሁኔታ (ት/ቤት) የሚፈለገውን ልምድ ለመቅሰም ምን ያህል ምቹ ነው? የሚሉትን ጉዳዮች ቀጥሎ በአንቀፅ በአንቀፅ ከተመለከተው የኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊ ንግግር መረዳት ይቻላል::

*እንደመርሃ ግብር ሲታይ ተማሪዎችን ልምድ አስቀስሟል ብለን እናስባለን:: ግን አንዳንድ መሰናክሎች ሊኖሩ ይችላሉ:: ለምሳሌ ት/ቤቶች በራሳቸው ጊዜ የሚፈጥሩት ችግር ሊኖር ይችላል:: የተማሪ ብዛትም ራሱ አንድ ነገር (ችግር) ነው:: (ከዚህም የተነሳ) አንዳንዶቹ በሆነ ጊዜ ት/ቤት ማድረስ ላይ፤ ት/ቤት ሄደው የሚፈለገውን ልምድ መቅሰም ላይ፣ የኛ አስተማሪዎች (የኮሌጁ) እነዚህን ተማሪዎች ተከታትሎ feedback መስጠቱ ላይ፣ የት/ቤት አስተማሪዎች feedback መስጠታቸው ላይ ችግር ይኖራል::*

*(በአሁኑም በኩል) ከፕራክቲከም አራት (IV) ወይም pract 312 ላይ ተማሪዎች ማስተማር ያለባቸው ለ6 ሳምንት ነው:: 1 ወር ከሁለት ሳምንት ማለት ነው:: (ይሁን እንጂ) ከሌሎች የክልሉ ኮሌጆች ጋር ባደረግነው ስምምነት Maximum 1 ወር ብቻ እንዲያስተምሩ ተወስኗል:: (ይህ ደግሞ እንደገና) በኮሌጁ ውስጥ ወደ 3 ሳምንት ነው የወረደው (የተቀነሰው)::*

*(ተማሪዎች) መጀመሪያ ሲመደቡ ራሱ ባለቀ ትምህርት ላይ የተመደቡ ተማሪዎችም ነበሩ። (ይሁንና) ከነዚህም የተወሰኑትን (እንደገና) ወደ ሌላ ቦታ መድበናቸዋል። የተቀሩት ግን ያለፈውን (ያለቀውን) ትምህርት revise አድርገው እንዲሰሩትም አድርገናል።*

ከላይ የቀረበው የኮሌጁ የፕራክቲከም ክፍል ኃላፊ ንግግር የት/ቤት መምህራንና ተማሪ አስተማሪዎች ቀደም ሲል የሰጡትን ምላሽ እውነትነት ያረጋግጣል። በአንፃሩ ደግሞ የኮሌጁ መምህራን የሰጡትን ምላሽ የሚያፈርስ ነው። ኮሌጁን ወክሎ አጠቃላዩን የፕራክቲከም መርሃ ግብር የሚንቀሳቀሰው ግለሰብ እንደገለፀው፣ በዚህ ረገድ ኮሌጁ በፕራክቲከሙ ሂደት ተገቢውን እገዛ ድጋፍ ለተማሪዎች አላደረገም። ተማሪ አስተማሪዎቹ ለፕራክቲከም ወደ ት/ቤቶች ሲሰማሩ በመሰናክሎች ውስጥ ሆነው ነው። ት/ቤቶች ችግር ሊፈጥሩባቸው ይችላሉ፤ ከበዛታቸው የተነሳ በአንድ ጊዜ ት/ቤት የሚያደርሳቸው ትራንስፖርት የለም (ስለዚህ በሰዓቱ ት/ቤት ላይደርሱ ይችላሉ)፤ አጥኚው ለዚህ ጥናት በቦታው በተገኘበት ወቅት ከ2000 ለሚበልጡ ተማሪዎች አንድ አውቶቡስና አንድ መለስተኛ አውቶቡስ ብቻ ነበር ኮሌጁ የነበረው። በዚህ ሁኔታ ተማሪዎቹ ወደ ት/ቤቶቹ መድረስ ቢችሉም እንኳን ተከታትሎ ተገቢውን ምጋቤ ምላሽ የሚሰጣቸው መምህር ላያገኙ ይችላሉ። ይህም ሆኖ በአጠቃላይ ለ6 ሳምንት ልምምድ ማድረግ የሚጠበቅባቸው ቢሆንም፣ የተለማመዱት ግን ለ3 ሳምንት ብቻ ነው። ሦስቱን ሳምንት እንኳን በአግባቡ የሚለማመዱበት አመቺ ሁኔታ ያላገኙም አሉ። ከዚህም የተነሳ የት/ቤቱ ተማሪዎች ቀደም ሲል በመምህሮቻቸው ተምረው ያጠናቀቁትን ትምህርት እየከለሱ ነው የተለማመዱት። ስለዚህ፡ ተማሪዎቹ ከፕራክቲከሙ መርሃ ግብር ተገቢውን ልምምድ ቀስመዋል? ለመርሃ ግብሩ የተዘጋጀው የጊዜ ሰሌዳስ ምን ያህል ተገቢ ነው? የተመደቡበት ሁኔታ (ት/ቤት) የሚፈለገውን ልምድ ለመቅሰም ምን ያህል ምቹ ነው? ለሚሉት ጉዳዮች ኮሌጁ ተገቢውን ምላሽ አልሰጠም ብሎ መናገር ይቻላል። በማስከተል ደግሞ አስፈላጊ የሆነ የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎችና ቁሶችን በማቅረብ በኩል ኮሌጁ ምን እንደሠራ የሚያመለክቱ መረጃዎችን እንይ።

ሰንጠረዥ 19፡- ለፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት አስፈላጊ የሆኑ የማስተማሪያ መማሪያዎችንና ቅፆችን ኮሌጁ ማዘጋጀቱን በተመለከተ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የኮሌጅ መምህራን፣ የት/ቤት መምህራንና የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ

| | ዝርዝር መጠይቆች | በጣም እስማማለሁ (5) | እስማማለሁ (4) | ድምር | በመጠኑ እስማማለሁ (3) | አልስማማም (2) | ጨርሶ አልስማማም (1) | ድምር | ያልተመለሰ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የኮሌጅ መምህራን ምላሽ | አስፈላጊ የሆኑ የማስተማሪያ መማሪያዎች (የመማሪያ መፅሐፍትና የመምህር መምሪያ (teacher's guide) ለተማሪዎች ቀርበዋል | 2 | 3 | 5 (45.4%) | 4 (36.4%) | 1 | 1 | 2 (18.2%) | - |
| | ለተማሪዎች ምልከታና ግምገማ የሚውል የመመዘኛ ቅፅ ተዘጋጅቷል | 7 | 2 | 9 (81.8%) | 1 (9.1%) | 1 | - | 1 (9.1%) | - |
| የት/ቤት መምህራን ምላሽ | አስፈላጊ የሆኑ የማስተማሪያ መማሪያዎች (የመማሪያ መፅሐፍትና የመምህር መምሪያ (teacher's guide) ቀርበዋል | 1 | 6 | 7 (41.2%) | 4 (23.5%) | 4 | 2 | 6 (35.3%) | - |
| | ለተማሪዎች ምልከታና ግምገማ የሚውል የመመዘኛ ቅፅ ተዘጋጅቷል | 7 | 9 | 16 (94.1%) | - | 1 | - | 1 (5.9%) | - |
| የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ | አስፈላጊ የሆኑ የማስተማሪያ መማሪያዎች (የመማሪያ መፅሐፍትና የመምህር መምሪያ (teacher's guide) ቀርበዋል | 4 | 11 | 15 (15%) | 21 (21%) | 29 | 34 | 63 (63%) | 1 (1%) |
| | ለተማሪዎች ምልከታና ግምገማ የሚውል የመመዘኛ ቅፅ ተዘጋጅቷል | 40 | 22 | 62 (62%) | 10 (10%) | 11 | 14 | 25 (25%) | 3 (3%) |

ኮሌጁ ለፕራክቲከም የማስተማር ልምምዱ ሂደት የሚያስፈልጉ የማስተማሪያ መማሪያዎችንና ቅፆችን ማዘጋጀቱን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ የተሰጡት ምላሾች ከሞላ ጎደል ወጥነት ይታይባቸዋል፡፡ ኮሌጁ አስፈላጊ የሆኑ የመማሪያ መፅሐፍትን፣ የመምህር መምሪያና ሌሎች አጋዥ የማስተማሪያ መማሪያዎችን ለተማሪ አስተማሪዎች ማቅረቡን በተመለከተ ለቀረበው ጥያቄ የኮሌጅ መምህራን 45.4% ብቻ አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ የት/ቤት መምህራን ደግሞ ከ35.3% አሉታዊ ምላሽ ጋር 41.2% ብቻ አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ፤ ተማሪ አስተማሪዎቹ ግን 63% አሉታዊና 75% አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም መረዳት

የሚቻለው ምንም እንኳን በሦስቱም በኩል የተለያየ ምለሽ ቢሰጥም አንዳቸውም ግን (ከአሉታዊ ምላሻቸው ጋር ሲነፃፀር) ከፍተኛ ሊባል የሚችል አዎንታዊ ምላሽ አልሰጡም:: በተለይ የት/ቤት መምህራን 35.3% አሉታዊ፣ ተማሪ አስተማሪዎች ደግሞ 63% አሉታዊ የሆነ ምላሽ ሰጥተዋል። አጥኚው በቦታው ተገኝቶ ያደረገው ምልከታም ይህንኑ አሉታዊ ጎኑን የሚያጠናክር ሆኖ አግኝቶታል። ስለሆነም ኮሌጁ ለፕራክቲከም የማስተማር ልምምዱ ሂደት አስፈላጊ የሆኑ የማስተማሪያ መማሪያዎችንና መፅሐፎችን ለተማሪ አስተማሪዎች አቅርቧል ለማለት አይቻልም። በአንፃሩ ግን በፕራክቲከሙ ሂደት የሚያስፈልጉ የተለያዩ የምልከታና የግምገማ ቅፆችን በማዘጋጀትም ሆነ በማቅረብ በኩል ኮሌጁ ከፍተኛ የሆነ ሥራ መስራቱን የተሰጡት ምላሾች ያመለክታሉ። ይህን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ የኮሌጅ መምህራን 81.8%፣ የት/ቤት መምህራን ደግሞ 94.1%፣ እንዲሁም ተማሪ አስተማሪዎች 62% አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ምናልባትም ኮሌጁ በፕራክቲከም የማስተማር ልምምዱ ሂደት በተገቢው መንገድ ማከናወን የቻለው በቸኛው ተግባር ቢኖር ይኼ ነው ለማለት ይቻላል:: በማስከተል ደግሞ ኮሌጁ ለተማሪ አስተማሪዎች እገዛ የሚሰጡ መምህራንን በመመደብ እና ክትትል በማድረግ በኩል ያከናወነውን እንመልከት።

ሰንጠረዥ 20። በፕራክቲከም የማስተማር ልምምዱ ሂደት ኮሌጁ ለተማሪዎች ተገቢውን እገዛ የሚሰጥ መምህር መመደቡን፣ መምህራኑና ት/ቤቶቹ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን መከታተሉን በተመለከተ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የኮሌጅ መምህራን፣ የት/ቤት መምህራንና የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ

| | ዝርዝር መጠይቆች | በጣም እስማማለሁ (5) | እስማማለሁ (4) | ድምር | በመጠኑ እስማማለሁ (3) | አልስማማም (2) | ጨርሶ አልስማማም (1) | ድምር | ያልተመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የኮሌጅ መምህራን ምላሽ | ለተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ምክር የሚሰጥ መምህር ተመድቧል | 4 | 2 | 6 (54.5%) | 2 (18.2%) | 1 | 2 | 3 (27.3%) | - |
| | መምህራን አስፈላጊውን እገዛ ለተማሪዎች መስጠታቸውን ክትትል ተደርጓል | 1 | 5 | 6 (54.5%) | 3 (27.3%) | 2 | - | 2 (18.2%) | - |
| | ተባባሪ ት/ቤቶች ተግባራቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን ክትትል ተደርጓል | 1 | 5 | 6 (54.5%) | 3 (27.3%) | 1 | 1 | 2 (18.2%) | - |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የተባባሪ ት/ቤት መምህራን ምላሽ | ለተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛና ምክር የሚሰጥ መምህር ተመድቧል | 5 | 3 | 8 (47.1%) | 3 (17.6%) | 4 | 2 | 6 (35.3%) | - |
| | መምህራን አስፈላጊውን እገዛ ለተማሪዎች መስጠታቸውን ክትትል ተደርጓል | 3 | 6 | 9 (52.9%) | 3 (17.6%) | 5 | - | 5 (29.4%) | - |
| | ተባባሪ ት/ቤቶች ተገቢውን ድጋፍ መስጠታቸውን ክትትል ተደርጓል | 4 | 5 | 9 (52.9%) | 2 (11.8%) | 3 | 2 | 5 (29.4%) | 1 (5.9%) |
| የተግባር ልምምድ ተማሪዎች ምላሽ | ለተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛና ምክር የሚሰጥ መምህር ተመድቧል | 14 | 12 | 26 (26%) | 28 (28%) | 21 | 25 | 46 (46%) | - |
| | መምህራን አስፈላጊውን እገዛ ለተማሪዎች መስጠታቸውን ክትትል ተደርጓል | 13 | 10 | 23 (23%) | 27 (27%) | 30 | 18 | 48 (48%) | 2 (2%) |
| | ተባባሪ ት/ቤቶች ተገቢውን ድጋፍ መስጠታቸውን ክትትል ተደርጓል | 11 | 20 | 31 (3%) | 26 (26%) | 26 | 11 | 37 (37%) | 6 (6%) |

በፕራክቲከም የማስተማር ልምምዱ ሂደት በኮሌጁ በኩል ለተማሪዎች ተገቢውን እገዛና ምክር የሚሰጥ መምህር መመደቡን፣ መምህራኑ አስፈላጊውን እገዛ ለተማሪዎች ማድረጋቸውን መከታተሉን፣ እና ት/ቤቶችም ተግባራቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን ክትትል ማድረጉን አስመልክቶ የተሰጡትን ምላሾች በሁለት ጎራ መለየት ይቻላል:: በኮሌጁና በት/ቤት መምህራን በኩል የተሰጡት ምላሾች በወጥነት ሊባል በሚችል መልኩ አዎንታዊ ናቸው:: ስለዚህ እንደመምህራኑ እምነት ከሆነ ኮሌጁ መምህራንን በመመደብና በመከታተል፣ እንዲሁም ተባባሪ ት/ቤቶችን በመከታተል በኩል ኃላፊነቱን በአግባቡ ተወጥቷል ለማለት ይቻላል:: ይሁንና ከፍ ሲል የተመለከተው የተግባሪ አስተማሪዎቹ ምላሽ ደግሞ ከዚህ ከመምህራኑ አቋም በተቃራኒ የቆመ ነው:: ተማሪዎቹ ይህን አስመልክቶ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች በወጥነት ዝቅተኛ የሆነ አዎንታዊና ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: ስለዚህ ይህን የተራራቀ የአቋም ልዩነት ወደ አንድ አቅጣጫ ለማምጣት ያስቻለን ዘንድ በቃለ መጠይቅ ከኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊ የተገኘውን መረጃ እንይ:: የፕራክቲከም ኃላፊው በተለይ ለተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛና ምክር የሚሰጥ መምህር በመመደብና ክትትል በማድረግ በኩል ያለውን ሁኔታ እንዲገልፁ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ የሚከተለውን ይመስላል::

> *በት/ቤት በኩል ተማሪዎች ሄደው ከአንድ አስተማሪ Subject ይቀበላሉ:: ያ ራሱ ነው የሚከታተላቸው:: ሌላ ምደባ አያስፈልግም:: በኮሌጁ በኩል ከተቻለ related በሆነ subject እንመድባለን:: በዚህ መንገድ ግን አስተማሪዎች ያጥሩናል:: በዚህን ጊዜ ግን እንደተገኘው እንመድባለን::*

*(መምህራንን) በተቻለ መጠን እንከታተላለን። (ነገር ግን) ይህ ሥራ... እንዳልኩህ የኮሚቴ ሥራ ነው ብዬሃለሁ። የኮሚቴ ሥራ ማለት እንዳንዴ ለይስሙላ ብቻም ይመስላል። ሁሉም የስትሪም ኃላፊዎች በዚህ ሥራ ላይ ይሳተፋሉ (በኮሚቴነት)። (ግን) ኮሚቴው ለስምነው። አንዳንዴ ሲጠሩ ብቻ መጥተው እንዲህ እንዲህ ይሁን ይላሉ እንጂ (ምንም አይሠሩም)። እኔ ብቻዬን ይሄን ሁሉ ት/ቤት (11) እቆጣጠራለሁ ማለት ትንሽ ውሸት ያስመስላል። ስለዚህ (መምህራንን) መቆጣጠር አስቸጋሪ ነው። ሁሉንም ነገር የምሠራው እኔ ብቻ ነኝ። ግንም አጠገቤ የለም!*

ከፍ ሲል የቀረበው የኮሌጁ የፕራክቲከም ክፍል ኃላፊ ንግግር፣ የተማሪ አስተማሪዎቹን ምላሽ ያጠናክራ፤ የኮሌጆና የት/ቤት መምህራንን ምላሽ ደግሞ የተቃረነ ነው። ምክንያቱም ተማሪ አስተማሪዎቹ እንዳሉትና የፕራክቲከሙ ኃላፊም እንዳረጋገጡት፣ በዚህ ረገድ ኮሌጁ ለተማሪዎቹ ተገቢውን ነገር አላደረገላቸውም። ለተማሪዎቹ አስፈላጊውን (ሱፐርቫይዘራዊ) እገዛ የሚሰጥ መምህር ተመድቧል ለማለት የሚያስችል ሁኔታ አይታይም። የኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊ እንደሚገልፁት፣ በተለይ ለተማሪ አስተማሪዎች በኮሌጁ በኩል የሚመደብላቸው ሱፐርቫይዘር ተገቢውን ድጋፍ መስጠት ይችላል ወይስ አይችልም ተብሎ አይደለም። ሌላው ቀርቶ ተማሪው በሚያስተምርበት ወይም በሚሰለጥንበት የትምህርት ዓይነት የሰለጠነ ሱፐርቫይዘር እንኳን የማግኘት ዕድላቸው አነስተኛ ነው። ኮሌጁ ካለበት ከፍተኛ የመምህራን እጥረት የተነሳ ለተማሪዎቹ ምን ያህል ብቁ የሆኑ ሱፐርቫይዘሮች ተመድበዋል የሚለው ጉዳይ ከናካቴው የሚታሰብ አይደለም። ስለሆነም እንደተገኘው ይመደባል። አጥኚው ለዚህ ሥራ በኮሌጁ በተገኘበት ወቅትም የጂኦግራፊና የሲቪክስ (በፖለቲካል ሳይንስ የተመረቁ) መምህራን ፤እንዲሁም አንድ የዕደ ጥበብ ባለሙያ (ቴክኒሺያን) መደበኛ የቋንቋ ስትሪም ተማሪ አስተማሪዎችን ሱፐርቫይዝ እንዲያደርጉ ተመድበው ተመልክቷል። እንደሚታወቀው የመምህራን ስልጠና ያለ ፕራክቲከም/ ማስተማር ልምምድ፤ የማስተማር ልምምድ ደግሞ ያለ ሱፐርቪዥን ዋጋ የለውም (Dukin 1987 Walters 1960 Gebhard 1990 Richards and Nunan 1990)፤ «ሱፐርቪዥን የፈለገውን ያህል የተደራጀ ቢሆንም እንኳን ፤ በብቁ እና ኃላፊነታቸውን በተገቢው መንገድ መወጣት በሚችሉ ባለሙያዎች ካልተከናወነ እውነተኞቹን መምህራን ሊያፈራ አቅም የለውም» (Sirvastava and Bose 1978)። ከዚህ አንፃር በሮቤ መምህራን ኮሌጅ ያለውን ሁኔታ ስንመለከት በጣም አሳሳቢ ይመስላል። በዚህ አካሄድ ኮሌጁ ምን ዓይነት (የቋንቋ) መምህራንን ለማፍራት እንደሚጠብቅ መገመቱም ይከብዳል። በኮሌጁ የሚከናወነው አጠቃላዩ የፕራክቲከም/ የማስተማር ልምምድ አቀራረብ (ሞዴል) ባህሪም ቢሆን «እንዲህ ነው» ብሎ ለማስቀመጥ የሚያስቸግር ነው። ኳሉት ሦስት ዋና ዋና የማስተማር ልምምድ ሞዴሎች (ኮረጃ፣ የልምምድ ወይም ሳይንሳዊ) መካከል በአንዱም ውስጥ ሊመደብ የሚችል አይደለም። በአጠቃላይ ኮሌጁ ለተማሪ አስተማሪዎችም ሆነ ለፕራክቲከም መርሃ ግብሩ ግብ መምታት ያደረገው ጥረት በጣም አነስተኛ ሆኖ ተገኝቷል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ አሰልጥኖ ለማስመረቅ የተዘጋጀው መምህራን ብቃትም አጠያያቂ ነው።

## 4.5 የተባባሪ ት/ቤቶች የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

በጥናቱ ለፕራክቲከም የማስተማር ልምምዱ ሂደት መሳካት ከሮቤ መምህራን ኮሌጅ ጋር በትብብር የሚሠሩት ት/ቤቶች ምን ያህል የበኩላቸውን ሥራ እየተወጡ ነው? የሚለውን ለመመልከት ተሞክሯል። ለዚህም የሚረዱ መረጃዎችን በፅሑፍ መጠይቅና በቃለመጠይቅ አማካኝነት ከኮሌጅ መምህራን፣ ከት/ቤት መምህራን፣ ከተማሪ አስተማሪዎች፣ ከት/ቤት ርዕሳነ መምህራንና ከኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊ ለማሰባሰብ ተችሏል። እነዚህንም ቀጥለን ጎን ለጎን እያነፃፀርን እንመለከታለን። በቅድሚያም ተባባሪ ት/ቤቶች ተገቢውን ልምድ ለመቅሰም የሚያስችል የጊዜ ሰሌዳ ለተማሪ አስተማሪዎች ማዘጋጀታቸውን በተመለከተ የተጠናቀረውን እንይ።

ሰንጠረዥ 21፡ ተባባሪ ት/ቤቶች ተገቢውን ልምድ ከት/ቤት ለመቅሰም የሚያስችል የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀታቸውን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ የኮሌጅ መምህራን፣ የት/ቤት መምህራንና የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ

| | ዝርዝር መጠይቆች | በጣም እስማማለሁ (5) | እስማማለሁ (4) | ድምር | በመጠኑ እስማማለሁ (3) | አልስማማም (2) | ጨርሶ አልስማማም (1) | ድምር | ያልተመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የኮሌጅ መምህራን ምላሽ | ተገቢውን ልምድ ከት/ቤት መቅሰም የሚያስችል የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቷል | - | 6 | 6 (54.5%) | 1 (9.1%) | 4 | - | 4 (36.4%) | - |
| የት/ቤት መምህራን ምላሽ | ተገቢውን ልምድ ከት/ቤት ለመቅሰም የሚያስችል የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቷል | 6 | 3 | 9 (52.9%) | 2 (11.8%) | 5 | 1 | 6 (35.3%) | - |
| የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ | ተገቢውን ልምድ ከት/ቤት ለመቅሰም የሚያስችል የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቷል | 12 | 28 | 40 (40%) | 33 (33%) | 18 | 8 | 26 (26%) | 1 (1%) |

ተባባሪ ት/ቤቶች ተማሪ አስተማሪዎችን ተገቢው ልምድ ከት/ቤት ለመቅሰም የሚያስችል የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቷል ወይ የሚለውን በተመለከተ ከፍ ሲል የተሰጠው ምላሽ በአመዛኙ አዎንታዊነት ይንፀባረቃል። በኮሌጅ መምህራን፣ በት/ቤት መምህራንና በተማሪ አስተማሪዎች በኩል ይህን አስመልክቶ ለቀረላቸው ጥያቄ ከሰጧቸው ምላሾች ውስጥ ከፍተኛውን ቦታ የሚያዘው አዎንታዊው ምላሽ ነው። ት/ቤቶች ለመርሃ ግብሩ ሂደት አመቺ/ተገቢ የሆነ የጊዜ

ሰሌዳ ማዘጋጀታቸውን በተመለከተ የኮሌጅ መምህራን 54.5%፣ የት/ቤት መምህራን 52%፣ ተማሪ አስተማሪዎቹ ደግሞ 40% አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ስለዚህ በነዚህ ምላሾች መሠረት ተባባሪ ት/ቤቶቹ ተማሪ አስተማሪዎች ተገቢውን ልምድ ከት/ቤት ለመቅሰም የሚያስችላቸው የጊዜ ሰሌዳ አዘጋጅተዋል ማለት ነው፡፡ ነገር ግን በቃለ መጠይቅ ከኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊና ከት/ቤቶቹ ርዕሰን መምህራን የተገኘው መረጃ፤ ይህንን ከፍ ሲል የቀረበውን በእጅጉ የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከሁሉም የተባባሪ ት/ቤቶች ርዕሳን መምህራንና ከኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊ የተገኘው መረጃ፣ እንዲሁም አጥኚው በቦታው በነበረበት ወቅት ለመመልከት እንደቻለው ከሆነ፤ ለፕራክቲከም መርሃ ግብሩ የሚሆን የጊዜ ሰሌዳ በማዘጋጀት በኩል ተባባሪ ት/ቤቶቹ ምንም ተሳትፎ የላቸውም የሚያስብል ነው፡፡ የጊዜ ሰሌዳውን ኮሌጁ ሙሉ ለሙሉ ብቻውን ነው የሚያዘጋጀው፤ በዚህ ረገድ ከት/ቤቶቹ ጋር የሚደረግ ውይይትም ሆነ ምክክር የለም፡፡ በኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊ አማካይነት የየት/ቤቶቹን የክፍለ ጊዜና የክፍል ብዛት የሚመለከት መረጃ ይሰባሰባል፡ ይህም ከፕራክቲከሙ መርሃ ግብር መጀመር ከሳምንት በፊት የሚከናወን ነው፡፡ ከዚያም ኮሌጁ በሰበሰበው መረጃ መሠረት ተማሪ አስተማሪዎቹን በቀጥታ ወደ ት/ቤቶቹ (ክፍሎቹ) ይመድባል፡፡ ከዚህ ውጪ ከት/ቤቶቹ ጋር የፕራክቲከም መርሃ ግብሩን የጊዜ ሰሌዳ በማዘጋጀት ሂደት ላይ ኮሌጁ የሚያደርገው ምክክርም ሆነ ውይይት የለም፡፡ ከዚህም የተነሳ በፕራክቲከሙ ሂደት ቀጥሎ የተመለከተው ዓይነት ከፍተኛ የሆነ ችግር ሲያጋጥም ችሏል፡፡

> *(ተማሪዎቹ) መጀመሪያ ሲመደቡ ፊሱ ባለቀ ትምህርት ላይ የተመደቡ ነበሩ፤ (ፊሁ ገና) ከዚህም የተወሰኑትን እንደገና ወደ ሌላ ቦታ መድበናቸዋል፡፡ የተቀሩት ግን ሲለፉውን (ያለቀውን) ትምህርት revises አድርገው እንዲያስተምሩ አድርገናል፡፡*

ከፍ ሲል ከተመለከተው የኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊ ንግግር መረዳት እንደሚቻለው፤ በኮሌጁና በት/ቤቶቹ መካከል በቅርበት አብሮ መስራትና መናበብ ባለመኖሩ ተማሪ አስተማሪዎች ለከፍተኛ ችግር መጋለጣቸውን ነው፡፡ በፕራክቲከም መርሃ ግብሩ ሂደት ት/ቤቶቹ እንዲሳተፉ ባለመደረጋቸው፤ ኮሌጁ በት/ቤቶቹ በተጨባጭ ያለውን ሁኔታ ለማወቅ አልቻለም፡፡ ከዚህም የተነሳ ተማሪ አስተማሪዎችን በተጠናቀቀ ትምህርት ላይ ሊመድብ ችሏል፡፡ በዚህ ሁኔታ ደግሞ ተገቢውን የማስተማር ልምድ ለመቅሰም የሚያስችል የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቷል ለማለት አያስደፍርም፡፡ ስለተባባሪ ት/ቤቶቹ የጊዜ ሰሌዳ ዝግጅት ይህን ካልን፣ በማስከተል ደግሞ ለተማሪ አስተማሪዎች ተገቢውን ሱፐርቫይዘራዊ እገዛ የሚሰጥ መምህር በመመደብና መምህራኑን በመከታተል በኩል ያከናወኑትን ተግባር እንመልከት፡፡

ሰንጠረዥ 22፡- በፕራክቲከም ሂደት ለተማሪ አስተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ የሚሰጥ መምህር በመመደብና ክትትል በማድረግ በኩል ተባባሪ ት/ቤቶች ያደረጉትን በተመለከተ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የኮሌጅ መምህራን፣ የት/ቤት መምህራንና የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ

| | ዝርዝር መጠይቆች | በጣም እስማማለሁ (5) | እስማማለሁ (4) | ድምር | በመጠኑ እስማማለሁ (3) | አልስማማም (2) | ጨርሶ አልስማማም (1) | ድምር | ያልተመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የኮሌጅ መምህራን ምላሽ | አስፈላጊውን እገዛ የሚሰጥ መምህር ተመድቧል | 2 | 3 | 5 (45.4%) | 2 (18.2%) | 3 | - | 3 (27.3%) | 1 (9.1%) |
| | መምህራን አስፈላጊውን እገዛ ተማሪዎች መስጠታቸውን ክትትል ተደርጓል | - | 6 | 6 (54.5%) | 2 (18.2%) | 3 | - | 3 (27.3%) | - |
| የት/ቤት መምህራን ምላሽ | አስፈላጊውን እገዛ የሚሰጥ መምህር ተመድቧል | 4 | 1 | 5 (29.4%) | 6 (35.3%) | 3 | 3 | 6 (35.3%) | - |
| | መምህራን አስፈላጊውን እገዛ ለተማሪዎች መስጠታቸውን ክትትል ተደርጓል | 1 | 5 | 6 (35.3%) | 6 (35.3%) | 3 | 1 | 4 (23.5%) | 1 (5.9%) |
| የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ | አስፈላጊውን እገዛ የሚሰጥ መምህር ተመድቧል | 18 | 21 | 39 (39%) | 31 (31%) | 15 | 15 | 30 (30%) | - |
| | መምህራን አስፈላጊውን እገዛ ለተማሪዎች መስጠታቸውን ክትትል ተደርጓል | 8 | 25 | 33 (33%) | 30 (30%) | 22 | 14 | 36 (36%) | 1 (1%) |

ከላይ ሲል ስለተባባሪ ት/ቤቶች የመምህራን ምደባና ክትትል አስመልክቶ ለቀረቡት ጥያቄዎች የተሰጡት ምላሾች ወጥ የሆነ ሁኔታ አይስተዋልባቸውም:: የኮሌጅ መምህራን የሰጡት ምላሽ አዎንታዊነት ሲያመዝንበት፣ የት/ቤት መምህራኑና የተማሪዎቹ ደግሞ ወደ አዎንታዊም ሆነ ወደ አሉታዊ የወገነ አይደለም:: የኮሌጅ መምህራን ተባባሪ ት/ቤቶች ለተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ የሚሰጥ መምህር መመደባቸውን በተመለከተ 45.4%፣ መምህራን ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን የተከታተሉ መሆናቸውን በተመለከተ

ደግሞ 54.5% አዎንታዊ የሆነ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህም ከሌሎቹ ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ ምላሽ ነው፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ት/ቤቶች ለተማሪዎች መምህራንን መመደባቸውን በተመለከተ ለቀረበው ጥያቄ የት/ቤት መምህራን 29.4% አዎንታዊ፣ 35.3% በመጠኑ እስማማለሁና 35.3% አሉታዊ ምላሽ ሲሰጡ፤ ተማሪ አስተማሪዎች ደግሞ 39% አዎንታዊ፤ 31% በመጠኑ እስማማለሁና 30% አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ት/ቤቶቹ ክትትል ማድረጋቸውን በተመለከተ ለቀረበው ጥያቄ የት/ቤት መምህራን 35.3% አዎንታዊ፣ 35.3% በመጠኑ እስማማለሁና 23.5% አሉታዊ ምላሽ ሲሰጡ፤ ተማሪ አስተማሪዎች በበኩላቸው 33% አዎንታዊ፣ 30% በመጠኑ እስማማለሁና 36% አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በት/ቤት መምህራንና በተማሪ አስተማሪዎቹ የተሰጡት አዎንታዊ፣ በመጠኑ እስማማለሁና አሉታዊ ምላሾች ተቀራራቢነት ያላቸው ናቸው፡፡ ይህም ተባባሪ ት/ቤቶቹ ለተማሪ አስተማሪዎች ተገቢውን ሙያዊ እገዛ የሚሰጥ መምህር መመደባቸውንና መምህራኑም ሥራቸውን በወጉ ማከናወናቸውን ቢያረጋግጡም፣ ነገር ግን በክትትሉ ላይ እርግጠኛ የሆነ አቋም ለመያዝ እንደተቸገሩ ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ ቀደም ሲል ስለት/ቤት መምህራን የሥራ ድርሻና ኃላፊነት በተመለከትንበት ወቅት ያገኘነውን መረጃ እና፤ ከኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊ ጋር የተደረገውን ቃለመጠይቅ ስንመረምር የት/ቤት መምህራንና ተማሪ አስተማሪዎቹ ለምን እርግጠኛ ለመሆን እንደተቸገሩ ለመገመት ይቸግራል፡፡

የት/ቤት መምህራን በፕራክቲከሙ ሂደት ለተማሪ አስተማሪዎች ያደረጉትን እገዛ በተመለከተ ቀደም ባለው ክፍላችን ያጠናቀርናቸው መረጃዎች እንዳመለከቱት ከሆነ፤ መምህራኑ ምናልባትም ከኮሌጅ አቻዎቻቸውም የበለጠ እገዛ ለተማሪዎች አድርገዋል፡፡ የኮሌጅ መምህራን፣ የት/ቤት መምህራንና ተማሪ አስተማሪዎቹ በፅሑፍ መጠይቃቸው ላይ የሰጡት ምላሽም ሆነ፤ የኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊ በቃለ መጠይቃቸው የሰጡት ምላሽ በወጥነት ያመለከተው የት/ቤት መምህራኑ ሥራቸውን በአግባቡ ማከናወናቸውን ነው፡፡ ይህም በተባባሪ ት/ቤቶች በኩል ለተማሪ አስተማሪዎች አስፈላጊውን ሱፐርቫይዘራዊ ድጋፍ የሚሰጥ መምህር ለመመደቡ በቂ ማስረጃ ይሆናል ይህ ማለት ግን በት/ቤቶች በኩል መምህራኑ ሥራቸውን በአግባቡ እንዲያከናውኑ ክትትል ተደርጎባቸዋል ማለት ላይሆን ይችላል፡፡ ከት/ቤቶቹ ርዕሳነ መምህራን ጋር የተካሄደው ቃለመጠይቅም ይህን ሁኔታ በተጨባጭ ሊመልስ የሚያስችል መረጃ አልሰጠም፡፡ ምናልባት የት/ቤት መምህራን ከት/ቤታቸው ያን ያህል ሊታይ የሚችል ክትትልና ቁጥጥር ሳይደረግባቸው ሥራቸውን አንፃራዊ በሆነ መልኩ በተገቢው መንገድ ያከናወኑትም፤ ተማሪ አስተማሪዎቹ ወደ ት/ቤት ሲመጡ የነሱን የሥራ ጫና ስለሚቀንሱላቸው ወይም ከማስተማሩ ተግባር ነፃ ስለሚሆኑ ይሆናል የሚል ግምት አጥኚው አለው፡፡ በአጠቃላይ ግን ከተለያየ አቅጣጫ የተጠናቀሩት መረጃዎች እንደሚያሳዩት ከሆነ በተባባሪ ት/ቤቶች በኩል ለተማሪ አስተማሪዎቹ አስፈላጊውን እገዛ የሚሰጡ መምህራን ተመድበዋል፤ (ክትትል ተደረገ አልተደረገም) ሥራቸውን በአግባቡ አከናውነዋል፡፡ ስለተባባሪ ት/ቤቶቹ የመምህራን ምደባና ክትትል ይህን ካልን፤

በማስከተል ደግሞ ት/ቤቶቹ ተማሪ አስተማሪዎች የሚፈለገውን ልምድ ከት/ቤት ለመቅሰም የሚችሉበት ምቹ ሁኔታ ምን ያህል እንዳመቻቹና ይህንንም ለማረጋገጥ ምን ያህል ክትትል እንዳደረጉ ቀጥለን እንመለከታለን።

ሰንጠረዥ 23፡- ተባባሪ ት/ቤቶች በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት ተማሪ አስተማሪዎች የሚፈለገውን ልምድ ከት/ቤት የሚቀስሙበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠራቸውንና ክትትል ማድረጋቸውን በተመለከተ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የኮሌጅ መምህራን፣ የት/ቤት መምህራንና የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ

| | ዝርዝር መጠይቆች | በጣም እስማማለሁ (5) | እስማማለሁ (4) | ድምር | በመጠኑ እስማማለሁ (3) | አልስማማም (2) | በጭራሽ አልስማማም (1) | ድምር | ያልተመለሰ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የኮሌጅ መምህራን ምላሽ | የሚፈለገውን ልምድ ከት/ቤት ለመቅሰም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል | - | 5 | 5 (45.4%) | 3 (27.3%) | 3 | - | 3 (27.3%) | - |
| | የሚፈለገውን ልምድ ከት/ቤት መቅሰማቸውን ለማረጋገጥ ክትትል ተደርጓል | - | 4 | 4 (36.4%) | 4 (36.4%) | 3 | - | 3 (27.2%) | - |
| የት/ቤት መምህራን ምላሽ | የሚፈለገውን ልምድ ከት/ቤት ለመቅሰም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል | 1 | 8 | 9 (52.9%) | 3 (17.7%) | 4 | 1 | 5 (29.4%) | - |
| | ተማሪዎች የሚፈለገውን ልምድ ከት/ቤት መቅሰማቸውን ለማረጋገጥ ክትትል ተደርጓል | - | 7 | 7 (41.2%) | 3 (17.7%) | 5 | 2 | 7 (41.2%) | - |
| የተማሪ አስተማሪዎች ምላሽ | የሚፈለገውን ልምድ ከት/ቤት ለመቅሰም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል | 9 | 26 | 35 (35%) | 35 (35%) | 16 | 14 | 30 (30%) | - |
| | ተማሪዎች የሚፈለገውን ልምድ ከት/ቤት መቅሰማቸውን ለማረጋገጥ ክትትል ተደርጓል | 8 | 28 | 36 (36%) | 33 (33%) | 20 | 10 | 30 (30%) | 1 (1%) |

ተባባሪ ት/ቤቶች ተማሪ አስተማሪዎች የሚፈለገውን ልምድ ከት/ቤት ለመስቀም የሚችሉበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠራቸውን እና የሚፈለገውን ልምድ መቅሰማቸውን ለማረጋገጥ ክትትል ማድረጋቸውን በተመለከተ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የተሰጡትን ምላሾች በሁለት

መመደብ ይቻላል፡፡ በኮሌጅ መምህራንና በት/ቤት መምህራኑ በኩል የተሰጡት ምላሾች ከሞላ ጎደል አዎንታዊ ናቸው፡፡ በመምህራኑ በኩል ከተሰጡት ምላሾች በዝቅተኛነት ሊጠቀስ የሚችል አዎንታዊ ምላሽ የተሰጠው፣ ተማሪ አስተማሪዎቹ የሚፈለገውን ልምድ ከት/ቤት መቅሰማቸውን ለመረጋገጥ ት/ቤቶቹ ክትትል ማድረጋቸውን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ ነው፡፡ በጥቅሉ ግን ከተማሪ አስተማሪዎቹ ጋር ሲስተያይ የመምህራኑ ምላሽ አዎንታዊ የሚባል ነው፡፡ በአንፃሩ ደግሞ የተማሪ አስተማሪዎቹ ምላሽ ከመምህሮቹ አነስ ያለ ነው፡፡ (ይህም ሆኖ ግን የተማሪዎቹ ምላሽ ከመምህራኑ ጋር ሲነፃፀር ነው እንጂ በራሱ ሲታይ አሉታዊ የሚባል አይደለም፡፡) በት/ቤቶቹ ምቹ ሁኔታ በእንደተፈጠረላቸው ለቀረበላቸው ጥያቄ 35% አዎንታዊ፣ 35% በመጠኑ እስማማለሁና 30% አሉታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ የሚፈለገውን ልምድ መቅሰማቸውን እንደተከታተሏቸው ለቀረበው ጥያቄ ደግሞ 36% አዎንታዊ፣ 33% በመጠኑ እስማማለሁና 30% አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ስለዚህ እንደ መምህራኑ እምነት ከሆነ ተባባሪ ት/ቤቶች የሚጠበቅባቸውን አከናውነዋል ለማለት ይቻላል፣ እንደተማሪ አስተማሪዎቹ ከሆነ ደግሞ አፍን ሞልቶ አዎንታዊ ወይም አሉታዊም ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡

ከፍ ሲል በፅሑፍ መጠይቅ የተጠናቀረው መረጃ ተባባሪ ት/ቤቶች የሚያስፈልገውን ልምድ ከት/ቤት ለመቅሰም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠራቸውንና ለዚህም እውንነት ክትትል እንደዳረጉ በርግጠኝነት ለመናገር አያስችልም፡፡ ጉዳዩን ይበልጥ ለማጣራትም በቃለመጠይቅ በፕራክቲከም ኃላፊውና በርዕሳነ መምህራኑ በኩል ያለውን ሁኔታ ለመፈተሽ ተሞክሯል፡፡ ይሁንና የርዕሳነ መምህራኑና የኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊ ሃሳብም እንዲሁ (እንደመምህራኑና እንደተማሪዎቹ ሁሉ) የማይጣጣምና ከአንድ ውሳኔ የሚያደርስ አይደለም፡፡ ይህንንም ለማሳየት ይረዳ ዘንድ፣ የአንድ የተባባሪ ት/ቤት መምህርንና የፕራክቲከም ኃላፊውን ሃሳብ ጎን ለጎን አያነፃፀርን እንመልከት፡፡

ከአሊ ቢራ ት/ቤት ርዕሰ መምህር ጋር በተደረገው ቃለ ምልልስ፣ «በት/ቤታችሁ ተማሪ አስተማሪዎች አስፈላጊውን የፕራክቲከም ተግባራት ማከናወን የሚያስችላቸው ምቹ ሁኔታ ምን ያህል ተፈጥሮላቸዋል?» ተብሉ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ፣

> *... አስፈላጊውን እገዛ ሁሉ እያደረግን ነው፡፡ ተማሪዎቹ ሲላኩልን በአግባቡ ተቀብለን መምህር እንመድብላቸዋለን፡፡ ክፍል ገብተው እንደኛው መምህራን፣ ተኩተዋቸው ያስተምራሉ፡፡ የኛ መምህራንም ይገመግማሉ (እነሱን)፡፡ ይህንንም በራሳችን መንገድ እንከታተላቸዋለን (መገምገማቸውን)፡፡...*

ይህ ከፍ ሲል የተቀነጨበው የአሊ ቢራ ት/ቤት ርዕሰ መምህር ሃሳብ፣ የሁሉም ርዕሰ መምህራን ሃሳብ ነው፡፡ ርዕሳነ መምህራኑ በጥቅሉ በተባባሪ ት/ቤቶች በኩል ምንም ያላደረጉት ድጋፍ አለመኖሩ ነው የሚገልፁት፡፡ ወይም በበኩላቸው ተገቢውን ሁሉ ለተማሪ አስተማሪዎች ማድረጋቸውን ነው የሚያምኑት፡፡ በኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊ በኩል ግን ይህ የርዕሳነ

መምህራን ሃሳብ ተቀባይነት ያለው አይመስልም:: የፕራክቲከም ኃላፊው ተባባሪ ት/ቤቶች ለፕራክቲከሙ ሂደት መሳካት የሚያደርጉት አጠቃላይ አስተዋፅኦ የጎላ አለመሆኑን ሲናገሩ *«አንድ የፕራክቲከም ኮሚቴ በየት/ቤቱ አለ (በኮሌጁ ካለው ሌላ):: ያ ግን ይህን ነገር ገብቶ ይሠራል የሚል ነገር የለም»* ይላሉ:: በኃላፊው አባባል፣ በየት/ቤቶቹ ያለው የፕራክቲከም ኮሚቴ ምንም የሚሠራው ነገር የለም:: ምክንያቱም «ይህን ነገር ገብቶ ይሠራል» (የሥራ ድርሻቸው ይኼ ነው) የሚል ነገር የለምና:: ስለዚህ በየት/ቤቶቹ የፕራክቲከም ኮሚቴ አለ፤ ግን ኮሚቴው ምን መሥራት እንዳለበት የተቀመጠለት የሥራ ድርሻ የለም፤ ከዚህም የተነሳ የሠራው ነገር የለም:: ከፍ ሲል ያየነው የአሲቢራ ት/ቤት ርዕሰ መምህር እንዳሉትም ተማሪዎቹ ሲመደቡ በቀጥታ ወደ የት/ቤቱ ኃላፊዎች አይደለም የሚላኩት:: በቀጥታ ወደ ተመደቡበት ክፍል ሄደው ነው ከመምህራኑ ትምህርቱን ተቀብለው የሚያስተምሩት:: ይህንንም ሁኔታ የፕራክቲከም ኃላፊው *«በት/ቤት በኩል ተማሪዎች ሄደው ከአንድ አስተማሪ Subject ይቀበላሉ:: ያ ራሱ ነው የሚገመግማቸው:: ሌላ ምደባ አያስፈልግም::»* በማለት ይገልፃሉ:: ስለዚህ ተማሪዎቹ ት/ቤት ሄደው አይደለም፤ ከዛ መምህር የሚመደብላቸው:: በዚህ ረገድ ግንኙነቱ ያለው በኮሌጁና በት/ቤቶቹ መካከል ሳይሆን በተማሪ አስተማሪዎቹ እና በትቤቶቹ መምህራን መካከል ነው ለማለት ይቻላል:: ከዚህም፣ በኮሌጁና በት/ቤቶቹ መካከል የጠበቀ ቅርርብ አለመኖሩን መረዳት ይቻላል::

ከፍ ሲል እንዳየነው ተባባሪ ት/ቤቶች ለተማሪ አስተማሪዎች ምቹ ሁኔታ በመፍጠርና ክትትል በማድረግ በኩል የሥራ ድርሻችንን በአግባቡ ተወተናል ብለው አፋቸውን ሞልተው መናገር በሚያስችላቸው ሁኔታ ላይ አይገኙም፤ ኮሌጁም ቢሆን ኃላፊነታቸውን በአግባቡ አልተወጡም ብሎ ት/ቤቶቹን ለመውቀስ የሚያችለውን ሥራ አልሠራም:: ቀደም ሲል በተለይ በተማሪ አስተማሪዎቹ በኩል የተሰጠው ምላሽም ሙሉ በሙሉ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ወደሚል ማጠቃለያ ያላዘነበለውም ለዚሁ ሳይሆን አይቀርም:: ተማሪ አስተማሪዎች በፅሑፍ መጠይቆቻቸው ላይ «ፕራክቲከምን በአግባቡ ለመተግበር ችግር የፈጠሩትን ጉዳዮች» ወይም «በአጠቃላይ ስለፕራክቲከም መርሃ ግብሩ ያላቸውን አስተያየት» እንዲገልፁ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ሁኔታውን የበለጠ ግልፅ ሊያደርግ ይችላል:: በዚህ ረገድ በርካታ ተማሪ አስተማሪዎች በተባባሪ ት/ቤቶች በኩል ችግር እንዳለ ገልፀዋል:: ይህንንም ከየተመደቡበት ት/ቤት አንድ አንድ ተማሪ በናሙናነት ወስዶ መመልከት ይቻላል::

1 በመደወላቡ ት/ቤት የተመደበ ተማሪ አስተማሪ የሰጠው አስተያየት፤

> *...እንቅፋት የሆነብን ነገር ቢኖር አንደኛና ዋንኛው እንቅፋት መጀመሪያ ፕራክቲከም ስንወጣ ኮሌጁ ለምንወጣበት ት/ቤት ደብዳቤም ሆነ ሌላ ነገር የደረሳቸው ነገር የለም:: ት/ቤቱ ስለፕራክቲከም የሚያውቀው ነገር የለም:: በዚህ ምክንያት ብዙ ቀን ተመላልሰን ጠይቀን ደብዳቤ አልደረሰንም፤ የምናውቀው ነገር የለም ብለው ተንገላተናል...*

2. ቢጋሰማ ት/ቤት የተመደበ ተማሪ አስተማሪ የሰጠው አስተያየት፤

...በውግንበት ት/ቤት ስንሄድ ከኮሌጅ የደረሰን ነገር የለም በማለት ሁለት ጊዜ ተባረናል። ለኛም ምንም አንዛና አስተያየት ነገር የሚሰጠን የለም።

3. በአሊ ቢራ ት/ቤት የተመደበ ተማሪ አስተማሪ የሰጠው አስተያየት፤

በአጠቃላይ የፕራክቲከም አተገባበር ጉድለት የሚታይበት ነው። ለምሳሌ ደብዳቤው ሳይፃፍ ተማሪዎችን አስቀድሞ ወደ ት/ቤቶች መላክ። በዚህ ምክንያት ት/ቤቶቹ ተማሪዎችን አንቀበልም በማለት ተማሪዎች /ሰልጣኞች/ መጉላላት።

4. በቶሉ ዲምቱ ት/ቤት የተመደበ ተማሪ አስተማሪ የሰጠው አስተያየት፤

ሳይታሰብበት ነው ዝም ብሎ ያለምንም orientation የምንላከው። እና ወደ ት/ቤቶች ከመውጣታችን በፊት ኮሌጁ ምንም ዓይነት ግንኙነት ከት/ቤቶች ጋር የለውም።

በአጠቃላይ ከፍሲል በአራቱም ተባባሪ ት/ቤቶች የተመደቡት ተማሪ አስተማሪዎች ከሰጡት አስተያየት እና ቀደም ሲል በፅሑፍ መጠይቅና በቃለ መጠይቅ የተጠናቀሩትን መረጃዎች እንደሚከተለው ማጠቃለል እንችላለን። በርግጥም ተባባሪ ት/ቤቶች ለፕራክቲከሙ ሂደት መሳካት ተገቢውን እገዛ ለተማሪ አስተማሪዎች አልሰጡም። ለዚህም ዋነኛው ምክንያት ምንም እንኳን በሁሉም ት/ቤቶች ውስጥ የፕራክቲከምን ጉዳይ የሚከታተል ኮሚቴ ቢኖርም፤ በተጨባጭ ለተማሪ አስተማሪዎች ያደረገው ድጋፍ ግን የለም። ምክንያቱም ኮሚቴው በመጀመሪያ ተቋቋመ እንጂ ይህ ነው ተብሎ የተሰጠው የሥራ ድርሻ የለም። ወይም ለተማሪ አስተማሪዎች ምን እገዛ ማድረግ እንዳለበት የሚያውቀው ነገር የለም። ከዚህም የተነሣ ሁሉም ት/ቤት እንደመሰለውና እንደተመቸው ነው ተማሪ አስተማሪዎችን የሚያስተናግደው። በፅሑፍ መጠይቅ ተጠኝዎች የሰጡት ምላሽም የተቀላቀለ የሆነውም ለዚሁ ሳይሆን አይቀርም። ቁርጥ ያለ የምዘና ሰመስጠት አልቻሉም። ት/ቤቶች ተማሪ አስተማሪዎች የተሟላ መምህር የሚያደርጋቸውን ብቃት የሚጎናፀፉበት ሙያዊ መቼት ናቸው (Brown 1975 Srivastava and Bose 1978 Gowers and Walters 1983)። ነገር ግን ከኮሌጁ ጋር የሚሠሩት ተባባሪ ት/ቤቶች ይህን ተግባራቸውን ተወጥተዋል ለማለት አያስችልም።

## 4.6 በኮሌጁ ፕራክቲከምን በአግባቡ ለመተግበር እንቅፋት የሆኑ ዋናዋና ችግሮች

በርካታ መምህራን ኮሌጅ ተጨባጭ ሁኔታ፣ የፕራክቲከም መርሃ ግብርን በአግባቡ ለመተግበር እንቅፋት ወይም ችግር የሆኑ ዋናዋና ጉዳዮች የትኞቹ እንደሆኑ ለመለየት፤ በፅሑፍና በቃለመጠይቅ አማካይነት መረጃዎች ተጠናቅረዋል። በየፅሑፍ መጠይቃቸው ላይ

የኮሌጅ መምህራን፣ የት/ቤት መምህራን እና ተማሪ አስተማሪዎች «ፕራክቲከምን በአግባቡ ለመተግበር እንቅፋት ፈጥረዋል የሚሏቸውን ችግሮች» እና «የፕራክቲከምን አተገባበር በተመለከተ ያላቸውን አጠቃላይ አስተያየት» እንዲገልጹ የሚጠይቅ ጥያቄ ቀርቦላቸው ምላሻቸውን ሰጥተውበታል። በቃለመጠይቅም ለኮሌጁ የፕራክቲከም ክፍል ኃላፊ እና ለተባባሪ ት/ቤቶች ርዕሳነ መምህራን ተመሣሣይ የሆነ ጥያቄ ቀርቦላቸዋል። ይሁንና ከኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊ በስተቀር ርዕሳነ መምህራኑ «አጠቃላዩን የትምህርት ፖሊሲ እንደመተች/ መንቀፍ የወሰዱት ይመስላል» ፕራክቲከም ጥሩና በጣም አስፈላጊ መሆኑን ብቻ ነው የጠቀሱት። ስለሆነም በዚህ ጉዳይ ላይ በት/ቤት ርዕሰ መምህራን በኩል ያለውን ሃሳብ ለማግኘት አልተቻለም። በአጠቃላይ ግን የተጠናቀሩት መረጃዎች እንደሚያሳዩት፣ በሮቤ መምህራን ኮሌጅ ፕራክቲከምን በተገቢው መንገድ በመተግበር ሂደት እንቅፋት የሆኑ ዋናዋና ጉዳዮች በጥቅሉ አምስት ሲሆኑ፣ እነዚህም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከኮሌጁ ጋር የሚያያዙ ሆነው ተገኝተዋል። በበላይም በኩል እነዚህ በኮሌጁ የተስተዋሉት ችግሮች ከዚህ ቀደም አለም (1989) እና ተሰጠ (1997) በኮተቤ መምህራን ኮሌጅ (የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ፅሑፍ ክፍል)፣ እንዲሁም Gebremedhin (2001) Kindalem (2005) በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሥነ ትምህርት ኮሌጅ ከተመለከቱት ችግሮች ጋር ተመሣሣይነት እንዳላቸው ለመመልከት ተችሏል። እነዚህንም ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታቸዋለን።

### 4.6.1 ኮሌጁ ለመርሃ ግብሩ የሰጠው ትኩረት አነስተኛነት

በሮቤ መምህራን ኮሌጅ በኩል ለፕራክቲከም መርሃ ግብሩ ተገቢ የሆነ ትኩረት እንዳልተሰጠ ቀደም ሲል ያየናቸው በፅሑፍና በቃለመጠይቅ የተጠናቀሩ መረጃዎች አመልክተዋል። ከዚህም በተጨማሪ ኮሌጁ ለመርሃ ግብሩ የሰጠውን ትኩረት የኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊ እንደሚከተለው ይገልፃሉ፣

> *በርግጥ ፕራክቲከም እንደኮርስ እየታየ አይደለም። ይህ ግን ለወደፊቱ እንደኮርስ ታይቶ ቢታሰበበት! ኮሌጁም ያለው አመለካከት... ለፕራክቲከም እስከዚህም ነው። ተማሪዎች ወጡ፣ ገቡ፣ እንጂ ምንድነው እንዲህ... ምንድነው ችግሩ ብሎ ትኩረት አይሰጥም። በኮሌጁ ደረጃም አይደለም even በሌላ በኦሮሚያ ደረጃ ራሱ ለዚህ ነገር ዝም ብሎ ነው። እንደ ፕራክቲከም፣ (ተማሪዎችን) ዝም ብሎ ወደ ት/ቤት ልኮ መተው! እና ሌላ ትኩረት ቢሰጥበትና ቢከታተሉት!*

ከዚህ ከኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊ ንግግር በኮሌጁ ለፕራክቲከም የተሰጠው ቦታ ምን ያህል ዝቅተኛ እንደሆነ መመልከት ይቻላል። በኮሌጁ ፕራክቲከም ማለት ተማሪዎችን ወደ ት/ቤቶች ማሰማራት ብቻ ነው። ተማሪዎቹ ት/ቤት ሄደው ለሚያከናውኑት ተግባራት ትኩረት ሰጥቶ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና ክትትል ማድረግ ያለ አይመስልም። በኮሌጁ ብቻ ሳይሆን በክልሉ

ትምህርት ቢሮ ደረጃም ለመርሃ ግብሩ የተሰጠው ትኩረት እንደፕራክቲከም ኃላፊው አባባል "ዝም ብሎ ነው"። ቀጥሎ የቀረበው የት/ቤት መምህር ሃሳብም ለጉዳዩ የተሰጠውን ዝቅተኛ ትኩረት የሚያመለክት ነው፤

> *በዚህ በፕራክቲከም ሂደት የኮሌጁ ሚና በጣም አናሳ ነው። እንደውም የኮሌጁ ማኔጅመንት እንደሌለ ይሰማኛል። ምክንያቱም አጠቃላይ መርሃ ግብሩ ሂደት ባለቤት የለውም። ምንም አይነት ቅርርብ ከት/ቤቶች ጋር የላቸውም። በዚያ ላይ ምንም አይነት ማቴሪያል የተሟላ ስለሌለ በጣም ችግር ፈጥሯል። ከዚህም ባሻገር የኮሌጁ መምህራን በሳምንት ለተወሰነ ሰአት ብቻ ብቅ ይሉና ከናካቴው አይመጡም። ምንም አይነት እገዛ ለተማሪዎች አያደርጉትም። ኃላፊነት አይሰማቸውም።*

ይህ የጋሰማ ት/ቤት መምህር አስተያየት በኮሌጁ ያለውን ሁኔታ በደንብ የሚያሣይ ነው። ቀደም ሲል የኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊ የተናገሩትንም የሚያጠናክር ነው። የፕራክቲከም መርሃ ግብሩ በርግጥም ባለቤት ያለው አይመስልም። የኮሌጁ ዋንኛ ስራ ተማሪ አስተማሪዎችን ወደ ት/ቤቶች መላክ ነው እንጂ፤ ተማሪዎች በት/ቤቶች ውስጥ የሚፈልጉትን ልምድ ለመቅሰም የሚያስችላቸውን ነገር አያመቻችም። ከት/ቤቶች ጋር ተገቢውን ቅርርብ አያደርግም። መምህሮችም ተገቢውን ድጋፍ ይሰጡ ዘንድ የሚደረግ ክትትል የለም። ለዚህም ዋንኛው ምክንያት ጉዳዩን ነገሬ ብሎ የሚከታተል አካል በኮሌጁ ስለሌለ ነው። የኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊም ይህን አስመልክቶ ሲናገሩ የሚከተለውን ይላሉ፤

> *ይህ የፕራክቲከም ስራ እንዳልኩህ የኮሚቴ ስራ ነው ብዬሃለሁ። የኮሚቴ ስራ ማለቱ አንዳንዴ ለይስሙላ ብቻም ይመስላል። ሁሉም የስትሪም ኃላፊዎች በዚህ ስራ ላይ ይሣተፋሉ (ኮሚቴ ሆነው) ። ተሣትፎአቸው ግን ለስም ነው። አንዳንዴ ሊጠሩአቸው መጥተው እንዲህ... እንዲህ ይሁን ይላሉ እንጂ ምንም አይሰሩም። እኔ ብቻዬን ይሄን ሁሉ ... እቆጣጠራለሁ ማለት ትንሽ ውሸት ያስመስላል። ሁሉንም ነገር የምሰራው እኔ ብቻ ነኝ። ማንም አጠገቤ የለም*

የኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊ ንግግር እንደሚያሳየውም፤ በኮሌጁ ፕራክቲከም እንደአንድ ክፍል ራሱን ችሎ ኮሚቴም ተሰይሞለታል። ሁሉም የኮሚቴው አባላት የስትሪም ኃላፊዎች በመሆናቸው የፕራክቲከምን ስራ የሚሰሩት በተደራቢነት ነው። ከዚህም የተነሳ ያላቸው ተሣትፎ ከስም ያለፈ አይደለም። በመሆኑም አጠቃላዩ የፕራክቲከም ጉዳይ በአንድ ሰው ትከሻ ላይ ተጥሏል። ይህን ሁሉ ተግባር የሚያከናውነው ሰው ደግሞ ከሌሎች ስራዎች ነፃ ሆኖ በፕራክቲከሙ ላይ ብቻ እንዲያተኩር ቢደረግ እንኳን ጥሩ ነበር። እውነታው ግን የዚህ ተቃራኒ

ነው። ይህ ፕራክቲከምን በኃላፊነት እንዲመራ የተወከለው ሰው ከማንኛውም የኮሌጁ መምህር ያልተናነሰ ከፍለጊዜ ይዞ ያስተምራል። ከሌሎቹ መምህራን እኩል ተማሪ አስተማሪዎችን ለፕራክቲከም ሱፐርቫይዝ ያደርጋል። ይህም ቀደም ሲል የት/ቤት መምህሩ «አጠቃላይ የመርሃ ግብሩ ሂደት ባለቤት የለውም» ያለውን አባባል ያጠናክራል። አንድ ተማሪ አስተማሪም «ፕራክቲከሙን አስመልክቶ እውነት ለመናገር አንድ ሰው ብቻ ነው ኃላፊነቱን ወስዶ እየሰራ ያለው» በማለት ይህንኑ ሃሳብ ያጠናክራል። ፕራክቲከምን በተመለከተ በኮሌጁ ካለው እውነታ አንፃርም፣ የኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊው፣ የት/ቤት መምህሩ እና የተማሪ አስተማሪው አባባል ተቀባይነት ያለው ነው። ከነዚህ መረጃዎችም፣ ኮሌጁ ለፕራክቲከም መርሃ ግብሩ የሰጠው ትኩረት ምን ያህል አናሳ እንደሆነ መመልከት ይቻላል። ፕራክቲከም /የማስተማር ልምምድ በመምህራን ስልጠና መርሃ ግብር ውስጥ ወሣኝና ቁልፍ የሆነ ነገር ነው። በበርካታ ምሁራን እምነትም (Walters 1960 Perrot1982 Ellis1986 Dukin1987 Wallace 1991 Reece and Walker 2001) በመምህራን ስልጠና መርሃ ግብር ውስጥ ከፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ የበለጠ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነገር ሊኖር አይችልም። በአዲሱ የኢፌዲሪ የመምህራን ትምህርትና ስልጠና መርሃ ግብር ውስጥም ፕራክቲከም ከፍተኛውን ቦታ ይዞ ይገኛል (TESO 2003)። ነገር ግን በርቢ መምህራን ኮሌጅ በኩል ለዚህ ጉዳይ የተሰጠው ትኩረት በጣም አናሳ ሆኖ ነው የተገኘ ው።

## 4.6.2 የመርሃ ግብሩ በበቂ ዕቅድና ቅድመዝግጅት ላይ አለመመስረት

በኮሌጁ ፕራክቲከምን በተገቢው በመንገድ ለመተግበር እንቅፋት ሆኖ የተገኘው ሌላው ጉዳይ፣ የመርሃ ግብሩ በበቂ እቅድና ቅድመ ዝግጅት ላይ ተመስርቶ አለመካሄድ ነው። ይህን አስመልክቶ በቀረበላቸው የዕሑፍ መጠይቆች ላይ የኮሌጁ መምህራን፣ የት/ቤት መምህራን እና ተማሪ አስተማሪዎች ብዙ ነገር ብለዋል። ከነዚህ መካከልም ናሙና ሲሆኑ የሚችሉትን እንመልከታለን። በቅድሚያ የኮሌጁ መምህራን የሰጡትን እንይ። ቀጥለው የቀረቡት ሃሳቦች ሁለት የኮሌጁ መምህራን የተሰጡት ነው።

> «ፕራክቲከም የመማር ማስተማር ሂደቱን effective የሚያደርግ መሆኑን አምናለሁ። ነገር ግን በአግባቡ schedule መደረግ አለበት። የሚመደብለት ጊዜና ተግባራዊ እየሆነ ያለበት ጊዜ ተመጣጣኝ አይደለም።»

> «ይህ ኮርስ በጣም ያስቸገረን ኮርስ ነው። የተሰጠው ጊዜ በዝቷል።»

ከላይ በተመለከተው የኮሌጁ መምህራን አስተያየት መሰረት፣ ምንም እንኳን ፕራክቲከም ተማሪ አስተማሪዎች በቂ የማስተማር ልምድ እንዲቀስሙ የሚረዳ ቢሆንም፣ አተገባበሩ ግን ችግር ያለበት መሆኑን ነው። በተገቢው መንገድ ታቅዶና ዝግጅት ተደርጎበት እየተተገበረ አይደለም። በመምህራን ስልጠና መርሃ ግብሩ ውስጥ ከፍተኛ ጊዜ የተሰጠው ቢሆንም

ተመጣጣኝ የሆነ ጊዜ ተመድቦለት በአግባቡ እየተተገበረ አይደለም:: ከዚህም የተነሣ ኮርሱ አስቸጋሪ ሆኗል። ይህን አስመልክቶ አንድ የት/ቤት መምህር እንደሚከተለው ይላል:: *«ብዙ ማለት ይቻላል። (ይህን) ለመናገርም አዝናለሁ–ግርግር ነው ባጠቃላይ::»*:: ቀጥለን የምንመለከተው ተማሪ አስተማሪ የሰጠው አስተያየትም ይህንኑ የሚያሳይ ነው::

> *የፕራክቲከም አተገባበር ሁኔታ በጣም ይቀረዋል ማለት እችላለሁ:: ምክንያቱም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሰራተኞች በሰአቱ አስቀድመው አስበውበት ሳይሆን፣ «ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ» አይነት ስራ ነው የሚሰሩት። በፕራክቲከም ስም ተማሪ አስተማሪዎችን ከኮሌጁ በመሸኘት ብቻ ፕራክቲከምን ተግብረናል ማለት አያስችልም:: ስለዚህ ስራው በአግባቡ እንዲሰራ ከተፈለገ አስቀድመው አስበውበት ቅድመዝግጅት ማድረግ አለባቸው። ማስታወቂያ ሲለጠፍ በመከታተል እንሄዳለን እንጂ ቀደም ተብሎ የሚነገረንና የምናውቀው ነገር እንደሌለነው::*

ከላይ ሲል የቀረበው የተማሪ አስተማሪው አስተያየት ቀደም ሲል የት/ቤት መምህሩ «ግርግር ነው ባጠቃላይ» ብሎ የገለፀውን የሚያጠናክር ነው:: መርሃ ግብሩ ቀደም ተብሎ ተዘጋጅቶበት የሚከናወን አይደለም። ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት አስቀድመው የሚያስፈልገውን ነገር አዘጋጅተው በሰአቱ አይገኙም:: ሌላው ቀርቶ ደብዳቤ ወደ ት/ቤቶች ግያላክ ነው ተማሪ አስተማሪዎች በት/ቤቶች የሚመደቡት (ስለተባባሪ ት/ቤቶች የስራ ድርሻ አስመልክቶ ተማሪ አስተማሪዎች የሰጡትን ሃሣብ ልብ ይሏል):: ይህን ጉዳይ አጥኚው በቦታው በነበረበት ወቅትም ተመልክቶታል። ለተጨማሪ አስረጅነትም ቀጥሎ የቀረበውን የሌላ ተማሪ አስተማሪ አስተያየት እንይ፤

> *ኮሌጁ በጊዜ ፕሮግራሙን አያቀናጅም:: የተማሪዎች ስም ዝርዝርና ክፍለ ጊዜ ለት/ቤቱ በጊዜ አይደርስም:: በፕሮግራሙ አወጣጥ ላይም ሆነ ስለፕራክቲከሙ ጉዳይ የኮሌጁ መምህራን የተወያዩ አይመስለኝም:: ምክንያቱም ከፕሮግራም አውጪ ኃላፊው ውጪ መምህራኖች ኢንፎርሜሽኑን ለማግኘት እኛን ተማሪዎችን ስለሚጠይቁ ነው::*

በአጠቃላይ ከላይ ከተመለከትናቸው አስተያየቶች መረዳት የሚቻለው፣ መርሃ ግብሩ በበቂ እቅድና ቅድመ ዝግጅት ላይ ተመስርቶ እንደ እንደማይከናወን ነው:: ምን መቼ እንደሚካሄድ አስቀድሞ የታወቀ አይደለም። ባለቀ ሰአት ላይ ለፕራክቲከም እንደሚወጣ ብቻ ይነገራል። ከዚህም በተጨማሪ በፕራክቲከሙ ሂደት ማን? ምን? ማከናወን እንዳለበት የሚታወቅ ነገር የለም። በኮሌጁ በኩል የሚዘጋጀው የመገምገሚያ ቅፅም ይህን ጉዳይ በተመለከተ የያዘው መረጃ በቂ አይደለም:: አጥኚው ኮሌጁ ለፕራክቲከም ያዘጋጃቸውን ሁሉንም ቅፆች ለመመልከት ሞክሯል። ተማሪ አስተማሪው መስራት ያለበትን እንጂ በኮሌጁም

ሆነ በት/ቤት መምህራን በኩል መደረግ የሚገባውን (የሥራ ድርሻቸውን) አያመለክቱም:: የተዘጋጁትም ለተማሪዎቹ ብቻ ነው:: (ቅጂያቸው ግን ለመምህራኑ ይሰጣል::) በዚህ ረገድ የፕራክቲከም አራት የመገምገሚያ ቅፅ ብቻ ነው መጠነኛ መሻሻል የሚታይበት:: ቢያንስ ተማሪ አስተማሪዎች በምን መመዘኛ መስረት እንደሚገመገሙ፤ ምን ምን ጉዳዮችን መከናወን እንዳለባቸው በዝርዝር ተቀምጧል:: ይህም የሆነበት ምክንያት ቅፁ (በኮሌጁ ሳይሆን) በክልሉ የሚገኙ የመምህራን ስልጠና ተቋማት አንድ ላይ ሆነው ያዘጋጁት በመሆኑ ሳይሆን አይቀርም:: ስለዚህ በኮሌጁ ያለው የፕራክቲከም አተገባበር በእቅድና በዝግጅት ላይ ተመስርቶ፤ ተገቢው የጊዜ መርሃ ግብር ተነድፎለት፤ ተሣታፊዎች የሚጠበቅባቸው የሥራ ድርሻና ኃላፊነታቸው ተቀምጦላቸው የሚከናወን አይደለም ለማለት ይቻላል:: ከዚህም የተነሳ የፕራክቲከሙ ሂደት አሰልቺና የተንዛዛ መሆኑን ከተጠኝዎች የተገኘው መረጃ ያመለክታል:: ቀጥሎ የቀረበው የሁለት ተማሪ አስተማሪዎች አስተያየት ለዚህ ዋቢ ሊሆን ይችላል::

*«አንድ ወጥ የሆነ ነገር ቢኖር ይመረጣል እንጂ እንዲሁ በደፈናው እንዲህ አድርጉትና ሪፖርት አምጡ እየተባለ ሁሉም ተማሪዎች የራሣቸውን የመሰላቸውን ሪፖርት የሚያደርጉት ነገር በጣም አስቸጋሪ ነገር ነው:: ምክንያቱም አንድ የሚሠራ ተማሪ ካለ ዝም ብሎ ከሱ ገልብጠው ነው የሚመጡት እንጂ በራሳቸው አይሰሩም::»*

*«ባጭሩ የፕራክቲከም አተገባበርን በተመለተ እኔ በበኩሌ ከ1ኛ ዓመቴ ጀምሬ ያገኘቸው ጥያቄዎች አንድ ዓይነት ናቸው:: ሁሌም ተመሣሣይ ጥያቄዎችን ነዉ: ስንሰራ ያስለፍነው:: ይህ ጉዳይ በምሁራን ታይቶ መስተካከል አለበት::»*

ከላይ የተመለከቱት የተማሪ አስተማሪዎች አስተያየት ከሞላጎደል የሁሉም ነው ማለት ይቻላል:: ከፍ ሲል የኮሌጁና የት/ቤት መምህራን የሰጡትን አስተያየትም በአስረጅነት መጥቀስ ይቻላል:: ይህን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ የኮሌጁ የፕራክቲከም ክፍል ኃላፊም የሚከተለውን ይላሉ::

*ሁሌ የተደጋገመ ነው::...ካለው ችግር አንዱ ይኼ ነው:: እንደውም ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ሄደው መጡ ከዛ በኋላ reflection ይባላል፤ ሪፖርት ማድረግ ብቻ ነው:: ሳይወጣ ሳይከታተል፤ ሪፖርት የሚያደረግ ተማሪ እንግዲህ እዚህ መሃል ብዙ ነው ማለት ይቻላል:: እንግዲህ ሄዶ መምጣትና ሪፖርት ማድረግ ነው ስራቸው::*

በአጠቃላይ እስካሁን የተመለከትናቸው የተጠኝዎች አስተያየት እንደሚያመለክቱት፣ በኮሌጁ ያለው የፕራክቲከም መርሃ ግብር በተገቢው መንገድ የተደራጀ ነው ለማለት አያስችልም:: የተዝረከረከና በተደጋጋሚ ተግባራት የተሞላ፤ ተማሪዎች በተጨባጭ ከቀስሙት የሚያስተማር ወይም የት/ቤት ልምድ ይልቅ ለፁሑፍ ዘገባ ትኩረት የሰጠ መሆኑ ፕራክቲከምን

አስልቺ እንዳደረገው መመልከት ይቻላል። ይህም መርሃ ግብሩ በበቂ ዕቅድና ቅድመ ዝግጅት ላይ አለመመስረቱን ያሳያል።

### 4.6.3 ከተባባሪ ት/ቤቶችጋር ያለው ቅርርብ መላላት

በሮቤ መምህራን ኮሌጅና ፕራክቲከንም በጋራ በሚያከናውኑ ተባባሪ ት/ቤቶች መካከል ተቀራርቦና ተናቦ የመስራቱ ነገር በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል። ከመርሃ ግብሩ የጊዜ ሰሌዳ ዝግጅት አንስቶ ያላቸው ተግባቦት ምን ያህል አነስተኛ እንደሆነ ከኮሌጁ የፕራክቲከም ክፍል ኃላፊ ጋርም ሆነ ከርዕሳነ መምህራን ጋር በተደረገው ቃለመጠይቅ ለመረዳት ተችሏል። የTESO (2003) ሰነድ ኮሌጆችና ተባባሪ ት/ቤት አብረው ሆነው ለተማሪዎች አስፈላጊውን ልምድ ለመቅሰም የሚያስችል የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀት እንደሚኖርባቸው ቢያመለክትም፤ ኮሌጁ የሚያዘጋጀው ግን ለብቻው ነው። የፕራክቲከም ኃላፊው የየት/ቤቶቹን የክፍል ብዛት ይሰበስብና በቀጥታ ተማሪዎችን ይመድባል፤ እንጂ ተወያይተውና አብረው የሚያወጡት የጊዜ ሰሌዳ የለም። ከዚህም የተነሳ ለምሳሌ ቀጥሎ የቀረበው ዓይነት ችግር ሊያጋጥም ችላል።

> *መጀመሪያ ሲመደቡ ፊት ባለቀ ትምህርት ላይ የተመደቡ ተማሪዎችም ነበሩ (ይሁንና) ከዚህም የተወሰኑትን እንደገና ወደሌላ ቢሮ መድበናቸዋል። የተቀሩት ግን ያለፈውን (ያለቀውን) ትምህርት revises አድርገው እንዲያስተምሩ አድርገናል።*

ይህ ንግግር የኮሌጁ የፕራክቲከም ክፍል ኃላፊ ነው። ቀደም ሲል እንዳነሣነው ኮሌጁና ት/ቤቶቹ አብረው መርሃ ግብሩን የሚያወጡ ቢሆን፤ ይህን አይነቱን ችግር በቀላሉ መቅረፍ በቻሉ ነበር። ይህ ባለመሆኑ ግን ተማሪ አስተማሪዎች እንዲያስተምሩ የተመደቡት፤ የት/ቤት መምህራን አስተምረው በጨረሱት ትምህርት ላይ ነው። ከዚህም የተነሳ ይመስላል በርካታ ተማሪ አስተማሪዎች *«(የት/ቤት) ተማሪዎች ለመማር ፍላጎት የላቸውም፤... በጣም ስንደጋገናል፤ ይሰለቹናል»* የሚል አስተያየት ሰጥተዋል። በመሆኑም የማስተማር ልምምዱ ሂደት ለይስሙላ የተከናወነ ነው ለማለት ይቻላል። አንዱ የኮሌጁ መምህር የሰጠው አስተያየትም ይህንኑ ያጠናክራል። *«ወቅቱ ት/ቤቶች የስራ ሰሌዳቸውን የሚዘጉበት ጊዜ ስለሆነ ፕሮፌሮ ነበረበት»* ይላሉ። ስለዚህ ኮሌጁና ት/ቤቶቹ መርሃ ግብሩን አብሮ ማቀድ ቢችሉ ኖሮ ለዚህ መሰሉ ችግር ተማሪዎች ከመስማራታቸው አስቀድሞ መፍትሄ ለማፈላለግ ያስችላቸዋል። ቀደምሲል ስለተባባሪ ት/ቤትቶች የሥራ ድርሻ ስንመለከት በስፋት እንዳየነውም ተባባሪ ት/ቤቶች ተማሪ አስተማሪዎች መቼ ወደነሱ እንደሚመጡ፤ ለምን እንደሚመጡ፤ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆዩ አስቀድመው የሚያውቁት ነገር የለም። ፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ደግሞ የቅንጅት ስራ ነው። የመምህራን ስልጠና ተቋማትና የተባባሪ ት/ቤቶች በጋራ የሚያከናወኑት ነው (Richards and Nunan 1990 TESO 2003)። ይህ ሁኔታ ግን በሮቤ መምህራን ኮሌጅና በተባባሪ ት/ቤቶች መካከል እንዳለለ ለመመልከት ተችሏል። *«እንደው አንዳንዴ ከህግ አንፃር*

እነሱም ተገደው እኛም ሆነን ተንተርሰን፣ የመንግስት ፖሊሲ ነው ብለን፣ እንሄዳለን እንጂ ስለንደት መቀራረባችን ብዙም አይደለም» የሚለውን የኘራክቲከም ኃላፊውን ንግግርም ልብ ይሏል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ደግሞ ፕራክቲከም በተገቢው መንገድ ተተግብሯል ለማለት አያስደፍርም።

### 4.6.4 የተማሪ አስተማሪዎችና የመምህራን ቁጥር አለመመጣጠን

በርቤ መምህራን ኮሌጅ ፕራክቲከምን በአግባቡ ለመተግበር ችግር የፈጠረ ሌላው መሠረታዊ ጉዳይ፣ በኮሌጁ መምህራንና በተማሪዎቹ መካከል ያለው የቁጥር አለመመጣጠን ነው። ኮሌጁ በመምህራን ስልጠና ዘርፍ በ10+3 እና በ10+1 መርሃ ግብር በቀንና በማታ 4043 ተማሪዎችን በማስልጠን ላይ ይገኛል። እነዚህም እንደየዓመታቸው አንድ ላይ (በአንድ ጊዜ) ለፕራክቲከም ወደ ት/ቤት ይሰማራሉ። ለምሳሌ የዚህ ዓመት (1998) የሁሉም መርሃ ግብር ተመራቂዎች በቁጥር ወደ 2500 የሚጠጉ ሲሆን፣ ለፕራክቲከም የማስተማር ልምምድም የተሰማሩት በተመሳሳይ ጊዜ ነው። ኮሌጁ ባጠቃላይ ያለው የመምህራን ቁጥር ደግሞ 36 ነው። እነዚህን ከ2000 በላይ የሆኑ ተማሪ አስተማሪዎችን ሱፐርቫይዝ የማድረግ ኃላፊነት የ36ቱ መምህራን ብቻ ይሆናል ማለት ነው። በዚህ ስሌት መሠረት እያንዳንዱ መምህር ቢያንስ 50 ተማሪዎችን ሱፐርቫይዝ ማድረግ ይጠበቅበታል። ይህ ሲሆን ባለመቻሉም በተለይ ለ10+1 መርሃ ግብር ተመራቂ ሰልጣኞች ታቅዶ የነበረው የፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ታጥፎ፣ በቢጤ ማስተማር (peer teaching) እንዲተካ ሆኗል። ወደ ት/ቤቶች የተሰማሩት የ10+3 መርሃ ግብር ሰልጣኞችም ቢሆን ያለበቂ መመሪያና ቅድመ ዝግጅት ነው የተላኩት። ከዚህም በተጨማሪ ሱፐርቪዥን እንዲያደርጉ ከተመደበላቸው (መምህራን) መካከልም ተዛማጅ ሙያዊ ስልጠና የሌላቸው (መምህራንም) ይገኙበታል። ከዚህም በኮሌጅ በመምህራንና በተማሪዎች መካከል ያለው ከፍተኛ የቁጥር አለመመጣጠን ያስከተለውን ተፅዕኖ ክብደት መረዳት ይቻላል።

### 4.6.5. የተማሪ አስተማሪዎችና የት/ቤቶች ቁጥር አለመመጣጠን

የተማሪዎችና የት/ቤቶች ቁጥር አለመመጣጠን በተማሪዎችና በኮሌጁ መምህራን መካከል ካለው ልዩነት ያልተናነሰ ተፅዕኖ በመርሃ ግብሩ ላይ ያሳደረ ችግር ነው። ከኮሌጁ ጋር ፕራክቲከምን ቢጋራ የሚያከናውኑ 11 ተባባሪ ት/ቤቶች አሉ። እነዚህም በርቤና በጎባ ከተማዎች ላይ የተወሰኑ ናቸው። ከ1ኛ-3ኛ ዓመት ያሉ የኮሌጁ ተማሪዎች ዓመቱን ሙሉ ለፕራክቲከም የሚሠማሩትም በነዚሁ ት/ቤቶች ላይ ነው። የአንደኛው ዓመት ተማሪዎች ሲመለሱ የሌላኛው ዓመት ተማሪዎች እየተተኩ በነዚሁ ት/ቤቶች ላይ ይፈራረቃሉ። ካለው ከፍተኛ የተማሪዎች ብዛት የተነሳም ት/ቤቶች ይጥለቀለቃሉ። በርካቶቹ በአንድ ክፍል ላይ በቡድን ይመደባሉ፣ በዚህም ተገቢውን ልምድ ለመቅሰም አለመቻላቸው ሳያንስ፣ የት/ቤቶችን የማስተማር መማር ሂደትም እስከማደናቀፍ ይደርሳሉ። ይህም በአብዛኞቹ ት/ቤቶች የነደፉትን የሥራ መርሃ ግብር

እንደሚያናጋባቸው ርዕሳን መምህራኑ ይገልፃሉ። በት/ቤቶች የሥራ መርሃ ግብር ላይ ይህን ያህል መስናክል ተፈጥሮም፤ አብዛኞቹ ተማሪ አስተማሪዎች *«ከመጀመሪያው ዓመት ጀምሮ በነዚህ ተማሪዎች ላይ ስንለማመድ ስለነበርን፤ ተማሪዎች እሺ ብለው አይማሩልንም»* በማለት ያማርራሉ። በሌላም በኩል ከሮቤ መምህራን ኮሌጅ ውጪ ቢያንስ ሦስት የግል ኮሌጆችም ተማሪዎቻቸውን የሚያስማሩት ወደነዚሁ ት/ቤቶች ነው። ይህም በፕራክቲከሙ ሂደት ላይ ከፍተኛ ተዕዕኖ ማሳደሩን ለመመልከት ይቻላል።

### 4.6.6 የምሣ ወይም የውሎ አበል አለመኖር

በፅሁፍ መጠይቅ የተጠናቀረው መረጃ እንደሚያሣየው የምሣ ወይም የውሎ አበልን እንደችግር ያላነሣ ተማሪ አስተማሪ የለም ለማለት ይቻላል። በፅሑፍ መጠይቃቸው ላይ «ፕራክቲከምን በአግባቡ ለመተግበር እንቅፋት ፈጥረዋል/ ሆነዋል የምትላ/ያቸውን ችግሮች ግለፅ/ጪ» ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ በርካቶች የሚከተሉትን ሳይጠቅሱ አላለፉም።

> *«(በወር) በሚሰጠን 155 ብር ምግብ ከውጪ ለመብላት አንችልም»*
>
> *«class ያለን ከስአት ቢሆንም ቁርሳችንን እንደበላን ሄደን ማታ ነው የምንገባው (ምሳ ሳንበላ)»*
>
> *«እየራበኝ ነው ት/ቤት ውዬ የምገባው»*

ይህ የተማሪ አስተማሪዎች አስተያየት ካለው ሁኔታ አንፃር እውነታነት ያለው ይመስላል። ይኸውም በኮሌጃም ሆነ በሌሎቹ የክልሉ የመምህራን ስልጠና ተቋማት ከ1996 ጀምሮ መደበኛ ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ ውጪ ሆነው እየተመላለሱ እንዲማሩ ሆኗል። በዚህም መሰረት ለምሣሌ በሮቤ በወር 155 ብር ለመኝታና ለምግብ እየተሰጣቸው ከውጪ ይመላለሳሉ። ይኼ እንዳለ ሆኖ በተለይ ለፕራክቲከም በጎባ ከተማ ባሉ ት/ቤቶች የተመደቡ ተማሪ አስተማሪዎች የትራንስፖርት እጥረት ስላለ ከትምህርት ሰዓት ቀደም ብለው ወደ ት/ቤቶቹ እንደሄዱ ይደረጋል። ከዚህ የተነሳ የጠዋት ፈረቃ ያላቸው ተማሪዎች ጠዋት ሄደው፤ የሚመለሱት ከምሳ በኋላ በጣም ዘግይተው ነው። የከሰአት ፈረቃ ያላቸውም እንዲሁ ከምሣ በፊት ወደ 4:00 ገደማ ላይ ሄደው ማታ ነው የሚመለሱት (12:00)። ይህም ለበርካታ ወጪ ዳርጓቸዋል ወይም ባዶ ሆዳዋውን አውሏቸዋል። ኮሌጁም ቢሆን የችግሩን መኖር ቢረዳም፤ ለመቅረፍ የቻለ ግን አይመስልም። ይህን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ የፕራክቲከም ኃላፊው የሚከተለውን ይላሉ።

> *በዚህ ርዕስ የተመደበ በጀት የለም። ይኼ አንድ ችግር ሆኖብናል። ለወደፊቱም (መኖሩን) I don't know ! ከእርሚያ የተሰጠን መልስም እንዲህ ብታደርጉ (እሁን ለተማሪዎች የምሣ ብትከፈሉ) የTDP በጀት በሚቆምበት ጊዜ ሌላ ችግር ሊፈጠር ይችላል ተብለናል።*

ከንግግሩ ንግግር መረዳት እንደሚቻለው ጉዳዩ ከኮሌጁም አቅም በላይ የሆነ ይመስላል። ቢያንስ ለቀጣይ ተማሪ አስተማሪዎች ሊታሰብ ይገባ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በክልሉም በኩል ለጉዳዩ ተገቢው ትኩረት የተሰጠ አይመስልም፡፡ ኮሌጁ ለፕራክቲከም በሮቤና ጎባ ከተማ ውስጥ ባሉ ት/ቤቶች ላይ ብቻ እንዲወሰን ያደረገውም ይኸው ችግር ሳይሆን አይቀርም፡፡ ምንም እንኳን በኮሌጁ ቀደም ሲል በትራንስፖርት በኩል የነበረበት ችግር በተወሰነ ደረጃ የተቀረፈ ቢሆንም (የክልሉ ትምህርት ቢሮ ተጨማሪ አውቶቡስ ስለላከ)፤ የጉዳዩ አሳሳቢነት ግን እንዳለ ነው።

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና የመፍትሔ ሃሳብ

## 5.1 ማጠቃለያ

በኦሮሚያ ክልላዊ መስተዳድር በሮቤ መምህራን ኮሌጅ በ10+3 የዲፕሎማ መርሃ ግብር ያለውን የፕራክቲከም አራት ኮርስ የአተገባበር ሂደት መፈተሽ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ነው:: በዚህም ጥናቱ TESO (2003) ለ10+3 የመምህራን ስልጠና መርሃ ግብር ያስቀመጠውን ሃገር አቀፍ መመሪያ መሰረት በማድረግ በኮሌጁ ያለውን የፕራክቲከም አተገባበር ሂደት ፈትሿል:: ለዚህም የሚከተሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች መሠረት አድርጎ ነበር::

1. በሮቤ መምህራን ኮሌጅ በ10+3 የዲፕሎማ መርሃ ግብር በቋንቋ ስትሪም ያለው የፕራክቲከም አራት ኮርስ እንዴት እየተተገበረ ነው?
2. የሮቤ መምህራን ኮሌጅና ተባባሪ ት/ቤቶች ለአጠቃላዩ የፕራክቲከም መርሃ ግብር ትግበራ መሳካት ምን ያህል የሚጠበቅባቸውን ሚና በአግባቡ እየተወጡ ነው?
3. በሮቤ መምህራን ኮሌጅ በ10+3 የዲፕሎማ መርሃ ግብር በቋንቋ ስትሪም ፕራክቲከምን በመተግበሩ ሂደት ያጋጠሙ ዋና ዋና እንቅፋቶች/ችግሮች የትኞቹ ናቸው?

እነዚህን መሠረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስም በፅሑፍ መጠይቅ፣ በቃለመጠይቅ፣ በምልከታና በገምገማ ቅፅ አማካይነት፣ ከኮሌጅ መምህራን፣ ከት/ቤት መምህራን፣ ከተማሪ አስተማሪዎች፣ ከኮሌጁ የፕራክቲከም ኃላፊ እና ከተባባሪ ት/ቤቶች ርዕሳነ መምህራን አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ተጠናቅረዋል። መረጃዎቹም በየፈረጃቸው ተለይተው በተዛማጅ ፅሑፎች ቅኝት ጋር በተመለከቱት ንድፈሃሳቦች መሠረት ተተንትነዋል:: ከዚህም በመነሳት የተደረሰበት መደምደሚያ የሚከተለውን ይመስላል።

1. የኮሌጅ ወይም አሰልጣኝ መምህራን የመምህራን ስልጠና መርሃ ግብሩ ዋልታና ማገር ናቸው። ያለነሱ ንቁ ተሳትፎና ኃላፊነት የተሞላበት እንቅስቃሴ፣ አስፈላጊውን ሙያዊ ክህሎትና ብቃት የተጎናፀፉ /የተካኑ መምህራንን ማፍራት (ፈዕሞ) አይታሰብም:: ለዚህም ዋነኛው ምክንያት የመምህራን ስልጠናው ጠቅላላ ሂደት በነሱ ግንባር ቀደም መሪነት ስለሚካሄድ ነው። ስለሆነም በተለይ ቅድመ ፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ተማሪ አስተማሪዎች ወደ ት/ቤት ከመሄዳቸው በፊት በት/ቤት ስለሚያከናውኗቸው ተግባራት፤ እና ስለመሠረታዊ የመማስተማር ክህሎት አብረው ይወስናሉ፤ ይወያያሉ:: በፕራክቲከም ሂደትም በት/ቤት ተገኝተው ተከታታይ ምልከታና ግምገማ በማድረግ ተማሪ አስተማሪዎቹ ያሉበትን ደረጃ ይፈትሻሉ፤ በሚሰጧቸው ገንቢ፣ ፈጣንና በቃልና በፅሑፍ የታገዘ አስተያየትና ምጋቤ ምላሽ አማካይነትም ተማሪ አስተማሪዎቹን በሂደት

እየቀረፁና እየሞረዱ ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ ያመጣሉ። በሮቤ መምህራን ኮሌጅ የሚገኙ የኮሌጅ መምህራን ግን ይህን ወሳኝ የሥራ ድርሻቸውን በአግባቡ አከናውነው አልተገኙም። መምህራኑ ስለፕራክቲከሙ በተለይም ስለሱፐርቪዥኑ ካላቸው አሉታዊ አመለካከትና ከተማሪ አስተማሪዎቹ መብዛትም የተነሳ፣ ቅድመ ፕራክቲከም፣ በፕራክቲከም ሂደትና ድህረ ፕራክቲከም ያደረጉት ሱፐርቫይዘራዊ እገዛ በተገቢው መንገድ የተከናወነ አልነበረም። ከዚህም የተነሳ ተማሪ አስተማሪዎች ያለ በቂ ሱፐርቫይዘራዊ ድጋፍና ክትትል ት/ቤት ውስው እንዲመለሱ ሆኗል።

2. የተባባሪ ት/ቤት መምህራን በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት ተማሪ አስተማሪዎች በት/ቤት ተገኝተው የሚያደርጉትን ልምምድ፣ በቅርበት ሆነው በሚሰጧቸው ሙያዊ ምክርና አስተያየት አማካይነት ያጠናክሩሉ/ ይደግፋሉ። እንዲሁም የት/ቤት መምህራን ከተማሪ አስተማሪዎቹ ቀድመው ወደ ማስተማሩ ሥራ የገቡ ከመሆናቸው አንፃር በት/ቤቶች ስለሚገኙ ጉዳዮች በርካታ ሙያዊ ልምዶችን ለተማሪዎቹ በማካፈል ረገድ አርዓያነታቸው የጎላ ነው። ተማሪ አስተማሪዎች በንድፈሃሳብ ደረጃ የተሰጧቸውን ሙያዊ ዕውቀቶች/ ግንዛቤዎች በት/ቤት ካለው ተጨባጭ ሙያዊ መቼት ጋር ለማዋሃድም የት/ቤት መምህራን የቅርብ እገዛ ወሳኝ ነው። በዚህ መንገድ ተማሪ አስተማሪዎቹ ከት/ቤት መምህራንና ከኮሌጅ መምህራን በሚያገኙዋቸው ሙያዊ ምክሮችና ድጋፎች ሥር ሆነው ተገቢውን የማስተማር ክህሎት ይቀስማሉ/ ይጎናፀፋሉ። ከዚህ አንፃር ከሮቤ መምህራን ኮሌጅ ጋር ፕራክቲከምን በጋራ በሚያከናውኑ ተባባሪ ት/ቤቶች የሚገኙ መምህራን ለተማሪ አስተማሪዎቹ ከፍተኛ የሆነ እገዛ አድርገዋል። በተለይ በማስተማር ልምምዱ ሂደት ተከታታይ ምልከታና ግምገማ በማድረግ፤ ገንቢ የሆነ አስተያየት እና ምጋቤ ምላሽ በፍጥነት ከመስጠት አንፃር ከኮሌጅ መምህራኑም የበለጠ ሥራ ሰርተዋል። ይህም ተማሪ አስተማሪዎቹ ከኮሌጅ መምህራኑ ያላገኙትን ሱፐርቫይዘራዊ ድጋፍ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን አካክሶላቸዋል። ምንም እንኳን የት/ቤት መምህራኑ በፕራክቲከም የማስተማር ልምምዱ ሂደት ማድረግ የሚችሉትን ሁሉ ከማድረግ አልተቆጠቡም፤ ይሁን እንጂ በተለይ የሱፐርቪዥኑ ሥራ በሙያው የተካኑ ባለሙያዎችን የሚሻ የመሆኑ ጉዳይ ለተማሪ አስተማሪዎቹ የተደረገውን ሱፐርቫይዘራዊ እገዛ ብቃት ወይም አስተማማኝነት ጥያቄ ላይ የሚጥል ሆኖ ተገኝቷል።

3. ተማሪ አስተማሪዎች የመምህራን ስልጠና መርሃ ግብሩ መነሻና መድረሻ ናቸው። እነዚህን ሰልጣኞች በንድፈሃሳብና በተግባር የተደገፈ ትምህርት በመስጠት በሙያቸው የበቁ መምህራን ማስኘት የማንኛውም የመምህራን ስልጠና ተቋም ብቸኛና የመጨረሻ ግብ ነው። ይህም እውን ሆኖ የሚታየው፤ ተገቢውን ንድፈሃሳባዊ ዕውቀት የሚስጨብጣቸው አሰልጣኝ መምህር ሲያገኙ፤ የቀሰሙትን ንድፈሃሳባዊ ግንዛቤ ወደተግባር ለመለወጥ የሚያስችል ሙያዊ መቼት (ት/ቤት) ሲመቻችላቸው፤ በተግባራዊ

ልምምዱ ወቅት በቅርበት ሆኖ አስፈላጊውን ሱፐርቫይዘራዊ ድጋፍ የሚሰጣቸው ባለሙያ ሲያገኙ ... ነው። ይህ በሌለበት ሁኔታ ውስጥ ተማሪ አስተማሪዎች በራሳቸው የሚያከናውኑት ተግባራዊ የማስተማር ልምምድ ፍሬ ያፈራል ብሎ መጠበቅ አይታሰብም። በርቤ መምህራን ኮሌጅ የሚስተዋለው እውነታ ግን ከዚህ የተለየ አይደለም። ተማሪ አስተማሪዎች ያለበቂ ንድፈሃሳዊ ግንዛቤ (ቅድመ ፕራክቲከም) ወደ ት/ቤት ይለቀቃሉ፤ እነዚህ ት/ቤቶችም አስፈላጊውን ሙያዊ ልምድ ለመቅሰም ምቹ አለመሆናቸው ሳያንስ፣ በት/ቤቶቹ ተገኝቶ ተከታታይና ቀጣይነት ያለው ሱፐርቫይዘራዊ እገዛ የሚሰጥ ባለሙያ (በብቃትም ሆነ በብዛት) አያገኙም:: ከፕራክቲከም በኋላም ቢሆን በት/ቤት ምን እንዳከናወኑ የሚከታተልና አቅጣጫ የሚያመላክታቸው የለም:: ከዚህም የተነሳ ተማሪ አስተማሪዎቹ በፕራክቲከም የማስተማር ልምምዱ ሂደት ከትምህርት ዕቅድ ዝግጅት እንስቶ ያከናወኗቸው አንዳንድ ተግባራት በበቂ ሁኔታ የዳበሩና የጐለበቱ አልነበሩም። ይህም ኮሌጁ በንድፈሃሳባዊ ዕውቀት የበለፀጉና በተግባራዊው ክህሎት የበቁ መምህራንን ለማፍራት የወጠነውን ዓላማ ከግብ ማድረሱን አጠያያቂ አድርጎታል::

4. የመምህራን ስልጠና ተቋም የአጠቃላይ የመምህራን ስልጠና መርሃ ግብሩ ባለቤትና የበላይ ተቆጣጣሪ ነው። የተቋሙ ብቸኛና የመጨረሻ ግብም አስፈላጊውን ሙያዊ ክህሎት የተጎናፀፉ መምህራንን ማፍራት ነው:: ከዚህ ግቡ ለመድረስም የስልጠና መርሃ ግብሩ የሚሻቸውን መሠረታዊ ግብዓቶች አሟልቶ ወደ ተግባር መለወጥ ይጠበቅበታል:: በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አስፈላጊውን ሁሉ ግብዓት አሟልቶ መገኘት የማይጠበቅ ቢሆንም፤ በእጅ የተገኙትን በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል መቻል ግን ወሳኝ ነው:: ከዚህ አንፃር በርቤ መምህራን ኮሌጅ በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ ሂደት የሚስተዋለው ሁኔታ የኮሌጁን የመጨረሻ ግብ የዘነጋ/ችላ ያለ ይመስላል:: ኮሌጁ ከውስጥና ከውጭ (ከተባባሪ ት/ቤቶች) ያለውን አቅም በአግባቡ አቀናጅቶ ተማሪ አስተማሪዎቹ ተገቢውን ሙያዊ ክህሎት እንዲቀስሙ ለማድረግ አልቻለም:: የተጠናከረ የፕራክቲከም መምሪያ አዘጋጅቶ አጠቃላይ መርሃ ግብሩን በማስተባበር፤ ከተባባሪ ት/ቤቶች ጋር በቅርበት በመሥራት ለተማሪ አስተማሪዎች ምቹ ሙያዊ መቼት በመፍጠር፤ ያሉት መምህራንና ተባባሪ ት/ቤቶች ተገቢውን ድጋፍ ለተማሪ አስተማሪዎች የሚሰጡበትን መንገድ በመቀየስ (ሁኔታ በማመቻቸት) እና አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር በመዘርጋት በኩል ኮሌጁ ከፍተኛ የሆነ ድክመት ይታይበታል:: ከዚህም የተነሳ ጠቅላላው የፕራክቲከም ሂደት በመመሰቃቀሉ፤ ተማሪ አስተማሪዎቹ በፕራክቲከሙ ሂደት ተገቢውን ሙያዊ ክህሎት ለመቅሰም አልቻሉም።

5. ተባባሪ ት/ቤቶች የተማሪ አስተማሪዎች የወደፊት የሥራ ቦታ ናቸው:: በስልጠናቸው ሂደት የሚማሯቸውና የሚለማመዷቸው ነገሮች ሁሉ ኋላ ላይ እዚህ (ት/ቤት) ተገኝተው ብቁ መምህር እንዲሆኑ ለማድረግ ያለሙ ናቸው:: ስለሆነም ት/ቤቶች ለተማሪ

አስተማሪዎቹ ሙያዊ ብቃት መጎልበት ወሳኝና ምትክ የሌላቸው ሙያዊ መቼቶች ናቸው። ይህም በመሆናቸው ተማሪ አስተማሪዎቹ ለፕራክቲከም ልምምዱ በሚመጡባቸው ወቅት ምቹ የሆነ ሙያዊ አውድ አዘጋጅተው ሊጠብቋቸው ይገባል። በዚህም ተማሪ አስተማሪዎቹ አስፈላጊውን ልምድ ከት/ቤቱ ቀስመው መመለሳቸውን ት/ቤቶቹ መረጋገጥ መቻል አለባቸው። ከሮቤ መምህራን ኮሌጅ ጋር ፕራክቲከምን በትብብር የሚያከናውኑ ት/ቤቶች ግን ይህን ወሳኝና አይተኬ ሚናቸውን በአግባቡ አልተወጡም። ከኮሌጁ ጋር የጠበቀ የሥራ ግንኙነት የሌላቸው ከመሆኑ የተነሳ፤ ተባባሪ ት/ቤቶች ለተማሪ አስተማሪዎቹ ምቹና አስፈላጊው ሙያዊ ክህሎት የሚገበይበት መቼት ሊሆኑ አልቻሉም።

በሮቤ መምህራን ኮሌጅ በ10+3 መርሃ ግብር በቋንቋ ስትሪም ያለው የፕራክቲከም ኮርስ ትግበራ ሂደት በተገቢው መንገድ በመተግበር ላይ እንደማይገኝ የተጠናቀሩት መረጃዎች ትንተና አሳይቷል። ለዚህም ምክንያት የሆኑት መሠረታዊ ችግሮች/ ጉዳዮችም ቀጥለው የተዘረዘሩት መሆናቸውን ከመረጃዎቹ ትንተና ለመመልከት ተችሏል።

1. በሮቤ መምህራን ኮሌጅ ፕራክቲከም፣ እንደ የመምህራን ስልጠና መርሃ ግብር የጀርባ አጥንትነቱ፣ ተገቢውን ትኩረት አላገኘም። ፕራክቲከም የቅንጅት ሥራ ነው። የመምህራን ስልጠና ተቋሙና ተባባሪ ት/ቤቶች በጋራና በአንድነት ያከናኑውታል። ይህን በአግባቡ ለማከናወን ደግሞ ኮሌጁ ከሁሉ በፊት ራሱን አደራጅቶ መዘጋጀት ይጠበቅበታል። መርሃ ግብሩን በተገቢው መንገድ የሚያንቀሳቅስና የሚያስተባብር ጠንካራ አካል ወይም ኮሚቴ ሊያደራጅ ይገባል። በሮቤ መምህራን ኮሌጅ በኩል ግን ፕራክቲከምን የሚያህል ጉዳይ ከሞላ ጎደል በአንድ ሰው ጫንቃ ላይ ተጥሏል። ከዚህም የተነሳ አጠቃላይ የፕራክቲከም መርሃ ግብሩ ከውስጥም ሆነ ከውጭ (በት/ቤቶች) የተመሰቃቀለ ሊሆን ችሏል።

2. በኮሌጁ ያለው የፕራክቲከም አተገባበር ሂደት በበቂ ዕቅድና ቅድመ ዝግጅት ላይ ተመስርቶ አይከናወንም። መርሃ ግብሩ መቼ ተጀምሮ መቼ እንደሚያልቅ፣ ማን ምን ማከናወን እንዳለበት፣ እንዴት ባለመንገድ መከናወን እንዳለበት አስቀድሞ ለተሳታፊዎች ማሳወቅና ዝግጅት ማድረግ አይስተዋልም። ይህም የፕራክቲከም መርሃ ግብሩን ሂደት አሰልቺ፣ የተዝረከረከ እና በተደጋጋሚ ተግባራት የተሞላ እንዲሆን አድርጎታል። ከዚህም የተነሳ የኮሌጅ መምህራን፣ የት/ቤት መምህራንና ተማሪ አስተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን የሥራ ድርሻና ኃላፊነት በአግባቡ ማከናወን አልቻሉም።

3. ፕራክቲከም በመምህራን ስልጠና ተቋሙ ተናጥላዊ እንቅስቃሴ ብቻ ሊከናወን አይችልም። ከተባባሪ ት/ቤቶች ጋር በመቀናጀትና በመዋሃድ እየተናበቡ መሥራትን ይጠይቃል። በዚህ ሂደት ተባባሪ ት/ቤቶች ዳር ቆመው የሚመለከቱ ሳይሆን፣ የሂደቱ ንቁ ተሳታፊዎች ሆነው ሚናቸውን መወጣት መቻል ይኖርባቸዋል። ይህ ሲሆን ነው ተማሪ አስተማሪዎች ከመርሃ

ግብሩ አስፈላጊውን ልምድ መቅሰም የሚችሉት:: ይህም እውን ሊሆን የሚችለው በመምህራን ስልጠና ተቋሙና በት/ቤቶቹ መካከል ተገቢው መቀራረብና ግንኙነት ሲመሠረት ነው:: በሮቤ መምህራን ኮሌጅና በተባባሪ ት/ቤቶቹ መካከል ግን ይህ ሁኔታ በአግባቡ ባለመኖሩ፤ ተማሪ አስተማሪዎች ተገቢውን ልምድ ከት/ቤቶች የሚቀስሙበት አመቺ ሁኔታ አልተፈጠረም::

4. ፕራክቲከም/ የማስተማር ልምምድ የተማሪ አስተማሪዎችን ሁለንተናዊ ሙያዊ ብቃት ለማጎልበት አማራጭ የሌለው መፍትሔ ቢሆንም፤ ቁልፉ ያለው ግን በውስጡ በሚኖረው ሱፐርቪዥንና ጥራትና ብቃት ውስጥ ነው:: በሮቤ መምህራ ኮሌጅ ግን ተማሪ አስተማሪዎች ለማስተማር ልምምድ ወደ ት/ቤቶች ይላካሉ እንጂ ተገቢውን ሱፐርቫይዘራዊ እገዛ/ ድጋፍ ያገኛሉ ለማለት አይቻልም:: ምክንያቱም ለተማሪዎች ተገቢ የሆነ ሱፐርቫይዘራዊ ድጋፍ የሚሰጡ መምህራን በኮሌጁ የሉምና:: ከዚህም የተነሳ ተማሪ አስተማሪዎች የተሟላ የማስተማር ልምድ ይቀስሙበታል ተብሎ በሚጠበቅበት በመጨረሻው ፕራክቲከም (4) ላይ እንኳን፤ መምህራኑ ከአንድ አንድ ጊዜ በላይ (በት/ቤት) ተገኝተው ሱፐርቫይዝ ማድረግ አልቻሉም:: ከነዚህም ሱፐርቫይዘሮች መካከል ከተማሪዎቹ ትምህርት ጋር ተዛማጅ ስልጠና የሌላቸውም ነበሩበት:: በዚህ ሁኔታ ውስጥ ተማሪ አስተማሪዎች ተገቢውንና አስፈላጊውን ሙያዊ ልምድ ቀስመዋል ለማለት አይቻልም:: ኮሌጁም ብቁና ጥራት ያላቸው መምህራንን አፍርቷል ለማለት አያስደፍርም::

5. ፕራክቲከም/ የማስተማር ልምምድ ተማሪ አስተማሪዎች በእውናዊው መቼት (በት/ቤት) ውስጥ በአካል ተገኝተው የማስተማርን ሙያ የሚለማመዱበት ሂደት ነው:: ለዚህ እውን መሆን ደግሞ ተማሪ አስተማሪዎች ተገቢውን ሙያዊ ልምድ ለመቅሰም በሚያስችላቸው ት/ቤቶች ላይ ሊሠማሩ ግድ ነው:: ይሁንና ከሮቤ መምህራን ኮሌጅ ጋር ፕራክቲከምን በትብብር የሚያከናውኑ ት/ቤቶች ከተማሪዎቹ ቁጥር ጋር አይመጣጠኑም:: በመሆኑም ት/ቤቶቹ ሙሉውን ዓመት (ለተለያዩ የፕራክቲከም ኮርሶች) በኮሌጁ ተማሪዎች ይጥለቀለቃሉ:: ከዚህም የተነሳ ተማሪ አስተማሪዎቹ አስፈላጊውን ሙያዊ ልምድ ለመቅሰም ከማይችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል:: ተማሪ አስተማሪዎቹ በነዚህ ት/ቤቶች በተደጋጋሚ የተለማመዱ በመሆናቸው በት/ቤቶቹ ተማሪዎች ዘንድ እንደመምህር አይታዩም፤ ሲያስተምሯቸውም ሊማሩላቸው ፈቃደኛ አይደሉም:: በዚህ ሁኔታ ውስጥ ተማሪ አስተማሪዎች ምን ዓይነት የማስተማር ልምድ እንደሚቀስሙ ለመገመት ይቸገራል::

6. የማስተማር ልምምድ የሚካሄድበት ዋነኛ ዓላማና ግብ የተማሪ አስተማሪዎችን ሙያዊ ክህሎት ለማዳበር ነው:: የአጠቃላይ የመርሃ ግብሩ ተሳታፊዎች ልፋትም ለነሱ (ለተማሪ አስተማሪዎቹ) ነው:: በዚህ ሂደትም ተማሪ አስተማሪዎችን ልምድ ወደሚያገኙበት ት/ቤት ከመላክ እና፤ ተገቢውን ሙያዊ እገዛ የሚሰጥ ሱፐርቫይዘር ከመመደብ ጎን ለጎን፤

ተማሪ አስተማሪዎቹ ተረጋግተው ልምምዳቸውን የሚያካሂዱበት ሁኔታም ሊፈጠርላቸው ይገባል። በሮቤ መምህራን ኮሌጅ ግን ለተማሪ አስተማሪዎች ይህ ሁኔታ የተመቻቸላቸው ሆኖ አልታየም። ይህ እንዳለ ሆኖ፣ በኮሌጁ የትራንስፖርት እጥረትም የራሱን ተፅዕኖ አሳድሮባቸዋል። ከዚህም የተነሳ ተማሪ አስተማሪዎቹ ያለ ምሳ ት/ቤት ውለው ለመግባት ተገደዋል።

በአጠቃላይ በሮቤ መምህራን ኮሌጅ በ10+3 የዲፕሎማ መርሃ ግብር ያለው የፕራክቲከም አራት ኮርስ ትግበራ ሂደት በአግባቡ አይከናወንም። ለዚህም ከላይ የተጠቀሱት ዋና ዋና ችግሮች እንቅፋት ሆነዋል። ከዚህም የተነሳ የኮሌጅ መምህራን፣ የት/ቤት መምህራን፣ ተማሪ አስተማሪዎች እና ተባባሪ ት/ቤቶች በፕራክቲከም ትግበራ ሂደት ያላቸውን የሥራ ድርሻና ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት አልቻሉም። ይህም በተለይ በኮሌጅ መምህራን፣ በት/ቤት መምህራን እና በተማሪ አስተማሪዎቹ ዘንድ ስለፕራክቲከም የተዛባና ተገቢ ያልሆነ አመለካከት እንዲፈጠር ሰበብ ሆኗል። የሚጠበቅባቸውን ለማከናወን እንዳይነሳሱና ቸልተኛ እንዲሆኑ ማድረጉንም ከመረጃዎች ትንተና ለመመልከት ተችሏል።

## 5.2 የመፍትሔ ሃሳብ

ይህ ጥናት በኦሮሚያ ክልላዊ መስተዳድር በሮቤ መምህራን ኮሌጅ፣ በ10+3 የዲፕሎማ መርሃ ግብር (በቋንቋ ስትሪም) ያለውን የፕራክቲከም ኮርስ አተገባበር በመፈተሽ፣ በትግበራው ሂደት ላይ እንከን የፈጠሩ ዋና ዋና ጉዳዮችን በማሳየት ተጠናቋል። በማጠቃለያው ላይ የተመለከቱት ዋና ዋና ችግሮች ተቀርፈው፣ የፕራክቲከም መርሃ ግብሩም በአግባቡ ተተግብሮ፣ ተማሪ አስተማሪዎች አስፈላጊውን ሙያዊ ብቃት ተጎናፅፈው፣ ብቃትና ጥራት ያላቸውን መምህራን ማፍራት ይቻል ዘንድ ቀጥለው የተመለከቱት የመፍትሄ ሃሳቦች ተጠቁመዋል።

1. ፕራክቲከም፣ የመምህራን ስልጠና መርሃ ግብር የጀርባ አጥንት ነው። በስልጠናው ሂደት ከሚሰጡት ኮርሶች ሁሉ የላቀውን ቦታ ሊይዝ የቻለውም ለዚሁ ነው። ስለሆነም፣ ኮሌጁ ይህን ወሳኝና ቁልፍ ጉዳይ በብቃት ሊያደራጅ፣ ሊያንቀሳቅስና ሊመራ የሚችል አካል ወይም ኮሚቴ ከነሙሉ ስልጣንና ተጠያቂነቱ ጋር ቢያዋቅር።

2. ፕራክቲከም ተማሪ አስተማሪዎች በዘፈቀደ ት/ቤት ውለው የሚመለሱበት ሂደት ተደርጎ መታየት የለበትም። ስለሂደቱ የኮሌጁ መምህራን፣ የት/ቤት መምህራን፣ ተማሪ አስተማሪዎችና ተባባሪ ት/ቤቶች የተሟላ መረጃና ግንዛቤ እንዲያገኙ መደረግ አለበት። ስለዚህም ኮሌጁ የትኛው የፕራክቲከም ኮርስ መቼና እንዴት ባለመንገድ እንደሚከናወን የሚያሳይ አጠቃላይ ዕቅድና መመሪያ ለተሳታፊዎች በማዘጋጀት፣ በዚያ መሠረትነት ቢንቀሳቀስ።

3. ያለበቴ ሱፐርቪዥን የማስተማር ልምምድ የሚጠበቅበትን ፍሬ ሊያፈራ አይችልም:: ስለሆነም ኮሌጁ ተማሪ አስተማሪዎችን ለልምምድ ከማሠማራቱ በፊት አስቀድሞ በሱፐርቫይዘሮቹ በኩል ያለውን አቅም ቢፈተሽ ተገቢ ይሆናል:: ተማሪዎች በሚሰለጥኑበት ዐብይ ስትሪም የሰለጠኑና የሥነ ትምህርት ዕውቀት ያላቸውን ሱፐርቫይዘሮች መመደብ የሚችልበትን አቅም (በቅጥር) መፍጠር መቻል ይጠበቅበታል::

4. ፕራክቲከም የመምህራን ስልጠና ተቋማት ብቻ ሥራ (ጉዳይ) አይደለም:: ተባባሪ ት/ቤቶችም ተመጣጣኝ የሆነ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት አለባቸው:: ይህን ኃላፊነታቸውን ከግምት ያላስገባ ፕራክቲከምም ግብ መምቱ አጠራጣሪ ነው:: ስለሆነም ተባባሪ ት/ቤቶች እንደ ጉዳዩ ባለቤት ፊላቸውን ቀጥረው የሚጠበቅባቸውን አስተዋፅኦ ማድረግ የሚችሉበት ሁኔታ ሊመቻችላቸው ይገባል:: ስለዚህ ኮሌጁ ከተባባሪ ት/ቤቶች ጋር ያለውን ግንኙነትና ትርርብ የበለጠ የሚያጠብቅበትን መንገድ ሊያስብበት ይገባል:: በተለይ ኮሌጁ በቂ የሆኑ የራሱ ሱፐርቫይዘሮችን ከመጠቀም ጎን ለጎን፤ ለተባባሪ ት/ቤት መምህራንም ልዩ የሱፐርቪዥን ስልጠና በመስጠት፤ ተማሪ አስተማሪዎች የተሻለ ሱፐርቫይዘራዊ እገዛ/ ድጋፍ ከት/ቤት መምህራን የሚያገኙበትን ሁኔታ ቢያመቻች::

5. የርቢ መምህራን ኮሌጅም ሆነ ሌሎች እቻ የክልሉ ኮሌጆች ብቁና ጥራት ያላቸውን መምህራን ማፍራት ይችሉ ዘንድ፤ በኦሮሚያ ክልላዊ መስተዳድር የትምህርት (አቅም ግንባታ) ቢሮ በኩል ተገቢው ትኩረት ቢደረግበት:: በተለይ ተማሪ አስተማሪዎችን ወደ ገጠር አካባቢ በሚገኙ ት/ቤቶች ለማሠማራት በሚቻልበት መንገድ ላይ አስፈላጊው በጀት ለኮሌጆቹ ቢያዝላቸው::

6. አዲስ የመምህራን ትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ በሃገሪቷ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ለተግባራዊው ስልጠና ከፍተኛ ትኩረት ሰቷል:: ይህም ጥሩ ጅምርና ሊጠናከር የሚገባው ጉዳይ ነው:: ይሁን እንጂ ከአዲስነቱ ጋር በተያያዘና ከግንዛቤ እጥረትም የተነሳ አተገባበሩ ላይ በርካታ የተመሰቃቀሉ ጉዳዮች መታያታቸውን/ መከሰታቸውን የተለያዩ ጥናቶች (ጎለም 1989፤ ተሰጠ 1997 Gebremedhin 2001 Kindalem 2005) አሳይተዋል፤ በዚህ ጥናትም በድጋሚ ተስተውለዋል:: ስለሆነም ትምህርት ሚኒስቴር (TESO) ይህን ጉዳይ ትኩረት ሰጥቶ በመከታተል ሂደቱ የሚቃናበትን መንገድ ቢያስብበት::

# ዋቢ ፅሑፎች


መለስ መኩሪያ (1990) "የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋም የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ትግበራ ሂደትን ከሥነ-ዘዴ አኳያ መገምገም በአዋሳና አርባ ምንጭ መምህራን ማሰልጠኛ ተቋም::" ያልታተመ የአትስት ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ፅሑፍ:: አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ::

ማስታወቂያ ሚኒስቴር (1994) <u>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ.መ. የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስትራቴጂና</u> ፕሮግራሞች:: አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ::

ተሰጠ አሰፋ (1997) "የፕራክቲከም የማስተር ልምምድና የሱፐርቪዥን አተገባበር በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሰርተፍኬት (10+1) መርሃ ግብር::" ያልታተመ የአርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ፅሑፍ:: አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ::

ትምህርት ሚኒስቴር (1994) <u>የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲና አተገባበሩ</u>:: አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ::

አለም እሸቱ (1989) "በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል ድህረ የማስተማር ልምምድ ውይይት የሱፐርቫይዘሮች ምግበ መረጃ ትንተና::" ያልታተመ የአርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ:: አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ::

የመምህራን ሚና <u>በትምህርትና ስልጠና ሂደት</u> (ጥር 1998):: አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ::

የትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር የመምህራን ማሰልጠኛ ክፍል በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገስት መንግስት (1952):: አዲስ አበባ::

የኢፌዲሪ መንግስት <u>የትምህርትና የአቅም ግንባታ ስትራቴጂና ፖሊሲዎች</u> (ጥር 1998):: አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ::

Alemayehu Debebe (1998). "Teachers Education Trends in some countries: Implications for the Ethiopian Context." In Proceedings of the National conference Held at Awassa College of Teacher Education. (12-18, July).

Alexander, J. L. (1979). <u>The Early Evolution of the curriculum of Elementary Teachers Education in England.</u> Lou vain: International standing conference on the History of Education.

Ausubel, D.P. and Robinson, F.G.(1969) <u>School Learning: An Introduction to Educational Psychology.</u> New York: Holt-Rinehart and Winston.

Azeb Desta (1984). "Elements of General Methods of Teaching." AAU. (Unpublished)

Boyan, N.J. and Copeland, W.D. (1978). Instructional Supervision Training Program. Ohio: Merrill.

Brown, G. (1975). Micro-teaching: a programme of teaching skills. London: Methuen.

Carroll, M. (1995).The Generic Tasks of Supervision. PhD. Dissertation: University of Surrey.

Clece - Murcia, M. (ed.) (1991). Teaching English as second or Foreign Language (2nd ed.) Boston: Heinle & Heinle publishers.

Cogan, M (1973). Clinical Supervision. Boston: Houghton-Mifflin.

Corder, S.P. (1973). Introducing Applied linguistics. London: Penguin Books.

Dent, H.C. (1961). Teaching. London: Batas ford career Books.

Department of Education and science (DES) (1981). Teacher Training and The Secondary School. London: DES.

Devroede, M. (1981). "The history of teacher Training". History of Education. 10(1) 1-8.

Dukin, M.J. (ed) (1987). The International Encyclopedia of Teaching and Teacher Education. Oxford: Paragon Press.

Ellis, R. (1986). 'Activities and Procedure for Teacher Training." ELT Journal. Vol. 40 No. 2 pp. 91-98.

Fanselow, J.F. (1990). 'Let's See: Contrasting conversations about teaching": In Richards, J. and Nunan. D. (eds). Second Language Teacher Education. Cambridge: CUP.

Fish, D. (1989). Learning Through Practice in Initial Teacher Training: A challenge for the Partners. Kogan page.

Freeman, D. (1990). "Intervening in Practice Teaching": In Richards, J. and Nunan, D. (eds). Second Language Teachers Education. Cambridge: CUP

Gebremdhin Simon (2001). "Aspects of Teachers Development for English Language: Implication for Quality of Education in Primary Schools." In proceedings of the National Conference Held in Adama Hotel (9-11 November).

Gebhard, J.G. (1990). "Models of supervision: Choices": In Richards, J. and Nun an, D. (eds). Second Language Teachers Education. Cambridge: CUP.

Goldhammer, R. et al (1980) Clinical Supervision: Special Methods for the Supervision of Teachers (2nd ed). New York: Holt-Rinehart and Winston.

Gower, R. and Walters, S. (1983) Teaching practice Handbook: A reference book for EPL, teachers in training. Oxford: Heinemann Imitational.

Hadley, E. (ed.) (1982) Teaching Practice and the Probationary Year. London: Edward Arnold Publishers.

Harris, H.M. (1985). Supervisory Behavior in Education (3rd ed.). New Jersey: Prentice Hall, Englewood Cliffs.

Herbst, J. (1979). Nineteenth Century Normal School in the United States: A Fresh Look: International. Lou vain, standing conference on the History of Education.

Holloway, E. and Carroll, M. (eds). (1999). Training Counseling Supervision Strategies, Methods and Techniques. London: SAGE Publications.

ICDR (1999) Teacher Education Handbook. Addis Ababa: OURAEL P. press.

Kelly, L. G. (1976). 25 Centuries of Language Teaching. Massachusetts: Newbury House Publishers.

Kindalem Damte (2005). "The Implementation of practicum in the Education Faculty of Addis Ababa University. ELT in Focus". Unpublished M.A. Thesis AAU.

Kolleejjii Barsiitota Roobe (1995). Barruulee Eebbaa. Finfinne: Commercial printing Agency.

Lovell, J and Kmballwiles, (1983). Supervisions for Better Schools. Prentice: Englewood Cliffs. (USA).

MOE (2003). "Teacher Education System Overhaul Handbook." (Unpublished)

_______ (2003) "Teacher Education System Overhaul Final Document". (Unpublished)

_______ (2003-2004). "Higher Diploma Program for Teacher Educators Course book " (Unpublished)

Pennington, M C. (1990) "A Professional development focus for the language teaching practicum": In Richards, J. and Nunan, D. (eds). Second Language Teachers Education. Cambridge: CUP.

Perlberg, A (1976). "Micro teaching –Present and future trends." Educational Media International. 1976 (2):13-20.

Perrott, E (1982). Effective Teaching: A practical Guide to Improving Your Teaching. New York: Longman Group.

Peters, S (1968) "Teaching practice in teacher training." Trends in Education. 9:3-9

Reece, I and walker, S. (2004). Teaching, Training, and learning: A practical Guide in Corporation FENTO Standards (3rd ed.). Great Britain: Business Education Publishers Limited.

Richards, J C and Nunan, D. (eds) (1990) Second Language Teacher Education. Cambridge: CUP.

Robe Teachers College (2004/5) Graduation Bulletin. Addis Ababa: Commercial Printing Agency.

Shiundu, J and Omulando, S. (1992) Curriculum: Theory and practice in Kenya. Nairobi: Oxford University Press.

_______ (1972) "An Approach to Systematic training". Teaching Practice. P.P. 231-244

Smith B O (1980). A Design for a School of Pedagogy. Washington. DC: United states Dept. of Education.

Srivastava, R.C. and Bose, K. (1978). Theory and practice of Teacher Education in India. New Delhi: Cough Publications.

Stones, E. and Morris, S. (1972). Teaching Practice Problems and Perspectives. London: Methuen & Co. Ltd.

Stones, F. (1978) "Psycho pedagogy: Theory and practice in Teaching" British Educational Research Journal 4(2): 1-19.

Stones, K. and Morris, S. (1972) Teaching practice: problems and perspectives: A Reappraisal of the practical professional Element in Teacher Preparation. London: Methuen.

Turney, C. (ed.) (1981). Anatomy of Teaching. Sydney: Noyak.

Venkataiah, S (ed.) (2004). Science Education In 21st Century. New Delhi: Anmol Publications Ltd.

Wallace, M. (1991). Training Foreign Language Teachers. Cambridge: CUP.

Walters, E.H. (1960). Teacher Training Colleges in the West Indies. Oxford: OUP

Weber, W.A. (1972). "Competency-based Teacher Education." In Houston, W.R. (ed.) Strategies and Resources of Developing a competency-based Teacher Education. New York: State Education Department.

Woodring, P. (1957). New Directions in Teachers Education: An Interim Report of the work of the Fund for the Advancement of Education in the Areas of Teacher Education and Recruitment. New York: Fund for the Advancement of Education, pp., 71-72.

# መዝገበ ቃላት

| | |
|---|---|
| መርሃ ግብር | program |
| ሙያ | profession |
| ሙያዊ ብቃት | professional quality |
| ማስተማር | teaching |
| ምልከታ | observation |
| ምጋቤ ምላሽ | feed back |
| ምዘና | assessment |
| ስልጠና | training |
| ሰልጣኞች | trainee |
| ሱፐርቪዥን | supervision |
| ተማሪ አስተማሪ | student teacher/ Trainee |
| ተባባሪ ት/ቤት | cooperative school |
| ተግባራዊ ትምህርት | practical education |
| ንድፈ ሃሳብ | theory |
| አሰልጣኝ/ የኮሌጅ መምህር | teacher educator |
| ግምገማ | evaluation |
| የመምህራን ትምህርትና ስልጠና | teacher education and eraining |
| የማስተማር ልምምድ | teaching practice |
| የስትሪም ትምህርት | stream subjects |
| የትምህርት ሥርዓት/ፖሊሲ | curriculum |
| የትምህርት ዕቅድ/ ዝግጅት | lesson plan/ preparation |
| የት/ቤት ልምድ | practicum |
| የት/ቤት መምህር | cooperative School Teacher |
| የክፍል ሥርዓትን ማስከበር | classroom management |
| ጥበብ | art |
| ፕሬዝ መጣጥፍ | portfolio |
| ዕብረቃ | reflection |
| ፕራክቲከም | practicum |

## አባሪ 1
## በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
## ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

### በርቤ መምህራን ኮሌጅ የቋንቋ ስትሪም መምህራን የሚሞላ የመጠይቅ ቅፅ

ውድ መምህር !

የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ በርቤ መምህራን ኮሌጅ በ10+3 የዲፕሎማ መርሃ ግብር ያለውን የፕራክቲከም ኮርስ የአተገባበር ሁኔታ መፈተሽ ነው። ለዓላማውም መሳካት ትክክለኛ የሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብና ማጠናቀር ያስፈልጋል። ስለሆነም በዚህ መጠይቅ ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች በትኩረት በማንበብና ተገቢውን ምላሽ በመስጠት ለጥናቱ መሳካት የበኩልዎን እገዛ ያደርጉልኛ ዘንድ ስጠይቅ በትህትና ነው። ጊዜዎን በመስዋት ለሚያደርጉልኝ ትብብርም የላቀ ምስጋናዬን በቅድሚያ አቀርባለሁ!

☞ ማሳሰቢያ፦ ይህን መጠይቅ በመሙላትዎ የሚያመጣብዎት ትገር አለመኖሩን ከወዲሁ አሳውቃለሁ።

I. አጠቃላይ መረጃ

1.2 የትምህርት ደረጃ 12+4 ☐ 12+6 ☐

1.3 በማስተማር ላይ የቆዩበት ዓመት 1-5 ☐ 6-10 ☐ 11-15 ☐ ከ15 በላይ ☐

1.4 የሚያስተምሩት ቋንቋ

አፋን ኦሮሞ ☐ አማርኛ ☐ እንግሊዝኛ ☐

1.5 በአሁኑ ሰዓት ያሉዎት መደበኛ የክፍለጊዜ መጠን 10-15 ☐ 16-20 ☐ 21-25 ☐ ከ25በላይ ☐

1.6 ለፕራክቲከም የተመደቡልዎት ተማሪዎች ብዛት

10-15 ☐ 16-20 ☐ 21-25 ☐ ከ25 በላይ ☐

II. ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ውስጥ በፕራክቲከም ትግበራ ሂደት የሚሳተፉ አካላትን ሚና የሚመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥያቄዎቹም እያንዳንዳቸው በጣም እስማማለሁ (5)፣ እስማማለሁ (4)፣ በመጠኑ እስማማለሁ (3)፣ አልስማማም (2) እና፣ ጨርሶ አልስማማም (1) የሚሉ አምስት አምስት አማራጭ ምላሾች አሏቸው። ምላሾቹም ከጥያቄዎቹ ትይዩ ከ5-1 በተራ ቁጥር ተመልክተዋል። ለጥያቄዎቹ ያልዎትን ምላሽም ከአምስቱ አማራጮች ውስጥ በመምረጥ በሰንጠረዡ ውስጥ የተመለከተውን ቁጥር ያክብቡ።

| ዝርዝር መጠይቆች | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | በመጠኑ እስማማለሁ | አልስማማም | ጨርሶ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 በፕራክቲከሙ ሂደት ከተማሪ አስተማሪዎች ጋር ተገናኝቼ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቻለሁ። | | | | | |
| 1.1 ከፕራክቲከም በፊት ተገናኝተን ትክክለኛ ሂደው ስለሚያከናውናቸው ተግባራት ወስነናል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1.2 ከፕራክቲከም በፊት ተገናኝተን ስለመሰረታዊ የማስተማር ክህሎት ተወያይተናል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1.3 ከፕራክቲከም በኋላ ተገናኝተን በትክክል ስላከናወኗቸው ተግባራት ተወያይተናል | | | | | |
| 2 በፕራክቲከሙ ሂደት በክፍል መምህርነቱ ለተማሪ አስተማሪዎች የሚያቀርቡትን እገዛ አድርጊያለሁ። | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 2.1 በትምህርቱ በመገኘት ቀጥታ ምልከታ(observation) አድርጊያለሁ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 2.2 ከሌሎች ባልደረቦቼ መስፈርት መሠረት የማስተማር ክንውናቸውን (performance) ገምግሚያለሁ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 2.3 ከምልከታ በኋላ ጠንካራ ጎኖቹ የሆኑ አስተያየትና ምጋቢ ምላሽ (feedback) ሰጥቻለሁ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 2.4 ከምልከታ/ግምገማ በኋላ በዛው ቀን ገንቢ የሆነ አስተያየትና ምጋቤ ምላሽ ስጥቻለሁ | | | | | |
| 2.5 ከምልከታ/ግምገማ በኋላ የቃልና የፅሁፍ ምጋቤ ምላሽ ስጥቻለሁ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 3. በፐሬክቲከም ሂደት የት/ቤት መምህራን ተከታዮቹን እገዛ/ድጋፍ ለተማሪ አስተማሪዎች ሰተዋል/አድርገዋል፡፡ | | | | | |
| 3.1 ስለማስተማሩ ተግባራት ተገቢ የሆነ መመሪያና መግለጫ ሰተዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 3.2 ተከታታይ ምልከታ አድርገዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 3.3 በተቀመጠው መስፈርት መሠረት የማስተማር ክንውናቸውን ገምግመዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 3.4 ከምልከታ/ግምገማ በኋላ ገንቢ የሆነ አስተያየትና ምጋቤ ምላሽ ሰተዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 3.5 ከምልከታ/ግምገማ በኋላ በዛው ቀን ገንቢ የሆነ አስተያየት ምጋቤ ምላሽ ሰተዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 3.6 ከምልከታ/ግምገማ በኋላ የቃልና የፅሁፍ ምጋቤ ምላሽ ሰተዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 4. በፐሬክቲከም ሂደት ተማሪ አስተማሪዎች ተከታዮቹን ተግባራት አከናውነዋል / ማከናወን ችለዋል፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 4.1 ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ አዘጋጅተዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 4.2 ተማሪዎችን ያማከለ (student centerd) ትምህርት አስተምረዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 4.3 ተማሪዎችን ንቁ (active) ተሳታፊ ያደረገ ትምህርት ሰተዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 4.4 ተከታታይ ምዘናን (continuous assessment) ተግብረዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 4.5 አጋዥ የማስተማሪያ መሣሪያችን አዘጋጅተዋል /ተጠቅመዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 4.6 ከማስተማር ውጪ ባሉ (co-curricular) ተግባራት ላይ ተሳትፈዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5. ለፐሬክቲከም ሂደት መሳካት በሁለኛ በኩል ተከታዮቹ እገዛ ች/ድጋፎች ለተማሪ አስተማሪዎች ተደርገዋል፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5.1 ተማሪዎች ተገቢውን ልምድ ከት/ቤት ለመቅሰም የሚያስችል የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቷል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5.2 በተገቢው ሰዓት ከት/ቤት ለመድረስ የሚያመች ትራንስፖርት ተዘጋጅቷል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5.3 ለተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛና ምክር የሚሰጥ መምህር ተመድቧል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5.4 አስፈላጊ የሆኑ የማስተማሪያ መሣሪያችን (የመማሪያ መፅሀፍትና የመምህር መምሪያ (teacher's guide) ለተማሪዎች ቀርበዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5.5 መምህራን አስፈላጊውን እገዛ ለተማሪዎች መስጠታቸውን ክትትል ተደርጓል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5.6 ለተማሪዎች ምልከታና ግምገማ የሚውል የመመዘኛ ቅፅ ተዘጋጅቷል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5.7 ተባባሪ ት/ቤቶች ተግባራቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን ክትትል ተደርጓል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6. ለፐሬክቲከም ሂደት መሳካት በተባባሪ ት/ቤቶች በኩል ተከታዮቹ እገዛች/ ድጋፎች ለተማሪ አስተማሪዎች ተደርገዋል፡፡ | | | | | |
| 6.1 ተገቢውን ልምድ ከት/ቤት ለመቅሰም የሚያስችል የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቷል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.2 አስፈላጊውን እገዛና ምክር የሚሰጥ መምህር ተመድቧል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.3 መምህራን አስፈላጊውን እገዛ ለተማሪዎች መስጠታቸውን ክትትል ተደርጓል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.4 የሚፈለገውን ልምድ ከት/ቤት ለመቅሰም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.5 ተማሪዎች የሚፈለገውን ልምድ ከት/ቤት መቅሰማቸውን ለማረጋገጥ ክትትል ተደርጓል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

III. በማስከተሉ ለቀረቡት ጥያቄዎች ያልዎትን አስተያየት በአጭሩ ይግለፁ::

3.1 በርቢ መምህራን ኮሌጅ (ተጨባጭ ሁኔታ) ፕራክቲከምን በአግባቡ ለመተግበር እንቅፋት ፈጥረዋል/ሆነዋል የሚሏቸውን ችግሮች ባጭሩ ይግለፁ::

3.2 በአጠቃላይ የፕራክቲከም አተገባበርን በተመለከተ ያልዎትን አስተያየት በአጭሩ ያስፍሩ::

## አባሪ 2
## በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
## ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

### በርቤ መምህራን ኮሌጅ በ10+3 የዲፕሎማ መርሃግብር የሦስተኛ ዓመት የቋንቋ ስትሪም የቀን መደበኛ ተማሪዎች የሚሞላ የመጠይቅ ቅፅ

ውድ ተማሪ !

የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ በርቤ መምህራን ኮሌጅ በ10+3 የዲፕሎማ መርሃግብር ያለውን የፕራክቲከም ኮርስ የአተገባበር ሁኔታ መፈተሽ ነው፡፡ ለዓላማውም መሳካት ትክክለኛ የሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብና ማጠናቀር ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም በዚህ መጠይቅ ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች በትኩረት በማንበብና ተገቢውን ምላሽ በመስጠት ለጥናቱ መሳካት የበኩልህ/ሽን እገዛ ታደርግ/ጊልኝ ዘንድ ስጠይቅ በትህትና ነው፡፡ ጊዜህ/ሽን በመሰዋት ለምታደርግ/ጊልኝ ትብብርም የላቀ ምስጋናዬን በቅድሚያ አቀርባለሁ!

☞ ማሳሰቢያ፡፡ ይህን መጠይቅ በመሙላትህ/ሽ የሚመጣብህ/ሽ ችግር አለመኖሩን ከወዲሁ አሳውቃለሁ፡፡

I. አጠቃላይ መረጃ

1.1 የተመራቂ ተማሪው/ዋ ትምህርት ክፍል ____________________

1.2 የተመራቂ ተማሪው/ዋ ቋንቋ

አፋን ኦሮሞ ☐ አማርኛ ☐ እንግሊዝኛ ☐

1.3 የተመራቂ ተማሪው/ዋ የከፍል ደረጃ 5 ☐ 6 ☐ 7 ☐ 8 ☐

1.4 በአማካኝ ያለህ/ሽ የክፍለጊዜ መጠን 10-15 ☐ 16-20 ☐ 21-25 ☐ ከ25በላይ ☐

II. ቀጥሎ ባለው ሰንጠዥ ውስጥ በፕራክቲከም ትግበራ ሂደት የሚሳተፉ አካላትን ሚና የሚመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ጥያቄዎቹም እያንዳንዳቸው በጣም እስማማለሁ (5)፣ እስማማለሁ (4)፣ በመጠኑ እስማማለሁ (3)፣ አልስማማም (2) እና፣ ጨርሶ አልስማማም (1) የሚሉ አምስት አምስት አማራጭ ምላሾች አላቸው፡፡ ምላሾቹም ከጥያቄዎቹ ትይዩ ከ5-1 በተራ ቁጥር ተመልክተዋል፡፡ ለጥያቄዎቹ ያለዎትን ምላሽም ከአምስቱ አማራጮች ውስጥ በመምረጥ በሰንጠረዡ ውስጥ የተመለከተውን ቁጥር አክብብ/ቢ፡፡

| | ዝርዝር መጠይቆች | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | በመጠኑ እስማማለሁ | አልስማማም | ጨርሶ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በፕራክቲከም ሂደት ከኮሌጁ መምህሮቼ ጋር ተገናኝቼ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቻለሁ፡፡ | | | | | |
| 1.1 | ከፕራክቲከም በፊት ተገናኝተን ትምህርት ቤት ሄጄ ስለማከናውናቸው ተግባራት መክሮኛል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1.2 | ከፕራክቲከም በፊት ተገናኝተን ስለመሰረታዊ የማስተማር ክህሎት ተወያይተናል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1.3 | ከፕራክቲከም በኋላ ተገናኝተን በትምህርት ቤት ስላከናወንኳቸው ተግባራት ተወያይተናል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 2 | በፕራክቲከም ሂደት ከኮሌጁ መምህራን ተከታዮቹን እገዛ/ድጋፍ አግኝቻለሁ/አተቀውሟል፡፡ | | | | | |
| 2.1 | ወትምህርት ቤት በመገኘት ተከታታይ ምልከታ (observation) አድርገውልኛል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 2.2 | ኮሌጁ ባዘጋጀው መስፈርት መሠረት የማስተማር ክንውኔን (performance) ገምግመዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 2.3 ከምልከታ/ግምገማ በኋላ ገንቢ የሆነ አስተያየትና ምጋቤ ምላሽ (feedback) ሰተውኛል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 2.4 ከምልከታ/ግምገማ በኋላ በዛው ቀን ገንቢ የሆነ አስተያየትና ምጋቤ ምላሽ ሰተውኛል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 2.5 ከምልከታ/ግምገማ በኋላ የቃልና የፅሁፍ ምጋቤ ምላሽ ሰተውኛል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 3. በፕራክቲከም ሂደት ከት/ቤት መምህራን ተከታዮቹን እገዛ/ድጋፍ አግኝቻለሁ / ሰተውኛል። | | | | | |
| 3.1 ስለማስተማር ተግባራት ተገቢ የሆነ መመሪያና መግለጫ ሰተውኛል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 3.2 ተከታታይ ምልከታ አድርገውልኛል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 3.3 በሁሉም በተቀመጠው መስፈርት መሠረት የማስተማር ክንውኔን ገምግመዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 3.4 ከምልከታ/ግምገማ በኋላ ገንቢ የሆነ አስተያየትና ምጋቤ ምላሽ ሰተውኛል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 3.5 ከምልከታ/ግምገማ በኋላ በዛው ቀን ገንቢ የሆነ አስተያየት ምጋቤ ምላሽ ሰተውኛል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 3.6 ከምልከታ/ግምገማ በኋላ የቃልና የፅሁፍ ምጋቤ ምላሽ ሰተውኛል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 4. በፕራክቲከም ሂደት በተማሪአስተማሪነቴ ተከታዮቹን ተግባራት አከናውኛለሁ። | | | | | |
| 4.1 ሳምንታዊ የትምህርት ዕቅድ አዘጋጅቻለሁ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 4.2 ተማሪዎችን ያማከለ (student centerd) ትምህርት አስተምሬያለሁ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 4.3 ተማሪዎችን ንቁ (active) ተሳታፊ ያደረገ ትምህርት ሰጥቻለሁ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 4.4 ተከታታይ ምዘናን (continuous assessment) ተግብሬያለሁ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 4.5 አጋዥ የማስተማሪያ መሣሪያዎችን አዘጋጅቻለሁ/ተጠቅሚያለሁ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 4.6 ከማስተማር ውጪ ባሉ (co-curricular) ተግባራት ላይ ተሳትፌያለሁ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5. ለፕራክቲከም ሂደት መሳካት በሁሉም በኩል ተከታዮቹ እገዛዎች/ድጋፎች ለተማሪ አስተማሪዎች ተደርገዋል። | | | | | |
| 5.1 የዩኒቨርሲቲው ልምድ ከት/ቤት ለመቅሰም የሚያስችል የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቷል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5.2 በዩኒቨርሲቲው ሰዓት ከት/ቤት ለመድረስ የሚያመች ትራንስፖርት ተመቻችቷል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5.3 ለተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ምክር የሚሰጥ መምህር ተመድቧል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5.4 አስፈላጊ የሆኑ የማስተማሪያ መሣሪያዎች (የመማሪያ መፅሀፍትና የመምህር መምሪያ (teacher's guide)) ቀርቧል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5.5 መምህራን አስፈላጊውን እገዛ ለተማሪዎች መስጠታቸውን ክትትል ተደርጓል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5.6 ለተማሪዎች ምልከታና ግምገማ የሚውል የመመዘኛ ቅፅ ተዘጋጅቷል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5.7 የትምህርት ቤቶች ተገቢውን ድጋፍ መስጠታቸውን ክትትል ተደርጓል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| ለፕራክቲከም ሂደት መሳካት በተባባሪ ት/ቤቶች በኩል ተከታዮቹ እገዛዎች/ድጋፎች ተማሪ አስተማሪዎች ተደርገዋል። | | | | | |
| 6.1 የዩኒቨርሲቲውን ልምድ ከት/ቤት ለመቅሰም የሚያስችል የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቷል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.2 አስፈላጊውን እገዛ ምክር የሚሰጥ መምህር ተመድቧል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.3 መምህራን አስፈላጊውን እገዛ ለተማሪዎች መስጠታቸውን ክትትል ተደርጓል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.4 የሚፈለገውን ልምድ ከት/ቤት ለመቅሰም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.5 ተማሪዎች የሚፈለገውን ልምድ ከት/ቤት መቅሰማቸውን ለማረጋገጥ ክትትል ተደርጓል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

III. በማስከተል ለቀረቡት ጥያቄዎች ያለህ/ሽን አስተያየት በአጭሩ ግለፅ/ጭ::

1. በጊምቢ መምህራን ኮሌጅ (ተጨባጭ ሁኔታ) ፕራክቲክምን በአግባቡ ለመተግበር እንቅፋት ፈጥረዋል/ሆነዋል የምትለ/ይውን ችግሮች ባጭሩ ግለፅ/ጭ::

2. በአጠቃላይ የፕራክቲክም አተገባበርን በተመለከተ የምትለ/ይውን አስተያየት በአጭሩ አስፍር/ሪ።

## አባሪ 3
## በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
## ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

### ከርቢ መምህራን ኮሌጅ ጋር ፕሪክቲከምን በጋራ በሚያከናውኑ የተባባሪ ት/ቤቶች የቋንቋ መምህራን የሚሞላ የመጠይቅ ቅፅ

ውድ መምህር !

በዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ በርቢ መምህራን ኮሌጅ በ10+3 የዲፕሎማ መርሃ ግብር ያለውን የፕራክቲከም ኮርስ የአተገባበር ሁኔታ መፈተሽ ነው። ለዓላማውም መሳካት ትክክለኛ የሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብና ማጠናቀር ያስፈልጋል። ስለሆነም በዚህ መጠይቅ ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች በትኩረት በማንበብና ተገቢውን ምላሽ በመስጠት ለጥናቱ መሳካት የበኩልዎን እገዛ ያደርጉልኝ ዘንድ ስጠይቅ በትህትና ነው። ጊዜዎን በመሰዋት ለሚያደርጉልኝ ትብብርም የላቀ ምስጋናዬን በቅድሚያ አቀርባለሁ!

☞ ማሳሰቢያ፦ ይህን መጠይቅ በመሙላትዎ የሚያመጣብዎት ችግር አለመኖሩን ከወዲሁ አሳውቃለሁ።

I. አጠቃላይ መረጃ

1.1 የሚያስተምሩበት ት/ቤት ______________________

1.2 የትምህርት ደረጃ 12+1 ☐ 12+2 ☐

1.3 በማስተማር ላይ የቆዩበት ዓመት 1-5 ☐ 6-10 ☐ 11-15 ☐ ከ15 በላይ ☐

1.4 የሚያስተምሩት ቋንቋ

አፋን ኦሮሞ ☐ አማርኛ ☐ እንግሊዝኛ ☐

1.5 በአማካኝ ያሉዎት መደበኛ የክፍል ተማሪዎች መጠን 10-15 ☐ 16-20 ☐ 21-25 ☐ ከ25በላይ ☐

1.6 ለፕሪክቲከም የተመደቡልዎት ተማሪዎች ብዛት

10-15 ☐ 16-20 ☐ 21-25 ☐ ከ25 በላይ ☐

II. ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ውስጥ በፕሪክቲከም ትግበራ ሂደት የሚሳተፉ አካላትን ሚና የሚመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥያቄዎቹም እያንዳንዳቸው በጣም እስማማለሁ (5)፣ እስማማለሁ (4)፣ በመጠኑ እስማማለሁ (3)፣ አልስማማም (2) እና፣ ጨርሶ አልስማማም (1) የሚሉ አምስት አምስት አማራጭ ምላሾች አሏቸው። ምላሾቹም ከጥያቄዎቹ ትይዩ ከ5-1 በተራ ቁጥር ተመልክተዋል። ለጥያቄዎቹ ያልዎትን ምላሽም ከአምስቱ አማራጮች ውስጥ በመምረጥ በሰንጠረዥ ውስጥ የተመለከተውን ቁጥር ያክብቡ።

| ዝርዝር መጠይቆች | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | በመጠኑ እስማማለሁ | አልስማማም | ጨርሶ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 በፕሪክቲከም ሂደት የኮሌጅ መምህራን ለተማሪአስተማሪዎች የሚያደርጉትን እገዛ እንደሚከተለው አድርገዋል። | | | | | |
| 1.1 ወደ ት/ቤት በመገኘት ተከታታይ ምልከታ(observation) አድርገዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1.2 ኮሌጁ ባስቀመጠው መስፈርት መሠረት የማስተማር ክንውናቸውን (performance) ገምግመዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1.3 ከምልከታ/ግምገማ በኋላ ገንቢ የሆነ አስተያየትና ግብረ ምላሽ (feedback) ሰጥዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1.4 ከምልከታ/ግምገማ በኋላ በዛው ቀን ገንቢ የሆነ አስተያየትና ግብረ ምላሽ ሰጥዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1.5 ከምልከታ/ግምገማ በኋላ የቃልና የፅሁፍ ግብረ ምላሽ ሰጥዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 2 በፕሪክቲከም ሂደት ወደ ት/ቤት መምህራኑ ለተማሪ አስተማሪዎች | | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ተከታዮቹን እባክዎ/ድጋፍ ስጥቻለሁ። | | | | | |
| 3.1 ስለማስተማሩ ተግባራት ተገቢ የሆነ መመሪያና መግለጫ ሰጥቻለሁ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 3.2 ተከታታይ ምልከታ አድርጌያለሁ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 3.3 በሙሉጃ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት የማስተማር ክንውናቸውን ገምግሜያለሁ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 3.4 ከምልከታ/ግምገማ በኋላ ገንቢ የሆነ አስተያየትና ምጋቤ ምላሽ ሰጥቻለሁ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 3.5 ከምልከታ/ግምገማ በኋላ በዛው ቀን ገንቢ የሆነ አስተያየት ምጋቤ ምላሽ ሰጥቻለሁ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 3.6 ከምልከታ/ግምገማ በኋላ የቃልና የፅሁፍ ምጋቤ ምላሽ ሰጥቻለሁ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 4. በፕራክቲኩም ሂደት ተግባራ አስተማሪዎች ተከታዮቹን ተግባራት አከናውነዋል / ማከናወን ችለዋል። | | | | | |
| 4.1 ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ አዘጋጅተዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 4.2 ተማሪዎችን ያማከለ (student centerd) ትምህርት አስተምረዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 4.3 ተማሪዎችን ንቁ (active) ተሳታፊ ያደረገ ትምህርት ሰተዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 4.4 ተከታታይ ምዘናን (continuous assessment) ተግብረዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 4.5 አጋዥ የማስተማሪያ መሣሪያዎችን አዘጋጅተዋል /ተጠቅመዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 4.6 ከማስተማር ውጪ ባሉ (co-curricular) ተግባራት ላይ ተሳትፈዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5. ለፕራክቲኩም ሂደት መሳካት በኮሌጁ በኩል ተከታዮቹ እገዛዎች/ድጋፎች ተግባራ አስተማሪዎች ተደርገዋል። | | | | | |
| 5.1 ተገቢውን ልምድ ከት/ቤት ለመቅሰም የሚያስችል የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቷል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5.2 በተገቢው ሰዓት ከት/ቤት ለመድረስ የሚያመች ትራንስፖርት ተመቻችቷል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5.3 ለተማሪዎቹ አስፈላጊውን እገዛና ምክር የሚሰጥ መምህር ተመድቧል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5.4 አስፈላጊ የሆኑ የማስተማሪያ መሣሪያዎች (የመማሪያ መፅሀፍትና የመምህር መምሪያ (teacher's guide)) ቀርቧል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5.5 መምህሩን አስፈላጊውን እገዛ ለተማሪዎች መስጠታቸውን ክትትል ተደርጓል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5.6 ለተማሪዎች ምልከታና ግምገማ የሚውል የመመዘኛ ቅፅ ተዘጋጅቷል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5.7 ተባባሪ ት/ቤቶች ተገቢውን ድጋፍ መስጠታቸውን ክትትል ተደርጓል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6. ለፕራክቲኩም ሂደት መሳካት በተባባሪ ት/ቤቶች በኩል ተከታዮቹ እገዛዎች/ ድጋፎች ተግባራ አስተማሪዎች ተደርገዋል። | | | | | |
| 6.1 ተገቢውን ልምድ ከት/ቤት ለመቅሰም የሚያስችል የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቷል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.2 አስፈላጊውን እገዛና ምክር የሚሰጥ መምህር ተመድቧል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.3 መምህሩን አስፈላጊውን እገዛ ለተማሪዎች መስጠታቸውን ክትትል ተደርጓል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.4 የሚፈለገውን ልምድ ከት/ቤት ለመቅሰም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.5 ተማሪዎች የሚፈለገውን ልምድ ከት/ቤት መቅሰማቸውን ለማረጋገጥ ክትትል ተደርጓል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

III. በማስከተል ለቀረቡት ጥያቄዎች ያለዎትን አስተያየት በአጭሩ ይግለፁ::

3.1 በሮቤ መምህራን ኮሌጅ (ተጨባጭ ሁኔታ) ፕራክቲከምን በአግባቡ ለመተግበር እንቅፋት ፈጥረዋል/ሆነዋል የሚሏቸውን ችግሮች ባጭሩ ይግለፁ::

3.2 በአጠቃላይ የፕራክቲከም አተገባበርን በተመለከተ ያልዎትን አስተያየት በአጭሩ ያስፍሩ::

# አባሪ 4

# በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

# ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

**ለርቢ መምህራን ኮሌጅ የፕራክቲክም ክፍል ኃላፊ የሚቀርቡ የቃለመጠይቅ ጥያቄዎች**

1. ለፕራክቲክም መርሃግብር የሚወጣው የጊዜ ሰሌዳ ምን ያህል ተገቢነት አለው?
   - ለተማሪዎች አስፈላጊውን ልምድ ከማስቀሰም አንፃር
   - በኮሌጁ ወይም በተባባሪ ት/ቤቶች ሊኖሩ የሚችሉ አንዳንድ ሁኔታዎችን የማገናዘብ ሁኔታ (ለምሳሌ የፈተና ወቅት)
   - በአካባቢው ያሉ ሌሎች ኮሌጆች ሊኖራቸው ከሚችለው የፕራክቲክም መርሃግብር አንፃር
   - በጊዜ ሰሌዳው ዝግጅት ሂደት የተባባሪ ት/ቤቶች ሚና ምን ያህል ነው?
2. የትራንስፖርት አገልግሎት ምን ያህል ሰዓትን ያከበረነው?
3. ለተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛና ምክር የሚሰጥ መምህር የመመደብ ሁኔታ ምን ይመስላል?
4. ለተማሪዎች ምልከታና ግምገማ የሚውል የመመዘኛ ቅፅ ማዘጋጀትና ለመምህራኑ የማሰራጨት ሁኔታ ምን ይመስላል?
5. መምህራን አስፈላጊውን እገዛ ለተማሪዎች መስጠታቸውን ምን ያህል ክትትል ይደረጋል? እንዴት ባለ መንገድ?
6. ለፕራክቲክሙ ሂደት የሚያስፈልጉ የማስተማሪያ መሣሪያዎች፣የመማሪያ መፅሀፍትና የመምህር መምሪያ (teacher's guide) ለተማሪዎች ምን ያህል በበቂ ሁኔታ ቀርቧል?
7. በኮሌጁና በተባባሪ ት/ቤቶች መካከል ምን ያህል ተቀራርቦና አብሮ የመሥራት ሁኔታ አለ? ለምሳሌ፡-
   - ኮሌጁ ለተባባሪ ት/ቤቶች የሚያደርገው እገዛ
   - የተባባሪ ት/ቤቶች ተማሪዎችን በተገቢው መንገድ ማስተናገድ
   - በኮሌጁ የፕራክቲክም ዩኒትና በተባባሪ ት/ቤቶች ም/ዳይሬክተሮች መካከል ያለው ቅርርብ
   - በኮሌጁ እና ት/ቤቶቹ መምህራን መካከል ያለው ቅርርብ
   - በተማሪዎቹና በት/ቤቶቹ መምህራን መካከል ያለው ቅርርብ
8. በርቢ መምህራን ኮሌጅ (ተጨባጭ ሁኔታ) ፕራክቲክምን በአግባቡ ለመተግበር እንቅፋት ፈጥረዋል /ሆነዋል የሚሏቸው ዋናዋና ችግሮች የትኞቹ ናቸው?
9. በአጠቃላይ የፕራክቲክም አተገባበርን በተመለከተ ምን አስያየት ይሰጣሉ?

## አባሪ 5

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

**ለተባባሪ ት/ቤቶች ርዕሳን መምህራን የሚቀርቡ የቃለመጠይቅ ጥያቄዎች**

1. ለፕራክቲከም መርሃ ግብር የሚወጣው የጊዜ ሰሌዳ ምን ያህል ተገቢነት አለው?
   - ለተማሪዎች አስፈላጊውን ልምድ ከማስቀሰም አንፃር
   - በኮሌጁ ወይም በተባባሪ ት/ቤቶች ሊኖሩ የሚችሉ አንዳንድ ሁኔታዎችን የማገናዘብ ሁኔታ (ለምሳሌ የፈተና ወቅት)
   - በአካባቢው ያሉ ሌሎች ኮሌጆች ሊኖራቸው ከሚችለው የፕራክቲከም መርሃግብር አንፃር
   - በጊዜ ሰሌዳው ዝግጅት ሂደት የተባባሪ ት/ቤቶች ሚና ምን ያህል ነው?
2. ኮሌጁ ለፕራክቲከም የሚመድብላችሁ ተማሪዎች ምን ያህል የት/ቤት ሰዓት አክብረው ይገኛሉ?
3. ለተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛና ምክር የሚሰጥ መምህር የመመደብ ሁኔታ ምን ይመስላል?
4. ለተማሪዎች ምልከታና ግምገማ የሚውል የመመዘኛ ቅፅ ምን ያህል ለመምህራኑ ተሰራጭቷል?
5. መምህራን አስፈላጊውን እገዛ ለተማሪዎች መስጠታቸውን ምን ያህል ክትትል ይደረጋል? እንዴት ባለ መንገድ?
6. በት/ቤታችሁ ተማሪአስተማሪዎች አስፈላጊውን የፕራክተከም ተግባራት ማከናወን የሚያስችላው ምቹ ሁኔታ ምን ያህል ተፈጥሮላቸዋል?
   - ምን ለማከናወን እንደሚመጡ በማወቅ አስቀድሞ መዘጋጀት
   - የመጡበትን በትክክል ማከናወናቸውን መከታተልና ማረጋገጥ
7. በኮሌጁና በተባባሪ ት/ቤቶች መካከል ምን ያህል ተቀራርቦና አብሮ የመሥራት ሁኔታ አለ? ለምሳሌ፡፡
   - ኮሌጁ ለተባባሪ ት/ቤቶች የሚያደርገው እገዛ
   - የተባባሪ ት/ቤቶች ተማሪዎችን በተገቢው መንገድ ማስተናገድ
   - በኮሌጁ የፕራክቲከም ዩኒትና በተባባሪ ት/ቤቶች ም/ዳይሬክተሮች መካከል ያለው ቅርርብ
   - በኮሌጁና ት/ቤቶቹ መምህራን መካከል ያለው ቅርርብ
   - በተማሪዎቹና በት/ቤቶቹ መምህራን መካከል ያለው ቅርርብ
8. ከርቢ መምህራን ኮሌጅ ተጨባጭ ሁኔታ ፕራክቲከምን በአግባቡ ለመተግበር እንቅፋት ፈጥረዋል /ሆነዋል የሚሏቸው ዋናዋና ችግሮች የትኞቹ ናቸው?
9. በአጠቃላይ የፕራክቲከም አተገባበርን በተመለከተ ምን አስተያየት ይሰጣሉ?

## አባሪ 6
## በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
## ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

**በርቢ መምህራን ኮሌጅ በ10+3 የዲኘሎማ መርሃግብር የሦስተኛ ዓመት መደበኛ የቋንቋ ስትሪም ተማሪዎች የክፍል ውስጥ የማስተማር ክንውን የመመልከቻ (obsrevation) ቅፅ**

I. አጠቃላይ መረጃ

ቀን ____________
የተማሪ አስተማሪው ስም ____________
የሚገመግመው መምህር ____________

ት/ቤት ____________
የክፍል ደረጃ ____________
የት/ቱ ዓይነት ____________
የት/ቱ ርዕስ ____________

II. በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ተግባራዊውን የክፍል ውስጥ የማስተማር ክንውናት (activeties) የሚመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡በነዚህም ጥያቄዎች መሠረትነት በምልከታው ወቅት የታዘቢቸውን ነጥቦች «X» ምክንያት በመጠቀም «አዎ»፣«እርግጠኛ አይደለሁም» ወይም «አይ» በማለት የመልከቱ፡፡

| | የማስተማር ክንውናት (activeties) | አዎ | እርግጠኛ አይደለሁም | አይ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የትምህርቱ ዓላማ (objectives) | | | |
| 1.1 | መርሃ ትምህርቱን መሠረት ያደረገ ነው | | | |
| 1.2 | ግልፅ/ ውስን (specific) ነው | | | |
| 1.3 | ሊለካ/ ሊመዘን ይችላል | | | |
| 1.4 | የሚደረስበት (attainable) ነው | | | |
| 1.5 | እውናዊ (realistic)ነው | | | |
| 1.6 | በጊዜ የተወሰነ ነው | | | |
| 2 | የትምህርት ይዘት (content) | | | |
| 2.1 | ከተቀመጠው ዓላማ/ግብ ጋር የተያያዘ ነው | | | |
| 2.2 | ለመረዳት የማያስቸግር/የማይከብድ ነው | | | |
| 2.3 | ከግብ መድረሱ ሊለካ/ ሊመዘን ይችላል | | | |
| 2.4 | ለተማሪዎች ግልፅ (demonstrated) ነው | | | |
| 3 | የክፍል ውስጥ ሥራዎች/ተግባራት (activities) | | | |
| 3.1 | በአግባቡ የተደራጁ (organized) ናቸው | | | |
| 3.2 | [illegible] የተውጣጡ (varied) ናቸው | | | |
| 3.3 | ተማሪዎችን በንቃት (actively) ያሳተፉ ናቸው | | | |
| 3.4 | ተማሪዎችን ማዕከል ያደረጉ (student-centred) ናቸው | | | |
| 3.5 | በክፍል ውስጥ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተጣጥሟል | | | |
| 3.6 | ተማሪዎች በትጋት እንዲሰሩ (challenge) ማድረግ ችለዋል | | | |
| 4 | ምዘና (assessment) | | | |
| 4.1 | ተገቢነት (appropriateness) አለው | | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 4.2 ብቃት (effectiveness) አለው | | | |
| 4.3 ተከታታይነት (continuity)አለው | | | |
| 4.4 ተማሪዎች ስለመመዘናቸው ያውቃሉ (aware) | | | |
| 4.5 ተማሪዎች ገንቢ ምጋቤ ምላሽ (feedback) አግኝታዋል | | | |
| 5. **የክፍል ተማሪዎች ሁኔታ (students)** | | | |
| 5.1 በትምህርቱ መማረካቸውን በግልፅ አሳይተዋል | | | |
| 5.2 በትምህርቱ ላይ በንቃት (actively) ተሳትፎ አድርገዋል | | | |
| 5.3 በትምህርቱ ላይ እንደግላቸው ልዩነታቸው ተሳትፈዋል (treated as individuals) | | | |
| 5.4 በትምህርቱ መጨረሻ ላይ የሚጠበቅባቸውን ተረድተዋል | | | |
| 5.5 ከመምህሩ ተገቢውን ማበረታቻ አግኝተዋል (encouraged) | | | |
| 5.6 በትምህርቱ ሂደት ተደስተዋል (enjoyed) | | | |

**III. በማስከተል ለቀረቡት ጥያቄዎች ያልዎትን አስተያየት በአጭሩ ይገለፁ::**

1 በአጠቃላይ ሲታይ የማስተማር ክንውኑ ብቃት ምን ይመስላል?

እንዱን ቁጥር በማክበብ ያመልክቱ

| ደካማ | ምንም አይልም | ጥሩ | በጣም ጥሩ | እጅግ በጣም ጥሩ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |

2 ከተመለከቱት የማስተማር ክንውን በጠንካራ ጎንነቱ የሚያነሱትን ጉዳዮች ያስፍሩ::

3 ከተመለከቱት የማስተማር ክንውን መሻሻል አለባቸው የሚሉትን ጉዳዮች ያስፍሩ::

4 የተመለከቱትን የማስተማር ክንውን በተመለከተ ያልዎትን አጠቃላይ አስተያየት (general reflection) ቢገልፁ::

## አባሪ 7
## በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
## ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

በርቢ መምህራን ኮሌጅ በ10+3 የዲፕሎማ መርሃ ግብር የሦስተኛ ዓመት መደበኛ የቋንቋ ስትሪም ተማሪዎች ዕለታዊ የማስተማር ክንውን ማስታወሻ (reflective diary)

I. አጠቃላይ መረጃ

1. ቀን ______
2. ት/ቤት ______
3. የተማሪዎች ብዛት ወንድ ______ ሴት ______ ድምር ______
4. የተማሪ አስተማሪው ስም ______
5. የገመገመው መምህር ______

II.

1. የክፍል ደረጃ ______
2. የት/ቱ ዓይነት ______
3. የት/ቱ ርዕስ ______
4. የት/ቱ ዓላማ ______
5. የት/ቱ ይዘት ______
6. የማስተማር መማር ክንውኖች (በሰዓት የተከፋፈለ)

| የመምህሩ ክንውን | ጊዜ/ሰዓት | የተማሪዎች ክንውን |
|---|---|---|
| | | |

7. አጋዥ/ ደጋፊ (aid) የማስተማሪያ መሣሪያዎች

8. የተደረሰባቸው ውጤቶች (outcomes)

9. የምዘና (assessment) ስልቶች

III በማስከተል ለቀረቡት ጥያቄዎች ያለህ/ሽን አስተያየት በአጭሩ ገለፅ/ጪ::

5. በአጠቃላይ ሲታይ የዕለቱ የማስተማር ክንውህ/ሽ ብቃት ምን ይመስላል?

- አንዱን ቁጥር በማክበብ አመልክት/ቺ

| ደካማ | ምንም አይልም | ጥሩ | በጣም ጥሩ | እጅግ በጣም ጥሩ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |

6. ከዕለቱ የማስተማር ክንውን በጠንካራ ጎንነቱ የምታነሳ/ሺውን ጉዳይ አስፍር/ሪ::

7. ከዕለቱ የማስተማር ክንውን ላሻሽላቸው ይገባል የምትላ/ያቸውን ጉዳዮች አስፍ ር/ሪ::

8. የዕለቱን የማስተማር ክንውን በተመለከተ ያለህ/ሽን አጠቃላይ አስተያየት (general reflection) ገለፅ/ጪ::

## ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች የፈረምኩት፣ ይህ ጥናት የራሴ ሥራና በጥናቱም ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ምንጮች በሙሉ የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ።

ስም

ሙሐመድ ጀማል ________________

ፊርማ

አድራሻ፡-
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ- ጽሑፍ
ትምህርት ክፍል
አዲስ አበባ

የማስረከቢያ ጊዜ፡- የካቲት 1999